


t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ታከ

© ዓለማየሁ ገላጋይ፤ 2011 ዓ.ም.
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

የመጀመሪያ እትም - ኅዳር 2011 ዓ.ም.
ሁለተኛ እትም - ታህሳስ 2011 ዓ.ም.

ትየባ፡- ቤተልሄም አመነሸዋ
ሽፋን ስዕል፡- ኤፍሬም ባይሳ

አሳታሚ፡- መካሻ አሳታሚ ድርጅት

t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ምስጋና

ለዘመኑ ሀዲስ ደሳለኝ

t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ክፍሊ ፩

# ጡረታ ድሊድይ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ምስጋና

ለደራሲና ሐያሲ ዓለማየሁ ገላጋይ ወዳጅነታችንን ሀብት አድርጎ የህይወቴን ትርክት ፈር በማስያዝ ላቆነጃጀልኝ ታላቅ ውለታው ምስጋና ከማበርከት ወዲህ ምን? አመሰግናለሁ አሌክስ።

አልአዛር(ታለሰው) ብዜን






t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## ሁለት
## የበኣት ነገር

ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ የምናውቀው እኔና ጠቢቡ ሰለሞን ብቻ ነን፡፡ በቀደመው ህይወታችን ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር ለማኖር ፍላጎት ነበረን፡፡ እኔ በቤቴ፣ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ ነገሥን፡፡ ከማከማቸት ብዛት የምትገኝ ሀብት ወደ ሀዘን እንደምትቀየር ሁሉ፣ ከማሰላሰልና ከማንበብ ብዛት የሚገኝ ዕውቀትም ወደ ተስፋ መቁረጥ እንዲመራ አየሁ፡፡

ለአመታት ቤቴን ዘግቼ እራሴን አልፈለግሁምን? በራሴ ላይ ከመዘባበት ውጭ ምን አገኘሁ? እንደ በኣት የምትቆጠር ቤቴን ከፍቼ የገባሁት የአስራ አንደኛ ክፍል ትምህርቴን አቋርጬ ነበር፡፡ የዘጋሁትን በር ከፍቼ ስወጣ በአንዲት ጀንበር ዕድሜ ሁለት ዓመታት አልፈው ነበር፡፡ እነዚህ ሁለት ዓመታት በውስጣቸው ብዙ ቅራቅንቦ እንደያዙ ትልብጭ ያሉ ሁለት ቀረጢቶች ነበሩ፡፡ አንዱ ቀረጢት ብዙ መፃህፍትን ይዟል፡፡ ሌላው ቀረጢት ውስጥ አያሌ ክንውኖች ቁልጭ ብለው ይታዩኛል፡፡ ክንውኖቹ የመፃህፍቱን ያህል ህይወትን ቁልጭ አድርገው የሚያስተምሩ ነበሩ፡፡

ከአንድም ሁለት ሦስቴ አምፑል ተቃጥሎ ተቀይሯል፡፡ የተቃጠለው ለልጆች መጫወቻ ይጣላል፡፡ ብርሃን የሚታሰበው ከፍ-ከፍ ይላል፡፡ ከመቃጠሉ በፊት የተዋጋቸው የጨለማ ክፍለ ጊዜዎች ባለመጣሉ ዋስትና አይሆኑም፡፡ ጡረተኛው አምፑል በልጆች ግዴለሽ አያያዝ ብዙም ሳይቆይ ይፈነዳል፡፡ ከፀሐይ በታች ምን አዲስ ነገር አለ?

ከአንድም ሁለት ሦስቴ እናቴ መጥታ መክራኛለች፡-

‹‹ትምህርት አስትቶ ከቤት የሚዘፈዝፍ ምን እክል ገጠመህ ልጄ?›› ብላኛለች፡፡

የሚገባና የማይገባ እውነት እንዳለ ለመጀመሪያ ጊዜ አየሁ፡፡ ‹‹በሻምበል ጠናጋሻው እውቀት ቀናሁ፤ ጫት በሚያመነዥጉት ፈላስፎች ፊት አፈርሁ. . .›› ብላት ይገባታል? እውነቱ ግን ይህ ነው፡፡

‹‹አይገባኝ አይምሰልህ፤ ያ ሻምበል እዚህ ቤት ከመጣ አንስቶ ልብህ እንዳቆበቆበ አውቃለሁ፡፡ እሱ ደሞ የጠቀመ ይመስል ይሄን የፈረንጅ ትብትብ ይዞልህ ይመጣል፡፡ አይንም ይደክማል፤ ጭንቅላትም ይሰንፋል፡፡ እስኪ አረፍ እያልክ. . .››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ከአንድም ሁለት ሦስቴ ሸምበል ጠናጋሻው መጥቶ ስለአለበት አሳዛኝ ኑሮ አጫውቶኛል። ሌላ ጊዜ ጨዋታ የሚጀምረው ባመጣው መጽሐፍ ላይ ተመስርቶ ሲሆን፣ ጨዋታውን የሚያጠቃልለው ባላመጣው ሌላ መጽሐፍ ላይ ማብራሪያ በመስጠት ነበር። ከእነሊያ ብርት ሦስት ቀኖች በአንዱ ግን ቀይ ፊቱ ላይ የትራፊታ ማዲያት እየተንከሳጠሰ ያመጣቸውን መፃህፍት አልጋ ላይ በትኖ አቀርቅሮ ተቀመጠ።

‹‹ታድለሃል፣ በአንተ እየቀናሁ ነው›› አለኝ።

‹‹እንዴትግ›› ያከፈከፈ ሀዘን እንደ መርግ ሊደንባብኝ እንደሆነ እየገባኝ።

‹‹የእኔን የምኞት ዓለም ኑሮ እየኖርክ ነው። ስምረትን ያገባኋት ለእኔ ያንን ያህል የከረረ ፍቅር ስለሴላት ለመጻሕፍት ንባብ ጊዜ ትሰጠኛለች ብዬ ነበር። ግን አልሆነም። ከዕለት-ዕለት መጽሐፎቼን እየጠላቻቸው መጣች. . .›› ካቀረቀረበት ቀና ብሎ እምሽክ፣ ድቅቅ ባለ ስሜት ተመልክቶኝ ንግግሩን ቀጠለ።

‹‹የሴት ጣውንቷ ሌላ ሴት ከመሰለችህ ተሳስተሃል። ወዳጄ የሴት ጣውንቷ ባሏ የሚወደውና ቀልቡን የሰጠው ነገር ሁሉ ነው። ልብ በል፣ ሴላው ቀርቶ ልጅህን እንኳን ከወደድክ የገዛ ልጇን ወደ ጣውንትነት ትቀይራለች።››

የሸምበልን ነገር በተለመደው ዘዬ ‹ከፀሐይ በታች አዲስ ነገር የለም›› ብዬ ሳልፈው እንዳልቻልኩ ይገባኛል። እህቴ እንግሊዟ ስምረት ትኩረቷ ሁሉ ከቤተሰቡ ፋይናንስ ጋር የተያያዘ ስለነበር ህይወቷን የሚገጥመው እንቅፋት ከገንዘብ ጋር ብቻ የተያያዘ እንደሚሆን እገምት ነበር። ከአንድም ሁለት ሦስቴ እዚህ እኔ ክፍል ድረስ መጥታ ሸምበልን እያካለበች ስታስወጣው ከእህቷ ከረቂት ጋር በገባችው እልህ እንዳይገናኙ ቀዳዳ ለመድፈን መስሎኝ ነበር።

‹‹እየሀ? ህይወት የስሴት ውጤት አይደለችም። የእናቴ ፍቅር ስላንገላታኝ ሳድግ የማገባው የማትወደኝን ነው እል ነበር። እናቴ የእኔን ታላቅ ወንድም በወንገዘ ተወስዶ ስላጣችው ከጓደኞቼ ጋር ዋና ዋኘቼ ስመጣ ምን ብጠነቀቅ ታውቅብኝ ነበር። ‹እስኪ አይንህ? እስኪ ገላህ. . . ዛሬም ዋናገ› ብላ እራሷን ትስት ነበር። እኔ ደግሞ ዋና እወዳለሁ። አሁን ደግሞ ስምረት ‹ግቢ› አንብቤ ስመጣ እስኪ አይንህ? እስኪ እጅህ? እንዳነበብኩ የምታውቅበት ማንፍንፊያ ተሰጥቷታል። ስምረት አፍቅራኝ አይደለም። ምናልባት ከፈታዷ መውጣት እንደሌለብኝ ንብረቷ ሳታየኝ አትቀርም።››

አንድ ቀን ልጇን ታቅፋ እኔ ቤት ስትመጣ ድምፄን አለስልሼ ነገርኳት፡-



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ተይው፣ ያንብብ!»

ስምረት ፊቷ ተለዋወጠ «ተይው ውሽግውጋ ይሂድ፥ ያልኳት መሰለች፡፡ መልኳ ከእኔ ይልቅ ሻምበልን ይዛመዳል፡፡ በወንድምና በእህት መካከል የገባሁ ባዕድ የሆንኩ እንዲመስለኝ አደረገች፡፡ ጉንጯ በፈረንጅ ስልት ቀልቶ እየተንቀጠቀጠ...

«የኛ ጉዳይ የኛ መሰለኝ!» ልጇን ዘጭ አድርጋ አስቀመጠቻት፡፡ ልጇ ሴላ ለቫሌት ዳንስ የሚሆን የእንግሊዝ ጨኸት አሰማች፡፡ «እኔ ምኑን ከምኑ እንደማደርገው ግራ ስጋባ እሱ መጽሀፉን ይዞ ጀርባውን ሊሰጠኝ? አይደረግም!»

ልጇን አነሳች፣ ተነሳች፡፡ እያመናጨቀች ጡቷን አውጥታ ከልሷን አጎረሰች፡፡

«እኔ የሚገርመኝ የእናንተ ለእሱ እንዲህ መቆርቆር!»

«እኛ ማንን?»

እኔና ረቂትን እንዳለች ገብቶኛል!

«ታውቃለህ» እናቴ ጨኸት ሰምታ ስትመጣ ተመናጭቃ ወጣች፡፡

ረቂትም «ተይው ያንብብ» ብላት ይሆን? አበደች፡፡

ከአንድም ሁለት ሦስት ጊዜ ረቂት እኔጋ መጥታ አልቅሳለች፡፡ ያደረባት ስካር እየነዳት እንደመጣች ገብቶኛል፡፡

ስታለቅስ (ለማልቀስ ጊዜ አለው አልሁ)

«እኔ እህትህ አይደለሁ?» (ለመስፋደድም ጊዜ አለው)

«ታዲያ ለምን ለእሷ ብቻ ታግዛላችሁ?»

«ለማን?» አልኳት

«ታውቃለህ» አለችኝ እሷም፡፡ እህቶቼ ሥም ያለመጠራራት ጥላቻ ላይ እንደደረሱ ገባኝ፡፡ (ሥም ለመጥራት ጊዜ አለው)

ረቂት እንደተጎዳች የሚገባኝ በስካር ፈረስ ስሜቷን ልቅ ስትጋልብ ሳይሆን በተቃራኒው ነው፡፡ ፀጥ-እረጭ ባለ ፊት፣ ፀጥ-እረጭ ባለ አቀማመጥ፣ ፀጥ-እረጭ ብላ ቂጠማ እየቀነጣጠበች ስትፈዝ፡፡ ሻምበልን ታፈቅረው እንደነበር በተለይ እኔ አውቃለሁ፡፡ ስምረትን ለማግባት ወስኖ ሽማግሌ ሲልክ ሊለክትራክ ያዛት፡፡ ጥዝዝዝ. . ያሚል ድምፅ ከረቂት ሰውነት ሲወጣ ሰምቻለሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ደረቀች፣ ፈዘዘች፣ ኤሌክትሪካ ሲስቃት እየበረረች ከጡረታ ድልድይ ጠፋች። እሁድን አድራ ሰኞ ስትመጣ ቤተሰቡ ለወቀሳ ተሰበሰበ። ፊቷን አይተው ፀጥ! ፊቷ ላይ ምን አነበቡ?

‹‹ሳምንት ሽማግሌ ይመጣል፤ በፍጥነት ማግባት እፈልጋለሁ›› አለች።

ቤተሰቡ ላይ ኤሌክትሪኳ ተጋባ። ፀጥ! ስምረት ብቻ ከንፈሯን እንደገጠመች በሽሙጥ ጆሮ ግንዷ ላይ አደረሰች። ‹‹እሆሆሆሆይ!››

እውነት የማይመስለው እውነት ሆነ። ጡረታ ድልድይ በአዳዲስ አምስት መኪናዎች ቀልቧ ተገፈፈ። ሽማግሌዎቹ አምስት ሰንጋ መስለው እየተጎተቱ ግቢያችን ውስጥ ገብተው ቆሙ። ቤታችን ለሁለቱ ሰንጎች እንኳ አትበቃ።

እናቱ ከጉልት እየተንጠለጠለች መጣች ‹‹አዋረደችን? አዋረደችን? አታደርገውም! ሂድ አባትህን ከጠጅ ቤት ጥራ ጉድ! ጉድ! እኔ ሙች ይሆናል አልኩ...››

እዚያው ግቢ ውስጥ ለአምስቱ ሰንጋ ወንበር ድብዳብ፣ ሳጥን፣ ዳካ. . . ወጥቶ ውጤቱ የሚታወተው ድርድር ተካሄደ።

አባቱ ጠጁን እያጣጣመ ‹‹የሰርጉ ይባስ! ጣ!›› አለ።

‹‹ወጪው ላይ አትስጉ›› አሉ ሰንጋዎቹ ላባቸውን በእኩል እየጠረጉ።

‹‹ምነው? ነውርም የለ ባገራችሁ? እኛ ለልጃችን የምናንስ ሆነን. . .ጣ!›› አባቱ የግንባሩ ላይ ብዩን አቀባብሎ የበረደ ጥይቱን ሊተኩስ ተሰናዳ።

‹‹ሳይሆን! ሳይሆን!. . . ሁለቱም ሰርጉ እንዲሆን የፈለጉት በጋራ ሆቴል ውስጥ. . .›› ላባቸውን በስልት እየጠረጉ። የላብ ባንድ

አባቱ ግንፍል ግንፍል አለ። ‹‹የናንተን ባላውቅም የእኔ ልጅ ሆቴል አሳደገች ከሆቴል ተሞሽራ የምትወጣው ጣ!››

እናቱ ጎሽም አድርጋ አባነነችው።

ረቂቅ ግን የወንድ ወጥመድ ነበራት እንዴ? በዚህ ፍጥነት ከየት አገኘችው? የእኛ ቤተሰብ የአማጩን፣ የመተጫጨቱንና የሠርጉን ፍጥነት መቆጣጠር ሳይችል ቀርቶ ከተመልካችነት ያላለፈ ተሳትፎ አስመዘገበ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ረቂት ኤሌክትሪኳን ለፍጥነት የተጠቀመችበት ሆነች። ወዲያው አረገዘች፣ በዚያው ፍጥነት መንጃ ፈቃድ አወጣች፣ በኤሌክትሮኒክስ ባህሪ ኤሌክትሮኒክስ መሸጫ ሱቅ ከፈተች፣ በእልህ ብር በተነች፣

‹‹ድሮም ዕጣ ፈንታዬ እሷ ነበረች ጣ!›› ተባለች። ስምረት ሳትሞሽር ረቂት የእልህ ልጅ ወለደች። እዚህ ላይ የሴት ወገን መሸነፉን እያወቀ አተካራ ገጠሙ።

‹‹ጥንትም ሴት ልጅ የበኩር ልጇን ስትወልድ የምትታረሰው በእናቷ ነው ጣ!››

የረቂት ባል አምስቱን ሰንጋዎች ለአማላጅ ላከ። የላባቸውን ጠረጋ ትርኢት ሳያቋርጡ

‹‹ለልጁም ለእናቲቱም ሆስፒታል ተወልዶ ቀጥታ ወደቤታቸው ቢሄዱ ነው መልካም። ለምን ያላችሁ እንደሆን. . .››

አባቱ አቋረጠ ‹‹ልጄ፣ ማለቱ የልጁ ልጅ ወንድ ነው እንዴ? ጣ!›› ሊተኩስ የአቶበቶበ መሰለ። እኔ ስወለድ እንዳደረገው. . . ጠመንጃው ከጓደኛው ከጋሽ ተገኜ ተነጥቆ ለሞከሼው ለብዙን መሰጠቱን ሳይረሳ የቀረ አይመስለኝም።

‹‹አልተረጋገጠም›› የላብ ባንድ መሰሰ።

መቼም ወንድ ከተወለደ አባቱ ቢያጣ፣ ቢያጣ በአፍንጫው የሳባትን የግንባሩን ጥይት መተኮሱም አይቀር።

‹‹ታዲያ በወጉ፣ በደንቡ እናቷ'ጋ ተገላግላ ጣ! በእናቷ ብትታረስ አይሻልም?››

የላባሞቹ ባንድ ነገር ሳተ...

‹‹ሠፈሩ ለአራስ እንደማይሆን ሳትረዱት አትቀሩም...››

‹‹እከደከ! እናቲቱ የት ተወልዳ? ጣ! የት አድጋ? ጣ! ጡረታ ድልድይን መናቃችሁ ነው? አፈዛርጢዎች ናችሁና ጣ!›› አባቱ ለብስራት የቆጠባትን የግንባሩ ላይ ጥይት ለንዴቱ እንዳይተኩሳት ሰጋሁ።

ሁከት ተፈጠረ። ጡረታ ድልድይ ሠንጋ ተራ መሰለ። አባቱ በግቢ መቀርቀሪያ ሠንጋዎቹን ሳይመታ መሬት መሬቱን እያለ ነዳቸው።

እናቱ ብቻ ‹‹ወይ ቅሌት! ወይ ቅሌት!›› እያለች ሳትንቀሳቀስ ቀረች።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሡንጋዎቹ ያስነሱት አቧራ ለሶስት ቀን አየር ላይ ሲንገዋለል ከረመ።

‹‹እይ ቢዘን፣ አላረጀም'ነ›› ተባለለት። ከእናቴ እውትና ውጭ ለተከናወነው ጀግንነት ማታ አባቴ ተመጣጣኙን ሽሙት አከናወነ።

‹‹ትሊቱ የእኛ አይደለም ወይ? ንግግር በንግግር ይመለሳል እንጂ እማላጅ ላይ ዱላ ማንሳት የአባውንት ወጉ ነው? ደርሶ ጀግና መሆን. . . ››

‹‹ተይ እንጂ አንቺቱ፣ ጣ! ለኔ ጀግንነት ምን ታወጪለታለሽ? የት ቦታ አሳፍሬሽ አውቃለሁ ጣ!››

‹‹ገዘም በሉ አንተ መልቲ...››

ክንብንብ፤ አቧራ የማያስነሳ ሽሙት። ጡረታ ድልድይ ያልመዘገበው የአባቱ ሽንፈት. . .

. . .አባቱ አኩርፎ ይሁን አፍሮ ረቂት ስትወልድ ለመጠየቅ አልሄደም። ቤት መውለዷን ሲሰማ ለእመሉ ጎፈላ. . .

ረቂት አባቷ ለምን እንዳልጠየቃት ስትሰማ እሷም ጎፈላች። ሡንጋዎቹ ላይ አፍጥጣ ‹‹ወላጆቹን ሰደባችሁ፣ አፋቱኝ›› አለች።

ለመፋታት ጊዜ አለው ተባለች። ልጅቷ ክርስትና ትነሳ በሚል፦

ረቂት ክርስትና ባነሳች ማግስት ካልሄድኩ አለች። ባኣ እየተነፋረቀ ጡረታ ድልድይ መጥቶ አባቴ እግር ላይ ወደቀ። ባኢን ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነበር - ሌላ ሡንጋ። አባቴ ከሰንጋዎቹ አንዱ መስሎት አንድ አምስተኛ አቧራ ሊያስነሳ ሲል እናቴ ነገረችው። እግሩ ላይ የወደቀውን ነፍራታ ሡንጋ እያየ ጥቂት ተንጠረበበ።

‹‹ለስድስት ወር ብቻ ትቆይልኝ ልጅቷ እስክምትጠና›› አለ አባቴ እግር ስር ተቆልሎ።

‹‹ይሁን፣ ጣ!››

ማታ ከጠጅ ቤት መልስ ‹‹ልጁ ምንም እንኳ ሴት ብትወልድም አኩርታኛለች›› አለ ‹‹ጣ!››

‹‹ማን ያዋረደህ አለ?›› አለች ስምረት፤ ረቂት በሽምጥ እጭታ፣ በሽምጥ አግብታ፣ በሽምጥ አርግዛ፣ በሽምጥ ወልዳ፣ በሽምጥ ልፋታ ስትል ስምረት ገና ለሰርግ አንድ ወር ይቀራት ነበር።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ጣ›› ሸሸት፡፡

ስምረትና ሻምበል የሙት አመት በመሰለ ድግስ፣ በተቆራረጠ ዘፈን፣ የገጠር ጎጆ መውጣት አለናወኑ፡፡ ረቂት ከአራስ ቤት ወጥታ፣ ፀጉሯን ተሰርታ መኪና እየነዳች መጣች፡፡ የነፍስ ይማር ዝክር የመሰለውን መናኛ ብፌ ለመቋደስ የተሰለፉት አብዛኞቹ እናቶች የሀዘን ልብሳቸውን አላወለቁም፡፡ በሸጎሌ ጥይት ፋብሪካ ፍንዳታ ወደትነትና ብነት የተቀየሩ ልጆቻቸው ሁለት አመት ቢሞላቸውም፡፡ የእናቶቹ ስሜትና አካል ማቅ እንደለበሰ ነበር፡፡ ረቂት ከኋላ ተሰለፈች፡፡

አንዳች የበቀል ሰይፍ ስምረት ላይ አረፈ፡፡ ረቂት እንደግረሰ አማልክቶች በቀኗ ከስፍር በላይ ሆኖ ታየኝ፡፡ ነገር የማይገባው አባቱ ነጭ ጋቢውን ትከሻው ላይ ቆልሎ የልጁ ጋባዥ ሆነ፡፡ በግድ ጎትቶ ሙሽሮቹ አጠገብ አስተመጣት፡፡ ወደ ብፌው ሄዶ ምግብ በዝርግ ሰሀን ሞልቶ አመጣላት፡፡

የእህቶቹ የመጎዳዳት ትርኢቱ አስጠላኝ፡፡ የጠቢቡ ጥቅስ መጽናኛ እንደማይሆን ሆኖ ከፊቱ ተንከታከተ፡፡ ረቂት ውስጥ ይሄ ሁሉ ነበር? ሰው ሁሉ በትዝብት እያየኝ ሠርጉን ትቼ እራቅሁ፣ እራቅሁ፣ እራቅሁ. . .



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## ሦስት

## የአጎራባች ነገር

ከአንድም ሁለት ሦስቴ እናቴ ደብተራ እምጥታ ፀበል አስረጭታኛለች። ልጅ እግሩ ደብተራ የእነቹቹን ቤት ከእናቴ ላይ ተከራይቶ ከአባቴ ጋር ይኖራል። ወደነቹቹ ቤት ባየሁ ቁጥር የደብተሮቹ ሁኔታ ከዘመኔ ጋር አልገጥም እያለኝ እቸገራለሁ። አባቴ የሩፋኤልን ጉልላት የሚያክል ጥምጥም ከምረው ሳይ የትዙስ ያሬድ ባህላዊ ስዕል ድቅን ይልብኛል። መጀመሪያ ሰሞን ከሩቅ ሲመጡ ሊጥ የገነፈለበት ቡሃቃ የተሸከመ ሰው ይመስሉኝ ነበር። ሲቀርቡ የጥምጥሙ ደርዝ በስራ ፈት መነኩሴ የተነቀሰና እንክን እንዳይገኝበት የተለፋበት ሆኖ አገኘዋለሁ። የኒህ ደብተራ ግርማ ሞገስ ያለው ትከሻቸው ላይ ሳይሆን የጥምጥማቸው ከፍከፋት ላይ ነው። ሁለት ቀን ጥምጥማቸውን አውልቀው ባያቸው ቀለው ከልጃቸው አንሰውብኛል።

ልጅ እግሩ ደብተራ እያልጎመጎመ ጣሪያውን፣ ግድግዳውን ይረጭና ወደእኔ ያጨኀንቁራል። አባቴ ጥምጥማቸውን ሲያወልቁ ግርማቸው እንደሚገፈፈው ያለ እንከን እሱም ላይ አለ።

‹‹ክርስትና ስምህ?››

‹‹እንጃ›› ሆነ ብዬ አክብሮት እነሳዋለሁ።

‹‹አታውቀውም?››

‹‹ምን ሊያደርግልኝ እይዘዋለሁ?››

እናቴ በር ስር ቆማ ‹‹መረጊታ እሱን ሰው ብለው?››

‹‹አሀደማሪያም፣ ጥፋቱ'ኮ የእናንተም ነው። ክርስትና ስሙን እናንተ ከምትይዙ እሱን ማስጠናት ይበጅ ነበር።›› ፊቱና ንግግሩ አይዋሃድልኝም። ‹‹ያለክርስትና ስም የመንግሥተ ሰማያትን በር ማ ይከፍትልሃል? በል ያዝ መጥምቀ መለከት ነህ። የክርስትና ሥም አንድም ወልደ፣ ካልሆነም ገብረ ሊኖረው ይገባ ነበር። ይሄን ክርስትና ሥም ያወጣልህ ቄስ ተሳስቷል። ግን ይሁን። የክርስትና ሥምህ የመጥምቁ ዮሐንስ መንፈሳዊ ስም ነው። ይሄ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ቤቱን የምንረጨበው ማይ የገድሉና የተአምራቱ መጽሀፍ የተነበበበት ውሃ ነው። ስማሽ ወይ አሀደማርያም?»

«አቤት መሪጌታ»

«ለመጥምቁ መስከት ቅዱስ ዮሐንስ በጌታ የተሰጠው ቃልኪዳን እጅግ ልዩ ነው። የገድሉና ተአምራቱ መጽሀፍ የተነበበበት ውሀ ጌታችን ከተጠመቀበት ዮርዳኖስ እኩል ነው። የተጠመቀበት የሰማኒያ ዓመት ኃጢያቱ እንደምትሰረይለት ቃል አለ። ጸበሉ የተረጨበት ቤት ረሃብ፣ በሽታና ሐዘን… አይደርስበትም።»

«እስቲ ያድርገዎ» እናቴ።

አባቴ ብቻ «አባይ ቂስ» ይለዋል። «አባቴ አባይ፣ እሱ አባይ። አባይ ቂስ ገና ሲቀርበኝ ትከሻዬ ይነግረኛል ባክ»

«እዩ የበረሃ-ጂኒዎ መልካም ነገር ያዛርርዎታል፣» ትላለች ደብተራዋ እንዳይሰማ ድምጿን ገታ አድርጋ።

አባቴ ሲሳደብ ደስ ይለኛል። መሪጌታ ያለ ከመስለኝ ወጥቼ ፈገግ እልበታለሁ። እሱም የደብተራ ተንኮል ያለበት ፈገግታ ያሳየኛል። በድግምቱ ተማምኖ ይሆናል። አባቴ መኖር አለመኖሩን አረጋግጦ መሆን አለበት ድንገት እናቴን በክርስትና ስሟ ይጠራታል።

«አሀደማርያም፤ አለሽ?»

«አለሁ መሪጌታ» ትለዋለች

«ቃሪያይቱን፣ ሽንኩርቲቱን፣ ቲማቲሚቱን አንድ;ጋ ጎረድ ጎረድ አድርገሽ ለየንታ ሳኪልኝማ» ይላል። አባቱን የንታ እያለ እንደሚጠራ በኋላ ተረዳሁ።

እናቴ አንዳንዴ ለማንም ከማታቀምሰው ጉልት ተቀምጣ ከምትሰራው የአደባባይ ወጧ ጨምራ ትልክለታለች። የንታውን ቆሞ ያበላል።

አንድ ቀን እናቴ በአጥር ትጣራለች። «መሪጌታ፣ መሪጌታ»

«ማን መሪጌታ አደረሰው?» አለ አንድ ጎርናና ድምፅ፤ «እሜቴ፣ መሪጌታ ነኝ አልዎትን? አጀብ አጀብ እሱን እዚያ ማን አደረሰው? የማዕረግ ሥሙ ረድ ነው። ረድ ሠርዌ ይበሉት። በፊትም የአቡነ ኤርሚያስ ወጥ ቀማሽ ነበር። አሁንም ያሉ እንደሆን የእኔ ወጥ ቀማሽ፣ ቆሞ አብዬ ነው። ዳግም መሪጌታ አይበሉት እመይቴ።»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ደስ አለኝ። እስካገኘው ቸኮልኩ። የማሰረግ ምሥጡን ከመደበኛ ስሙ ደባልቄ በመግፍ ጠበኩት። አካሄዱ የራሱ ዜማ አለው። የአካሄዱን ስልት ተከትሎ ትከሻው፣ አንገቱና ጭንቅላቱ የየራሳቸውን ውዝዋዜ ይተገብራሉ። ከሩቅ ሲታይ ያስታውቃል። ይሄንን እንደቅርስ የሚቆጠር አካሄድ አባቴ ሳያስለምዱት አልቀሩም።

‹‹ረድ ሠርዌ እንደባለጌ ስተተተተት ብለህ ትሄድ ጀመርን በልናግ ተማር። የው እንዲህ አንገትህን ከእግርህ እኩል ወዝ‐ወዝ አድርገው። ከትከሻህ ደግሞ ኀብደድ ትልና ጭንቅላትህ ጥምጥምህን እንዳይከነብልብህ ቀጥ አድርገህ ለአመል ደፋ፣ ደፋ. . .›› አባቴ እንዲህ እያሉ አካሄዱን እንደዝማሚ የቄስ ስልት ሳያሲዙለት አልቀሩም።

አጠገቤ ሲደርስ ወረቀቱን አንበበ ‹‹ረድ፣ ረድ ሠርዌ›› አልኩት። ያቺን የደብተራ ተንኮል ቅልቅሉን ፈገግ ብሎ፦

‹‹ምቱረ ክሳድ መጥምቀ መለኮት›› አለኝ። በሚያውቀው ተሳድቦ በማላውቀው መሰደቡ ቆጠቆጠኝ። ምን ማለት ይሆን? ቃሉንም አልያዝኩት። ማብሸቂያ መሆኑን ግን ከፊት ገፅታው አውቄአለሁ።

የማይታወቁ ቃላት የማይታወቁ በቃቄን ሲኮሰኩሱኝ አደሩ። ማንበብም፣ መተኛትም አልቻልኩ። ምናልባት እንደድግምት ሆኖ በቃላት ትብትብ ማንበብና መተኛቴን አጥፍቶት ይሆናል። ወደ ረድ ሠርዌ ማደሪያ ቀልቤን ጥዬ ማልደ ‹‹እምምምምም…›› የሚል ድግምቱን እስኪጀምር ጠበቅሁ። ድግምቱን እርኩስ ሆነ ቅዱስ መንፈስ ሳይሆን እናቴ እንድትሰማው አድርጎ እንደሚያልጎመጉም አውቃለሁ። እናቴ በሰማች ሰዓት እንደ አስተዳሽ እጇን ጭኗ ላይ አድርጋና ተከናንባ በራችን ላይ ትቆማለች። ድጋሙ የሚጠናቀቀው ‹‹አቡነ ዘበሰማያት›› ተብሎ ነው።

ይሄን ጊዜ አባቴ ካደፈጠበት ይወጣና ‹‹ይሄ እንኳን መልካም ነበር ጣ! ‹አቡነ ዘበሰማያት› ስንደግመው የኖርነው ነው። አሁን ግን ሴጣን ሲያብል የደነገረው መሰለኝ››

እናቴ በአይኗ ትገሸልጠዋለች።

ገሃም!

‹‹አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ. . .›› ረድ ሠርዌ እናቴ ሙሉውን እንዳትይዘውና ብቻዋን እንዳትህልየው በመፍራት ይመስላል በሎቱን ነፋስ የወሰደው አስመስሎ ያጠፋውና ደግሞ በግ ያደርገዋል።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሲሳየነ ዘለሰዕትነ፣ ሀበነ ዮም ኀድግ...›› ጥፍት ደግሞ ዘሉሉ ቦግ ‹‹...እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ...›› ጥፍት፡፡ ሀሎቱ በዳንስ ቤት መብራት ስልት ጥፍት ብልጭ እያለ

‹‹...ሰላም ለኪ ቡሩክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርስኪ ተፈሥሒ ፍሥሕት... ወስአሊ ምሕረተ ኀበ ፍቁር ወልድኪ እየሱስ ክርስቶስ ከመ ይሥረይ ለነ ኀጣውኢነ ... አሜን፡፡››

‹‹አሜን!›› እናቴ፡፡ ለዚህ የማለዳ ድግምት እናቴ ወድዳ ሂሳብ ታወራርዳለች፡፡ ረድ ሠርዌ አፍታም ሳይቆይ፡-

‹‹አሀደማሪያም›› አላት፡፡

‹‹አቤት መሪጌታ›› ትላለች እናቴ፡፡

‹‹የቤት ኪራዩ መቼ ነው? ንገሪኝና የንታ ሲመጡ እንዳስታውሳቸው...››

‹‹አ-ዬ፣ እስዎ ዳይት መድገምና ጠበል መርጨት ከጀመሩ ወዲህ የተስተካከለው ብዙ ነው፡፡ እሱ ምን ያውጣና የተቀመጡበትን ልቀበል? ይተዉ አያስቸግሯቸው...››

ይሄንን አባቴ ከሰማ ያልጎመጉማል፡፡

‹‹በፊትም ጠንቋይ፣ አሁንም አባይ...›› እናቴ በአይኗ አፉን ብላዋለች ማለት ነው፡፡ ንግግሩ ይቋረጣል፡፡

የእናቴ ቁጭት እኔም ላይ የተጋባ ይመስለኛል፡፡ የደብተራውን ሁኔታ በአንክሮ እከታተላለሁ፡፡ ብልጠቱ ሲገባኝ ብስጭት እንጂ ሌላ የሚተርፈኝ የለም፡፡

‹‹አሀደማሪያም››

‹‹አቤት መሪጌታ››

‹‹እንሆ ከኢየሩሳሌም፣ ከቦታው የመጣ ትብዓ-ሚሮን፡፡ የጌታችን መቃብር ላይ ሳምንት ተቀምጦ ነው የሚመጣ. . .››

‹‹አ-ይ መሪጌታ፣ ምን አድርጌልዎት. . .››

‹‹በፊትም ጠንቋይ...››

አሁንም አባይ፣



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ቤታችንን የሚያደናይ፤ በእናቴ ግልምጫ የተቋረጠ የአባቴን ግጥም በራሴ አጠናቀቅሁት። የሚገርመው እኔና አባቴ ረድ ሠርዌን ለፀብ ስንፈልገው ያውቃል፤ አይገኝም። አንዳንዴ መንፈሱን እንደንሥር ለቅቆ ቁልቁል እያየን የሚያደባ ይመስለኛል። ስንዘናጋ ከች!!

ረድ ሠርዌን ከማግኘቴ በፊት ሻምበል ጠናጋሻው ቤቴ መጣ። የያዛቸውን ሁለት ዳጎስ ያሉ መጻሕፍት አልጋዬ ላይ ወርውሮ አረፍ አለ። እኔን በዚህ ሁኔታ ሲመለከት የራሱን ተመሳሳይ ዘመን እንደሚናፍቅ አውቃለሁ።

‹‹ምን አዲስ ነገር አለ? ጥሩ!››

‹‹ምንም፣ ሰሞኑን ከልቤ ያነበብኩበት ጊዜ ጥቂት ነው።››

‹‹ምነው?››

‹‹አንድ ደብተራ፣ እዚህ ጓሮ፣ የእነቹቹን ቤት የተከራይቶ...››

‹‹እ-ና››

እንድነግረው ሲገፋፋኝ ጉዳዩ ለወግ የማይበቃ ያህል ቀለሙ ታየኝ። ያውም ከፍታ ያለው ሀሳብ ከኔ ለሚጠብቅ ሰው ቢቸግረኝ...

‹‹ማርክስ ያለው ትክክል ነው እምነትን በተመለከተ። መብዝበዣ መሳሪያ ነው። ሥራ ጠል የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች የሰራተኞቹን ምንዳ አስፈራርተው የሚቀራመቱበት፤ አላማው ከምድርና ከቁሳቁስ እንቶፈንቶ የማያልፍ ተራ ማታለያ...››

‹‹ጥሩ›› አለኝ አቋርጦ።

‹‹ምኑ?››

‹‹እነ ማርክስ ያላዩት አንድ እውነታ ያለ አይመስልህም? የሰው ልጅ ሰላማዊ ኑሮ ለመምራት ከሚያየው ምድራዊ ሥርዓት ውጭ የማያውቀው፣ ምናልባትም የሌለ ሰማያዊ ሥርዓት እንደሚያስፈልገው?››

‹‹አልገባኝም››

‹‹ጥሩ››

‹‹ምኑ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እነ ማርክስ የሚመኙት ፍትሕ የሰፈነበት፣ ብዝበዛ የሌለበት፣ እኩልነት የተረጋገጠበት ዓለም ቢመሰረት የሰው ልጅ ሰላማዊና ደስተኛ ሕይወት የሚመራ ይመስልሃል? በእንደዚያ ያለ ኑሮ የሰው ልጅ ሪከቶ የሚቀመጠው ምድራዊና ሥጋዊ ብቻ ቢሆን ነበር። የሰው ልጅ ሰማያዊና መንፈሳዊ አፈጣጠርም አለበት። ባይኖርበት እንኳን የማይጨበጡት ሰማያዊና መንፈሳዊ ትርክቶች ብቻ መልስ ሆነው የሚያሳርፉት ልዩ ጥያቄ ውስጡ አለ።»

«ጥያቄውም ሆነ የአፈጣጠሩ ግንዛቤ በእነዚያ በዝባዦች ውስጡ ተከትቶ ከሆነስ? ማራገፍ ነው ያለበት ተሸክሞ መኖር? በነበረበት እንዲቀጥል መበየን የማመቻቸት ጊዜያዊ ብያኔ አይሆንም?»

«ጥሩ፣ ጥሩ» ጠናጋሽው ሲፈጥረው «ጥሩ» ማለቱን ይደጋግመዋል። «ጥሩ...በዝግመተ-ለውጥ ካየኸው የሰው ልጅ ነባር ድርጊያዎች ተፈጥሮው እንደሚሆን ይረጋገጥልሃል። ለምሳሌ ሴቶች ልጆቻቸውን የሚያጠቡት ወተት ከጡታቸው የሚፈልቀው የተፈጥሮ ድጋፍ ስላለበት ብቻ አይደለም። በወሰዱ ቁጥር የሚያጠቡት እነሱ ሴቶቹ ስለነበሩ ነው። ያ - ባይሆን፣ ሴቶቹ ሲወልዱ ወንዶች ቢያጠቡ ኖሮ የወንዶቹ ጡት ቀንጥሮ አይቀርም ነበር። ካልሆነ ወንዶች ደረት ላይ ጡት ምን ያደርጋል? ድርጊት ተፈጥሮ እንዲሆን እራሷ ተፈጥሮ ክፍተት ስጥታለች ማለት ነው።»

ለጠይቀው ስል በእጁ አስቁሞኝ ቀጠለ።

«የእምነትም ጉዳይ እንደዚያው ነው። የሰው ልጅ አምልኮን ከባፍ፣ ከመብረቅና ከወንዝ ጀምሮ በአማልክቱ በኩል እስከ ረቂቁ አምላክ የደረሰበት እረጅም የዘመን ጉዞ እሚታመን እንኳን ባይኖር ማመን ግዱ የሆነበት ተፈጥሮ ላይ ያደርሰዋል። ስለዚህ እውነት እንኳን ባይሆን በእውነት ሥም ውሸቱንም፣ ተረቱንም፣ አፈታሪኩንም... እያግበሰበሰ ሰላማዊ ኑሮ መምራት የሰው ልጅ የተፈጥሮ ግዴታው ነው። ለዚህ ይመስለኛል ቮልቴር እንዲህ ያለው "If there be no God, he should have been invented." የዚህ ዘመን የሰው ልጅ እዚህ አጣብቂኝ ውስጥ ሆኖ ይሰቃያል። እግዚአብሔር ካለ ማጥፋት፣ ከጠፋም ዳግም እንዲኖር ማድረግ»

ጠናጋሽው ሲያሳርግ ወይም በክርክር ሲረታኝ እንደሚሆነው ሁሉ ከባድ ፀጥታ ወረደብን። እኔ እትከነከናለሁ። ጭንቅላቴ ጠናጋሽውን በሀሳብ እንዲጋተር (በወቅቱ) ለአንድ ዓመት ከስድስት ወር ከሁሉም ነገር እርቄ መጻሕፍት ውስጥ ተደብቄአለሁ። ዛሬም ግን ሀሳብ ከማንሳትና እየጠየቁ ከመቆስቆስ ያለፈ በእኔ አሸናፊነት የሚደመደም ክርክር የለም። ከወደጠና ጋሽው እንዴት የከሸፈች ሳቅ አፈተለከች። በጉዳዩ ላይ በጥልቀት እያሰበ ነበር ማለት ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ኡሁ፣ ቮልቴር ለዚህ ዘመን እንደ ዮሐንስ መጥምቁ መንገድ ጠራጊ እንደነበር የሚያመላክቱ ብዙ ሀሳቦች አሉት...››

ቮልቴርም እንደእኔ ክርስትና ስሙ መጥምቀ መለኮት ይሆናል፡፡ ለዚህ ነው ጥሩ መንገድ ጠራጊ የወጣው፡፡ ፈገግ አልኩ፡፡ ግር በመሰኘት ሲመለከተኝ ‹‹ጥሩ›› አልኩት፡፡

‹‹አሁን ለተነጋገርንበት ጉዳይ ቃል በቃል ምን ይላል መሰለህ፡፡ ብልአለማዊነትን መቃወም ወይም ዘላለማዊነት እንዳለ መካድ ከሞላ ጎደል የጅላጅሎች ድርጊት ነው፡፡ ይሁንና ዘላለማዊነት ሥፍራው የትነው? የተወሰነ ቦታ ወይስ ሁሉም ስፍራ ይገኛል? ነው ወይስ የተወሰነ ሥፍራን በመያዝ የሚከናወን ጉዳይ አይደለም? ብላችሁ ብትጠይቁኝ እኔ የማውቀው ነገር የለም እላችኋለሁ፡፡ ሁሉን ነገር እንደራሱ ከራሱ አውጥቶ ፈጠረው? አላውቅም! የሚዳሰስና የሚገናዘብ ነገር ሳይኖረው ግዘፍ ይነሳል? አላውቅም! እኔ የማውቀውና የሚገባኝ በሬቱ ስለክብሩ መስገድ እንዳለብኝና ልክ ለመሆን መጣር እንደሚያስፈልገኝ ነው፡፡

‹‹ጥሩ፣ ይሄ ዘመን ብዙ አደናጋሪ ሀሳቦችና ፈጠራዎች የሞሉበት ጊዜ ነው፡፡ ጨርሶ ማመንም፣ ጨርሶ አለማመንም ሁለቱም ስህተት የሆኑበት፡፡ ይሁንና መስገድ እንኳ ቢያዳግት ክብር አለመንፈግና ለፍርድ ትክክለኛ መሆን ተፈጥሯችን ግድ ይለናል፡፡››

እንደ ጠናጋሻው ማሳመኛ ከሆነ አባይ ቁሶቹን አባይ መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ሳልሞክር ጠበሳቸውን፣ ስብከታቸውንና ከእስራኤል የመጣ ቅብዱ ማሮናቸውን መቀበል ግዴ ነው ማለት ነው፡፡ይሄ ደግሞ የፍልስፍና ጥበብ ግድ የሚለውን ሁሉን የመመርመር ዝንባሌ በስልታዊ ማፈግፈግ ገደል የሚከት ይሆናል፡፡ አንድ ተመራማሪ እምነትን ካልፈተሸ የሚመስለውን ከማይመስለው ለይቶ ካልበየነና አቋም ካልያዘ ምኑን ፈላስፋ ሆነ? የፍልስፍና ትምህርትስ ምኑን አስፈለገ? ያሰብኩ እየመሰለኝ ለፈለፍኩ ልበል? ጠየኩት ግን በመጨረሻዋ ጥያቄ ቀጥታ ወደጠናጋሻው የተኮሰኩ አስመሰለብኝ የፍልስፍና መምህር ስለሆነ...

‹‹ጥሩ›› አለ፣ የቅሬታ መልክ ሳያሳይ ጥቂት ጊዜ ወሰደ፡፡ ፈገግ ብሎ ‹‹ጥሩ፣ ጥሩ...›› አሁንም ጥቂት ጊዜ፣ አስጨንቂዋለሁ ማለት ነው፡፡ መንፈሴ ከፍ ለማለት ቃጣው፡፡

‹‹ቮልቴርን ብቻ ሳይሆን ሌሎቹንም ፈላስፎች በቁንፅል ለማስተዋወቅ መሞከር ችግሩ ይሄ ነው፡፡ ያቺ የተቆነፀለችው ብዙ ክፍተቶችን ትፈጥራለች፡፡ ከዚህ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

በፊት Religion and communism የሚል መጽሐፍ አምጥቼልህ ስለነበር ሳወራህ ያነበብከውን ታስታውሳለህ በሚል ግምት ነበር?››

‹‹አንብቤዋለሁ!›› ደግሞም እውነቱን ነበር። ግን የጠናጋሻውን ያህል በጥልቀት ላስታውሰው ያዳግተኛል። ይሄንን መናዘዝ ይኖርብኝ ይሆን?

‹‹ጥሩ፣ የጠቀስኩትን የተናገረው ስለኤደን፣ ስለእግዚአብሔር ባህርያትና ክብር በማብራራት ስታወቁት እንደ ሊብኒዝ ላሉ ሀሳባውያን ፈላስፎች ምላሽ ለመስጠት ነው። ቮልቴር በሳይንስና በዕውቀት የእምነት ጉዳይ እንዲመዘን ስለሚሻ ኒውተንና ሎክን ይመረኩዝ ነበር።››

ጥቂት ዝም ብሎ ከቆየ በኋላ በለበጣ ስቆ ‹‹መምህርነት ሞኝነት ነው። ጊዜና ቦታ አይመርጥም ትምህርት አደረኩት. . .››

‹‹አሪፍ ነው›› አልኩት ጉዝጓዜ ላይ የተጎዘጎዝኩበት ሁኔታ መጠነኛ ህመም እንዲሰማኝ ስላደረገኝ የአቀማመጥ አቅጣጫዬን እየለወጥኩ...

‹‹አንብቤዋለሁ ያልከው መጽሐፍ ላይ የውይይታችን መደምደሚያ አለልህ። የሩሲያ አብዮት ስልጣን ይዞ ከተቸገረበት ነገር ዋነኛው ጉዳይ እምነት ላይ የተካሄደው የባህል አብዮት ግቡን አለመምታቱ ነው። በመጨረሻ ሌኒን ከሞተ በኋላ እነጎርኪ ክርክሩን ለአደባባይ አበቁት። መከራከሪያቸው የሰው ልጅ የሥልጣኔ ታሪክ በእምነት መሰረት ላይ መገንባቱ ነበር። ‹ስለዚህ› ይላል ጎርኪ ‹ስለዚህ ለሩሲያ ሁሉን ነገር ጠቅልለው ለእሱ የሚይሰጡት ገለልተኛ ፈጣሪ ያስፈልጋል። ለመኖሩ ብቻ ዕውቅና ሰጥተን አምልኮውን በማጥፋት በራስ መተማመናችንን ማበልፀግ ከሥጋው ያመኛ ነኝ ከመረቁ አውጡልኝ አይነት ነው።››

ውይይታችንን ሲያዳምጥ የቆየ ሰው ያለ ይመስል ድንገት በሩ ብርግድ አለ። ስምረት ነበረች። ልጇን እንደታቀፈች በእንግሊዝ ንዴት ቁና-ቁና እየተነፈሰች አፈራርቃ አየችን። ለጠናጋሻው እኔ ስቅቅ አልኩ። ስትመናጨር ለእይታ እንኳ ወግ ታጣለች።

‹‹ታለ፣ እንተከካህ የትዳሬ ዐር። እንዳንተ መሬት ላይ ተጎልቶ መጽሀፍ ሲነዘንዝ እንዲኖር ነው ፍላጎትህ?...››

ታላቅ እህትነቷ እኔን እንዲህ ለመናገር ያበቃት ይሆን? ምን ተፈጠረ? ምን አየች? እኔን በመናገር እሱን ማሳቀቅ ትፈልግ ይሆን? አፈጠጥኩባት፣ ወደ ባኋ ዞረች!



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እንካ፣ ስትፈልግ ብላት›› ልጇን እንዘጭ አድርጋ አጠገቡ አስቀመጠቻት፡፡ ልጅቷ አሪሪሪ... ብላ አለቀሰች፡፡ በመርበትበት ልጅቷን አንስቶ ታቀፈ፡፡ እየተመናጨረች ከቤት ስትወጣ ልጁን እንደታቀፈ ተከተለ፡፡ ይሄ መከታተል መቆሚያው ገዳም ሠፈር አይመስልም፡፡ ሰዝንት አለም የምትቆናጠር ሴት መከተል የሻምበል ጠናጋሻው ዕጣ-ፈንታ የሆነ ይመስላል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አራት

## የበቀል ነገር

‹‹ምንድነው ይሄ ሠፈር?›› ሲል ረድ ሠርዌ መሆኑን አውቂ ተፈናጥሬ ተነሳሁ። የማይዘጋ ደጃፌን ከፍቼ ወደጓሮ ዞር አልኩ። ደብተራው በአረንጓዴ ገመድ መሰል ክር የተሰፋ ቡልኮ ተከናንቦ ወደ እግሩ ይንትታል። ከበረደው ለምን ከቤት ወጣ?

‹‹ምንድነው ይሄ ሠፈር?››

እኔን የሚጠይቅ መሰለኝና አፈጠጥኩበት።

‹‹ምንድነው ይሄ ሰፈር ጭር ያለው? የጡረታ ድልድይ ሆጥታና ቅዝቃዜ እጥንት ሰርስሮ ይገባል። የምውታን ጠባይ፣ ዝም፤ ቅዝቅዝ፤ መካነ መቃብር ውስጥ ያለሁ ይመስለኛል። እንዴት ነው ነገሩ? እሳተመለኮት ታቅሮ ቅዝቅዝ? እንደበተ ኢጋንንትን ወርሶ ፍዝዝ?...››

‹‹ቤት መከራየት የነበረብህ ገዳም ሠፈር ነበር፣ የማይፈዝ የማይቀዘቅዝ እዚያ ነው›› ቆቡን የቀደደው ለሙቀትና ለሁካት ሳይሆን ይቀራል? ይታወመኛል ብዬ ሳስብ...

‹‹እኔስ ብዬ ነበር›› አለኝ።

‹‹እ››

‹‹እኔ ብያለሁ፤ የንታ እምቢ አሉ። የጠሳሁትን መውደድ፣ የወደድኩትን መጥላት አይደል ሥራቸው? መቼም ሲፈጥራቸው መናጢ ናቸው።››

‹‹መናጢ?››

‹‹አዎ፣ ምን ክፋት አለው?››

‹‹አባትህን?››

‹‹አዎ፣ ተንኮለኛነታቸውን ለመግለፅ መሰሎኝ››

በጥንት-ጥንት ዘመን፣ ከጥንት ጥንት ሰው ጋር የማወራ መሰለኝ። የእነቸቸ ቤት ብቻዋን ተነጥላ እንደስምረት እየተመናጨረች ወደ ብዙ ትውልድ ወደኋላ. . .



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ምን ትሰራለህ?›› አልኩት ድንገት፡፡

‹‹እማራለሁ››

‹‹አባትህስ?››

‹‹የሩፋኤል አስተዳዳሪ ሆነው ነው እዚህ የመጣነው››

‹‹ታዲያ ለምን...›› አውቂ ዝም አልኩ

‹‹ታዲያ ምን ሆነ?›› ሐሳቤን ለመስማት ጆሮውን ሲያጋድል ቤቷም ከሸፈተችበት የወደኂላ ዘመን ቀረብ ያለች መሰለኝ፡፡

‹‹ታዲያማ...››

‹‹እ⊦ ታዲያማ?››

‹‹ታዲያማ ለምን ትለምናላችሁ?››

‹‹መች ለመንን፤ የት አየሽን?››

‹‹ኡይ፤ ቤት ኪራይ እከፍላለሁ ብሎ ካልከፈሉ ያው ስለማሪያም ባይባልም...››

ከት ብሎ ብሎኩው እስኪወድቅ ሳቀ፡፡ ግራ ተጋባሁ፡፡ ቀርባ የነበረችው ቤት ወደ ጥንት ዘመኗ የተመለሰች መሰለኝ፡፡

‹‹እነሆኝ፤ ምቱረ ክሳድ መጥምቀ መለኮት›› አለኝ፡፡ ባለፈው በዚህ ስያሜ ነበር የጠራኝ፤ የክርስትና ስሜን ትቼ የኂለኛውን ሁለት ቃላት ለመያዝ ደጋገምኩ፡፡

‹‹ምቱረ ክሳድ... ምቱረክሳድ...››

‹‹ቢገባህ ልመና አልነበረም›› የተንሸራተተ ብሉኮውን መልሶ እየተከናነበ፡፡ ‹‹እኛ በዘለዓለሚቱ ነፍስ፤ እናንተ በአመት ልብስ በእለት ጉርስ እንድንቻቻል መስሎኝ ኃጥእ እና ፃድቅ አድርጎ ያጣመረን፡፡››

ለጊዜው የምለው ጠፍቶኝ ዝም አልኩ፡፡ ረድ ሰርዌ ፊት ተረትቶ ዝም ማለት እንደ ጠናጋሽው ያለ አይደለም፡፡ እሳት እንደመታተፍ ነው፡፡ ዝም ማለቴን ተጠቀመበት፡፡

‹‹ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብኦ›› አለ፡፡

‹‹ምን ማለት ነው?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ቆይ ልተርጉምልህ እንጂ፤ እንደማይዘልቅህማ አውቀዋለሁ። ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብኦ ማለት «የሚያከማቹለትን ሳያቁ ይሰበስባሉ።» ማለት ነው። ስለአጋበስክ ያንተ አይሆንም።» የደብተራ ፈገግታውን አንበባረቀብኝ።

«ይሄንን አባትህ ያውቃሉ?»

«የንታ? ግዕዙን? ያስተማረኝ ማ ሆኖ?»

«አይደለም» አልኩት በአንድ ጊዜ ወደመርበትበት መግባቱ እያበረታታኝ።

«ታ-ዲ-ያ?»

«እየለመንክ እንደምታበላቸው፣ ቤት ኪራይ ሳትከፍል እንደምታኖራቸው...»

«እ?» መብረቅ ብልኩውን ገፈፈው።

«ለመመለስ አትቢኄንቅ፤ ካወቁ ስጠይቃቸው ይመልሱኛል። እንዳንተ በግዕዝ አስውበው»

ሮጦ የሰንሰል አጥራችን ላይ ተደፋ። «መጥምቀ መለኮት» የቆረጣት ተቀጥላ ስድብ መሆኗን አወቅሁ። «መጥምቀ መለኮት፣ በአቡነ ዘርአብሩክ ይገርሃለሁ ከየንታ እንዲታጣላኝ። በአቡነ አሮን፣ በአቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ፣ በአቡነ ሕዝቅያስ፣ በአቡነ ሳሙኤል ዘደብረ-ቆልዋን፣ በአቡነ...»

ቡብዙ አቡን ተኩበቤ በኩራት ወደ ክፍሌ ገባሁ። ኩራቱን ጠናጋሸው ቢያይብኝ አልሸማቀቅም? እንደዚህ ጥቃትን ነገሮችን ተከታትሎ ለማስተካከል ወይም ለመበቀል መሞከር የትልቅ ሰው ተግባር ነው?... ግን ረድ ሠርዌ እንደዚያ የተርበተበተው አባቱ ምን ቢያደርጉት ነው። በደብተራ ሽሙጥ ስለሚበልጡት (መናጢ ስለሆኑ) እያሸሚጠጡ ቁም ስቅሉን ያበሉት ይሆን? ወይስ የቅኔ መምህሩ ስለሆኑ በቅኔ ሁለት መልክ ያለው፣ ተፈልጎ ለመገኘት የሚከብድ ስድብ ያከናንቡት ይሆን? ወይምክ በድግምት በአውታረ-ነፋስ ተሰፈው በማንጠልጠል እንደ አምጉል ባሪያ አሳስመው ያሳድሩት ይሆን ይሆናል፤ ድግምት ከበለጡትማ የሚያዋርደውን መርጠው ይበይኑበታል እንጂ

«ረድ ሠርዌ፣ ተው ስንልህ አልሰማ በማለትህ፤ የተከበርኩትን የሩፋኤል አስተዳዳሪ እየለመንክ በማብላትህ፣ በነፃ በማሳደርህ አንድ ሳምንት የሚቆይ ፊስ እንዲቆራኝህ ስንል ፈርደንብሃል። ፍርዱ ተፈፃሚ ይሁን፣ አጋንንታዊ መዝገቡን ዘግተን ወደ እንጦሮጦስ መዝገብ ቤት...»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ከዚህ በኋላ ረድ ሠርዌ በተቆራኘው ሬስ እየታጀበ ‹‹ምንድነው ይሄ ሠፈር ሙቀትና ጩኸት የበዛው?›› ማለት ይጀምራል፡፡

በገዛ ቀልዱ ሳቅሁ፡፡

ይሁንና እናቴ ስትመጣ አፍታም አልቆየች ‹‹ታሰ? አንተ? ምንድነው? መሪጌታን ምን አልካቸው?...››

‹‹ምን አልኩ?›› ከኋላዋ ረድ ሠርዌ ብቅ አለ፡፡

‹‹በጡቴ ይገርሃለሁ...››

‹‹ምን አልኩ?›› ነገሯት እንደሆን ለማረጋገጥ፡፡

‹‹ምንም ይሁን ካባታችው ጋር እንዳታጋጫቸው፡፡ እንደአንተና አባትህ የሥጋ ዝምድና መሰለህ? አይደለም! በጡቴ፣ በጡቴ ይገርሃለሁ...››

አባቴ በጡቱ እንዳይማፀነኝ ተፈጥሮ ሳይሆን ድርጊት ያለማከናወኑ አግዶታልና የእናቶች ብቻ ማስማያ ሆኖ መቅረቱ ነው፡፡

‹‹ታሰ? አንተ?...›› መማፀኗን እንደአዲስ ከጀመረችበት ልትቀጥል እንደሆን ተሰማኝና አይኔን ጨፍኜ ‹‹ምንድነው? መሪጌታን ምናልካቸው?›› የሚል ጠበኩ፡፡

‹‹በጡቴ ስልህ? ኧረ ተው አንተ ልጅ›› እናቴ ጎርምሼባት ከመቆጣት ወደ በልመና ማግባባት እንደተዛወረች ገባኝ፡፡

‹‹እሺ፡፡››

‹‹ሙች በለኝ፡፡››

‹‹አባቴ አያውቁም ስላለኝ እጠይቃቸዋለሁ አልኩ እንጂ ሰብቅ አልነበረም፡፡››

‹‹ሙች በለኛ፡፡››

‹‹ሙች፡፡››

‹‹እሰይ›› ረድ ሠርዌ በነባሩ በአባቶቻችን ስልት እየተራመደ መጥቶ ፊቴ ተገተረ፡፡ በርከክ ብሎም የእርቅ መተቃቀፉን አከናወነ፡፡ ሁኔታው የደብተራ ብልጠት የለበትም፡፡ እውነተኛ ፍርሃት ያስከተለው እውነተኛ መደንገፅ ይታይበታል፡፡ አባቴ ሽፍጡን ሲሰሙ ምን አይነት ቅጣት ቢወስኑበት ይሆን?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ማወቅ አጓጓኝ። ረድ ሠርዌ ምንም ሳይናገር ተነስቶ በነባር ስልቱ ወደ እናቱ ተመልሶ ተያይዘው ወጡ።

ረድ ሠርዌ አደነጋገጡን አይቼ እናቱን በጥቃቅን የጥቅም ጉዳይ ወጥሮ መያዙን ያቆማል ብዬ ገምቼ ነበር። ግን አንድ ቀንም ሳያድር ቀጠለ።

‹‹ምንድነው ይሄ ሠፈር? ቁር ከማለቱ መቀዝቀዙ፣ እትትትትት... ፀጥታውና ቅዝቃዜው አጥንት ሠርስሮ ይገባል። አሀደማሪያም፣ አሀደማሪያም...››

‹‹አቤት መረጊታ፡፡››

‹‹በዚህ ብርድ የንታ ሰውም አይሆኑ። እስቲ ተልባ ስፈሪልኝና አመስ፣ አመስ አድርገሽ እቴቱ ትውቀጥልኝ። እሱ ነው ለብርድ መዳኒቱ። ታዲያ ተልባን አጋንንት ይወደዋል፣ ምች መስሎ እንዳያጣፋሽ ጥሪኝና እኔ እማትቢ አወስደዋለሁ። አቤት! አቤት ከቅዝቃዜው ቁር ማለቱ...››

ስለምን እቴቱን በክርስትና ስሟ እንዳልጠራት ገረመኝ። ነው እቴቱ ክርስትና ስም የላት ይሆን?... ያም ሆነ ይህ የረድ ሠርዌ ድርጊት ብቻ ሳይሆን በእኛ ላይ ያለው ንቀትና ሥድብ ቀጥሏል ማለት ነው። አንዳች ግሰገ ተናግሮ ሲተረጉም ምን ነበር ያለው?

‹‹ለማን እንደሆነ ሳያውቁ አጋብሰው ትተራቸውን ይሞላሉ›› በሱ ቤት እናቴ ጉልት ጎልታ የምትውለው ለማጋበስ ነው። ግንኮ ከሳምንት ሦስት ቀን ብትሰራ አይበቃት ይሆን? አራቱ ቀን ማጋበስ ይሆን?... እናቴ የጉልት ንግዷን የምትፈልገው ሀብት ለማጋበስ ሳይሆን ለሥራው ፍቅር ያስመሰለባት አንድ ታሪክ አላት። ረቂቅ ጉልት አትስሪ ስትፈልጊ ዘመናዊ ሱቅ ልክፈትልሽ እያለች ስትለምናት እንቢ ብላለች። ያም ሆነ ይህ ረድ ሠርዌ ሌላም ብሏል። እኛ ኃጢያተኞች እሱና አባቱ ፃድቆች። ከማልኩበት ውጭ ከአባቱ ጋር የሚያጋጭ ሌላ ሰበብ ማፈላለግ ያዝኩ። አገኘሁ።

ትዝ ይለኛል አባቱ በቅርሳዊው የአባቶቻችን አካሄድ የጡረታ ድልድይን ቀጭን አባራማ መንገድ ሲያቆራርጡ የዘመንን ድልድይ ፉት ብዬ ፊታቸው ተገተርኩ። እግራቸው ያስነሳችውን ስስ አቧራ በእጃቸው እያባረሩ አጨንቀሩብኝ። ፊታቸው ስገተር የጥምጥማቸው ግርማ ሞገስ ተጫነኝና አቀረቀርኩ። እግራቸው በኪሎ ሜትር ሳይሆን በዘመናት የሚቆጠር አቧራማ መንገድ በማቆራረጡ የሞተ ዛፍ ግንድ መስሎ ህይወት አይነበብበትም። እንግዲህ ረድ ሠርዌ ማታ ማታ አጥቦ የሚስመው ይሄንን ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ምነው? ምን ሆነ? የእመይቴ ልጅ አይደሉም እንዴ? እመይቴ ምን ሆኑ?...›› ጥያቄዎች አከታተሉብኝ።

‹‹አይ ደህና ናት። አንድ ግእዝ ልጠይቆት ነበር››

‹‹ጥሩ፣ ጥሩ ይበሉዋ፣ ይገለቱ...›› ብለው የቤታቸውን መንገድ መገለጥ ጀመሩ። ከቅድመ አያቶቻችን ጋር በተአምር ተገናኙ፤ በተአምር ከጎናቸው የምራመድ መሰለኝ፦

‹‹ምቱረ ክሳድ ምን ማለት ነው?››

‹‹ማነው እንዲህ ያለው? ማነው እንዲህ የተባለው?›› ንግግራቸው እንደአተያያቸው ማጨንቆር አለበት።

‹‹አይ ክርስትና ስሜን ተከትሎ ነው።››

‹‹ክርስትና ስምዎ ማነው?›› ረድ ሠርዌ ያላከበረኝን አባቱ በእንቱታ ያስተናግዱኝ ጀመር።

‹‹አ-አ ክርስትና ስሜ መጥምቀ መለኮት ነው። እኔ ግን የፈለኩት የተከታዩን ትርጉም ነው።››

‹‹ይሰሙኛል? ይያያዛል፤ ማነው ይኼን ያለ? ከቶ እያወቅሁት መጠየቄ እኔውም... ረድ ሠርዌ፣ ረድ ሠርዌ፣ ረድ... ይሄማ የሥራ ቤት ተንኮል ነው። የተስተማረ ይሄን አያደርግም፣ ረድ ሠርዌ...››

‹‹የንታ እነሆኝ›› እያለ ከቤት ሲወጣ፣ ካባቱ ኋላ እኔን አየኝ። ድንጋጤ መብረቅ ሆኖ እኩሌታ ሰነጠቀው።

‹‹ይምጡ›› እሉኝ ዘወር ብለው። ገባን። ቤቱ በተልባ ብጥብጥ መአዛ እና በቁርበት ሽታ ታውዷል። ረድ ሠርዌ ከድንጋጤ መብረቁ ገና አልተላቀቀም።

‹‹የሥራ ቤት ባለሟልነቱ፣ ምግብ ቀቃይነቱ፣ ቆሞ አብይነቱ አልለት ብሎህ እንጂ የተማረ ሰው እንዲህ ያለ የክርስትና ስም ያወጣል? እንዲህ ያለ ሟርትስ ከክርስትና ስም ጋር ያዳብላል? ምቱረ ክሳድ... ና-ና ወዲህ›› በርጩማ ላይ ቁጭ ሲሉ ረድ ሠርዌ በተከላተፈ ቤተክህነታዊ አረማመድ ተጠግቶ በመንበርከክ ጭናቸው ላይ በደረቱ ተኛ፤ ያልጠበኩት ነበር። ረድ ሠርዌ በአባቱ እንደአሚረካውያን የልጆች ቅባት ዘዬ ጭን ላይ ተኝቶ ቲጡን ሊጠበጡብ?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የረድ ሠርዌ አባት ልጃቸው ጭናቸው ላይ በአግባቡ መደላደሉን ካዩ በኋላ ጋቢያቸውን ሰቅስቀው አወሰቁና ለእኔ ሰጡኝ። በሽቱ ተጠምቋል። ካኪ ሸሚዛቸውን እጅታ ሰብስበው ክርናቸውን ወደልጃቸው ጀርባ ደገኑ። የክርናቸውን ጉጥ ከላይ ለቀቀው ሀይበል ቢሉት ከሠርዌ ሆድ የተጠራቀመ አየር አፈተለከ። በክርን ሲደግሙት

‹‹ሀ-እ›› አለ

አባቱም እንደ ጌሾ ወቃጭ ያቃስታሉ እሱም ያቃስታል።

‹‹ሀ-እ››

‹‹ሀ-እ››

‹‹ሀ-እ››

‹‹ሀ-እ››

ሲበቃቸው ጋቢውን ከእኔ እየተቀበሉ። ‹‹በል ተነስ፣ እንዲህ ያለ የሥራ ቤት ተንኮል ዳግም እንዳልሰማ፣ ተነስ እንጂ!›› ተቆጡ።

ረድ ሠርዌ እየተወለጋገደ ተነሣ።

‹‹እግዚሃር ይባርክህ›› ሲሉ መረቁት።

‹‹አሜን›› አለ በተወለጋገደና ትንፋሽ በበዛው አኳኋን... ‹‹እ-ሁሁሁሁ...››

‹‹ንሳ፣ አሁን ለሳቸው ተስረ መስረቱ አንስተህ ሟርቱን ንገራቸውና ይቅርታ ጠይቃቸው። እኔ ነገ አረጋግጣለሁ።››

‹‹እ-ሺ›› አጎንብሶ ያንን የሞተ ግንድ እግራቸውን ሳመ። ከግንዱ ላይ ወደ ከንፈሩ የተጋባ ጥቂት አልጌ አፉ ላይ ያየሁ መሰለኝ።

‹‹የንታ፣ ተልባ በጥብጫለሁ ልስጦትና ልሂድ?››

‹‹ይሁን፣ ስትመለስ ይደርሳል።››

ወጣን። እየተሽመደመደ ወደ እኔ ቤት መራኝ። ይወቅሰኛል ብዬ ስጠብቅ አባቱ ፊት ያሳየውን አክብሮት ሳያጓድል ማብራሪያውን ቀጠለ፦

‹‹እንግዲህ ምቱረ ክሳድ መጥምቀ መለኮት ማለቱ ትልቅ ስህተት ነበር። የንታ እንዳሉት የሥራ ቤቶች ተንኮል አለበት። እንጂማ እንደኔ መስተማር እንዲህ ያለ ሟርት ከክርስትና ሥምህ ጋር ማጣበቅ አልነበረብኝም።››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ምንድነው ሚርቱ?››

‹‹ልመጣ ነኝ፤ እንዳልኩት መጥምቁ መስኮት ቅዱስ ዮሐንስ የሚታወቅበት ተቀጥላ ስሙ ነው። እኔ መናጢ ነኝና የጠማቂውን ክብር፣ የተገባለትን ቃልኪዳን አውስቼ ከክርስትና ስምህ ጋር ማገናኘት ሲገባኝ መጥፎ ዕድሉን ወደአንተ ለማምጣት ምቱረ ክሳድ ብያለሁ››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹ልመጣ ነኝ›› በአባቱ ክርን የደቀቀ ወገቡ ስላልቻለ አልጋው ጫፍ አረፍ ብሎ በረጅሙ ተነፈሰና ቀጠለ፡-

‹‹እንግዲህ የመጥምቁ መስኮት ቅዱስ ዮሐንስ ታሪክ እንደሚያስረዳው...›› ተሰላቸሁ።

‹‹ታሪኩን አውቃለሁ የቃሉን ፍቺና እንዴት ሚርት እንደሚሆን ንገረኝ›› እኔም ጆርባዬን በክርን እንደተደቆስኩ ሁሉ መጥመልመል ተሰማኝ።

‹‹ልመጣ ነኝ››

‹‹ና››

‹‹እኮ ልመጣ ነኝ››

‹‹በቃ ትርጉሙን ብቻ ንገረኝ››

‹‹ትርጉሙማ አንገቱ የተቆረጠ፣ የተቆረጠ አንገት ያለው እንደ ማለት ነው። ቅዱስ ዮሐንስ እንደምታውቀው የሞተው አንገቱን በሄሮዳድያ ልመና፣ በሄሮድስ ትዕዛዝ ተቆርጦ ነው። ነገር ግን የዮሐንስ ራስ ቢቆረጥም ክንፍ አውጥቶ ከሄሮዳድያ እጅ በማምለጥ እንደበረረና አስራ አምስት ዓመት እንዳስተማረ ገድሉ ይነግረናል።››

‹‹ሉና? ሚርቱ የእኔም ጭንቅላት እንዲቆረጥና ክንፍ አውጥቶ አስራ አምስት አመታት እየበረረ እንዲያስተምር ነው?››

‹‹ክንፍ ማውጣቱ፣ መብረሩና ማስተማሩ ቢቀርም እንዲቆረጥ በስያሜ ምሪት ሲደጋገም እውነት ይሆናል ነው የየንታ ስጋት።››

ዝም አልኩ። በማይገባኝ በጥንት አስተምህሮት፣ ከጥንት መምህራን ጋር የምዳረቅ መሰለኝ። ስንትና ስንት ዘመን ወደኋላ?...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ይቅርታ አደረክልኝ? እባክህ? በፊትም ስምህን ያቆራኘሁት ‹‹እስመ ግብሩ ይመርሖ ኀበ ስሙ›› እንዲል ቤትህን ዘግተህ በአርምሞ መቀመጥህን አይቼ ‹‹ዘአርምሞ›› ከሚለው ጋር ነበር››

‹‹ይሄም ሚርት ነው?››

‹‹አይደለም፡፡ በጥንት ዘመን አቡነ ሳሙኤል የተባሉ ጻድቅ ነበሩ፡፡ በኣታቸውን ዘግተው ለረጅም ዘመን በአርምሞ አጋንንትን ስለቀጠቀጡ የሚታወቁት አቡነ ሳሙኤል ዘአርምሞ በሚለው ነው፡፡ ታዲያ አንተም ትምህርትህን አቋርጠህ ቤትህን ዘግተህ...››

‹‹ይሄንንም ከአባትህ አረጋግጣለሁ...››

‹‹በዚያ ደረቅ ክርናቸው ከደገሙኝስ ጭርሱኑ ሽባ መሆኔ ነው፡፡ ከእንግዲህ ወደሳቸው አትሂድብኝ፡፡ ዘአርምሞ በማለቱ አሚርቹ እንደሆን በእኔ ላይ ሱሱሱ ይዙር፤ በአቡነ ዘርአቡሩክ ይገፎሃለሁ፤ በአቡነ አሮን፣ በአቡነ...››

‹‹እሺ...እሺ...››

‹‹ይቅርታ አደረክልኝ?››

‹‹አዎ፤››

‹‹በል ሻይ ግዛልኝ፣ ወደ ሩፋኤል ማርገኛ ሄደን ሻይ ግዛልኝ፡፡››

እመል እንጂ ክፋት እንደሌለበት ገባኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## አምስት

## የህልም ነገር

በህልሜ ጭንቅላቴ ከአንገቴ ተለያይቶና ክንፍ አውጥቶ በጡረታ ድልድይ አናት ላይ እንደደመና ሲያንገዋብብ አየሁ። የጡረታ ድልድይ እናቶች በመገረም አንጋጠው ሲያስተውሉ በምዕት ቀን የተከነነ ነፍሳት ይመስሉ ነበር።

በእንትልፍ ልብ እራሴን አፅናናለሁ...

‹‹...ማየቱም፣ መናገሩም፣ መስማቱም ያለው ጭንቅላት ላይ ነው። የሰው ልጅ ምን ሲሆን ከአንገት በታች ተንዘላዝሎ ተፈጠረ? ቢቀር እጅና እግር ነው፣ ለእሱም ቢሆን ክንፍ አለ፤ ኧረዲያ መኖርስ ከአንገት በላይ...››

ህልም ሥር የሰደደ ድብቅ ፍርሃት እንደሆነ በራሴ አረጋግጫለሁ። ረድ ሠርቄና አባቴ በእኔ ሟርት ሲወራከቡ፣ ነገሩን ችላ ያልኩት መሰልኩ እንጂ ፍርሃትስ ነበር ማለት ነው፤ ካልሆነ...

የጭንቅላቴ አክናፍ ደክመው አየሩን አልቀዝፍ ሲሉብኝና መውደቂ እርግጥ ሲሆን የጡረታ ድልድይ እናቶች ‹‹ተዘጋጅ›› እንደተባለ ስልፈኛ ንቃት ታየባቸው። ምን ሊያደርጉኝ እንደሆን ባላውቅም ፍርሃት አደረብኝ። መቅዘፊያ እንደሌላት ጀልባ ጭንቅላቴ በንፋስ እየተገፋ ሲሄድ ያስፈሰፉት እናቶች ይንቀሳቀሱ ጀመር። አቅጣጫውን እያማተሩ ሲደርሱ ጭንቅላቴ ሊወድቅ እኩል ሆነ። ለመያዝ ሲሻሙ ብርድ ልብሴን እንደመቃብር ድንጋይ በርቅሼ ተነሳሁ። ፍርሃቱ አለቀቀኝም። ቀን ከንዘንዘኩበት፣ ማታ ካሸሉብኩበት ምንጣፍ ላይ ተነስቼ በሩን ዘጋሁት። ሰውነቴ በፍርሃት ይንቀጠቀጣል።

‹‹የህልም ዓለም ፍርሃት ስለምን ወደ እውን ዓለም ፍርሃትነት ይሸጋገራል?›› ስል እራሴን ጠየኩ። መንፈሳችን የታበተበት የሞት ፍርሃት ልኩ የሚታወቀው በእውን ዓለም ማገናዘብ ሳይሆን በህልም ዓለም ደመ ነፍሳዊ ድንጋጤ ውስጥ ነው። የእኔ መኖር ለእኔ ሆነ ለተቀረው አለም አስፈላጊነቱ እምን ላይ ነው? እስከመቼስ ከህልም ዓለም ወደ እውን ዓለም ፍርሃት ሳመላልስ እኖራለሁ?...

...አንዳች የሚስቅብኝ ህቡዕ ልቡና መርማሪ አካል አንዳለ ተሰማኝ። ስለስንፍናዬ በፊቱ ሊያሳፍረኝ እየሞከረ እንደሆነ የገባኝ መሰለኝ። ያ ልቡናዬን



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የሚበረብር ኃያል ሀቡዕ አካል እርሱ ማነው? ልቡናን የመፈተሽ ስልጣን ማን ሰጠው? እራሱ የሥልጣኑ ሰጪና ተቀባይ ይሆን? ሰጪና ተቀባይ አንድ የሆነበት አካባቢ እንዴት ያለ ፍትህ፣ ንዕህናና ቅድስና ይኖራል?... ይሄ የሰው ልጅ የአፈጣጠር ትብታብ ነው፡፡ ሰጪና ተቀባይን፣ አልፋና ኦሜጋን፣ ግዝፈትና ረቂቅነትን በአንድ የሚያዳብል የሰው ልጅ ተንኮል ብቻ ነው፡፡ ግዴላችሁም፣ ‹‹ኑ በአካላችን በአምሳላችን እንፍጠር›› ያለው ፈጣሪ ሳይሆን እራሱ ሰው ነው፡፡ ‹‹ኑ እግዚአብሔርን በአካላችንና በአምሳላችን እንፍጠር››

ከሆት ተነስቼ እምንጋ እንደደረስኩ ጠፋኝ፡፡ ይሁንና ፍርሃቱ ጠፍቶ በሬጌ ተንደርድሬ በመዝጊያቱ በራሴ ላይ ሳትሁ፡፡ መንፈሴ ተዛና... ለማንበብ አኩበኩብኩ፡፡ ወረፋ የሚጠብቁ ብዙ መጻሕፍት አሉብኝ፡፡ አንዳንዶቹ ጀምሬአቸው መንፈሴን ስላጨፈገጉብኝ የተውኳቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የአልበርት ካሙ "The Plague" ገና ስጀምረው በአይጦች ትርምስ ሲሞላ አቆምኩት፡፡ ሌላው ስሙ የማይያዝልኝ ሩሲያዊ ደራሲ፤ እንግሊዝኛ ተናጋሪዎች በቋንቋቸው ስሙን ሲሰሩ ሳያበላሹበት አይቀርም፡፡ SOLZHENITSYN (ሶልዘኒትሳይን) ይባላል፡፡ "Cancer ward" ይሄም መጽሐፍ ያው ነው፡፡ ተስፋ የሌለው የነቀርሳ ታማሚ፤ መጨረሻውን በመፍራት ተውኩት፡፡ ሦስተኛው የብርሃኑ ዘሪሁን ሦስቱ ማዕበሎች ናቸው፡፡ ረሃብ? ወደኋን፡፡ አንዳንዶቹን መጻሕፍት ተራ የማስጠብቃቸው የአንድ ደራሲ ሥራዎችን አከታትዬ ላለማንበብ ነው፡፡ አንዳንድ ደራሲዎች ደግሞ አንቀፅ የሌለው ሃምሳ ስድስት ገፅ ይፅፋሉ፡፡ ለምሳሌ ፈረንሳዊው ፈላስፋ ሳርት እና አየርላንዳዊው ጆምስ ጆይስ፡፡ ተራራ ወጪ አይደለሁም፤ ገና ዳገት እንዳየሁ ሃሞቴ ፍስስ ይላል፡፡ አንቀፅ ያልገባበት ፅሁፍ ደረቱን የሰጠ አቀበት ነው፡፡ አዲዮስ!

ያልተነበቡ መጻሕፍት የሚቀመጡበት ጠረጴዛ የዕዳ መዝገቤ ሆኖ ይወቅሰኛል፡፡ እንደ የንታ ጥምጥም ከርከም ያለ አመል ያላት የሳጠራ ሼልፍ የድል መዝገቤ ሆና ብሥራቱን ትለፍፋለች፡፡ አንብቤ ባልገቡኝ እንደ ጉርጂፍ እና በርትራንድ ራስል ያሉት ፀሐፍያን ላይም ሥራዎቻቸውን አንብቤ በመጨረሴ ብቻ እኩራራለሁ፡፡

‹‹አቤት ይሄ ሠፈር፣ አቤት ይሄ ሠፈር ቍርታውና ቀፈኑ ጆሮ ይበጥሳል...›› በሰፈሩ ላይ እንዲህ የሚተናባው አባቱ ቀድመው ወደ ሩፋኤል ሲሄዱለት እንደሆን ገብቶኛል፡፡ ‹‹ህልው የሚኖርበት አይመስልዎ? የምውታን ጠባይ፣ የምውታን መንደር...››

ድምፁን አጥፍቶ ከፀለየ በኋላ መወትወቱን ቀጠለ፡፡ ‹‹ቢ-የእንግሊዝኛ ሁለተኛ ፊደል



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ቢኤ- የመጀመሪያ ዲግሪ/ኅብረተሰብ ሳይንስ ትምህርቶች

ባብል- ጫጫታ፣ ፍልትልትታ/ለወራጅ ውሃ መንተባተብ/ መዘላበድ መወሻከት...››

በቶሎ ተማሪ ስለት ዘመናዊው ዕውቀት ላይ ለመድረስ በመሞከር ላይ ነው:: ከትናንት በስቲያ እኔ ቤት መጥቶ፣

‹‹ሠላም ለጊርጊሴኖን፣ ሠላም ለአልአዛር ዘአርምሞ›› ሳፈጥበት ቀጠለ::

‹‹እሱን የንታጋ ሄጄ አጣራለሁ›› ስለው ቀልድ እንደሆነ ገብቶት

‹‹እሳቸውጋም አያደርስ፣ አዲስ ኪዳንህን መግለጥ ነው:: አልአዛር ዘአርምሞ በእቱን የተከላት ጊርጊሴኖን ውስጥ መሆኑ ያስከፋል?››

ከእያት ቅድም አያቶቼ ጋር በመንፈስ ተገናኝቼ የማወራ ያክል ይሰማኛል::

‹‹አማርኛውስ ይሁን የእንግሊዙ አፍ ገብቶህን ነው የምታነበው?››

‹‹ቀላል ነው::››

‹‹እንዴት? ለስሙ አስረኛ ደርሻለሁ ግን አይሆንልኝም::››

‹‹ቃላት ከጠፉ መዝገበ ቃላት ላይ መፈለግ ነው::››

መዝገበ ቃላቱን ተቀብሎ በእጁ ሲመዝናት አሳቀኝ:: ‹‹አሁን ይቺን ሸምድጀ ብይዛት እንግሊዝ አፍን ዝም ብዬ ማንበብ ይሆንልኛል?››

‹‹ይሄን ሁሉ ቃላት መሸምደድ አይከብድም?››

‹‹ይሄን?››

‹‹እ››

‹‹ሳምንትም አይፈጅብኝ›› ብሎ ተዋሰኝ::

ትናንት የ‹‹ኤ›› ክፍል ቃላትን ጨርሶ ዛሬ ‹‹ቢ›› መግባቱ ነው:: እንዴት እንደሚያጠና ለማየት የቀረቀርኩትን በር ከፍቼ ወጣሁ:: ባለአረንጓዴ ክር ንቅሳታማ ብሉኮውን አጣፍቶ ቀጥ ብሎ ቆሞ መዝገበ ቃላቷን እንደዳዊት ይዞ ያነበንብና አይኑን ጨፍኖ ይደግመዋል:: ብርዱ አያስቆምም:: ለመግባት መለስ ስል እናቲ ነጠላዋን መስቀለኛ አጣፍታ በሯ ላይ ቆማለች:: የእንግሊዝ አፍ ቃርሚያው ፀሎት ስለመሰላት አይኖቿን ጨፍና እጆቿን በትህትና ትወዘውዛለች:: ሀዘንና ሳቅ ስለተቀላቀሉብኝ ቶሎ ወደ ውስጥ ገባሁ::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አፍታም ሳይቆይ ሀዘኔታዬና ሳቂ የራሴ ወቀሳ ሆኑ:: ሁሉን ለማወቅ መጣጣርና በሰው ልጅ የታሰበውን ሁሉ ለመሰብሰብ መፍጨርጨር ትርፉ ምንድነው? በቀላሉ አለመርካትና ሁሉን መጠራጠር አይደለምን? የታለ ደስታዬ? የታለ ከእምነት የሚገኝ እረፍቱ? ከእኔ ይልቅ እናቴ ደስታና እረፍት አላት አይደለምን? ስባዝንና ስባትል ማደሬ ትርፉ ምንድነው? የከንቱ ከንቱ፣ ከንቱ ንፋስንም እንደመከተል አይደለምን? ታዲያ ማነው በማን መሳቅ ያለበት? ማነውስ ለማን ማዘን የሚገባው? የኑሮ ሸክሙ ቢከብደኝም የሚያሳርፉ አማልክት የሌለኝ፤ የሚጠቅመኝና የማይጠቅመኝን የኑሮ ቅራቅንቦ ተሸክሜ የምባትል ከንቱ፣ የከንቱ ከንቱ እኔ አይደለሁምን?...

...ረድ ሥርዌ የእንግሊዝ አፍ ቃርሚያውን ጨርሶ የማሳረጊያ አቡነ ዘበሰማያትን መድገም ጀመረ:: ፀሎት የመሰላት እናቴ ግር እንዳይላት ይመስላል:: በየመካከሉ ንፋስ የሚወስደውን ቁርጥራጭ ፀሎት እንደጨረሰ እናቴን የማሰናበት ሥነ-ሥርዓት አከናወነ:: ምናልባትም ይሄኔ በአጥር ላይ መዝገበ ቃላቱን ያሳልማት ይሆናል:: ለእርሷ ምን ለውጥ አለው? ልቧን ጥርጣሬ እስካልጎበኘው ድረስ በእምነት እረፍት ልቧ ምላሽ ማግኘቱ ይቀራል?

ይብላኝ ለእኔና ለጠቢቡ ሰሎሞን፤ እምነትና እረፍትን ላጣን፤ ህይወት የከንቱ ከንቱ ከንቱ ለሆነችብን፤ ኑሮ መልሶ መላልሶ የማመንገርክ ዑደት ለሆነብን፤ ደስታና ረፍትን ላጣን...በመጨረሻ በእኔና በጠቢቡ ሰሎሞን ሳትሁ፤ ለእኔና ለጠቢቡ ሰሎሞን አዘንሁ... ለተፈጠርንበት ያልኖርን የከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ... ንፋስ ተከታዮች::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ስድስት

## የጉዳት ነገር

... ከእኔና ከጠቢቡ ሰለሞን ይልቅ እናቴና አባቴ እንዲሻሉ አወቅሁ፡፡ በህይወት ለመርካት ከረገጧት ምድር ስር ተድላን ቆፍረው ለማውጣት አልተቸገሩምና፡፡ ከእኔና ከጠቢቡ ሰሎሞን ይልቅ እናቴና አባቴ እንዲሻሉ አወቅሁ፡፡ የፈጣሪን ነገር ለፈጣሪ ሰጥተው እረፍታቸውን አግኝተዋልና፡፡ ከእኔና ከጠቢቡ ይልቅ እናቴና አባቴ እንዲሻሉ አወቅሁ፡፡ ካላቸው እንጂ ከሌላቸው ነገር ጋር ደስታቸውን አላቆራኙምና...

...ያቺን ቀን የህይወቴ ኬላ አደረኳት፡፡ ከድብቅ አለሜ ወጥቼ ግዘፍ የነሳውን ውጫዊውን አለም ለመፈተሽ ቆረጥኩ፡፡ የተቋረጠ ትምህርቴን ለመቀጠል ቃልገባሁ፡፡

አመሻሽ ላይ ሻምበል ጠናጋሻው በሬን ገፋ አድርጎ ገባ፡፡ ያለወትሮዬ ውሳኔዬን ያማከለ አቀባበል አደረኩለት፡፡ ከጉዝጓዜ ላይ ተፈናጥሬ በመነሳት «ሻምበል» አልኩት፡፡

«ዛሬም ሻምበል?» ሳቀ፤ አሳሳቁ ውዱታውን መስፈፊያ መንገድ ይመስላል፡፡ አለወትሮው ነጭ ቆብ ደፍቷል፡፡ እንደወትሮው በእጁ መፃህፍት ይዟል፡፡

«የሻምበል ማዕረግ ከተሰጠኝ ዛሬ ልክ አራት አመት፡፡ ይሄኔ የጀብዱ ቢቀር በደረጃ ሻለቃ መሆኛዬ ነበር» እንደተከዘ እልጋዬ ጫፍ ቁጭ ብሎ የያዛቸውን መጻሕፍት አቀበለኝ፡፡ እያገላበጥኩ ማየት ጀመርኩ፡፡ ሦስቱም ደም ነካክቷቸዋል፡፡ ቀና ብዬ ሳየው በጭንቅላቱ «እዎ» አለኝና ቆቡን ከራሱ ላይ አነሳት፡፡ የአናቱ አካፋይ ለአመል ወደግራው አዘንብሎ ፕላስተር ተለጥፎ ነበር፡፡

«ጦር ሜዳን ሳይሆን ህይወትን ያማከለ ጀብድ ላይ ነኝ፡፡ የጀኔራልነት ማዕረግ የሚገባው ጀብድ፡፡» ለመቀለድ ሞከረ፡፡ ውስጡ ግን እንዳች መስልቸት እንዳለበት ያስታውቃል፡፡

የምለው ጠፍቶኝ ያመጣልኝን መጻሕፍት ማገላበጥ ጀመርኩ፡፡ A Happy Death የምትል የአልበርት ካሚዩ አነስተኛ መጽሐፍ፡፡ ወደ ሁለተኛው አቀናሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ካህሊል ጅብራን ነው። A TEAR AND A SMILE ትላለች። ሦስተኛው የኸርማን ኸስ DEMIAN - ሁሉም ደም ነካክቶታል።

‹‹ከአንድ መጽሐፍ ውጪ ሁሉንም ቀዳዳ ጨርሳለች። ያ ያልነካችው መጽሐፍ ምን ይመስልሃል?››

የግዴን ገመትኩ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ?››

‹‹አይደለም። ፍልስፍና የማስተምርበት Questions That Matter የሚለው የሚለር መጽሐፍ። ታውቃለች፤ አየህ፣ እያወቀች ነው የምታጠፋው።››

‹‹ጀኔራል›› አልኩት።

የቅሬታ ፈገግታ አሳየኝ። ምንም እንኳን መርጦ የገባበት ህይወቱ ቢሆንም አንዳች አልፎ ሄያጅ ወቀሳ ሳይነካካኝ አያልፍም። ስምረት እንዴት አደገች? እንዴት ያለችውን አረም ምርት አስመስለን ገበያ አወጣን?...

‹‹ተከትላኝ ሳትመጣ ልውጣ›› አለኝና ተነሳ። ‹‹መጻሕፍቱ ሲናፍቁኝ እንተጋ መጥቼ አያቸዋለሁ›› ብሎኝ ወደበሩ ሲያመራ

‹‹ጀኔራል፣ ቆቡ ተረሳ›› በግድ ለመቀለድ እየሞከርኩ ይሆን? የቅሬታ ፈገግታው ፊቱ ላይ እያንገፈበበ

‹‹የሆነን መሸፈን በሱሪ ይብቃን›› አለ። ምን ማለቱ ይሆን? ሄደ። በኋላ ግን የገባኝ ክብሩን መጠበቅ እንደሰለቸውና ገመናውን መግለጥ እንደጀመረ ነው። ገመናው የማነው? የእሱ? የስምረት? የወላጆቿ? ወይስ የአብሮአደጊዎቿና የአብሮ ተወላጆቿ?...

እቅጩን ሰዓት ባላውቅም ብቻ መሽቷል። ሰዓት አይደለም ቀንና ወሩን የማወቅ ፍላጎቱ ከጠፋ ሰነባብቷል። የቤቱ መብራት ስለማይጠፋ የመሸበትን ባበራሁበት ጊዜ ለማስታወስም አልችልም። ብቻ ረቂቅ በሬን ከፍታ በጨለማ የተከበበች ጨረቃ መስላና ተንቦግቡጋ ብቅ አለች። ለወትሮው ስትሰክር ስለምትመጣ አሁንም አልተጠራጠርኩም። እልፍ ክንፍ ያለው ቀሚስ ለብሳ ‹‹ክረምት-አገቢ›› መስላለች። አለባበሱንና አቀነጃጀቷን ከየት እንደተማረችው አልገባህ ይለኛል። ትለፋደዳለች ብዬ ስጠብቅ ደረቷን በሚያምሩ ጣቶቿ ደገፍ አድርጋ...

‹‹ታለ? ምንድነው? ልቤ የሚፈራው? ጭንቅ፣ ጭንቅ የሚለኝ? ታለ? አባዬ ደህና አይደለም? እማዬስ?...››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ክረምት አግቢዬን ቀና ብዬ አየሁት ከአባቷና ከእናቷ በፊት ልጇን መጠየቅ አይገባትም ነበር? እሷ ግን ልጇን ስታላቅ እህታችን ካስተሳሰረች በኋላ ሙሉ ትኩረቷን ጠናጋሻውና ስምረት ላይ አድርጋለች:: አሁንም እናትና አባቷ ያሳሰቢት የምትመስለው ተሸከርካሬ የጠናጋሻውን ሁኔታ ለመስማት እንደሆን ገብቶኛል:: ለመጀመሪያ ጊዜ ሳትንገዳገድና ሳትለፋደድ መጥታ አልጋዬ ላይ ቁጭ አለች::

የሚገርም ነገር ሆኖብኛል:: አጋጣሚ ወይስ ምን? የጠናጋሻውን መፈንከት ደመነፍሷ ነግሯት ይሆን ጭንቅ ጭንቅ ያላት? ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ ነገር አድርጋ አታውቅም፤ ታዲያ አሁን ምን ከጠናጋሻው ጋር አስተሳሰራት መንፈስ ቅዱስ ወይም እርኩስ? ያልተፈቀደ ቁርኝት ከሆነ እህቷ ስታገባው ሙቶም አልነበረበትም?

ቦርሳዋን ወርውራ አልጋ ላይ ስትቀመጥ እግሮቿ አኩዮቹ ሆኑ:: አየኋቸው:: የኢየሱስ ዘመንን የሚያስታውስ ጥልፍልፍ ጫማ አድርጋለች:: ጣቶቿ እንደአፋሩም ልጃገረዶች ገርበብ ባለ ቀዳዳ በኩል ተደርድረው ያሎልቃሉ:: ከቀሚሷ ጋር የሚናበብ ጥፍር ቀለም ተቀብተዋል::

‹‹ምነው ዝም አልክ? እንዴት እንደጨነቀኝ ባየህ? ከምሳ ሰዓት አንስቶ መቀመጥ፣ መሄድ፣ መተኛት አስጠልቶኝ...››

ቀና ብዬ አየሁት:: ከፊቴ ላይ አንዳች ነገር ለማንበብ ትጣጣራለች:: ምንም ያገኘች አይመስልም፤ የሩቁን የጠናጋሻውን መንፈስ የጠቆማት ደመነፍስ አጠገቧ ያለሁትን ወንድሟን ጋርዶባታል::

ከተቀመጠችበት ነቅነቅ ብላ ከስሯ ቶቡን መዝዛ አወጣችው:: አየችው፤ መልሳ ቶቡን ትካ ብላ አይታ በመጠራጠር ወደ አፍንጫዋ አቀረበችው:: እርግጠኛ ነኝ ጠረኑ እዚያ አለ:: እንኳን ከሰበሰው ከነካካው መጻሕፍቱ ውስጥ ጠረኑን አፈላልጋ ማግኘት ተክናለች:: እንባዋ ዝርግፍ ዝርግፍ አለ::

ጨነቀኝ:: ምን ብለው ያፅናኗል?

‹‹ደም ነክቶታል›› ቶቡን ደረቷ ላይ እንቅ አድርጋ ያዘችው:: ‹‹ይሄኮ ለእሱ አይገባም፤ ወይኔ፣ ታለ? ታውቀው የለ? ይሄ ለሱ ይገባል? አውቂዋለሁ! አውቂዋለሁ! ኡኡኡ...›› እየጮኸች ካልጋው ላይ ወደመሬት ወረደች:: አፏን ለመያዝ ስታገል እናቴ በሩን በርግዳ ገባች...

‹‹ምንድነው? ምንድነው ጉዱ...››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ረቂቅ ከተደፋችበት ቀና ብላ በገንተረ ፊት አየቻት፡፡ አልፈራችም፤ በአንፃሩ እናቱ የፈራች መሰለች፡፡

‹‹ውጪ! ውጪ! ውጪ!›› ብላ የሚወረወር ሰቃ ፈለገች፡፡ የእኔ ነጠላ ጫማ ብቻ ነበር፡፡ እሱኑ አንስታ እናቷ ላይ ወረወረች፡፡ ከእናቱ ጀርባ እቴቱና አበባ ፊታቸውን እያፈራረቁ ያዩ ነበር፡፡ እናቱ በረቂት ቁጣና ቅጥ ያጣ ጥላቻ ተገፍትራ ልጆቿን ጠራርጋ ሄደች፡፡

‹‹ምንድው?ጣ! ምንድነው? ጣ!›› አባቴ ድምፁ ይሰማኛል፡፡

‹‹ምንም አይደል ግባ››

ሆዮ!!

ረቂቅ እየተንፏቀቀች ጭኔ ላይ ተኝታ ማልቀስ ጀመረች፡፡ የተተኮሰው ሀጉሯ በላቧ እንደአንቴና ቆሞና ሻክሮ ነበር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## ሰባት

## የሲሳው ዓለም ነገር

ረቂትን ፍራሹ ላይ አስተኝቼ እኔ አልጋው ላይ ወጣሁ። ቦታ ስቀይር ማንበብም ማሰብም ተስኖኝ አደርኩ። ጠዋት ስነቃ ረቂት ፀጉሯ ተንጨፍሮ ክፉል በተረጋጋ ፊት ፍራሹ ላይ እንደተቀመጠች አገኘኋት። የቤቱ ጠረን ተለውጦ ሲጋራ፣ ሲጋራ ሸተተኝ።

‹‹እማዬ ሲሊት መጥታ ትኩሳቱን ለመለካት እጇን ግንባሬ ላይ አድርጋ ነበር። ትንሽ ቆይታ ቀዝቃዛ ውሃ ደረቴ ላይ አደረገችልኝ። አሁን እኛ ከእሷ ተፈጠርን? የሷ ልጅ ከሆንኩ ለምን ልጅን እንደሷ አልወደድኳትም? ያቺስ ብትሆን እኔን ለመጉዳት ብላ ያንን ሁሉ ሣክኔ እሱ ላይ መፈፀም ነበረባት? ሁለታችንም የእማዬ ልጆች አይደለንም።››

የእንቅልፍ ልብ ነግቧኔ ይመስላል። የብዙን ፋርን ተበጣጥሶ በየፊናው ከተፈነቻቸረ ቆየ ስለ አሰብኩ። ያኔ እንደነበሩት፣ ሰልፋቸውና መከባበራቸው ሳይዛነፍ በአይን ህሊናዬ ላይ አለፉ። የጋራ ቤተሰባዊ ሀላፊነታቸው እህታማቾቹ የጉንዳንን ስልት እንዲከተሉ አስገድዷቸው ነበር።

‹‹ጥፋቱ የኔ ነው። እርፉ በተቀመጠችበት ሄጄ ፍቅሬን እነግራት ነበር። እሱን ክፍ-ከፍ አድርጌና ከሰውነት ተራ አውጥቼ፣ መልአክ አድርጌ እተርክላት ነበር። እሱ የቋንቋት ሲሊት ሲያሳልፍ እኔ ምን ያህል እንደምሰቃይ እናዘዝላት ነበር። እሱን እንቅልፍ በመንሳት እኔን ማሰቃየት እንደምትችል ገብቷታል።››

ለመጀመሪያ ጊዜ ረቂት ከራሴ እውነት ጋር አጋፈጠችኝ። ሲፈንስ? ሲፈንስ?... እኔ እንቅልፍ ሳጣ እሷ ስታይ የበዛበት ሲሊት ታሳልፍ ይሆን? የት ናት?... ሲፈንን ማሰብ ሽንፈት ሆኖብኝ ስሸሸው ኖሬአለሁ። ገርጊሴኖን ውስጥ ዘእርምጥ ተብዬ ለሁለት ዓመታት መቆየቴ በእርግጥ እውቀት ፍለጋ ነበር? ነው ሲፈንን የመሸሽ ውጤት?...

ረቂት ተነስታ ለኔ በተቀመጠው የጠርሙስ ውሀ ፊቷን ታጠበች። ወደ ትልቁ ቤት ደርሳ ተመለሰች። ፀጉሯን በእርጋታ ወደኋላ አስተኝታ ሜፉን ቋጠረች። አለባበሷ ያው ቢሆንም በፀጉሯ ብቻ ፍፁም ከማታው መልኳ ጋር አልገጣጠም አለችኝ። መከራ ቆዳዋ ተፈልቅቆ አዲስና ውብ ፊት ብቅ አለ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

በርሳዋን ከፍታ ያልቆጠረችውን ብር በግምት እኩሌታ ላይ እየከፈለች:: «ኢንካ ላንተ፤ ይሄ ደሞ ለሱ...» አለችኝ::

በረቂት ዘንድ «እሱ» እና «እሷ» ለአንድ አንድ ሰዎች ብቻ የተሰጠ መጠሪያ ከሆነ ቆይቷል::

«ክብሩ ይልቅ ዛሬ ይዘሽኝ ብትወጪ ደስ ይለኝ ነበር»

ተአምር የሰማች መሰለች::

«እሺ፣ ደስ ይለኛል:: ብሩንም ያዘው፤ ምሣ ሰዓት ላይ እመጣለሁ» ብላ ክረምት አግቢዋ ሄደች::

እግሯን ተከትሎ ረድ ሠርቄ ገባ::

«እሰይ፣ እሰይ፣ እሰይ....» አለ ከአባቱ በወረሰው የአረማመድ ቅርስ ወደ ውስጥ እየዘለቀ::

«ምንድነው? ምንተገኘ?»

«ጨኸትና ሙቀት ለዚህ ህዝብ አቃመስከው:: አቤት ጭር ማለት፣ አቤት ቅዝቅዝ ማለት፤ እኔስ እዚያ ጨኸት ውስጥ ለዝንታዓለም ብኖር መረጥኩ:: ጧሂት ስትወጣ አይቻታለሁ ሸጋ ናት::»

«እህቴ ናት፣ አንተኮ መኖር ያሰብህ ውቤ በረሃ ነበር:: ጨኸቱም ሙቀቱም የማይበርድበት::»

«የንታ ናቸው:: እኔ ደስ ሲለኝ አይወዱ፤ መናጢ ናቸው» አለና አፍንጫውን እያነፈነፈ «የበአትህ ጠረን እንኳን እንዴት እንደተለወጠ አየህ?» አለ::

«ረድ፣ እህቴ ናት አልኩኸ»

«እኔስ ይሄንን ‹ረድ› ብትተወኝ በወደድኩ»

ሆን ብሎ እህቴ ናት ማለቴን እንደሚሸሽ ገባኝ:: አልተዋጠለትም ማለት ነው::

«ቁጭ በሉ ረድ» ደገምኩት

«መቼም የንታ መናጢ ጠባይ አለባቸውና አመሌን ለማጎሸት ሆን ብለው ስድብ የሆነ ግብር ለጠፉብኝ እንጂ እኔስ ‹ረድ› አይደለሁም::»

«ረድ መጥፎ ነው?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ኡ-ሀ ምን ትላለህ? በጉልበቱ ዕድት የሚሻ የወጥ ቤት ርምጥምጥ እኮ ነው። ዕውቀት የሌለው ጨዋ፣ ጡርደት የሚሸከም። ፍቺው የሚገባው ቢሰማ ሰውም አያደርገኝ። የንታም እንጂ፣ እኔን የጎዱ መስኢቸው የራሳቸውንም ልፋት ገደል ይከታሉ?››

‹‹እንዴት?›› ስንተኛው ክፍል ዘመን ወደኋላ ሸሽቼ ከየትኛው ምንዥርላቴ ጋር እያወራሁ እንደሆነ አሰላስላለሁ።

‹‹ኡ-ህ፣ ምን ማለትህ ነው? ከተወለድኩ በራት ዓመት፣ ከዐራት ወር፣ ከዐራት ቀን ሲሆነኝ በዐራተኛው ሰዓት፣ በዐርባ ዐራተኛው ደቂቃ ላይ ፊደል መቁጠር ያስጀመሩኝ የንታ ነበሩ። የዜማ ሊቅ ስለነበሩ ለዜማ ትምህርት ሌላ ሊቅጋ አልሰደዱኝም። ያን ሁሉ ለፍተው በትቶታል ብለው ሲያስቡ ወደ ዋሽራ ሰደውኝ ቅኔ ተማሪ ሆንኩ። ግሱንና ዘይቤውን በቶሎ አጠናቅቄ ከጉባኤ ቃና እስከ ሥላሤ አስለቅቄአለሁ››

‹‹ምንድነው ያስለቀከው?›› ግራ ተጋባሁ።

‹‹ማስለቀቅ የጀመርኩውን ማጠናቀቅ ነው። የኔ ነገር ከኩታራ ጋር እንደማወራ ዘንግቼው...›› ብሎ ፍራሹ ላይ ተዘረፈጠ። ለካ መቀመጥ የለመደው አልጋው ላይ ሆኖ ግራ ተጋብቶ ኖሯል ቆሞ የቆየው።

‹‹ዘይእዜና መወድስ ጥቂት እንደቀፀልኩ ተው ተው፣ ተው የሚል ሀሳብ ተጠናወተኝ። ብፀልይ፣ ብፆም አልሆነም። ሱባኤ ገባሁ፣ መልሱን አገኘሁ። «የሚሆንህ ዘመናዊ ትምህርት ነው።» አይ እንግዲህ ብዬ የንታጋ ተመለስኩ። ቢሉኝ፣ ቢሠሩኝ እምቢ አልኩ።››

‹ቢሉኝ ቢሰሩኝ› ውስጥ ያ ክርን እንደነበር ጠረጠርኩ። አይኑ ተጎልጉሎ ውጭ እስኪያድር ድረስ ‹‹ኡ-ህ›› እያሉ ጀርባውን ደቅድቀውት ይሆናል። ‹‹እህ›› እያለ ተቀብሎ ይሆናል...

‹‹በኋላ የንታ እንዳልሆነላቸው ሲያውቁ በኑሮ ያጥርዱኝ ጀመር። ወጥ ቀቃያቸውና ፋና ወጊያቸው አደረጉኝ።››

‹‹ፋና ወጊ?››

‹‹አዎ፣ ሲበሉ ጧፍ ይዞ መቆም።››

‹‹መብራት እያለ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ያጠፉታል፣ ሲፈጥራቸው መናጢ አይደሉ? ይሁን ብዬ ከአስኳላ ትምህርት ገባሁ፡፡››

ንግግሩ ወደሩቅ ዘመን የመውሰድ ምናባዊ ኃይሉ እየጨመረ መጣ፡፡ የምናወራው ከበት እያገድን ወይም የአፄ ሱሱኒዮስ ጦር ሲያልፍ እያየን ወይም አጼ ዮሐንስ የቦሩ ሜዳ ሲያከራክሩ ሲሉ ታድመን... ይመስለኝ ጀመር፡፡ ወደድኩት፤ ከዚህ ውጥንቅጡ ከወጣ እውናዊ ዓለም ይልቅ የትርክቱ ምናባዊ ዓለም የጠራና የነፃ ሆኖ ይሰማል፡፡

‹‹እንደው የጨከነ ሰው ‹ደብተራ› ይለኝ እንደሆን እንጂ ‹ረድስ አይደለሁም፡፡›› ለእኔ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እያወጀ ሳይመስለው አልቀረም፡፡

* * *

እራሴን ፍርግርግ ጎጆ ውስጥ ተዘግቶባት እንደኖረች ወፍ ቆጠርኩት፡፡ ለሁለት ዓመታት አልፎ አልፎ የጡረታ ድልድይን መንደር ገርመም ከማድረግ ውጪ ራቅ ብዬ የሄድኩበት ቀን ትዝ አይለኝም፡፡ ከረቂት ጋር መውጣቱ እርግጥ ሲሆን ልቤን ፍርሃት ፍርሃት አለው፡፡

‹‹ልማድ ሁለተኛ ተፈጥሮ ነው›› ያለው ማን ነበር? አዎ ፈረንሳዊው ፈላስፋ ፓስካል ነው፡፡ ‹‹ልማድ ተቀዳሚውን ተፈጥሮ የሚያጠፋ ሁለተኛ ተፈጥሮ ነው›› የመጀመሪያ ተፈጥሮዬ መጓዝ እንድችል ተደርጌ መፈጠሬ ነበር፡፡ ይሁንና በልማድ መበርታት ያንን ተፈጥሮዬን የምፈራ ሆኜ ተገኝቻለሁ፡፡ እንደምንም ራሴን አበረታትቼ እቴቱን ልብስ ጠየኳት፡፡ ግር በመሰኘት አየችኝ፡፡ እሷም ባለመውጣቴ ልማድ ውስጥ ከትቻት ልሄድ ነው ማለቴን ጆሮዋ እንዲጠራጠር ሆነ፡፡ የሁለት ትንድቦቿ አካፋይ ላይ ያለው ጠባሳ መልከ-መልካምነቷን ለመሸፈን እንደባለጌ ልጅ ቀደም ቀደም ይላል፡፡

‹‹ምነው? ምን ሆንክ? የት?...›› ተርበተበተች? ምን ያርበተብታል? ልማዷ ተፈጥሯዊ ጠባይዋን እጥፍቶባት...

‹‹ከረቂት ጋር አንድ ቦታ ደርሰን ለመመለስ...››

‹‹ከዚች ወፈፌ ጋር ቢቀርብህስ?...›› ዝም ብዬ ሳያት ስህተትዋ የገባት መሰለች፡፡ ሀፍቷን ለማድበስበድ ጎንበስ ቀና እያለች ሳጥን ስትከፋፍት እኔ ወደ ራሴ ቤት ሄድኩ፡፡

የመጣልኝ ልብስ አንዱም አልሆነኝ፡፡ ሱሪዎቹ አጥረዋል፣ ካናቴራዎቹ ጠበዋል፤ ሸሚዞቹ ነትበዋል፤ ሹራቦቹ ታጥፈው ከመቀመጣቸው ብዛት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የታጠፉበት ቦታ ላይ ተበገዘበዘዋል። ግራ ገባኝ። እኛ ቤት እንደሚመጡት የታረዙ ሰዎች የአባቴን ልብስ ለብሺ አባቴን አባቴን እየሸተትኩ ልሂድ?

የተረኘ አማራጭ ተጠሮውን መሰረዝ ነው። ወደ ፍራሺ ተመለስኩ። «ደሞ ለስራ፣ የሆነን ነገር ለመሸፈን፣ የታወቀን ነገር ለመከላከል፣ ሁለት እግር ያለው መጋረጃ» ከትራሱ ስር ረቂት ለእኔና ለጠናጋሻው የሰጠችን ብር አለ። ስምረት ለወትሮም ‹እንግሊዝ› ስለሆነች ጠናጋሻውን በጭቅጭቅ ብቻ ሳይሆን በገንዘብም እንደምታስጨንቀው ረቂት ጠርጥራለች። ብሩን ለጠናጋሻው ማድረስ ሌላ ጭንቀት ነው። እንዴት ይሰጠዋል? ለምን? በማን?...

ጠናጋሻውን ሳስብ ረቂት መጣች። ጠዋት ስትሄድ የተንጨፈረረ ፀጉሯ በወጉ ተፈሽኗል። ደማቅ ባለብዙ ክንፍ ቀሚስ አድርጋለች። ከረምት-አግቢ ደማቅ ቀለም የሳትምና ወደ ቢራቢሮንት አደላችብኝ። ኩርፊያ እንደኖላ ወጥቶ ፊቷን ሲጋርደው ታወቀኝ።

«ታለ? ልትቀር?» በእግሯ ጭምር አኩረፈች። ቀኝ እግሯን ከነጠላ ጫማዋ አውጥታ ግራ እግሯ ላይ ደረበች። የእግር ኩርፊያ።

«እዎ» እልኳት እግር እግሯን እያየሁ።

«ለምን? ታለ? አትገተኸኝ? ለጓደኞቼ ነግሬ?..እ? ታለ?...» የቢራቢሮዋ ቀለም የእግሯ ጥፍሮች ላይ ረግፈዋል።

«ሉካ ሱሪ የለኝም፣ ለካ ሸሚዝ የለኝም...» ከጠበቀችው በታች የሆነ ምክንያት እንደሰጠኋት ገብቶኛል።

መለስ ብላ ስትሄድ የአባዬን ልብስ ልታመጣልኝ መስሎኝ ነበር። በአባዬ ጠረን አካባቢውን እያወድኩ፣ በአባዬ ኩራት ምላሴን ከላንቃዬ ጋር እያጣበኩ ጣ!....

...ስለልብስ እንዲህ አስባለሁ ብዬ ገምቼ አላውቅም። የምንጨነቅባቸውን ነገሮች የሚያመጣቸው ጊዜ ብቻ እንደሆነ አስቤ ተገረምኩ። ረቂትን ትንሽ አስቤ ተውኳት፣ እቴቱን ተካኋት-ምላ አምጥታልኝ እየቃምኩ ወይም እያልቃምኩ ለማንበብ ተዘጋጀሁ። ምንም እንኳን ከፀሀይ በታች አዲስ ነገር ባይኖርም፣ ምንም እንኳን ጥሬ፣ ግሬ እናቴ ያገኘችውን እምነትና እረፍት ላገኝ ባልችልም...

በሩ ተከፍቶ እቴቱ የፊቷን ጠባሳ አስቀድማ ብቅ አለች። የረቂትን አቅፋለች። አንድ ጡቷ ከአንገትጌዋ ብቅ ያለ መሰለኝ። የእህቷን ልጅ ጡት ታጠባት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ይሆን እንዴ? ያልወለደች ሴት ጡቷ ወተት ይኖረዋል? ወይስ እንደ እንጀራ እናት ጡጦ ደረቅ ጡቷን ታጎርሳታለች?...

«ወፊፌዋ ሄደች እንዴ? የእሷ ነገር...» ብላ ያስገገችውን እንገቷን ሰበሰበች። እውነቴ ተቀባገረብኝ። ማጥባት የምትችለው እናት ልጇን ስትገፋ፣ ማጥባት የማትችለው ተቀብላ በእንጀራ እናት ጡት ታሳድጋለች። በእውነት ሥጋ እየኖርን ያለነው ህልምና ተረትን ይሆን? ገራ ያጋባል፣ አንገቴ ተቆርጦ፣ ጭንቅላቴ ክንፍ አውጥቶ ስበር ሰው ሆኜ አስብኩ? ወይስ ሰው ሆኜ ሳለም አንገቴ ተቆርጦ ጭንቅላቴ ሲበር አየሁ?... ከንባብ ጋር ግንኙነት ላላቸው ሰዎች ህልምና እውን ሁልጊዜም ይጣረሳሉ። የአንዱ እግር ያለው ሌላኛው ድንበር ውስጥ ነው። ፓስካል ግን ህልምና እውን የሚደበላለቅበት በልቡ ምናምኒት ኃይማኖታዊ እምነት የሌለው ነው ይላል። እኔ ስላነበብኩ ነው ወይስ እምነት ስለሌለኝ ህልምና እውን የሚጣረሱብኝ?... እንደምንጊዜውም ከየት ተነስቼ የት እንደደረስኩ ጠፋኝ።

በር ተከፍቶ የእቴቱን ምሳ ስጠብቅ የረቂት ፈገግታ ቀረበልኝ። ቢሚዋ ክረምት አገቢ በእጆቿ የተደራረቡ ፌስታሎችን አንጠልጥላለች። በተራ በተራ አልጋው ላይ እየጣለች።

«ይኸው፣ ይኸው፣ ይኸው...» አለች፤ ቀጥላ እየዘረገፈች እያንዳንዱን ልብስ ታንዘፈዝፈው ጀመር።

«ይኸን ከዚህ ስንወጣ ትለብሳለህ፣ ይሄን ምሳ ስንበላ ትለብሳለህ፣ ይሄን ስንቅም ትለብሳለህ፣ ይሄን ለማምሻ ትለብሳለህ፣ ይሄን ናይት ክለብ ስንሄድ ትለብሳለህ...» አልጋዬ ላይ ተከመረ።

እኔ በመገረም ላይ የነበርኩት በልብሱ ሳይሆን በረቂቅ ሁኔታ ሆነ። እንጓችና ብዙን ልጃቸውን ያልወለዷት ያህል፣ ያላሳደጓት ያህል፣ በፉርጎው ስልት ያላጣመሯት ያህል ጊዜ ባመጣው ግድ ውስጥ ፈፅሞ ሌላ ሰው ሆናለች።

«ደስ አይልም?»

ስሜቷ ደስታንና ሀዘንን የማይቋቋም በቀላሉ ተረቺነት ያለው ሆኖ ታየኝ። እንደክረምት አገቢ ይሄንን ትቋቋማለች የማትባል የተፈጥሮ ስጋነት አለባት።

«ልበሳ፣ ይሄን ልበስ፣ ከውስጥ ይሄን አድርገው። ከዚህ ጋር የሚሄደው ሱሪ የጨርቅ ነው-እንካ»

አንዱን በሌላኛው ላይ ስትደራርብብኝ ዝም ብዬ አየኋት። አሰብ አድርጋ...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እሀትህ አይደለሁ? እኔ ፊት ልብስህን ማውለቅ ትፈራለህ? ከዚህ ቤት ውጭ እንዳትለኝ ብቻ፤ ይኸው ፊቴን አዞርልሃለሁ፡፡››

ፊቷን አዞረች…

…ለበስኩ፡፡ የልብስ ምርጫዋ ላይ ትንሽ ጥርጣሬ ነገር ገበኘኙ፡፡ ዲዛይን ያለው ሰማያዊ ሹራብ ከሰማያዊ ሱሪ ጋር፡፡ ከውስጥ ከሹራቡ ዲዛይን ጋር በቀለም የሚናበብ ቡኒ ሸሚዝ እንዲህ ያለ አለባበስ የሻምበል ጠናጋሻው ነው፡፡

‹‹ውይ ሲያምርብህ›› አለች ወደኔ ዞራ፡፡

የልብስ ምርጫዋ ላይ ናፍቆት ማስታገሻ ዘዴ ወይም ድንገት ቢ ረት ብትመለከት መልእክት ማስተላለፊያ ብልጠት አለበት፡፡

ሌሎቹን ልብሶች በወጉ ወደ ፌስታሎቹ ውስጥ ስትከት ተከላከልኳት፡፡

‹‹እኔ ከዚህ ሌላ ልብስ አልቀይርም፡፡››

ኩርፊያዋ በነፋስ እንደሚንገላታ ጉም ፊቷ ላይ ተንከላወሰ፡፡ የሴት የመሰለ ልጥፍ ቆዳ ጫማ ወደ እግሬ ገፋች፡፡

‹‹እውነቱን ነው እንኳን በቀን በሳምንትም ልብስ እንደማልቀይር ታውቂ የለ?›› የእሷንም የተዘነጋ የአልባሳት ችግር እየነገርኳት ይመስላት ይሆን? ትንሽ ተከዛ…

‹‹እሺ ይሄኛውን እንያዘው፤ ስንቅም ሺሻ የሚያጨሱ ካሉ ልብስህ ላይ ተላክኮ… እንደቢጃማ እኮ ነው…እ?››

‹‹ጥሩ›› መጽሐፍ ሳነሳ፣

‹‹ዛሬማ አታነብም፡፡›› ነጥቃ አልጋው ላይ ጣለችው፡፡

ስንወጣ ከቦርሳዋ ጋር አዳብላ የያዘችውን ፌስታል ተቀበልኳት፡፡

‹‹ታለ? ታለ? ታለ?….›› እቴቴ

‹‹እንዳትዞር፣ ዝም በላት?…››

ልጇን ላለማየት ይሆን? ልጇ እንደሆን የእንጀራ እናት ጡት ለምዷ፤ ከጡት ወተት መገኘቱን ዘንግታ፣ ጡት የአፍ ማጫወቻ እንሆነ ደምድማ… እየገፋችኝ የቀኝ መንገዳችንን ስታሲዘኝ እናታችን ጉልት ተቀምጣ እንዳታያት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እንደፈለገች ገባኝ። ስታከታልፈኝ አካሄዴ ተወለካከፈብኝ። አዘውትሬ እግሬን አጣጥፌ የመቀመጤ ውጤት እንደሆነ አላጣሁትም።

መኪናዋ ውስጥ አንድ ሰው እንዳለ አየሁ። የሳት ላንቃ በመሰለው የፀጉር ቀለሟ ላይ፣ የእሳት ላንቃ የመሰለ ክንፍ ያለው ቀሚስ የለበሰች። በአለባበሷ የረቂቅ የመንፈስ እህት እንደሆነች ገባኝ። ፊት ለፊት ያለውን መስታወት አሁራ እራሷን ትሞሽራለች። እኔ ከኋላ ገባሁ።

‹‹አልአዛር›› አልካ.ት እጄን ዘርግቼ።

‹‹አውቅሃለሁ፤ ራኪ ስላንተ እንደወተወተች አይደለም እንዴ?››

‹‹ጠና ጋሻው አይደለሁም'ነ›› ልላት ከጀለኝ። የእጇ ቅንጦታ፤ ፀጉሯ እሳት፣ ቀሚሷ እሳት እነዚህ መካከል ያለ እጇ...

በቢጫና በቀይ ክረምት አግቢ ታጅቤ ወደከተማ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## ስምንት

## የከተማ ነገር

ከተማ ሙቀትና ጩኸት ነው። እውነትም ጡረታ ድልድይ የገዳም ትካዜ እንዳላት የተረዳሁት የከተማው ሙቀትና ጩኸት ውስጥ ስገባ ነው። ሰው ይጮኻል፣ መስታወቱ ይጮኻል፣ ቀለሞች ይጮኻሉ፤ መኪናው ይጮሃል፣ ውሾች ይጮኻሉ፣ ዝንቦች እንኳን ጩኸት ያዋጣሉ…

…ህይወት በከተማ ቅጥ አጥታለች፤ ተፈጥሮ ህብረ ዝማሬዎቿን ይዛ ተሰድዳለች። ወፎች አይዘምሩም፣ ውሆች ፀናፅናቸውን አያንሿሹም፣ ዛፎች ከነፋሳት ጋር አይላፉም። ድርቅርቅ ያለ የሰው ልጅ ጣልቃ ገብነት በጉልህ ይታያል።

ሁለተኛው ተፈጥሮ፣ ልማድ ቀዳማዊውን ተፈጥሮ አጥፍቶ የገነነበት ቤት ውስጥ ምሳ በላን። ልብሳቸው ሳይሆን እራሳቸው በካውያ የተተኮሱ የሚመስሉ ሰዎች በሹክሹክታ እያወሩ አስተናገዱን። ከፀጥታ ያልተሻለ ፒያኖ እወዲያ ጥግ በሚወዘወዝ ሰው ይጠቀጠቃል። የት ነው? ብላችሁ ብትጠይቁኝ እኔም አላውቀውም። ብቻ በፒያሳ መሀል ለመሀል ሰንጥቀን ስናልፍ አንዳች ትዝታ ልቤን እንዲዳስሰው ሆነ።

ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሲፈን…

የሠራተኛ ሰፈርን ወደቀኝ ትተን ስንጓዝ አሁንም ሌላ ትዝታ

ሲ-ፈ-ን! የት ትሆን? እሷን ማሰብ ቀርቶ ማስታወስ ለኔ ሽንፈት እንደሆነ አውቃለሁ። በረጅሙ ተነፈስኩ…

ረቂቅ የመኪናውን መስታወት አስተካክላ አየችኝ። ዓይኖቻችን ተናበቡ። መተያያችንን ወደነበረበት መለሰች።

ምሳ ላይ ድምፃቸውን ቀንሰው ሲያወሩ የነበሩት ሁለቱ የመንፈስ እህታማቾች ብቻ ናቸው። በቢጫ እና በቀይ ክረምት አግቢ ወግ…

-ሂጅ?

-አትይኝም?

-ወይኔ ጉዴ፣ ምን ነካት?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

...ሲባባሉ ይሰማኛል። ያኔ ሬቂቅ ጠና,ጋሻውን ስታፈቅር እህቶቿ እነዚህን አጋኖዎች የተቃውሞ ድንጋይ አድርገው ወርውረውባታል። ምን ያህል አቁስለዋት እንደነበርም ትዝ ይለኛል። ሰው ሰራሽ ሀሞታን እቀናበሮ፣ ሰው ሰራሽ ዜማ ያደረገው ፒያኖ ተጫዋች ሲጨርስ ልብ ያለው አልነበረም።

ግብረመልስ ማጣት የማያቆስለው የጥበብ ሰው አለ? ወይስ በሰው አምሳል የተፈጠረ የከተማ አሻንጉሊት ነው?...

ከምሳ በኋላ ቀዩዋን ክሪምት አግቢ አንድ ቦታ ጥለን፣ እኔ ወደ,ጋቢና ተጋባሁና ጉዟችን ቀጠለ። መስቀል አደባባይን አቋረጥን እንጂ የሬቂት ቤት የት እንደሆነ አላወኩም። ገቢው በጠባቂ ተከፍቶልን ገባን። የቤቱ ግርማ ሬቂትን የሚያሳጣና በባለቤትነት የማይቀበል አይነት ነው። ከልጇ አባት ጋር ስትለያይ ወላጆቹ በሞት ሲለዩ ያወረሱትን አወረሳት። በተጨማሪ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና የመዋቢያ ዕቃ መሸጫ ሁለት ሱቆች ደርሷታል።

ቤቱ ከስባት በላይ ክፍሎች አሉት። መቀዝቀዙ እና ፀጥ ማለቱ የጡረታ ድልድይ አምሳል አድርጎታል። ከጠባቂ ውጭ የቤት ውስጥ ሰራተኛ አለመኖሩ ከሬቂት አንዛር ቤቱ ተገቢውን የመኖሪያነት ትኩረት እንዳልተሰጠው ያሳያል።

‹‹ሕዚያ ሽንጣም የወላጆቻችን ቤት ውስጥ እንደአውቶቡሱ ተሳፋሪ ማገሩን ይዛ እንዳላደረች...››

ስስቅ አየችኝ...

‹‹ምን እንዳሰብክ ገብቶኛል።›› ሳቀችና ‹‹ሕዚያጋ መታጠቢያ ቤት አለ፣ ይሄኛው ያንተ ክፍል ነው። ክፍልህ ውስጥ ፎጣ አለ። ታጥበህ ስትወጣ የመቃሚያ ልብስህን እንደቢጃማ ተጠቅመህ ናፕ ማድረግ ትችላለህ።››

(ወይ ናፕ!)

የሚጨንቅ ነገር አለው። የኛ ቤተሰብ መታጠቢያ ቤት ሽንት ቤቱ ወዳለበት ጓሮ ዞር ብሎ ጆንያ በመጋረድ የተዋቀረ ነው። ገላ ለመታጠብ የፈለገ ባሊ፣ ብረት ምጣድና መጥለቂያ ጣሳ ከጥሯ ሳሙና ጋር ይዞ ወደመታጠቢያዋ ክልል፣ የራሷ መተዳደሪያ ደንብና ሉአላዊነት አላት። የብዜን ፋርጎ ከእድካሚ ሥራ በኋላ ሁለት ሁለት ሆኖ እየተቀባበሉ መተጣጠብ...

‹‹ታለ ይሙት፣ እረፊ››

‹‹ፀጉሬ ላይ? ትናንት ተተኩሼ? ታለ ይሙት መተኮሻዬን ታመጪታለሽ...››

‹‹ኧረ ሳሙናው አቃጠለኝ፣ የትሄድሽ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሲያበዙት አባቱ የመታጠቢያ ክልሉን ህገ-ደንብ ሳይጥስ ራቅ ብሎ...

«ጫጫታ ብቻ፤ ጣ!» ይላል።

ሬቲትን ይሄ አይናፍቃት ይሆን?

ከዚህ በኋላ የተከናወነው ድርጊት ያለምንም መነጋገር ከመደጋገም በተገኘ ሥነ-ሥርዓትና ሥነ-ምግባር ነበር። ባይፃፍም ይሄንን አንብቤአለው።

› ከ8 እስከ 8:10 እንግዶች መንገድ ዳር ይወጣሉ።

› በ8:15 ሬቂቅ መኪና ላይ ይሳፈራሉ።

› በ8:30 እንግዶች መቃሚያ ቤት ይደርሳሉ።

› 8:31 እንግዶች ቦታ ቦታቸውን ይይዛሉ።

› 8:32 የሚፈልጉትን ያዛሉ።

› 8:40 መቃም ይጀምራሉ።

› 10:00 ሺሻ መቅረብ ይጀምራል።

› 12:40 የመቃም ሥነ-ሥርዓቱ ፍጻሜ ይሆናል።

› 1:00 ጥርስ የማፅዳት ተግባር ያበቃል።

› 1:15 ቀለል ባሉ መጠጦች ጨብሲ ይጀመራል።

መቃሚያ ቤቱ «ጊዜ ተዋርዶ»ን የሚቀኝ ኩሩ የመኳንንቶች መኖሪያ የነበረ ነው። ውርጋጥ እንግዶቹን ለማስተናገድ አንድ ክፍል አዘጋጅቷል። በአለባበሳችን የሱዳን ልዑክ መስለን ስንገባ ጫቱ የጢያ ሀውልት በኩባ ተጠቅልሎ እንደመሰለ መካከል ላይ ተጋድሟል። ዛሬ «ታሪክና ቅርስ» ተቀነጣጥቦ ሊቃም ነው ስል አሰብኩ። «አረቢያን ናይት» ላይ ያለው የአስማት ገንቦ ውሃ ተሞልቶ እየጠበቀን ነበር። እንደሴቶቹ የቻሉትን ያህል የተኳኳሉ የመዳብ ኩባያዎች በትሪይ ላይ በአፋቸው ተደፍተው ተደርድረዋል።

የቃሚው ቡድን ተለምዶ ባፀናው ሥነ-ሥርዓት ቦታ-ቦታውን ያዘ። እኔ አጠገብ ተቀመጠችው የሬቂቅ መንትያዋ አሸን ነበረች። በሃሳብ ወደየትም እንዳልፈረጥጥ አድርጋ በአይኖቿ ትጠባበቀኛለች።

«ተጫወት»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እሺ››

‹‹ሁሴ ዝም ነው የምትለው?›› አይኖቿ ከብበው መፈናፈኛ ያሳጡኛል።

በሽቶና በቅባት ስውስራሽ ሽታ ውስጥ እየዋኘን ጫት ጀመርን።

ጫቱ ላይ የሚቀርበው ወሬ ፍልስፍና፣ የእግዜርን አይን መደንቆል ወይም ፖለቲካ አይደለም። ሰው ነው። ረቂቅና መንትያዋ ከረምት አግቢ የጀመሩትን በጋራ ቀጠሉ።

-ሂጅ?

-አትይኝም?

-እሱ ግን ምን ነካው?

-ጓደኞቿን ሁሉ በነካ አዳረሰ'ኮ...

በኑሮ ከፍ የሚሉት በአስተሳሰብ አዘቅት የወረዱት እንደሆኑ የገባኝ መሰለኝ። በኑሮ አዘቅቱን የተላመዱት ደግሞ በአስተሳሰብ እንደባሊሎናውያን ግንብ ወደሰማይ የተመነጠቁት ለመሆናቸው ዋቢዎቹ የናዝሬት ራስ ገዞች ናቸው። እነሱጋ ከሄድኩ ድፍን ሁለት ዓመት መሆኑ ነው።

አልፎ አልፎ የረቂቅ መንትያ ‹‹ተጫወት›› ትለኛለች። ረቂቅ ግን ዞሬ የምትመለከተኝ ፊር የለቀቀ ነገር ከጓደኞቿ ሲነገር ነው። ከአራቱ በቀለምም፣ በድምጽም፣ በሽታም ጨኸት ከበዛባቸው ሴቶች አንዷ ደዘደዝ ለቡድኑ ወሬ የመቃረም ልዩ ተልዕኮ ያለባት ትመስላለች። የሴትና የወንድ ታሪክ አጣፍጣ ካወራች በኋላ ወጣ ስትል። ሀሜቱ ከአይን ወደ አፍ ይተላለፋል።

‹‹ቅናት እኮ ነው››

‹‹እንግዲህ ምን እናድርጋት››

‹‹ለዚህ መልክ የሚሆን ወንድ የት ይገኛል?››

‹‹ያውም ገንዘብ ያለው››

‹‹ካካካካካ...››

ደዘደዟ ብቅ ብላ ‹‹አማችሁኝ? ሙዳ ስጋ ከላዬ ላይ ሲነሳ ታወቀኝ...››

‹‹ምንበጣሽ?››

‹‹ምን የሚታማ አለሽ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ሕኛ እቴ»

ቀይዋ ክረምት አግቢ ቀይ የበዛበት ድሪያ ሰብሳ በተንቀሳቀሰች ቁጥር ብብቷ እስከ ጡቷ መጋጠሚያ ይታየኛል። የጡቷ አበታቀል «የእንጀራ ጡት» እንደሆነ ያሳብቃል። አልፎ አልፎ ጫት ቀንጥሳ ትሰጠኛለች። ስጎርሰው ሹቶ- ሹቶ ይላል። ሹቶ የሚወድ አዶከበሬ ካሰብኝ እንዳይቀሰቀስ ሰጋሁ። ሲፈን በቡና ማፍላት መቀስቀስ ያቃታትን የአዶከበሬ ሞተር ቀይዋ ክረምት አግቢ በሹቶ «ተረክ» እንዳታደርገውና የጫቱን ሥነ-ሥርዓት የአውሊያ መለማመኛ እንዳላደርገው ብቻ... ሳቅሁ። አሁንም ስስቅ ከረቂቅ ጋር ተገጣጠምኩ።

«ተጫወት»

«እሺ»

«ሁሴ ዝም ነው የምትለው?» በሹቲዋ ስር ብብቷንና የጡቷን መብቀያ እያየሁ ዝም። ግን ለምን ጡት መያዣ አላደረገችም?

ድብዳብ ፊቷ የዩጋንዳ ቃሚዎች ልዑክ ወሬዋን እንዳባቲ እያጣጣመች ቀጠለች።

«ሳልነግራችሁ...» የኳንም ሰው አልተገኘ፤ የስለቸች ወሬኛ ሳትሆን አትቀርም።

«ያቺ ባለፈው ሳምንት የነገርኳችሁ፤ ምነው እንኳን ካናዳ ብዙ አመት የቆየ ሀብታም ተቀላጥፋ፤ ኑሮዋን ቀይራ... ምነው እንኳን ቤተሰቦቿ ድሆች ነበሩ ያልኳችሁ... ምነው እንኳን እናቷ ጉልት...»

«አውቀናታል፤» አጠገቤ የተቀመጠችው ክረምት አግቢ ዝም የማስኘት ድምፀት ባለው አኳኋን መለሰች። «ባለሀብቱ ግንባሯን በጥይት ያለው አይደል? እ?...»

«ማነገረሽ?»

«አንቺ ከዚህ ውጪ ታወሪያለሽ እንዴ?»

ረቂቅን ሳያት እንደቀረቀረች ነው። የጫት ቃሚው ልዑክ ትርምስምሱ በወጣ ስሜት ውስጥ ነው። «ያለ ስምምነት ተበተነ» እየተባለ ዜና የሚሰራው እንዲህ ያለው የጫት ሊግ ውስጥ እንዳች ያሉ....

...እኔም ልናደድ ይሆን? ረቂቅ እናቴ የጉልት ንግዷን እንድትተው ደጋግማ የለመነቻት ለዚህ ይሆን? ...ጡረታ ድልድይ ላይ ብዙ ሴቶች ተመኝተውትና



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሞክረውት ያልተሳካላቸው የጉልት ሥራ ያለቦታው ሲገኝ ማሽማቀቂያና ማጥቂያ ይሆናል።

‹‹ለሁሉም ጊዜ ሳይሆን ቦታ አለው። ለመኩራት ቦታ አለው፤ ለመሽማቀቅም ቦታ አለው፤ መልስ ለመስጠት ቦታ አለው፣ መልስ ላለመስጠትም ቦታ አለው…››

ረቂት የሰማቻት አይመስልም። እንደ አደጋ መከላከያ ጠናጋሻውን ለብሳ ይሆናል ያልሰማችው። ባኒያን መልኪ ቢኳኳልም በትገዞታ ደብዝዞ ከወደውስጧ ያለውን ብሩህ ህይወት ወደውጭ አያንፀባርቅም።

‹‹ተሜወት››

‹‹እሺ››

‹‹ሁሌ ዝም ነው የምትለው?›› የሽቶ ሜት።

ሁሉም ነገር ይሰለቻል። መቼም ሰው ሁሉ በተዳማይ ተፈጥሮ አንድ አይነት የነበረ መሆን አለበት። ጉዱ በሁለተኛው ተፈጥሮ ልማድ ባህሪን ሲገስስ ሳይሆን አይቀርም። ይሄ ቦታና፣ የዚህ አካባቢ ተሳታፊዎች ያልተስማሙኝ ስለምን ይሆን?

በተኳኳለው ኩባያ ውኃ ስጎነጭ አጋሳኝ። ሽቶ ሽቶ የሚል አየር ያስወጣሁ መሰለኝ። ለሽቶዬ የምታደን ጥርኝ ልሆን ነው። ሀገሬም ብርቅየው የሰው ጥርኝ መገኛ ልትሆን?

ሺሻ መቀራረብ ጀመረ። ያለንበት እንደሴቶች ክፍል ተቆጥሮ ይሆናል ወንድ ‹‹አፈንጂ›› (ሺሻ ጀማሪ) ተመድቧል። ጭንቅላቱ ብቻ የቀረ ከአንገት በታች ዓይን የማይሞላ፤ መዋሰሉን በሚጢጢ መቀስ ከታትፎ ካደቀቀ በኋላ ቡሬውን ሞላው። በገስተር የቡሬውን አፍ ከድኖ እንደልብስ ስፌት መኪና በፍጥነት በመርፌ ሲወጋጋው የሚዋልል ልብሱ አውሎ ነፋስ እንዳገኘው ጨርቅ ሰውነቱ ላይ ተውለበለበ። የሺሻ ዕቃውን አቀባብሎ ጨረሰ። እንደ አቀበት የሚቆጠረውን የመጀመሪያ ሺሻ መማግ ሲጀምር ለመጮህ አይኑን የጨፈነ አውራዶሮ መሰለ። ከአፉ የሚወጣው ጭስ እየጨመረ ሲመጣ፤ እጁ፣ እግሩ፣ ሆዱ፣ ጭኑ… በጭስ ተከልሎ ከልብሱ ውስጥ ተኖ እንዳያልቅ ያሰጋል። ጭንቅላቱ ጆሮውን እንደክንፉ ተጠቅሞ ወደላይ…

…ህልሜ ትገ! አለኝ። ምቱረ ክሳድ መጥምቀ መለኮት ሚርቱ ቆሟል? ከሽፏል? ወይስ ቀጥሏል?… ጭንቅላቷ ክንፍ አውጥታና ድቡልቡል ቁራ መስላ ጡረታ ድልድይ ላይ ስታንገብብ ስለምን እናቴን አላየኋትም? የተዘገን



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ቆሎ ለመቀበል እንዳሰበች ሁሉ ቀሚሷን በሁለት እጇ ወጥራ ጭንቅላቱን ለመቅለብ ሥር ሥር ስትል ስለምን አላየኋትም?...

...ደባደቦ ፊቷ የሺሻውን መሳቢያ ገመድ ተቀብላ ጭስ ማቡነን ጀመረች። በምርቃና ፊቷ በላብ ተነክሮ ከደባደቦነት ወደ ድብዳብነት የተቀየረች መሰለኝ። በፊትም ፊቷ እንደሰምድ ፀጉር ነበረው እንዴ?

‹‹ተጫወት››

‹‹እሺ››

‹‹ሁሌም ዝም ነው የምትለው?›› ሽቶ የተንጨፈጨፈበት ጫት አቀበለችኝ። በሽቶ የራስ የጫት ክትፎ... ውኃ፣ ግሣት፣ ሽቶ፣ ጥርኝ... ቤቱ ናፈቀችኝ። በግልብ ሰው ተከቦ መቀመጥ ትርፉ ምንድነው? ከማትጣጣመው ጋር አንድ ጣሪያ ስር መዋል መክነን አይደለም? የማይጣጣሙ ሰዎች ስለምን አንድ ቤት ቀርቶ አንድ አገር ውስጥ ይኖራሉ? የብዙዎቹ አገራት ችግር የማይጣጣሙ ሰዎች በአንድ ላይ መተዳደራቸው ሳይሆን ይቀራል? ለምሳሌ እኔና ጠናጋሻው ሁለት ዜጎች ያለው ሀገር ብንመሰርት። ወይም የናዝሬቱን ራስ ገዝ ብንደባልቅና...

...ሳቅሁ፤ ስስቅ አሁንም ረቂቅ አየችኝ። ደባደቦ ፊቷ የሺሻ መማጊያውን በላባም መዳፏ ጠራርጋ ስትሰጣት ወደኔ ገፋችው። በማጨስና ባለማጨስ መካከል ዋለልኩ። ረቂቅ እኔ ፊት ነፃ ሆና የምታጨሰው ሳጨስ ብትመለከት ነበርና፤ ግን አልሆነልኝም።

‹‹ትንሽ ቆይቼ እስባለሁ›› አልኩ ድምፄን ጎላ አድርጌ። ቀይዋ ክረምት አግቢ ተቀብላ ለቢጫዋ ክረምት አግቢ አስተላለፈች።

ከፍሉ የሸንሌ ጥይት ፋብሪካ ሲፈነዳ የነበረውን ድባብ ይዟል። ጭንቅሉ የሻሸ ፍም ያራግባል። ስንት አመት ሙሉ አርገብግቦ ይሆን? ስንትስ አመት ወደፊት ያርገበግባል?...

...ክፍላችን ውስጥ ወንዶች ተቀላቀሉ። አንዱ አባዬ እንደሠንጋ የነጻው የረቂቅ ሽማግሌ ነው። ነጭ ቀሚስ ለብሶ የጭስ እርጎ ውስጥ ጥቂት ተንሳፎ ተቀመጠ። የተለምዶ ደንብ ስለደነገገው መምጣታቸው በሴቶቹ ልብ አልተባለም። አንዱ እንደሺሻ አፈንጂው ጭንቅላቱ ብቻ የቀረ ነው። ሴሎቹ ተነጥሎ የሚታይ ነገር የለባቸውም። እንዴት? አተኮርኩባቸው፤ ተለምዷዊ ፊትና ተለምዷዊ ቁመና፤ አለመጥቆር አለመቅላት፤ አለመወፈር አለመክሳት፤ አለመመለጥ አለማጎፈር፤ ጢም አለማጎፈር፣ ጢም ሙልጭ አድርጎ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አለመሳጨት፣ አለመርዘም፣ አለማጠር... በምንም ነገር ተነጥሎ አለመታየት የመኖር ህልውናን አይፈታተንም? ተደባልቆ ኖሮ ተደባልቆ ከመሞት እንደእኔ መፍጨርጨር አይሻልም?... ምን ተፍጨረጨርኩ? ለዚህ ለዚህ የአባዬ ሠንጋዎች ይሻላሉ። ቀና ብዬ በሚንገዋለለው ጭስ ውስጥ አየሁ። ሠንጋው የበሬ ሰላምታ በጭንቅላቱ ሰጠኝ።

አስታውሶኝ ይሆን? እኔም ለበሬው ሠላምታ አፀፋዬን የከብት ሠላምታ ሰጠሁ። ፊቱን ቅር ሲለው አየሁ።

‹‹አረሳሽኝ?›› ሠንጋው።

‹‹አባቴ ያሯሯጠህ አይደለህ? እንዴት እረሳኻለሁ?›› ልበለው?

‹‹እኔ እንጃ››

‹‹እንዴ? ኸረ በደንብ ነው የምንተዋወቀው›› ተቁነጠነጠ፣ ጭንቅላሉ የሺሻ እቃ ያቀራርብላቸው ጀመር፣ በገዛ እጁ የአባቴን ጀብዱ ሊያወራው ይሆን?

‹‹እኔንጃ››

አጠገቡ ካለው ደብዛዛ ጋር ጥቂት አወራ። ረቂት ፊቷ ተብለጭልጮና የፈነዳ የጭስ ቧንቧ መስላ ጆሮዋን እኛ ላይ ጥላለች።

‹‹ተቀባ አይደለህም? እሱም ያውቅሃል››

‹‹አይደለሁም›› ፈገግ አልኩ።

‹‹እንዴ? ምንድነው? የምትደብቀው ካለ አታጋልጠኝ በለኝ እንጂ አንተ ተቀባ መሆንህን ይቺን ያህል አልጠራጠርም...›› የተደበቀ በማግኘቱ የሴቶቹን አድናቆት በአፀፋ እንደሚፈልግ እያስታወቀበት ድምፁን ከፍ አደረገ።

‹‹አዎ፣ ተቀባ ነው›› አለ ደብዛዛው በደበዘዘ ድምፅ።

ሴቶቹ ጣልቃ ገቡ...

‹‹ተቀባህን ሌላ ቦታ ፈልግ፣ እሱ የረቂት ወንድም ነው››

‹‹ረቂት ወንድም አላት እንዴ?›› ሠንጋው።

‹‹ብላለች›› ደባደቦ ፊቷ።

‹‹ያኔ፣ አላየሁትም›› ሠንጋው፣



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ምናልባትም የአባቴን የማጥቃት እርምጃ በመልሶ ማጥቃት ለመመለስ ለደባደቦዋ የእናቴን ጉልት መቀመጥ የነገረው እሱ ይሆናል።

«ቤት ቆጠራ ነበር የሄድከው?» ረቂት በማያዳግም ከባድ ድምፀት ጣልቃ ገባች።

ሡንጋው እየተልመጠመጠ፣ «አቤት የሰው መመሳሰል? አቤት! አቤት!...» አለ።

«አንተ ሁሉንም እንዲህ ነው የምትለው። አይንህ የማያጣራ ከሆነ ተመርመር»

«እኔ ብቻ አይደለሁም፣ እሱም...» ወደ ደብዛዜ ጠቆመ። ደብዛዛው ፀብ ውስጥ ገብቶ ደብዛዛነቱ እንዳይጠፋ የፈራ መሰለ።

«የ-ው» አለች ረቂት፣ ሁሉም ነገር ሀጥ ያለ መሰለ። ምን የሚጮህ ነገር ነበር? እንጃ!

«የ-ው፣ ይሄ ሰውዬ አንተን ተከትሎ እዚህ ክፍል ቢመጣ ድብልቅልቅ ያለ ፀብ ይነሳል።»

የልጇን አባት እንደሆነ ወዲያው ገባኝ። ድብልቅልቅ ባለው ፀብ ውስጥ እኔ ምን አደርጋለሁ? የአባቴን ፈለግ ተከትዬ ሡንጋዎቼን እየነዳሁ አቧራ አስነሳለሁ? ወይስ ምን?

«ኡ-ኡ-ኡ... በል ሺሻውን እዛኛው ክፍል ትሠራልናለህ።» ሡንጋው የፈራ መሰለ። ፍርሃቱን ተከትሎ የሺሻ አፈንጂው መንታ ቀልጠፍ ብሎ በመነሳት የሡንጋውን እጅ ይዞ ጎተተ። ሡንጋው ከተዘረፈጠበት ተነስቶ ልዑኮቹን እየመራ ክፍላችንን ለቀቀ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ዘጠኝ

## የመቃመቅ ነገር

እንደ ሳጥናኤል አንድ ሺህ መዐልትና አንድ ሺህ ሌሊት ወደ መቃመቅ የወረድኩ ያህል ተሰማኝ። ለአንዲት ቅጽበት እንኳ፣ ድምፁ የማያንቀሳፋበት፣ ሙቀቱ የማይጠፋበት ጨረሩ የማይበዘንበት፣ ዝንጋኤ የሌለበት የኃጥአን ዓለም። እንዲህ የምለው ፃድቅነት ተሰምቶኝ እንዳልሆነ ግልፅ ማድረግ እሰብኝ። እኔም ከኃጥአቹ ወገን ነኝ። የእኔ ‹መቃመቅ› ግን ዘይቤው ለየትል ነው። ፀጥታው የማያንቀሳፋበት፣ ውርጩ የማይጠፋበት፣ ጨለማው የማይዘናጋበት. . . የተኮነነች ነፍስ የደጋና የቆላ ትባላለች? ከተባለች እኔ ደገኛ የተኮነንኩ ነፍስ በመሆኔ የቆላው ኩነኔ አልተስማማኝም ነበር ማለት ነው. . .

. . . ረድ ሠርዊ የቆላ ኃጥእ በመሆኑ ይሆን የደጋው ኩነኔ ያንዘፈዘፈው? ረድ ከአያት ቅድማያቱ የወረሰውን ለሹበሽባ የቀረበ አረማመድ እኔ ያመሸሁበት ቦታ ሲተገብረው በዓይነገቢናዬ እይቼ ፈገግ አልኩ። ምናልባትም በዚያ በአረማመዱ ይደንስበት ይሆናል። ፈገግታዬ ወደ ሳቅ ተቀየረ።

ቆላው የኃጥአን መናኸሪያ እየጋመ የሚሄደው ቀስ በቀስ ነው። የሜቱ ሥነ-ሥርዓት እንዳለቀ ወደቤታችን ሄድን። ረቂት እንደምሣ ሠዓቱ ሁሉ ተረጋግታ የምታጠብበትን ክፍል አሳየችኝ። በሙቅ ውሃ ተለቃልቄ የቀኑን ልብሴን በመልበስ፣ ጠናጋሻውን መስዬ ብቅ አልኩ።

ረቂት ተጣጥባና ተኳኩላ ሌላ ክንፋም ቀሚስ ለብሳ ነበር። ምንድነው ጉዱ፤ ጠዋት ቢጫ፣ ማታ ሰማያዊ ክረምት አግቢ መሆን በተፈጥሮ ህግ ይቻላል? የተፈጥሮን ሥነ-ሥርዓት ሁለተኛው ተፈጥሮ፣ ልማድ ይሽረዋልና ሆነ። ያቺኛዋ ቀይ እሸን ምን አይነት ሆና ይሆን?

በመኪና ወጥተን ቀይዋን እሸን ጫንን።

‹‹ታለ?›› አለችኝ እንደቤተሰብ መሆኗ ይሆን? ሰማያዊ ክረምት አግቢ እህቴ ስለሆነች ያው የክረምት አግቢ ቤተሰብ ነው ብላ ይሆን?

‹‹ታለ፣ እንኳን አብረሽን ለማምሸት መጣህ። እኔ በበኩሌ በጣም ነው ደስ ያለኝ››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ማን የከፋው አለ?›› ረቂት፡፡

‹‹ራኪ ደሞ፣ ነገር አታጣሚ››

ረቂት በምን ሂሳብ ሲያጥር ‹‹ራኪ›› ሆነ? በቶለኞቹ ዘንድ ይቻል ይሆናል፡፡ በደገኞቹ ዘንድ ግን -

‹‹ሰምተኸኛል?›› አለች ቀይዋ ክረምት አገቢ፡፡ ፈረንጅ ይመስል የተሰማትን ሁሉ ስትገልፅ፣ እኔም ‹‹ታንክዬ›› ስል ላመሽ ይሆን?

‹‹አመሰግናለሁ››

‹‹እኔ ነኝ የማመሰግነው›› ከክረምት አገቢዎች ጋር የህፃናት ቴአትር የምሰራ መሰለኝ፡፡ ስለክረምት አገቢዎች ምን መተረክ ይቻላል? ምናልባት ለረጅም ጊዜ ሲጠብቁት የኖሩትን ክንፋቸውን ካገኙት በኋላ አስራ ሁለት ሰዓት ብቻ እንደሚጠቀሙበት፡፡ ይሄ ታዲያ እንዴት አሳዛኝ እንጂ አስቂኝ የልጆች ቴአትር ይወጣዋል? ተፈጥሮ ካሳጣችው ሀብት ምን አስስቷት ክንፍና ነፃነትን ለፍጡሯ ትቶኒጥራለች? በትልና በትልነት መካከል የተሰነቀረች ቀጭን ክንፋምነት. . .

‹‹ተጫወት››

‹‹እሺ››

‹‹ሁሌም ዝም ነው የምትለው?››

ምን እንድላት ነው የምትፈልገው? ‹ይገርምሻል፣ ስወለድም አላለቀስኩም ነበር...› እያልኩ ዝም የማለት ጣጣዬን እንድተርክላት? ቀኑን የዋልንበት ‹ተጫወት› ሊሊቱን ልናነጋበት፡፡

‹‹ተጫወቺ›› አልኳት አንገቴን በግማሽ ወደኋላ መልሼ

‹‹እሺ›› አለችኝ

‹‹ሁሌም ዝም ነው የምትይው?››

ቀድማ ረቂት ከት ብላ ሳቀች፡፡ ቀይዋ ክረምት አገቢ ተደናግራ በመቆየት ቆይታ ሲገባት. . .

‹‹አንቺ፣ ይሄ ወንድምሽ ተጫዋች ነው››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

መጀመሪያ ጨለምለም ያለ ስፌ ቤት ውስጥ ገባን። ግድብ የመሰለ ረጅም ጥምዝ ባልኮኒ አለው። ባልኮኒው ላይ ለመድረስ የተንጠራሩ የሚመስሉ ሎጋ፣ ሎጋ መቀመጫዎች ግድቡን ተጠግተው ተደርድረዋል። ሙዚቃው ተቀንሶ ጆሮን አባብሎ ይደፍራል። ገለፃዬ ግራ አጋቢ ይመስላል - ግን እንደዚያ ነው። ጆሮ በርግዶ የሚገባ ሙዚቃ አለ፤ ሙዚቃውን ፈልጎ - እስፈልጎ የሚያገኝ ጆሮ አለ።

ሁለት ክረምት አግቢዎቼን ይገፎ ባልኮኒውን እጅብኩ። ቢራ አዘዝን። እንደኛ በጋራ የሚጠጡ አሉ። በነጠላ የቆዘሙም አሉ። ሙዚቃው የመረጋጋት ግፊት አለው። መጠጥ ቀጂ ጎረምሶቹ ጥቁር ሱሪ፣ ጥቁር ሰደርያና ጥቁር ቢራቢሮ ከረቫት በነጭ ሸሚዝ ለብሰዋል። ከረቫቱ ቢራቢሮ ነው አሸን?

ሁለቱ አሸኖች እኔን መካከል አድርገው በአፍና በአይን ያወራሉ። የወሬ መሸጋገሪያ መሆኑን እልወደድኩትም ነበርና ወደዳር መውጣት አሰኘኝ። አንዳንዴ ቀይዋ አሸን እኔን በጣም ተጠግታ፣ ክርኔን በሚሞቅ እጅዋ ትይዘኝና ረቂቅን ታናግራታለች። መልእክቱ የሚደርሰው ግን ለእኔ እንጂ ለሰማያዊዋ ክረምት አግቢ አይደለም። ይሄን ሴት ከመጣሽ ሙቀት ካጣጣምኩ ስንት ጊዜ ሆነኝ? ረቂቅ ወደ መፀዳጃ ቤት የቀሚሷን ክንፍ እያውለበለበች ስትሄድ

«ተሚወት» ተባልኩ። መስስ ብዬ ተመለከትኳት። ዓይኖቿ በደማቅ ጥቁርና ነጭ መፈራረቅ ውበትን ለማረጋገጥ የሚጥሩ ነበሩ። ከውበታቸው መልእክታቸው። ስካ እስካሁን «ተሚወት»ን በጆሮዬ እያደመጥኩ ነው የተሰላቸሁት። በአይኖቼ «እሺ» አልኳት። ለእሷም ከአፌ ይልቅ ለአይኔ እሺታ ስሜት ሳይሰጣት የቀረ አይመስለኝም። እጇን ከክርኔ ከፍ አድርጋ በማሾለክ በጉንጮቿ ጡንቻዬን ለአፍታ ተንተራሰች።

አንዳንድ ቅዕበታዊ ክንውኖች ከዕድሜያቸው እጅግ ብዙ እጥፍ ለሚሆን ጊዜ የሚቆይ መልእክት አላቸው። ምናልባትም የአሸን ቅዕበታዊ ክንፋምነት እንደዚያ ሊሆን ይችላል። እጇን ከእጄ ቀለበት ውስጥ ወዲያው ያወጣችው ቢሆንም፣ ለረጅም ጊዜ ያለ እየመሰለኝ ቆየሁ።

ቀይዋ አሸን በተራዋ ወደመጸዳጃ ቤት ሄደች። ረቂቅ፣ የቢራ ብርጭቆዋን በተቀመጠችበት እያሽከረከረች በሙዚቃው የምትተክዝ መሰለች። ይሄኔ ነበር «ተሚወች» የሚለው መቀስቀሻ የሚያስፈልገው።

«አልደበረህም አይደል?» አለችኝ

«አሪፍ ነው» ከትካዜዋ ስትወጣ ማውራቷ እንዳልተለመደ ነገር እየታየኝ፦



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ቤት እንቀይር እንዴ?››

ሙቀትና ጩኸት የፈለኩ ሳይመስላት አልቀረም። ሄዳ ቆስኛዋን አትፈልግም! ፈገግ አልኩ።

‹‹ከተገናኘን ጀምሮ አንዳች ምስጢራዊ ሳቅ እየሳቅክ ነበር።›› ፊቷን ሳትመልስ እንዴት አየችኝ።

‹‹ሳቅኩ? እኔንጃ››

‹‹ታለ? ታዝበኸኛል?››

‹‹ኖ! እንደውም ሳልጠይቃት ለምን ቀድማ ይዛኝ አልመጣችም ነበር ነው ያልኩት?›› ዋሸሁ? ከእሷ በተቃራኒ ያለ ትከሻዬን ይዛ ሙሉ አካላቴን አስጠጋችኝ። ጀርባዬን ቸብቸብ ብታደርገኝ የፈረንጅ መዕናኛ ይሆን ነበር።

ቀይዋ አሸን ብዙ አይኖች ሰብስባ መጣች። ቲሻ ላይ የተጣበቁትን ዓይኖች ብቻ በእጇ ካራገፈች በኋላ ተንጠራርታ ባለጌ ወንበሩ ላይ ተቀመጠች። አቀርቅሬ የሁለቱን እግሮች እያፈራረቅሁ አየሁ። የረቂቅ ጫማ የጣቱቿን መብቀያ በመጠኑ የሚያሳይ ድፍን አብረቅራቂ ነው። ከየት እንዳገኘው የማይታወቀውን አፋራም ብርሃን እላዩ ላይ እያጫወተ ያንፀዋል። የቀይዋ አሸን ጫማ እንደ ረቂቅ ረዘም ያለ ሆኖ ጥልፍልፍ ነው። የእግሯ ጣቶች እንደመጠናቸው ቀያይ ባርኔጣ የደፉ አጫዋቾች መስለዋል። (ምን ማለቴ ነው ግን?)

‹‹ተጫወት››

ቶሎ ብዬ ወደ አይኖቿ። ያቺን ቅዕበታዊ ደስታ ሳትበር ደረስኩባት። በአይኖቼ እሺ አልኳት።

ባዶ የቢራ ጠርሙሶች እየበዙ የምኝቱ አቶጣጠር ጠርሙሰኛ እየሆነ ሲሄድ ድንገት የቤቱ ሁኔታም ተለወጠ። ሙዚቃ አጫዋቹ በግልፅ ሥራ ጀመረ። ጠጪዎቹ በለስላሳ ሙዚቃ እንዲያምቁት የተገደዱትን ስሜት በጩኸት ፈትቶ ለመልቀቅ ተጋ። የቤቱ መብራት አፋራምነቱን ትቶ የቆሰኞች መሆኑን በግልፅ መሰከረ። ብዙ የመብራት ጢንዚዛዎች በላያችን ላይ በረሩ፣ እላያችን ላይ ተንሸራሸሩ። ቀይዋ ክረምት አግቢ እንደ አዲስ ነገር ወደ ጆሮዬ ተጠግታ ‹‹ተጫወት›› ትለኛለች ከአፏ እምልጩ አይኖቿን እቀልባለሁ።

ተነስተው እንደእብድ የሚያደርጋቸው ደናሾች በየመካከሉ ‹‹ኡኡኡ...›› የሚሉ የሙዚቃ ወፈፌዎች... ቀጠሉ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ረቂቅ ቤቴ ስትመጣ የምትሆነውን ለመሆን ጥቂት ሲቀራት ለብቻዋ መወዛወዝ ጀመረች። ወንዶች አብረዋት ለመደነስ ሲሞክሩ ጀርባዋን፣ ወይም ጎኗን ትሰጣቸዋለች። ፊቱን ከባንኮኒው ወደ ተወዛዋዦቹ መለስኩ። የኔዋ እሸን እንደእኔ ፊቷን ሳትመልስ ትከሻዬን በጭንቅላቷ ተደገፈች።

‹‹ምናባቷ!›› የሚል ስድብ ከልቤ ፈለቀ። ደስ የሚል ስድብ።

‹‹ምናባሽ፣›› አልኳት።

‹‹እኔ እንጃ!›› ብቻ አለችኝና ተባራሪ አይኖች ተለጣጥፋ ልትመጣ ወደ መፀዳጃ ቤት. . .

. . . ረቂቅ እየደነሰች ወደኔ መጣች።

‹‹እዚህ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ ይዞኝ የመጣው ማን ይመስልሃል?››

ብገምትም አልተናገርኩም።

‹‹ጠኔ›› አቤት እንዳንዱ ሥም። ሲያጥር ሲቆላመጥ...

‹‹ጠና ጋሻው?››

‹‹እ›› ቢራዋን አነሳች።

‹‹ቅድም የቃምንበት ሲቅም፣ እዚህ ሲጠጣ ዝም ብዬ አየሁት። ሙዚቃው መድመቅ ሲጀመር ይዞኝ ወጣ። እ-ና፣ እስካሁን እሱ ያለ ይመስለኝና ሙዚቃው ሲጀመር የወጣ ይመስለኛና. . .››

ወደ ዳንሷ...

...ከዳንሷ ተመልሳ...

‹‹...ከዚህ ስሄድ ምን ቢሆን ጥሩ ነው?››

‹‹ምን ሆነ?››

‹‹ስላመሸሁ ደበደባችሁኛ...››

‹‹ማን፣ ማን...››

‹‹አንተ፣ እቴቴ፣ እማዬ፣ በዛብሽ... የሁላችሁም አላመመኝም። ያቺ ግን...››

‹‹እኔ መትቼሽ?›› ስምረት ላይ ቆይታ ስሜቷ እንዳይጎሽ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እኔ እንጃ! ሳስበው ግን ይመከለኛል። የሚገርመው እንዳንዴ አበባም ያለችበት ይመስለኛል። እሷ ግን አትማታም፣ እንዴት መሰለሽ ታዲያ...»

ወደ ዳንሷ. . .

ጫት ቅሜ አነባለሁ እንጂ ጠጥቼ አላውቅም። በሁለት ሴቶች መካከል መሰንቀሬ ሀሳፊነት እንዲሰማኝ አድርጎኝ ይሆናል አልሰከርኩም። ቀይዋ ከሄደችበት ስትመጣ ደባደቦ ፊቷን ይዛ ነበር። ሪቂቅ ስላልተደነቀች ሁኔታው በተለምዶ የተከናወነ እንደሆነ አወኩ። ትንሽ ቆይታ እስካሁን በሙሉ አይኔ ያላየኋት አብራን የቃመችው ልጅ መጣች።

«የሴት ደብዛ» ያልተለመደ ሆነብኝ። ተቀባብታም ጎልቶ የሚታይ ነገር የለባትም። ለሴት ልጅ ትኩረት ካለመሳብ የበለጠ ክፉ ነገር ያለ አይመስለኝም። ወደመፀዳጃ ቤት ሄዳ ጥቂት እንኳን የወንዶች ዓይን ሳይለጥፉ መምጣት?...

...አንዳች መጥፎ ነገር ተፈጠረ። ሪቂቅ ይዛ ስትደንስ የነበረውን ቢራ ደባደቦዋ ፊት ላይ ደፋችው። ያ-ድብዳብ ፊት ለጥቂት ጊዜ በቢራ አረፋ ተሞላ። ብልጭልጭና ተባራሪ ሙብራቶች አረፋው ላይ ሲያርፉ ድንገት ኩፍ ያለ ፊት ሆነች። እኔ ላይ የተፈናጠተውን ሹራብ እንደተጠማ ሁሉ ዋጠው።

ሁኔታውን የተከታተሉ ሰዎች መካከላቸው ቢገቡም ድብዳብ ፊቷ ሰውን እንኳን አልተፍጨረጨረችም። ሪቂቅ የሰማቻት አልመሰለኝም ነበር። ለካ ጠኔዋ ስለነበር እሱ ፊት ላለመጣላት ነበር።

ድብዳቧን የእኔዋ ቀይ አሸን ይዛት ወደመፀዳጃ ቤት ሄደች። ለደቂቃዎች ፀጥ ያለው ሙዚቃ ወደነበረበት ተመለሰ። ሪቂቅ ከቀሚሷ ወገብ ላይ የተጣጠፈ ብዙ ብር አውጥታ ለኔ ሰጠችኝ። ጉርድ ቀሚስ? የተጣጠፉ ብሮች?... ሲፈን፣ ሲፈን... የሚያስተጋባ ድምፅ የውስጤን ገመገም እያተረማመሰ፣ ሂሳብ ከፍለን ወጣን። መኪና ውስጥ እንደገባን ሦስቱ ሴቶች መጥተው ከኋላ ተሳፈሩ። ሥጋት ደባደቦ ብድር ልመልስ ብትልስ?... ስካሬ በመጠኑ በሥጋት ተቀነሰልኝ።

ከየት ወጥተን ወዴት እንደምንሄድ አላወኩም። የቆላው መቀመቅ አቅጣጫው ግራ አጋቢ ነው። ብቻ ሙቀትና ጩኸት የበዛበት አንድ ጊቢ ውስጥ መኪናችን ቆመ። ሞቅ ደመቅ ያለ ዘፈን ይሰማል። ስንገባ አንድ አርጋን፣ አንድ ጊታርና አንድ ድራም የያዘ ባንድ መድረኩ ላይ ይታያል። ድምፃዊው ከፍ እኩል ብቅ ብሎ «እንቺ ልቤ እኮ ነው» ማለት ሲጀምር ምድረ ቆለኛ በተለመደ ማዳመቂያ «ኡኡኡኡ...» እያሉ ፉጨት አከሉበት። ቦታ ለማግኘት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

በተቸመቸመው የሰው አጥር መካከል አይናችንን አሹለከለክን፡፡ ያውም ይቺ ደባደቦ ፊት የከመረችውን ሥጋ ይዘን ቦታ ማግኘት የማይታሰብ ሆነብን፡፡

አንድ አስተናጋጅ መጥቶ በሴት ማዳመት ‹‹ራኪ›› ብሎ ተጣራና ጉንጭ ለጉንጭ ተሳሳመ፡፡ ወደ ቀይዋ ክረምት አግቢ ዞሮ፡-

‹‹ሰጊ! እኔ አላምንም›› አሷምን ሳማት፡፡ የተቀረነውን እጁን እያሞላተተ ጨበጠን፡፡

ግራ ተጋባሁ የቀይ አሸኗን ስም እስካሁን አልሰማሁም ነበር፤ ስንተዋወትም እኔ ነገርኳት እንጂ እሷ አልነገረችኝም፡፡ ‹‹ሰጊ›› ምን አይነት ስም ነው፡፡ በእነዚህ ሁለት ፊደላት የሚያቆላምጡት የትኛውን ሥም ይሆን፡፡

‹‹ሰጊ፣ ሰጊ፣ ሰጊ... ሰገዳዲ ነው? ወይስ ሰገሀር ይሆን እንዴ? ሳኩኝ፡፡ የእሷ ስም ሰገሃር ከሆነ የአባቷ ባቡር፣ የአያቷ ደግሞ ጣቢያ መሆን አለበት፡፡ ሰገሃር ባቡር ጣቢያ፡፡ ሳኩ፡፡

አስተናጋጁ እየተሹለከለከ መራን፣ ተሹለክልከን ተከተልነው፡፡ አንድ ባለጌ ጠረጴዛ (ይባላል) የከበቡ ጎረምሶች ጋ ስንደርስ ‹‹እስኪ ልቀቁላቸው›› አላቸው፡፡ መጠጣቸውን ይዘው ዘወር አሉ፡፡ አራት ሴት ይገቴ፤ ወይም በአራት ሴት ተይገቴ መምጣቴ የሴት እጥረት ያለባቸውን ወንዶች ዓይን እንደጦር ተከሰብኝ፡፡

ረቂቅ ወደ ጆሮዬ ተጠግታ

‹‹እዚህም ይዞኝ መጥቷል ደግሞ›› አለችኝ፡፡ የሚያሳዝን መልኳን ለአንዴም ማየት አልቻልኩም፡፡ ‹‹እንዳንተ ሰብሶ፣ ልክ እንዳንተ›› የትዝታ መጫኛ ወይም የትዝታ አጋሰስ መሆኔ ከነከነኝ፡፡ ሰገሃር ባቡር ጣቢያ ወዲያው ተተከታ፡፡

‹‹ተጫወት›› አለችኝ

‹‹እሺ የእኔ ጣፋጭ ዓይን›› አልኳት በአይኔ

‹‹እንደሱ አትየኝ›› አለች፡፡ ሳኩላት፡፡

ደባደቦና ደብዛዜ በከፉ ዓይናቸው ያዩኛል፡፡ ድብዳብ ፊቷ ሰነገ አንድ የቢራ አረፋ የሚያሸልም ታሪክ እያውጠነጠነች ይሆናል፡፡

‹‹ይኸውላችሁ፣ ወንዱ እናቱ ምስኪን የጉልት ቸርቻሪ. . .›› ስትል፡፡ እንደ አሁቴ እንደ አበባ ዝም በይ! ዝም በይ! ይሏታል፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ያዘገዘነው፣ መጠጥ መጣ፣ ብዙ አይነት ቀለም ያለው ነው። የኔ ሮዝ፣ የረቂት ሰማያዊ፣ የለገሃር ቀይ፣ የደባደቦ ወይንጠጅ፣ የደብዛዜ እንደሷ ደብዛዜ ቢዥ። ባርቴንደሮቹ ሲሳደቡ ይሆን? እኔን ሲታሴት፣ ረቂትን ሰማያዊ ከረምት አግቢ፣ ለገሃርን ቀይ ክረምት አግቢ...

ለገሃር መጥታ ‹‹ና እንሂድ›› አለችኝ።

‹‹የት?››

‹‹መፀዳጃ ቤት፤ ያንን ሁሉ ቢራ ስንጠጣ አንዴም አልሄድክም››

‹‹አልመጣብኝማ።››

‹‹እኔን እየጨነቀኝ ነዋ! ባትሸናም እንሂድ›› እንዴት ያለ ግብግቦ ነው? ተከተልኳት፡-

‹‹እንቺ ልቡስ ነው›› ሲያልት ‹‹እምጪ ልቤ እኮነው›› የሚከተል መስሎኝ ጠበኩ። ወደ መፀዳጃው ዞር እንዳልን መሪዬ ዞር ብላ ከንፈሬ ላይ ሳመችኝ። ልብ ሳልል ወገቧ ላይ ተጠመጠምኩ። ከከንፈሯ ይልቅ የተከፈተ ጥርሷ ሲነካኝ ደስ አለኝ። በከንፈሬ ገበር ከንፈሯን በዙር አዳረስኩት።

‹‹እንዴ?›› አለች በግድ ተላቃ ‹‹እናትን!››

‹‹ምነው?›› ደንግጬ።

‹‹እንዴት የሚያም አሳሳም ነው? እንዴት ነው የሳምከኝ?››

‹‹እንደ ሲፈን?›› ልበላት?

‹‹ሁለተኛ እንዲህ እንዳትስመኝ››

‹‹እስኪ?››

መልሼ ሳምኳት።

‹‹እንዴት ነው ያደረከኝ? እናትን!›› አካባቢውን ቃኘሁ። መሟሟቂያ ሳይሆን አይቀርም ብዙ ወንድና ሴቶች በKiss ተመሳስጠው ይታያሉ።

ከዚህ በኋላ ጥቂት ነገሮች ትዝ ይሉኛል። ለስላሳ ዘፈን ሲጀምር ረቂት ወደ ህዝቡ እራሷን ቫልስ እያስደነሰች ትሄዳለች። ለገ፣ ለገሃር ደግሞ እንደህፃን ልጅ እጇን አንክርፍፋ ወደኔ... እንደህልም ሆኖ ደባደቦ ያንን ሺሻ አፈንጂ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አቅፋ ተመስጣ አየኋት። ከአንገቱ በታች የሚውለበለብ ልብስ ሆኖ ደባደቦ ላይ ይለጠፋል።

ወደ ቤት ልንሄድ ስንል ድብዳብ ፊቷ ያንን በጆሮው የሚበር ጭንቅላት ይዛው መጣች።

‹‹የት ታስገቢው?›› አሏት።

‹‹እዚህ፣ በናታችሁ...›› ልታለቅስ፣

‹‹ከኋላ ሞልቷል እኮ››

‹‹በእናታችሁ እኔ እቀራለሁ እንጂ እሱን እዚህ ትቼ አልሄድም...›› የስካር ለቅሶ።

‹‹የራስሽ ጉዳይ›› ለገሃር ተቆጣች።

‹‹የመኪናውን ማርሽ ነቅላችሁ ጭንቅሉን ትከሉና እየነዳንበት እንሂድ›› ያልኩ ይመስለኛል። ረቂቅና ለገሃር ከት ብለው ሳቁ። ለገሃር ለቀልዴ ከኋላ እንቅ አድርጋ ሳመችኝ።

‹‹በሩን ልቀቂው›› ብለን ትተናቸው ሄድን። ደባደቦን፣ ማርሹንና ድብዛዜን።

ጠዋት ለገሃር አንድ እግሯን እኔ ላይ ጭና ተኝተን ነበር። ከእነ ልብሳችን ነን እራሴን የሚታ መጠጥ ወቀረኝ። ረቂቅ ቤት። ቤቱ ናፈቀኝ። ፍራሿ፣ መጻህፍቷ፣ ጠርሙስ ውሃዋ፣ የረድ ሠርዌ የጠዋት ፀሎት።

ለጊ፣ ለገሃር ጠዋት ሳያት ትንሽ ሆና ታየችኝ። ማታ ትልቅ መስላኝ ነበር? የታላቅ እህቱ ጓደኛ ስለሆነች ይሆን? ፀጉሯን ከፊቷ ላይ ገፍፌ አየኋት። አይኗን እንደጨፈነች ፈገግ አለች።

‹‹አትሳቂብኝና አንድ ነገር ልጠይቅሽ?››

‹‹ምን?››

‹‹ምንም አላደረግሽኝም?›› ራሴን ያዝኩ።

‹‹እናትን! አስቸግረህ ነበር፣ እምቢ ብዬ ነው። ደሞ ባንተ ብሶ...›› ደስ የሚል ሳቅ።

‹‹ሌላ...››

‹‹ሌላ ምን?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ጥያቄ››

‹‹እሺ››

‹‹ስምሽ ማነው?›› ክላዬ ላይ ተነሳች። አየችኝ፣ ተገረመችብኝ፣ ልትነክሰኝ የፈለገች መሰለች። ክረምት አገቢ ይናከሳል?

‹‹አልነግርህም!!››

‹‹ለጊ ነው፣ አውቀዋለሁ››

‹‹እያወክ ለምን ጠየክ›› ተመልሳ ደረቴ ላይ ተኛች።

‹‹ሙሉውን አላውቀውም። ሁሉም ለጊ ይሉሻል። ለገሃር ነው ስምሽ?››

ሌላ የሳቅ ኳኳታ።

‹‹አዎ ለገሃር ነኝ። አንተ ልጅ ግን...›› ዝም፣ ዝም፣ ዝም ሦስት ዝም። ዝም ይቆጠራል?

‹‹ለራኪ እንዲህ ብትላት የዘላለም ማብሽቂያ ታገኛለች። ሥሟ ለገሃር ሳይሆን ለገነት ነው። ለገነት ሺፈራሁ እባላለሁ። ምን አይነት ትውውቅ ነው ግን? እብሮ አድሮ?. . .እኔ ግን ራኪን ካወኩ አንስቶ አውቅሃለሁ። ታሳዝነኝም ነበር...››

‹‹ለምን?››

‹‹በፍቅር መጎዳትህን አውቃለሁ። ሁለት ዓመት ሙሉ በር መዝጋትህን፣ ትምህርት ማቆምህን፣ እራስህን መጉዳትህን... ራኪን ውሰጂኝ ብያት ነበር››

ያልታወቀ የፍቅር ገድል ዕፈውልኝ ኖሯል። አንፅተው፣ አቆንጅተው... እራሴ በማባረሬ መጠሰፌን እያውቁትም፤ አረገዘኩ ስትለኝ መካዴን፣ ጭንቅላቱ ላይ ውጥረቱ እየጨመረ ሄደ...

‹‹ስሟ ሲፈን ነው? አይደል?››

ተነሣሁ ‹‹ልሂድ›› እልኳት።

‹‹ቆይ ራኪ ትነሣ፣ ቁርሳችንን እንብላ። አሰበሰቢያ ራስህን በጣም ያምሃል።››

‹‹አንቺ አድርሺኝ፣ ለገሃር›› አመሰጠኝ

‹‹ለገነት፣ የምን ለገሃር ነው? እናትን›› ልፊያ ጀማመረችኝ። ልፊያ...

..ገድል ለምን ሁልጊዜም የጠራ እና የበራ ይሆናል? ‹‹ገድለ ምቱረ ክሳድ መጥምቀ መለኮት›› ሲፈንን የቅዱስ ተዓራሪ፣ አጋንንት፣ ከሀዲ... ያደርጋል።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ልሂድ፣ ሸኚኝ፣ ታክሲ እይዛለሁ...»

«በእናትህ» ሳመችኝ::

ለካ ገንዘብ አልያዝኩም:: ሪቺት የሰጠችኝን አዚያው ቤት ውስጥ ጥዬው ነበር የመጣሁት::

በተስፋ መቁረጥ ለገሃርን ታዘዝኩ:: ይቅርታ ለገነትን:: እሷ ለገነት የተዘጋጀች እኔ ከገነት ለመባረር የተዘጋጀሁ:: ለገነት እየተለማመጠች ነው ወይስ እየተልመጠመጠች?

«እንደማታው ሳመኝ?»

ትክ ብዬ ሳያት አንገቴ ውስጥ ተወሸቀች:: ወደየት እየወሰደችኝ ነው? ለምንድነው የመጀመሪያ ግንኙነት እንዲህ የሚጥመው? ለያታ ግንኙነት መስፈርቱ በደንብ አለመተዋወቅ ይሆን? ውስጤ አንዳች የሚቁነጠነጥ ነገር የሚሰማኝ ዛሬ ከየት መጥቶ ነው?

«በእናትህ እንደማታው...»

«እምቢ!!» ሰውነቷ ሽምቅቅ ሲል ታወቀኝ::

«እኔም ማታ እስለምኜሃለሁ»

«ወንድ ለመለመን ነው የተፈጠረው?»

«ሴትስ?»

«ለማስለመን»

«እኔ ግን ሴት ሆኜ ለመንኩሁ-እ?» ልፌያ፣ ልፌያውን የማያም መቧጠጥና መንከስ እጅቦታል::

«ሌላ ነገር ብትሰማ እንዴት ትኮራ እንደነበር?»

«ምን»

«ራኪ አንተን አገናኝሻለሁ ብላ በመኪና አምጥታኝ አንተጋ ገብታ ቀረች:: መኪና ውስጥ አደርኩ::»

ወዴት፣ ወዴት ሰርስራ እየገባች ነው?

«ብቻዬን»

ዝም!

«አልፈራሁም» እንባ ቅልቅል

ዝም!



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሰው የማያውቀውን እንዲህ ይወዳል?››

ዝም፤ ምኗን እየቃኘችው ነው? የተወለጋገደ፣ ሠልፍ ያዛነፈው ዜማዬ እየተቃኘ፣ እየተገራ ሬሮት የሚለቅ ከባድ የሀዘን ዜማ ወጣው። ምንድነው? ሆን ብዬ ቅኝቱንና ሠልፉን ማዛነፍ አሰኘኝ። የምችል አልመሰለህ አለኝ። ጀርባዋን አሻሸሁላት። ፈረንጆች ጥሩ ዘይደዋል፤ እንባ ለጀርባ ቅርብ ሳይሆን አልቀረም፤ እስኪወጣለት አነባች።

እሷ ብቻ ሳትሆን እኔም ቀለለኝ። ዝግ ባለ ሁኔታ ተነሳች፣ ተነሳሁ። ገላዋን ታጠበች፣ ገላዬን ለመታጠብ ገባሁ። ቀዝቃዛ ውሃ ብፈልግም ሰገነት ስላሞቀችው እየከበደኝ መታጠብ ጀመርኩ። ነፍሴ ቅዝቃዜንና ጭርታን ታበዛች። እራሴን ሳሙና ስመታ በሁለት ብብቱ ውስጥ ሁለት እጆች አለፉ። ዓይኔን ገልጬ ማየት ተሳነኝ። ድንጋጤዬ ውነስ ቢያደርገኝም ድርጊቱ የሰገነት ብቻ እንደሆነ አስቤ ተረጋጋሁ።

‹‹ለምን እኔ ስታጠብ አልመጣህም?››

‹‹ልታስለምኚኝ?››

‹‹ሴትን መለመን የወንድ ወግ ነው አላልከኝም? ወደፊቱ ዞራ ሁለት እጆቿን ትከሻዬ ላይ ሰቀለች። አበታቀለ መልካሞቹ ጡቶቿን ለመሸፈን ያህል ፎጣ ከፍ አድርጋ አገልድማለች። ወደ ደረቱ እስጠግቼ አቀፍኳት። ምን እየፈጠረች፣ ምን ድግምት እየሰራች፣ ምን እየፈተለች እንደሆን አልገባኝ አለ። ከመተዋወቅ በፊት ያለ ስሜት ጉጉት ተከናንቦ ወረረኝ።

‹‹ታከ?›› በውሀ ጫጫታ ተከባ

‹‹እ?››

‹‹ስወድህ››

እሳዘንችኝ መሰለኝ። እናቱ እኔ ላይ የነበራት ፍርሃት ሲፈንን እስሮ ሰኔ ሰጠኝ። የረቂቅ መውደድ ደግሞ ሰገነትን አጥምዶ ክንዴ ላይ ጣላት። እኔ፣ እኔን ሆኜ፣ እኔነቴን ገልጬ የምወደደውና የምጠላው መቼ ነው?... መቀዝቀዝ ጀመርኩ።

...ሳሙና ለመምታት የራቅሁት ውኃ ውስጥ ይገኘት ገባሁ። ፀጉሬ ላይ መድረቅ የጀመረው የሳሙና አረፋ ታጥቦ ሲወርድልኝ ዓይኖቼን ገልጬ አየኋት። በእንፋሎቱ ውስጥ ተንሳፋፊ፣ ጉም ጋላቢ መተተኛ መስላ ታየችኝ። የትንሽ ልጅ መልክ አላት። ዓይኖቿ የፊቷ ገዢ ሆኖ በየዋህነት ተደም-ተደም ይላል። መልኳን አይቶ ዳግም ለማስታወስ ይከብዳል። ተቀርፆ የሚቀር ልዩ ነገር የለውም። ደብዛዛ መልኳን በባህሪ አግዛው ጨርሶ ከመረሳት ተርፋለች።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አይኔን ጨፍኜ መልካን ለማምጣት ሞከርኩ - አልቻልኩም። ተውኩት… ሆን ብዬ ስሜቱን እየሸሸሁት ይሆን?

እጄን ሰድጄ ከጀርባዋ ላይ ፎጣዋን አላላሁት። እቅፌን ሳላላው ፎጣው እግሯ ላይ ወደቀ።

«ይቅር፣ እሺ? ሳትፈልግ መጥቼ ገፋፋሁህ አ?...»

ዝም ብዬ እጄን ጀርባዋ ላይ ሳንሸራሸር አፌ ላይ ሳም አድርጋኝ

«ሳንሳቀቅ እኔ ቤት፣ እሺ? ራኪ ሰው አታደርገኝም፣ እሺ?.. ስማኛ እሺ?...»

«አነሳስቶ ላስጨረሰኝ» የሚለው ምስጋና ሀይለቃሉ አሁን ገባኝ። አነሳስታ የማታስጨርስ አንጋዳ ልኩብኝ። በቻልኩት ሁሉ እራሴን አረጋግቼ ለገነትን ወደ መኝታ ክፍል ልኬ ተጣጡብኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስር

## የጊዜ ነገር

ለጥቂት ጊዜ አዳዲሶቹ ልብሶቼ ቀልቤን ገዝተውት ቆዩ:: ከራሳችን ጋር የምንተዋወቀው በእንዲህ ያለ ተሀዝቦ ብቻ ይመስለኛል:: የሰው ልጅ ፀጋው ተገፎ ከገነት ከተባረረ በኋላ ለራሱ ሌላ ጣያት ሰራ:: ጣያቱ ግብንን መሸፈኛው ቅጠል ነው:: በድርድር፣ በትልትል፣ በሹብሹብ... እያደረገ ጥበብ በመጨመር ሌላኛ መሸነፊያውን በገዛ እጁ አበጀ:: አዲስ ልብስ ሲለብስ ስለምን መንፈስ የታደስ ይመስለናል? የጣያቱ መግቢያ በር ይህ ነው...

...እየሰበኩ አይደለም:: የሰው ልጅ ሊሸፍነው የማይችል፣ ጊዜ ጠባቂ የተፈጥሮ ድክመት እንዳለበት ለመሰፈፍ ነው:: ዓይኔን ከልብሶቼ ላይ ለመንቀል አቅም ሳጣ ታወቀኝ:: እጆቼን ማዘዝ ሲሳነኝ አየሁ:: ሱብሼ መስታወት ወዳለበት ከመሄድ እንዲታቀቡ ብፈልግም እግሮቼ አሻፈረኝ አሉ... መንፈሴ ሲደክም ሥጋዬ ሲበረታ በግልፅ አየሁ:: ድክመቱ የሰው ልጅ ብቻ የመሰለኝ ምስጢረ ሰማያትን ስለማላውቅ ይሆናል:: ምናልባት ቅዱሳን መናፍስት ወደስራ ሲሰማሩ በልካቸው የተሰፋውን «ፀጋ» መለስ-መለስ እያሉ ያዩ ይሆናል:: ርኩሳኑም ቀንዳቸውን እንደፀጉር ነካ-ነካ ካደረጉ በኋላ የብርሃን ፀጋቸውን ተገፍፎ የተቀበሉት ከቁራ ሰባት ጊዜ የጠቆረ መልካቸው ምን ያህል አስፈሪ እንደሆን ለመሰለል መስታወት ፊት ይቆሙ ይሆናል::

እንዲህ ሳስብ ብዙ ጊዜ ረድ ሠርዌ ይገባል፡-

«ሠላም ለጌርጌሲኖን፣ ሠላም ለአልአዛር ዘአርምሞ...» በተጠናው ቅርሳዊ አረማመድ ይገባል::

«ምን እያሰብክ ነው?»

«ስለ መላእክት» እለዋለሁ ሳልደብቅ...

«ምሥጢራት ምድርን ጨርሰህ ወደ ምስጢረ ሰማያት ዘለቅህ?» ይልና ሲደጋግመው የያዝኩትን ግዕዝ ያነበንባል...

«ስምዐ ኮነ መልአክ ለዮሴፍ እንዘ ይብል ኢትፍራህ እስመ ዘተወልደ እምድንግል ውእቱ አማኑኤል ይልብሃል::»

ከጥንት ጥንት፣ ጥንት ዘመዶቼ ጋር የማወራ መስሎኝ እደመማለሁ::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ወይም...

..ሬቲት ድንገት ትመጣና ፊቷ ላይ ስካር ስፈልግ መገረም እገኛለሁ።

«ምን አደረግካት ይቺን ልጅ? ጨርሰህ አትሿን ሳተች» ትላለች።

«አትሌን ስላልሳትኩላት ነው» እላለሁ።

«አትጨክን፣ መጨከን ያንተ አይደለም። የውሸት ቢሆንም የጨከንክ አትምሰል፤ ሂድና መኪናው ውስጥ አናግረሃት ና»

«አህት ክረምት አግቢ፤ እንኳን አንቺ እኔም እራሴን አላውቀው» ልላት እየከጀለኝ ወደ ለገነት እሄዳለሁ።

አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስመለስ እናቴ ጉልት ላይ ተቀምጣ አየኋት። ደረቷ ላይ ያለችውን የሳንቲም ማጠራቀሚያ ኮሮጆ እየነካካች ታወራታለች። እንዳች የህይወት አዙሪት ውስጥ የድግግሞሽ ኑሮ የተፈረደብኝ መሰለኝ።

ይሄኔ «አንጓች» እያለች ትጠራት ይሆናል፤ ለገነት ህይወቱ ውስጥ ለመግባት የምታከናውናቸው ነገሮች በሙሉ እርሷን እያደበዘዙ ሲፈጉን የሚያጎሉ ይሆናሉ።

ወይም...

...ጠናጋሻው ድንገት ይመጣና አልጋ ላይ ይቀመጣል። ሬቲት፣ ያስቀመጠችለትን ብር እንደተጠቀለለ እሰጠዋለሁ።

«ህ» ብቻ ይላል። ጥቅሉን ብር አስጠግቶ ያሽተዋል። የብር ሽታና የዘሚች ጠረን የአንድ ሰው እንደማይሆን እንዴት ሳይገባው ቀረ ስል እስባለሁ።

«ሶትራጠሰ ብርን የማስበው ብር ሳይኖረኝ ሲቀር ነው ይል ነበር እሱ። ስታገኘው ትርፍና እንቀራባጭ የሚሆነውን ያህል፤ ስታጣውና ለምትገዛው ነገር ሲያስፈልግህ ሰማይ ላይ የተሰቀለ፣ የማይደረስበት ጌትነት ይጎናፀፋል።»

እንደእኔ ልብሶች። የልብሶች ባህርይ ግን ሲገኙ ሥራ ማስፈታት ነው።

«ገንዘብ ኪሴ ሲገኝ ሌላ ጭቅጭቅ ነው። አንድ ቀን ወደ ሥራ ስሄድ እቀብልህና እዚያ አስቀምጬ ለአንዳንድ ነገር እጠቀምበታለሁ።» ወደኔ መለሰው። ከፍንከቱ ላይ ፕላስተሩ ተነስቶ በክቡ የተላጨው እቀምቅሟል። መታከት በሁለንተናው እንደተሰራጨ በግልፅ ያስታውቃል።

ወይም...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

...ስምረት ድንገት ትመጣለች። ጠናጋሻውን ስታጣ ልጇን እኔ ላይ መወርወር ይቃጣታል። አልጋ ሥሩን በዘዴ ታያለች፤ ፍራሹን ገልጣ መፈተሽ ይቃጣታል።

ጠናጋሻው አልጋ ሥር መደበቅ ጀምሯል ማለት ነው? የማያደርገው ከሆነ ጭንቅላቷም ላይ ጉዳዩ ሲከሰት አይችልም። ከመሳት ይልቅ ሀዘኔ ይበረታል። ይሄ ሁሉ ለምን?

አመናጭቄ አያታለሁ፤ ቀልቧ ሲያፈገፍግ ይታወቀኛል። «ግቢ፤ ቁጭ በይ» ያለችበትን ሁኔታ እስክታገናዝብ ትታዘዘኛለች።

«ለምንድነው እንደዚህ የምትሆኚው?»

አልጋ ላይ ቁጭ እንዳለች ቁልቁል ታየኛለች። የምትለው ይጠፋታል። ለተንዘላዘለች ልጇ ጡቷን ታጎርሳለች፤ ትነጥቃለች፤ ትከታለች...

«እስኪ መለስ ብለሽ በፊት የነበረሽን ግርማ ሞገስ፤ መፈራት፤ መከበር... አስቢው። እንዲህ ከመሆን ምን ይገኛል?»

«እኔ እንጃ...» አይኖቿ እንባ ያቁራሉ። «የሚሰማኝ አጥቼ ነው እንጂ አሞኛልኮ፤ ሌሊት አልተኛ፤ ስፈራ ነው የማድረው...»

አሳዘነችኝ። «እንደዚህ ሆነሽ የምትቀይሪው አይኖርም።» ድምፀቷ ተቀየረብኝ። ድርቅርቅ ብላ ፍጥጥጥ አደረጋት...

«እሱማ ልክ ነህ፤ የምቀይረው አይኖርም አንድ ቀን ልብሱንና ልጁን ጥሎልኝ እሷ ጋ ይገባል። ይሄን ልትነግረኝ ነው ቁጭ በይ ያልከኝ። ሰርጎገብ ነው ታለ፤ እኔም እህትህ ነበርኩ። ከማንም አስበልጬ የምወድህ። እሷ ዛሬ ሀብት አገኘችና ልብስ ገዛችልህና የምትቀይሪው የለም ትለኛለ?...» ልጇን እያንዘላዘለች ትወጣለች።

«እማዬ የልጅሽን ጉድ ስሚ...» ጉልት ድረስ እየቀባጠረች ትሄዳለች።

ወይም...

...ረቂቅ ክረምት አግቢ መስላ የቤቱን በር ትበረግዳለች።

«እህትህ ደህና ናት?» ብዙ ፈርጥ ያለበትን ቦርሳ ወደ አልጋው ታሽቀነጥራለች።

«እኔም እህትህኮ ነኝ» ወገወገ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ደግሞ በደለችኝ እንጂ አልበደልኳትም። ህይወቴን ደስታ የራቃት ያደረገችው እሷ ናት። አንተን ግን እንዴት እንደምወድህ? ጌታየነህ! ጌታዋ… አንድ ቀን ሳልነግርህ የሆዴን አውቀህ ብር ሰጠኸኝ። ሂጂ አልከኝ። ፈጣሪህ እንኳን የሆድህን በማያውቅበት ዘመን። እንዴት ያንን ውለታህን ልረሳ እችላለሁ?››

መወቀስ ይሻላል ከመወደስ።

‹‹ተኚ››

‹‹መኪናዬስ?››

‹‹ምንም አይሆን››

ዝርር ትላለች። ጫማዋን አውልቄ እግሯን ወደ አልጋው እሰዋለሁ። ትተኛለች፣ ልቤ ግን አያርፍም። እዚያ መኪና ውስጥ ለሌላ ጊዜ ወቀሳ፤ በደል የምታጠራቅም ሴት ትታየኛለች። እሄዳለሁ። እጣታለሁ፣ ወይም አገኛታለሁ።

‹‹መጣህ ጌታየነህ?›› ትላለች። ተመካክረውብኛል እንዴ። በድብቅ ወደኔ ቤት ይገፋት እገባለሁ። ያለወትሮው በሩን ከውስጥ እቀረቅራለሁ። እስኪነጋጋ እናወራለን፤ ምን? እንጃ።

ጠዋት ረቂቅ አልጋው ላይ ቁጭ ብላ ስታፈጥብን እናገኛታለን።

‹‹እናንተ ባለጌዎች፣ እማዬን ልጥራ!››

እኔ እስቃለሁ፣ ለገነት ትፈራለች።

ወይም፣ ወይም፣ ወይም…

…እዚህ መካከል ሳይታወቅ የሚሙለጨለጭ ጊዜ አለ። ሁነቶችን ዱካ አድርገው ካልነቁበት ጊዜ መቼም ድምፅ የማያሰማ አድቢ ነው። በሁለት ዓመት ሁለቱን መደበኛ የትምህርት እርከኖች አልፌ ነጥብ ሳመጣ ከእኔ በላይ እናቴና አንዳንድ እህቶቼ ተደሰቱ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ አንድ

# የፀፀት ነገር

ቃል ሥጋ ሲሆን እዩ...

‹‹...አቤት ይሄ ሠፈር፣ ጭርታው ቆፈኑ፣ ነፍስ ያለው የሚኖርበት አይመስል እሳተመለኮት ተሰጥቶት ቁሩን ከየት አመጣው?...››

ቃል ሥጋ ሆኖ እኔ ውስጥ ነፍስ ሲዘራ ይታወተኛል። አንዳንዴ ‹‹ገዠምበል!›› እላለሁ ሳላስበው። ጭርታ፣ ቆፈን... ድግምት ይሄ ይሆን? እንዱን ቃል እየደጋገሙ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት? ነው እንጂ። ጡረታ ድልድይ ያለ አፈጣጠሯ ጠል ሲወርድባት አይ ጀመር፣ በድን ሲነግስባት...

...አይብዛ እንጂ አንዳንዴ የአባቴ ሞክሼ ስክሮ ይፎክርባት የለም?

‹‹የደርግ ሠራዊት መሽጓል፤ ሠላምና መረጋጋቱን ለማደፍረስ ከደርግ ኢሠፓ ጋር ተማምሏል!››

‹‹ገዠም በል!›› እሱንም።

እና ይሄ ጫጫታ አይደለም? ወብቶኝ ብርድ የሚመስለኝ ታዲያ ለምንድነው? የረድ ሠርዊ የማለዳ ድግምት አይደለም?

የአባቴ ሞክሼ ሠክሮ በተለፋደደ ቁጥር እኔን ትካዜ ውርጭ ሆኖ ይመታኛል።

...አባቴ በእግሩ፣ እኔ በሀሳቤ ለሀሠሣ ከቤታችን ወጣን። አባቴ አሁን የት ነው? የወጣበት ቤቱ ውስጥ አይደለምን? ለዚች ሀገር የለፋበት መታሰቢያው ምንድነው? ምንም!! ድካሙ፣ ዕድሜው፣ ውጣ-ውረዱ የትጋ፣ እምን ሥፍራ ምን አፈራ? ምንም!! እንደ ጠማማ ቀስት አብዝቶ መወንጨፉ መነሻውን መድረሻው አላደረገበትም?

እግርና ሀሳብ ምን ቢጓዙ መድረስ ከሚገባቸው አንድ ጋት ፈቅ እንደማይሉ አወቅሁ፤ አባቴ ቆጬ ከቤት ባይወጣ አሁን እቤት መገኘቱ ይቀር ነበር? ምን አባቴ ብቻ እኔስ? ምን እኔ ብቻ-ጠቢቡስ???

??? በቀደም ህይወታችን እኔና ጠቢቡ ከሀሖይ በታች አዲስ ነገር ለማኖር ፍላጎት አድሮብን አልነበረምን? በሰዎች መካከል የማይገሰስ ሞገስ ለማግኘት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እኔ በጊርጊሲኖን፣ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ አልነገሥንምን? ታዲያስ? ምን አገኘን? ከመከማቸት ብዛት የምትገኝ ሀብት ሀዘን እንደምትቀፈቅፍ ሁሉ ከመሻት ብዛት የምትገኝ እውቀትም ወደተስፋ መቁረጥ እንድትመራ አላወቅንምን???

??? ሁሉም ነገር የከንቱ፣ ከንቱ፣ ከንቱ... ነፋስንም እንደመከተል አይደለምን? ከፀሐይ በታች ምን አዲስ ነገር አለ?...አባቴ ከብዙ የእግር ትግሥት በኋላ መንሻው ላይ መገኘቱ ለመንገዝ-ንገዝ የሸከፈውን ሌላ ሰው አያስተምረውም፤ ግንባሩ ላይ ፈጥ ካለችው ጥይት ውጭ አባቴ መታሰቢያው ምንድነው? ምንም!!

በእኔና በአባቴ መካከል ያለው ዋነኛ ልዩነት እሱ፣ እራሱን እንደባከነ ሰው አለማየቱ ነው፡፡ መታደል!! ረቂት እንኳን ጠናጋሻውን አጣሁ ብላ ብዙ ተስፋ መቁረጦችን አስተናግዳለች-እሱ ግን እስኪ!! እንደውም ለሌሎች ስጦፈንታ ይቆረቆራል፡፡

‹‹አሁን ተገኔ፣ እንደዚያ ከወገቡ በታች የማይላወስ ሆኖ ወንበር ላይ መዋል ነበረበት? እንኳን ለራሱ ለሰው የሚተርፍ፣ የጥጋበኛ መዳኒት...›› በፊት አባቴ ሲያወራ አፉን እንዳላባጣመ፤ አሁን የሚያንጓው ጠጅ እንደሌለ ሁሉ... ለነገሩ ረቂት እንደልቡ ገንዘብ ትሰጠዋለች፡፡

ጋሽ ተገኔ በቀይ ሽብር ክስ ተመስርቶባቸው እስኪጣራ ሦስት ዓመታት የተኙበት ሲሚንቶ እግራቸውን በድን አደረገው፡፡ ብጣቂ ብርድልብስ እግራቸውን ሸፍነው በዘላለማዊ ጭርታ ውስጥ በራቸው ላይ ተቀምጠው ስመለከት አንዳች ያልተገለፀልኝ ወቀሳ ለበቅ ሆኖ ልቤን ይሸነቁጠኛል፡፡ ይሁንና አልቀርባቸውም፤ ሲጠሩኝ እንኳ እርምጃዬን አፈጥናለሁ እንጂ አላዋያቸውም፡፡

‹‹ሲፈንስ?›› ቢሉኝ...

‹‹ከድቼ አበረርኳት›› እላለሁ?

አባቴ ከጋሽ ተገኔ አንፃር ያሉብኝን ዕዳ ለመክፈል (ይመስለኛል) ከፍ ገቶ ይላል፡፡ ረቂት ብር በሰጠችው ሰዓት ጋሽ ተገኔን በሁለት ወጠምሻ ወዛደር አሸክሞ ጠጅ ቤት ይወስዳቸዋል፡፡ ከጠጡ በኋላ በተመሳሳይ መንገድ (አንዳንዴም እየተጣሉ) ወደቤታቸው ያደርሳቸዋል፡፡

አንድ ቀን ጠዋት ከቤቴ ስወጣ እንደተነፋፋች ላም እግሩ ወደላይ የተንጨፈረረ ወንበር አተኩሮ ሲመለከት ደረስኩ፡፡ የግንባሩን ብይ እያንቃነቀ የሚያተኩርበት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ወንበር የጋሽ ተገኔ እንደሆን አውቃለሁና ቆም አልኩ። ለጥቂት ጊዜ ከመረመረ በኋላ ወደ ትልቁ ቤት ገብቶ መደሻና ምስማር ይዞ መጣ። አከታትሎ የወንበሩን መከዳ ነቀለው። የእጀታው አግድም እንጨት የጋሽ ተገኔን አፍንጫ ይመስል የተቆለመመ ነበር።

ከምስማሮቹ የተወሰነ በአፉ ቅሞ አንዳንዱን እያወጣ እጀታውን የወንበሩ እግሮች ላይ መምታት ጀመረ። የፊትና የኋላ እግሮቹ ላይ የተመታው እጀታ ወንበሩን የጀልባ ቅርስ እንዲኖረው አደረገው።

ወንበሩ እንዳለቀ ጫማ ከፊቱ ተና ያለውን እጀታ ላይ ሆኖ ተወዘወዘ። አባቴ የተረፉትን ምስማሮች ካፉ ሳያወጣ አንዳች ነገር እያጉረመረመ ወንበሩ ላይ ተቀመጠ። ወንበሩ ወደ ፊትና ወደኋላ እየተወዛወዘ ያናፍሰው ጀመር።

‹‹ጋሽ ተገኔ በመወዛወዝ መናፈስ ነበር የጎደላቸው?›› በአባቴ የዋህነት ሳቅሁ። ሳቄን ያደመጠ ይመስል ዞር ብሎ በግንባሩ ብይ ውሃ ልክነት አየኝ።

‹‹ዝም ብለህ ታስተውላለህ?›› አለኝ አሁንም ምስማሮቹ አፉ ውስጥ እንዳሉ። ምስማሩ በሰርን ገብቶ ከግንባሩ ጥይት ጋር እንዳይጎራበት ፈራሁ።

‹‹ና [illegible]ህ›› ከወንበሩ ተነሳ፤

ዝም ብዬ ሳየው ‹‹ቁጭ በል እስቲ›› አለኝ አሁንም ያ መዘዘኛ ምስማር አፉ ውስጥ እንዳለ። ይሄኔ ጦርሜዳ ላይ ትርፍ ጥይት በአፉ ይዞ እየተዋጋ ሲያወራ ይሆናል ጥይቷ በሰርን በኩል ግንባሩ ላይ የተቀረቀረችው።

እኔንም ሊያናፍሰኝ ነው? ከጥርጣሬ ጋር ቁጭ አልኩ። እጄን የጀርባ መደገፊያው ላይ አድርጌ ሲገፋኝ ወንበሩ እግሩ ላይ በተጣበቀው እጀታ ወደፊት ተንሸራተተ። ልጅነትና የልጅነት ትዝታ ልቤን ለአፍታ ነበኙት።

‹‹ጥሩ አይደለም? እ? ግሩም አልዘየድኩም? ተገኔን በኩሊ አሸከሞ ወደጠጅ ቤት ከመሄድ እዚህ ላይ አስቀምጦ ሽረረረረረ እያሉ መሄድ...›› የጠጁ ማር አፉን ያጣበቀው ይመስል ምላሱን ከላንቃው ጋር አጣብቆ እያላቀቀ የሚፈጥራት ‹‹ጣ›› ናፈቀችኝ። ሲናገር ሲል ምስማሩን ከአፍህ ውስጥ አውጣው ለማለት ፈለኩ...

‹‹ጠጅን እቤት ሲያመጡት ምን ሞገሱን እንደሚገፈው እንጃ፤ ከጠጅ ቤት እንዳይወጣ፤ ከወጣም እንዳይረባ አድርገው ሳያስደግሙበት አይቀርም።››

‹‹ይሄንን ረድ ሠርዌንና አባቴን ጠይቅ›› ብለው



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ከወንበሩ ላይ ስነሳለት እኔን ሲገፋ በነበረበት አኳኋን ከጊቢያችን ወጥቶ ሄደ። ያንን ምስማር አፉ ውስጥ ረስቶት በጠጅ ሳያወራርደው አይቀርም። የተረሳው ምስማሩ ብቻ አልነበረም። መደሻውም ተልዕኮውን ከፈፀመ በኋላ እንደተንጋለለ ቀርቷል። ውሰታ ቢቆጥርስ? ቢታዘብስ? የከንቱ ከንቱ ከንቱ... ብሂል የእኔና የሰለሞን ሳይሆን የመደሻው መሆኑ ይቀር ነበር?... ከፀሐይ በታች ምንም አዲስ ነገር እንደሌለ ማን በነገረው...

...ተከዳህ? መከዳት በሳይንስ አንድ ሚሊዮን፣ በእምነት ስምንት ሺህ ዓመታት የሞላው የሰው ልጆች ሁሉ ያረጀ-ያፈጀ ታሪክ ነው...

• • •

የአባቴ ፈጠራ የታከለበት ወንበር ጉድ አፈላ ሲባል ያንኑ ሰሞን ሰማሁ። በደህና ጋሽ ተገኔን እየገፋ ጠጅ ቤት ገብተው የሚችሉትን ያህል ጠጥተው የጉዞ መልስ ይጀምራሉ። ወንበሩ «ሰርቪስ» አልተደረገለት ኖሮ አንዱ እጀታ ወልቆ የፊት እግሩ መሬት ላይ ይተከላል። አባቴ በመግፋት ላይ ስለነበር በጋሽ ተገኔ አናት ላይ አልፎ አንድ ሁለት ምዕራፍ በአየር ላይ ተጉዞ በግንባሩ ይተከላል። ወዲያው ጥይቷ «ቷ» ብላ ከግንባሩ ላይ በመተከስ የገባችበት ትጠፋለች። አባቴ፡-

«ጥይቴን፣ ጥይቴን ፈልጉ» አለ አሉ። ብትፈለግ፣ ብትፈለግ ጠፋች። አባቴማ ሀሳቡ ብትገኝ፣ (ቀለሁም ቢሆን) መልሶ ግንባሩ ውስጥ ከትቶ ሊያስፋ ነበር። ታሪክ ነዋ፣ ታሪክ ሲጠፋ ዝም ይባላል?

እኔ ቤት ስገባ ጭንቅላቱ ላይ የእናቴን እርጎ ነጠላ ጠምጥሞ የረድ ሠርዌን አባት ይመስል ነበር።

«የኖረች ጥይት! ሀኪሙ ላውጣት ሲለኝ በስንት መከራ ተከላክዬ ያኖርኳት ጥይት...» ይላል።

በነጋታው ማለዳ ተነስቶ መርካቶ ምናለሽ ተራ ዘልቆ ነበር አሉ። ሀሳቡ ጥይት ቢያገኝ ለመግዛት ነበር። አላገኘም እንጂ ሀኪም ዘንድ ሄዶ ጥይቷን በጥይት የመተካት ቀዶ ጥገና ሊያደርግ ነበር።

«ክፉ ቀን፣ ክፉ ቀን፤ በፊት በኛ ጊዜ ማጓዳው ሁሉ ጥይት ነበር። አሁን እኔውስ እቤቴ ካዝና ይቅር አንድ አምስት ጥይት እንኳን ባስቀምጥ ምን ነበረበት ይ! ይ!» አለ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

በቀጣዩ ቀን ወንበሩን ይዞ እኛ ግቢ መጣ። የፊት እግሩ ተቀልጥሟል። በቦንዳ ለማያያዝ ይጣጣር ጀመር። እናቴ ከጉልት ዕቃ አረስታ ስትመጣ፣ «አንቱ ስውዬ ጨርሶ ጃጁ እንዴ?» አለች።

«ገዛም በይ! ያጃጃሽ!! አሁን ተገኜን መርዳት ምን ከፋት ኖሮበት ምን እንደው...»

ከዚህ ሁሉ ለወንበሩ የሦስተኛ ወገን ኢንሹራንስ ቢገባ ከአደጋው በኋላ ወንበሩም ተሰርቶ፣ ጥይቱም ተተኩቶ...

ወንበሩ ተጠግኖ፣ መንሽራተቻውም እንደተፈለገ ሆኖ ሲጠናቀቅ እየገፉ ጋሽ ተገኜ በር ላይ አቆመው።

«ተገኜ፣ ተገኜ ከወንበሩ ሳድርግህና ወደ ጠጅ ቤት እንሂድ» አላቸው።

ድንጋይ ላይ እንደተቀመጡ «ና ቤት ግባና አሁን ያነፍኩት አለ አምጣልኝ» አሉት። አባቴ ገብቶ ዕሁፉን ቢመለከት «ገብርኤል ተከተለኝ» የሚል ጽሁፍ። ጋሽ ተገኜ ዕሁፉን ጀርባቸው ላይ ለጥፈው ተሳፈሩ። አንዳንዶች ያዛፈው አባቴ ነው ይላሉ።

«እኔ ብዜን? ጥይት እንደበረዶ ሲዘንብብኝ፣ መድፍ ሲያፏጭብኝ፣ ቦምብ ሲፋጭርብኝም ተከተለኝ አላልኩ። እራሱ ተገኜ ነው። እስኪ ይከተለው እንደሁ አያለሁ...»

አባቴን ያናደደው አልገባኝም። ጋሽ ተገኜ «ብዜን ተከተለኝ» ብለው ማፃፍ ነበረባቸው?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ ሁለት
## የድግምት ነገር

‹‹አቤት ውርጭ፣ አቤት ጭጭ!! - በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ እጀምራለሁ…

…‹ሓተርጊሳር

‹‹ኦቼሊ

‹‹ቶሬክስ

‹‹ቶራሲክ (አቤት ብርድ!)

‹‹ፕሮሎግ

‹‹አብዶሚናል ሲክ

‹‹ፑፓ (ትል ደሞ ምን ያደርጋል?)

‹‹ፕሮቶራክስ

‹‹ሚታቶራክስ (አቤት ፀጥታ)››

ለድግምቱ ጆሮዬን አነቃሁ። እንግዲህ ጡረታ ድልድይ የወትሮውን ላትሆኝ ነው። ጭርታው፣ ጫጫታ፣ ቁሩ ሀሩር ይሆንብሻል። ነዋሪዎችሽ ምክንያቱን ሳያውቁ ይዘፍናሉ፣ ዳንኪራ ይመታሉ። በረድ ሠርዌ ድግምት አባቱ እንኳን ሳይቀሩ ጥምጥማቸው ከላያቸው እስኪከነበል ይውረገረጋሉ የልጃቸው መተት እንደሆነ ሲያውቁ።

‹‹እንዴት አድርጎ አራብን፣ ይሄ ወጥ ቀቃይ፣ ነገር አማሳይ…›› እያሉ ጥምጥማቸው ከአቧራ ላይ ያነሳሉ።

‹‹ፋሪክስ-

‹‹ኢሶፋገስ -

‹‹ፓይሎረስ - (አቤት - አቤት)

‹‹ፓንክረስ -

‹‹ዶውድነም -

‹‹ጀጁነም (እግዞኦ…)

‹‹ኢሊየም



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሙቀትና ጨኸት እየጠበኩ አንዳንድ የማውቃቸውን ቃላት ረድ ሠርዊ ድግምቱ ውስጥ እንዳከተታቸው ገባኝ:: እስኪከልሳቸው ጠበኩ:: እንዴ፣ እንዴ፣ እንዴ... ለካ ባዮሎጂ እያጠና ነው::

ረድ ሠርዊ አልፎ አልፎ እያልጎመጎመ የሚጠራቸው «አከራ — አኮቴፓራ — ፒእት — አሚእት — ኢያብሳት — ፋኢላክ — አርኬፍ — አውላላኤል — ፍልልምዮስ...» የሚሉት አስማቶች ከነዚህ ላቲን ቃላት ጋር ተምታቱብኝ:: እኔም እናቱን የሆንኩ መሰለኝ:: ብችኩል ኖሮ ረድ ሠርዊ ፊት ቆሜ «አትድገምብን!» በማለት ወይ እፈጣለሁ፣ ወይ እስማመጣለሁ:: መልሶ መላልሶ የላቲኖቹን ቃላት ካነበነበ በኋላ አሳርጎ አቡነ ዘበሰማያትን መድገም ጀመረ::

እናቱ ወጥታ በር ላይ ቆማ ሀሉቱን እየተከታተለች ነበር ማለት ነው...

...ዛሬ ደግሞ ባዮሎጂ መጽሐፍ ሲያሳልማት? ለእናቴ መቆርቆር ተሰማኝ::

«ሠላም ለጊርጊሴኖን፣ ሠላም ለአለአዛር ዘአርምሞ» በእባቱ አረማመድ ገባ::

«ሳይገስ ጅል ነው፤ በትሉም በቅጠሉም ሰው ሲያባክን ያውላል:: አዳም ፍጡሩን ሁሉ አንድ አንድ ቃል እየሰጠ መሰየሙ ሲገርመን የዚህ ዘመን ጅል ሰው ደግሞ ቁንጫን በብልት እየተነተነ ይታከታል::»

ዝም አልኩት

«አልአዛር ዘአርምሞ»

«እነሆኝ ረድ-ሠርዊ» አልኩት

«ይሄን ስም ተወኝ»

«አባትህ መሰሰውኝ...»

«እሳቸው መናጢ ናቸው አንተ ብቻ ተወኝ»

«አይሆንልኝም» ሳቁ እየመጣ

«ብአቡነ አሮን ይገፍሃለሁ፣ በአቡነ ሐራ፣ በአቡነ ብስጣውሮስ፣ በአቡነ አኖሬምስ፣ በአቡነ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን...»

«አቡነ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን?»

«አዎ፣ ያውም በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ የተመረጡ፤ በአስራ ሁለት ዓመታቸው የመነኑ:: በጥላቸው ያረፈበትን ሁሉ የሚፈውሱ... ታዲያስ? እሳቸውን ረግጠህ፣ እልፌህ በዚያ ስም ትጠራኛለህ?...»

«እሺ» ብዬ ሸኘሁት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የአባቴ አገር አቡን መሆናቸው ነው። ይሄኔ በልጅነታቸው ከአባቴ ጋር ጨዋታ እየፈለሰፉ የባልንጀርነት ዓለማቸውን ሲቀጩ የነበሩ ይሆናሉ። ያን ለጋሽ ተገኔ ያበጀውን የወንበር ባቡር ከአቡነ ፊሊጶስ ዘደብረ ቢዘን ያየው ይሆናል። ያኔ በወንበሩ ሲጫወቱ እጅታው ከእግሩ ተላትቆ ስለተቸከለ በአቡነ ፊሊጶስ እናት ላይ ተሸቀንጥሮ ወድቆ ይሆናል። ያኔም አቡነ ፊሊጶስ ለዳግም የወንበር ሽርተቴ ጨዋታ «የደብረ ቢዘን አባቴ ተከተሉኝ» የሚል አስፀፊው ይዘው የነበረ ይሆናል።

የአባቱን አስቂኝነት ያጎላ ትዕይንት ነበር። ግንባሩ ላይ የነበረችው ጥይት ተተኩሳ ግንባሩ ወከክ ሲል የረድ ሠርዊ አባት ከቅጠላ ቅጠል የተቀመመ መዳኒት ይዘው መጥተው ነበር።

«ጌቶች፣ ይቺ መዳኒት ፍቱን ናት፣ እራሴ ያደራጀኋት ስለሆነች አታስጋም» ብለው ሲቀርቡት።

«ይቅርብኝ፣ ጣ!» አለ። የረሳውን ላንቃ ማጣበት ከየት አመጣው?

«ለምን? ጌቶች»

«ጥይቷ ትገኝ ይሆናል። የሀበሻው ወዳኒት አንጄ ከተለሰነ፣ ተለሰነ ነው። የፈረንጁ ይሻላል። አሽገው ስለሚያሞቀሙቁት ቀይቱ ሲገኝ ገለጥ አድርጌ ለመወሸቅ ያመቸኛል።»

«እንግዲያውስ፣ ቁስል ከተመኙ ቀላል አይደለ? እንዱን ቁስል እያሸሞንሙኑት።» ብለው ልቃቂት እራሳቸውን እየነቀነቁ ሄዱ። ለካ ይሄ ንግግራቸው ትንቢት፣ ወይም እርግማን፣ አለበለዚያም ሟርት፣ ካልሆነም ድግምት ኖሯል። በሦስተኛው ቀን ያንን የወንበር መንኮራኩር ሲያሽከረክር ተመሳሳይ አደጋ ደረሰበት። ሁለተኛ ፍንከት ግንባሩ ላይ ተደመረ።

«እሄሄ፣ እኔ ብዜን እንኳን ወንበር አየር እነዳለሁ። ግን ምን ያደርጋል ጠላቴ ተገኔ ነው።»

«እንዴት?» አሉ ከወደቀበት ደግፈው የሚያመጡት

ዐቃቢ መልአከትኮ የየራሳቸው ግዛት አላቸው። ምንስ መላክ ቢሆኑ በግዛታቸው ሌላው መጥቶ ሲገንባቸው ይወዳሉን? አይወዱም!! ተገኔ ይሄንን ሳያውቅ በሩፋኤል ግዛት ገብርኤልን ጠባቂ አድርጎ ‹ተከተለኝ› አለ። ሩፋኤል እስኪ ገብርኤል ሲጠብቅህ ልይ? በሚል የእልህ ሥራውን ሰራ። ከኋላዬ ምንጥቅ ሲያደርገኝ እግሬ መሬትን ለቆ ሲወነጨፍ ጠርጥሬ ዘወር ብል የብርሃን ካባ የተጎናፀፈ ወጣት ቆሞ በተንክል ሲስቅ አየሁት። ሩፋኤል ነው። በሚቀጥለው «ሩፋኤል ተከተለኝ» ካላልን አይሆንም።»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ጋሼ ተገኔ ይሄን ሲሰሙ ተበፁ፡ ‹‹ወንድሜን አስገድዬ ነበር›› አሉ፡፡

ወደ ሬቲት ደውዬ ነገርኳት ገና ‹‹አባትሽ...›› ስላት

‹‹አሁንም ወደቀ?›› አለች፡፡

‹‹ሕ›› ስላት የክረምት አግቢ ክንፏን ያርገበገበች ይመስል የተቆራረጠ ትንፋሽ ሰማሁ፡፡ ለካ እየሳቀች ነው፡፡

‹‹ወይኔ ጉዴ፤ ታሰ? ይቅርታ! ሳቁ እምቢ ብሎኝ ነው፡፡ አሁንም ያንን ወንበር ሲገፋ ነው?››

‹‹አዎ›› እኔም ሳቁ መጣ

‹‹ሕሱ ለምን አይቀርበትም?››

‹‹አይመስለኝም...››

‹‹አሁንም ሲገፋ?››

‹‹አዎ፤ የሞተረኛ አደጋ መከላከያ ቆብ ግገርሰትና ነይ›› አልኳት፡፡

አሁንም፤ ያ የእሽን ክንፍ ማወናወን የመሰለ ሳቅ ተደገመ፡፡

‹‹ከሰዓት መጥቼ አየዋለሁ፡፡›› አለች፡፡

ወደቤት ስመለስ በአባቴ ፊከራ ግቢያችን ደምቋል፡፡ አራት አይና ሆኖ የግንባሩን አንድ አይን በጨርቅ እንደሸፈነ ብቻውን ይምላል፡፡

‹‹እኔ በሩፋኤል አመካኛለሁ ለካ የተጫወተብኝ አባይ ቂስ ኖሯል፡፡ በእንተ አልታከምም ስለው እንግዲያው ቁስልህን ሁለት አደርገዋለሁ ብሏል፡፡ ይሄን እሱም አይክድም፡፡ ስለፈነጠር መሰስ ብዬ ያየሁት ብርሃን የተንናጠፈ መልአክ የመሰለኝ አባይ ጋኔን ነው፡፡ ተልኮብኝ፡፡ አሁን ይሄን ቤት ይልቀቁ...››

እናቴ ከጉልት እጇን እያርገበገበች መጣች፡፡ ከበስተኋላዋ ‹የሬቲት› (የሬቲት ልጅ) እያለቀሰች ትከተላታለች፡፡

‹‹ኧረ‐ጉድ፤ ኧረ ጉድ ስንት አድባር ስንት አውጋር ያከበራቸውን ሰው ጠጅ በጠገበ ልቦናዎ ተነስተው ራሳቸው ላይ ይውጡ? ስንት ገዳም፤ ስንት ደጅ ሰላም አክብሮ ተለማምጦ የተገዛላቸውን?...›› ሮጣ አባቴ ፊት ላይ ተጋረጠች፡፡

‹‹አልለማሽም? እንዴን ቁስል አታሽሞንሙን ሲል?...››

‹‹አልሰማሁም! ጠጅ ገፍትሮ ቢያሽቀነጥሮ እንደትንሽ ልጅ መዳኒታቸውን ይዘው እሰው ቤት የማይሄዱት አንተ ጋ መጡ፡፡ እኒህ ሰውዬ ባከበሩ ይሻረሩ? ሲባረሩስ እንደው እንደተራ ተከራይ መዘዙ ያበቃል?...››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«በአባይ ጠንቋይና በአባይ ቄስ የምታስጠቂኝ አንቺ ነሽ» ምላሱን ከላንቃው አጣብቆ ማጣጣም ፈሳ?

ነገሩ እንዲበርድ በማሰብ ጣልቃ ገባሁ።

«ሩፋኤል አግኝቻቸው ጌቶች ጥሩ ህልም አይቼላቸዋለሁ፣ ይጠብቁ ብለውኛል» አልኩ። ምናልባት ረቂቅ ሄልሜቱን ገዝታለት ከመጣች ክሊያ ጋር ቢያያይዘው ብዬ።

«አባይ ቄስ በቡናስ አይጠነቁልም? እንዲህ ያል ጊዜ...» እያለ ወደ ትልቁ ቤት ገባ።

አመሻሽ ላይ ረቂቅ ዘመናዊ የታካሚዎች ወንበር ገዝታ መጣች። ከኋላ ትላልቅ፣ ከፊት ትናንሽ ጎማዎች አሉት። አባቴ ያፈረሰ ቂስ መስሎ ብቅ አለ።

«አዬ ወጪ፣ አዬ ገንዘብ ማባከን። ዝም ብለሽ የብረት ወንበር ብትገዢ፣ ጣሊያኑ ጋ ወስጄ ባሌስትራ እግሩ ላይ አስበይድበት አልነበር?»

ረቂቅ የአሽን ሳቋን በሆዷ ታከናውናለች።

«አሁን ይሄ ስንት ፈጀ? ጣ!»

«ትንሽ ነው» እቴቴ የረቂቅን ይዛ ብቅ አለች። ረቂቅ ሆን ብላ ፊቷን አዞረች።

«ትንሽ ስንት?»

«ምን ያደርግልሃል? ተገዛ፣ ተገዛ፣ በቃ» የተበሳጨች መሰለች። ልጇን ስላየች? ወይስ?...

አባቴ ተሽከርካሪ ወንበሩን አገላብጦ አየው። የታጠፈውን ዘረጋው የእግር ማስቀመጫውን አጠፍ ዘርጋ እያደረገ ጥንካሬውን መዘነ። እንደ እንጨቱ መንክራኩር ሁሉ እኔ ላይ ልሞክር እንዳይል ቶሎ ወደ ቤቴ ገባሁ።

«አባይ ቄስ እስካለ ድረስ በዚህም መገልበጤ እሙን ነው» አለ።

ረቂቅ ተከትላኝ ገባች። ከስስ ጨርቅ የተሰፋ ሱሪ ለብሳለች። ስፋቱ እረጅም ቀሚስ ያስመስለዋል። ወገቡ ላይ ሽብሽብ ኖሮት እስከ ብብቷ ይዘልቃል። በጌጥ የተበጀ አበባ መሰል ጥብጣብ አለው። በጎን በኩል ጉንድሽ ከንፍ የመሰለ ሽብሽብ ጨርቅ ከብብቷ አንስቶ እስከ ቁርጭምጭሚቷ ይወርዳል። ምናልባት የምትስቀው በእነዚህ ሽብሽቦቿ ይሆናል።

«ሰጊ መኪና ውስጥ ናት»

ዝም (ሰጊ፣ ሰገዛር ባቡር ጣቢያ ሥም እስከአያት)

«ሄደህ አታያትም?»,



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ዝም

‹‹ተጣልተሃታል እንዴ? ተጣልቶኛል ትላለች፤››

‹‹መጣላት አይደለም››

‹‹እ-ሁ-ስ?››

‹‹ይሰለቻል፣›› እህቴ ብትሆንም በዖታ ከእኔ ይልቅ ለእሷ እንደምትዛመድ ገብቶኝ ሙሉ ስሜቴን ከመግለፅ ተቆጠብኩ። የረቂቅን ልብስ ንፋስ ነካክቶ ያንሿሿው መሰለኝ። ቀና ብዬ አየኋት። በረጅሙ ተንፍሳ ዝም አለች።

‹‹እውነቱን ነው፣ መሰልቸት አይገልፀውም። ይታከታል›› ጨመርኩላት።

በሽብሽቦቿ ዳግም በረጅሙ ተነፈሰች።

‹‹እኔ የምፈልገው...›› አቋረጠችኝ

‹‹አንተ የምትፈልገው አንዲት ብን ብላ የጠፋች ልጅ እያሰብክ ባዶ ቤት ተዘግተህ መኖር አይደል? ብታውቀው የሚጨንቀውና የሚሰለችው ይሄ ህይወትህ ነበር።››

‹‹ትምህርቴን እየተከታተልኩ አይደለም?››

‹‹እሱን ተወው››

እውነቱ ተምታታብኝ። እዚህ ቤት ተዘግቼ ውጭው የሚያስጠላኝ ለምንድነው? ሲፈንን ለማሰብ ነው? አስቤያት የማውቅ አይመስለኝም። ምናልባት ውስጤ አንዳች ድብቅ ጥበቃ ሳይኖር አይቀርም። እንደምሰሶ ቀጥ ብሎ የህይወቴን ወጋገራ የተሸከመ ጥበቃ! ቀን ሆነ ሌሊት ደጃፌ ከውስጥ ሲሸጎር ስለሚጨንቀኝ ጥበቃ ውስጥ እንዳለሁ ይገባኛል እንጂ...

ክረምት አግቢዩ ተወርውራ አልጋ ላይ በሆዷ ተንበለበለች። እንደምታለቅስ የገባኝ የሰውነቷን መንዘፍዘፍ አይቼ ነው። ለቅሶው ለእኔ ወይስ ለሷ??? ለጠናጋሻው ወይስ ለለገነት???



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ ሶስት

## የፍቅር ነገር

ጻዋ የዋጣት መንደር፤ ከየብሽሽቷ ሆዋታና ብርድ ይፈልቃል፡፡ የሚባርቅ ጭርታ እንደ ጥይት በገላ ውስጥ ሾልኮ የሚያልፍ ውርጭ...

...እናቴና ለገነት ግንባር ፈጥረዋል፡፡ ያደፈጠ ነፋስ ድምፅ ሳያሰማ ልብሳቸውን ሲገፋቸው ይታገላል፡፡ ለገነት ሲፈንን ሆና ትተውናለች፡፡ አባቴ የወንበር ተሽከርካሪ ይነዳል፡፡ ጋሽ ተገኔ እንደ ልጅ በእሽኮለሌው ነፍሳቸው ምንጥቅ እስኪል የተደሰቱ ይመስላል፡፡ ውርጩ ሽንኅብታቸው ላይ ተጠራቅሟል...

...የረድ ሦርዊ አባት ከተከሴ አቋቋም የተቀዳ አካሄዳቸውን እንደ ትርኢት ያቀርባሉ፡፡ አባቴና ጋሽ ተገኔ ጋ ሲደርሱ እጃቸውን እንደመስቀል ያሳልማሉ፡፡ አባቴ አቀርቅሮ መዕናኛ ቃል ይቀበላል፡፡ በሌሉበት ይኃፈላል፤ ባሉበት ይኅናበሳል...

...ሙቀትና ጨኸት የሚለጥ ዕዕ ገዝቼ ጆርባዬ ውስጥ ከትቻለሁ፡፡ እናቴና ለገነት እንዳያዩኝ ተጠንቅቄ ቤቴ ገባሁ፡፡ ጠናጋሻው አልጋ ላይ ቁጭ ብሎ መጻሕፍቶቼን እያገላበጠ ነበር፡፡ ድንገት ከፍቼ ስገባ መርበትበት ታየበት፡፡ ከቀን ወደ ቀን እምሽክ ድቅቅ የሚል አንዳች ነገር እላዩ ላይ አያለሁ፡፡ እናቴ «ቆሌ የራቀው» የምትለው እንዲህ ያለውን አካል ላይ የማይታይ የመንፈስ ድቀት ይሆን?...

«ኖር! ኖር» አለኝ፤ ሰማያዊ ሹራብ ከሰማያዊ ጨርቅ ሱሪ ጋር አድርጓል፡፡ መርበትበቱን በማህበራዊ ስርዓት እየሸፋፈነ መሰለኝና ፈገግ አልኩ፡፡

«በዓድቃን»

«ዓድቃን ማነው?» አለኝ «ጥሩ!»

«እኔና አንተ» ፍራሽ ላይ ተዘረፈጥኩ፡፡

«ጥሩ! እኔና አንተ በማለትህ ቢያንስ አንተ ተኮንነሃል፡፡ እምነት መታበይን አታዳብልምና፡፡»

«እሹ ታገኘማላችሁ አልተባለምን?»

«አንኳኩ ይከፈትላችሁማልስ አልተባለምን?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ታዲያ»

«መሻትና ማንኳኳት መታበይ አይደለም» አለና ትንሽ ሳቅ ብሎ «አንተ መሻትህን በመቀማት፣ ማንኳኳትህን በመበርገድ አከናውነሃል።»

«የላይኛው ችሎት እንዲህ ይሆን የሚያከራክረው?» አልኩት።

«ይመስለኛል፣ ካልሆነም ከኛ ክርክር መማር ይኖርበታል። ጥሩ! የተማሪዎቹን አሳይመንት እዚህ ማረም ፈልጌ ነበር የመጣሁት» ብሎ አጠገቡ የተቀመጠ የእጅ ቦርሳ ዳሰሰ

«ጥሩ ነዋ፣ ምናልባት...»

«እስከስራ መውጫ እንችላለን። ማስቴ የኔ ሸይጣን አይነሳባትም።»

«ቀይ ሸይጣን» ስምረትን ቦጨቅናት የጀርባዬን «ዕፀ-ቅዱሳን» አውጥቼ ፊቴ ላይ ዘረጋሁና ሳልጠይቅ ሁለት እንጨት አቀበልኩት።

«እንግዲህ ለማንኛውም በሩ ይዘጋ» አለ

የእኔ ቤት መዘጋቱ እውስጥ አለመኖሬን አይናገርም። ይሁንና የጎፈላ በርግዶት እንዳይገባ ይከላከላል። እቴቱን ለምኜ ደጃፉን ከውጭ አስቆለፍኩ። ቁጭ ስል እየተገረመ...

«ዛሬ ፈተና ላይ ፍልስፍና ምንድነው? ብዬ ጠየኩ። ጥሩ! አንዱ ምን ብሎ ቢመልስ ጥሩ ነው?»

«ምን አለ?»

«ፍልስፍና ብዙ ነው። አትፈላሰፍ ከተባለ አትራቀቅ ነው፤ መፈላሰፍህን ተወኝ ከተባለ መዋሸት ይሆናል፣ ፈልስፎ ያወራል ከተባለ፤ ምክንያት የሌለው ነገር ይናገራል ነው... ጥሩ»

ተሳሳቅን።

«ልጁ ችግሩ ክፍል አለመግባትና የተሰጠውን መጽሐፍ አለማንበብ ብቻ ነው። ጥሩ ጥሩ ቢያንስ ቢያንስ ማህበረሰብ ስለፍልስፍና ያለውን ግምት ያውቃል። ስለዚህ ግማሽ ራይት ሰጠሁት።

ወዲያው በሩ ተንኳኳ፤ ተደገመ። የጠናጋሻው ፊት ወዙን መጠጠ።

«አንጓች፣ አየሽው ይሄንን ልጅ ከውጭ ሲያስቆልፍ?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ተዋት›› ብዬ አረጋጋሁት፡፡

‹‹እቴቴ ክፈችልኝ! አላውቅም እጮሃለሁ! እምቢ ክፈችው! ከሌለም አይቺው እሄዳለሁ››

ተውሼ ያልመለስኩት፣ ተበድሬ ያልከፈልኩት ምን እንደሆነ አሰቤ ግራ ተጋባሁ፡፡ ባለዕዳ ሆኛለሁ ግን የተበደርኩትም ሆነ የተዋስኩት ነገር የለም፡፡ ኡፍፍፍፍ

ጠናጋሻው በሀዘኔታ ያየኛል...

‹‹ያንተን ህይወት እየደገምኩት ነው›› አልኩት ለዘብ ብዬ...

‹‹ዴፍንትሊ!››

በሩ ተንቀጫቅጮ ተከፈተ ብርድና ለገነት ገቡ፡፡ ጭርርርር... ለምን ባለዕዳነት ይሰማኛል? ለምን እቀረቅራለሁ?!...

‹‹እወድሃለኋ! እወድሃለኋ!!››

ቀና ብዬ አየኋት፡፡ ተንከራታ፣ ተንከራታ የደከማት ክረምት አገቢ፡፡ ፊቷ ላይ ጊዜ የሚጠብቅ ፈንጂ ተጠምዷል፡፡ አይኗ ውስጥ በቀል የእባብ ጫጩት መስሎ እስኪያድግ ያደባል፡፡

ዷ! ብትንትን

ሃኘ! ምርዝርዝ

‹‹ይቅርታ!›› አለች ወደ ጠናጋሻው እያየች

‹‹ጥሩ›› አላት

‹‹ትንሽ ተቀምጬ፣ ትንሽ እቀፈኝና፣ ትንሽ አውራኝና እሄዳለሁ፡፡››

ከአፍቃሪዎች ይልቅ ተፈቃሪዎች ብፁአን ናቸው፡፡ በዚህ ሰዓት የተሰማኝን መደናቀፍ የትኛው ሰማዕት ተቀብሎታል?

የማልፈልግ መወሸቋን ተቀበልኩ፡፡ ለአስገዳጅ መታቀፏ የግድ ተንበረከኩ፡፡ አሁን ይሄን የጎን ችንካር የትኛው ፃድቅ ታግሶታል?

‹‹በቃ ሂጂ›› ስላት

‹‹ትንሽ፣ ትንሽ›› ትላለች



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ጊዜ አቆጣጠራችን ተዛንቋል። የእሷ ትንሽ የእኔ ዘለዓለም ነው። አለመፈለግና መፈለግ ድንበሩ የት ነው? የጊዜ አቆጣጠር ቅጣችንን ምን እንዲህ የግርንቢጥ አደረገው?

‹‹በቃ፣ ሂጂ››

‹‹ትንሽ - ትንሽ››

ፍቅር ልማድ ነው ወይስ ነባር የተፈጥሮ ባህርይ? መታቀፍና ማቀፍ የትኛውን ተፈጥሯዊ ፍላጎት ያስታግሳል? አለመታቀፍና አለማቀፍ እንዴት ህይወትን ስልቹ ለማድረግ ይችላል? እዚያ ውስጥ ምን አለ? አማልክቶቹ ሲፈጥሩን ምን አኖሩብን?...

ቀና ስል ጠናጋሽው ዓይኔን ጠብቆ ጠብቆ ቀለበ፣ በምልክት ‹‹ልሂድ?›› አለኝ። እንዲቆይ ነገርኩት። የህይወት ግዳችን በሀላፊና ጠፊ ነገር ላይ ለመመስረቱ ምስክር ይኸው...

‹‹ለገነት፣ ለገነት›› እናቴ ከውጭ ሆና ተጣራች።

‹‹እንጓች ደሞ›› አለች ከእቅፌ ላለመውጣት እየተፍለከለከች።

‹‹እስኪ አንዴ ብቻ ነይና...›› የእናቴ ቃል እንደ ቴክሳሶች ገመድ ጠልፎ ጎተታት። እንደአባያ በሬ እግሯ ከወለሉ አልነሳ እያለ ተጎትታ ወጣች።

‹‹የ-ሱ ሚስት የመጣች እንደሆን...›› ይዛት ሄደች። ተነስቼ በሩን ቀረቀርኩት።

‹‹አትወዳትም?›› ሁሉን የሚያውቅ መለኮታዊ ምርመራ ጀመረ። ቀና ብዬ አየሁት የተማሪዎቹን ወረቀት ማረሙን ቀጥሏል።

‹‹አዎ›› መዋሸት አይቻልም

‹‹ጥሩ››

‹‹እንዴት?››

‹‹ማለቴ... ለምን?››

ምክንያቱን አውቀዋለሁ? ትንሽ አሰብኩበት።

‹‹ምክንያቱን አታውቀውም?›› አሁንም እጅና ዓይኖቹ ወረቀቶቹ ላይ እየተላወሱ ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹አውቀዋለሁ እንጂ›› አውቀዋለሁ እንዴ?

‹‹ጥሩ፣ መንገር ካላስፈለገህ...››

‹‹ግዴለም፤ ብትሰማውም መጥፎ አይደለም፡፡›› በረጅሙ ተንፍሼ ቀጠልኩ...

‹‹ሌላ ሰው ሆና ነው የመጣችው፡፡ ወይም ወከላ፤ ማስታወስ የማልፈልገው ሰው እሷ በመጣች ቁጥር ትውስታዬ ውስጥ ይሰነቀራል፡፡››

‹‹አልገባኝም›› ቀና አለ ‹‹ጥሩ? የምታስታውስህ ማንን ነው?››

‹‹ሲ-ፌ-ን›› ባለሦስት አፍ ጦር

‹‹ምኗ ነው እሷን የሚመስለው?››

‹‹ሁለመናዋ! የምታፈቅርበት አኳኋን፣ ፍቅሯን የምትገልፅበት መንገድ፣ ከእናቱ ጋር ያላት ቅርበት፣ በኔ ላይ ያላት የበላይነት፣ እልኋ...››

‹‹ሴቶች ሲወዱም ሲጠሉም ተመሳሳይ ነገር ያንፀባርቃሉ፡፡ ሰገንትና ሲፊን መመሳሰላቸውን እንደ ልዩ ነገር አትየው፤ ጥሩ!›› አለና ቀጠለ፡-

‹‹እርግጠኛ ነህ? አትወዳትም?››

‹‹እርግጠኛ ነኝ››

‹‹ታዲያ'ኮ አንተ የምታደርገው የሚወድ ሰው የሚያደርገውን ነው፡፡››

‹‹እንዴት?››

‹‹ጥሩ፣›› ጥቂት አስቦ መናገር ጀመረ

‹‹ሴትን ስትወድ ያልወደድክ፣ ስትጠላ ደግሞ ያልጠላህ መምሰል ነው የሚያዋጣው፡፡››

‹‹እንዴት?›› የረሳሁትን ጫት አንስቼ ቀነጣጠብኩ፡፡

‹‹ለምሳሌ በዚች ልጅ ላይ ሙከራ አድርግ፡፡ እሷ ከመምጣቷ በፊት የምትገኝበት ቦታ ሄደህ ፈልጋት››

‹‹እኔ?››

‹‹አዎ››

‹‹አላደርገውም››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሕሷን በመፈለግህ ብቻ ብዙ የሚገፋፏትን መጥፎ ስሜቶች ታስወግዳለህ፡፡››

‹‹ለምሳሌ››

‹‹ጥሩ፣ ለምሳሌ ያስመፈለግ እልኂን ታስወግዳለህ፡፡ ሌላው የተሸናፊነት ስሜቷም ወደ አሸናፊነት ይሸጋገራል፡፡ በመጨረሻ የቀመሰችውን ለማቅመስ ስትል ሸሽት ሸሽት ትላለች፡፡››

‹‹ህይወት ቀመር ብትከተል...››

‹‹ይሄን መጥፎ ስሜት በሙሉ እሷ ውስጥ የፈጠርከው አንተ ነህ፡፡ እሷን ባለመፈለግና በመሸሽ ጥሩ!››

የጠናጋሻው ቀመር ከስራ እንዴት ህይወቱ በሴቶች ሲተራመስ ዝም አለ? ወዲያው ግን አንዳች ነገር መንፈሴ ላይ ተሰነቀረ፡፡ ጠናጋሻው ይሄን ዘዴ ለመጠቀም ቢፈልግም እንኳን ረቂትን መቅረብና ያስመፈለግ እልኂን እንድትቀይር ሊረዳት አይችልም፡፡ ረቂት መፍትሄ በሌለው ደዌ ተይዛ ዕድሜ ዘመኗን እንድትማቅቅ የተፈረደባት መሰለኝ፡፡ እንደ ጡረታ ድልድይ ብርድ አጥንት የሚሰረስር መቆርቆር ስለሷ ተሰማኝ፡፡

ከዚህ በኋላ ስለብዙ ያልተሳኩ ፍቅሮች አጫወተኝ፡፡ በይበልጥ ለጥበብ ኃይል እንደሚሆኑ ምሳሌ እየሰጠ ተንተነልኝ፡፡ የተቃጠለውን ጊዜ ለማካካስ ይመስል ጫቱን ቶሎ፣ ቶሎ እየቀነጠሰ ከጎረሰ በኋላ

‹‹ከሁሉም ከሁሉም የሚደንቀኝ የዳንቴ የፍቅር ታሪክ ነው፡፡ ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለ በፍሎረንስ ጎዳና ላይ ሲዘዋወር አንዲት ልጃገረድ ተመለከተ፡፡ ጥሩ! እንዳያት ወደዳት፡፡ ከመውደዱ ፅናት ሊከተላት እንኳ አልቻለም፡፡ ቢትሪቼ ፓርቲናሪ ትባላለች፡፡ ዳንቴ ያገኛት ለትንሽ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ገና የሃያ አራት አመት ወጣት ሳለች ሞተች፡፡ ጥሩ! እንግዲህ ዳንቴ የጥበብ መልህቁን የጣለው እዚች ሴት ላይ ነው "The New Life" የተሰኘው የግጥም መጽሀፉ ብቻ ይበቃል፡፡ "The Divine Comedy" ይችው ሴት ገፀ ባህርይ ሆና የምትመጣበት የህይወት ታሪኩ የተካተተበት መጽሐፍ ነው፡፡ በተለይ ለጥበብ ሰው ፍቅር ሲገኝ ሳይሆን ሲታጣና ስቀቀን ሲያወርስ ነው የዕድሜ ልክ ስንቅ የሚሆነው፡፡ ለነገሩ ገጣሚ ብትሆን ከዚህ ስትሄድ እንዴት ያለ ቅኔ ትዘርፍ ነበር? ጥበብ የፍቅር ቁስቆሳን ይፈልጋል፡፡››

‹‹የጥበብ መጀመሪያ ፍቅረኛን ማጣት ነው›› የሚል ጥቅስ አይኔ ሀሊናዬ ላይ ሙጥኝ አስፈገኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የማሽን ያህል እየቀነጣጠሰ ወደ አፉ ከትቶ ‹‹ጥሩ›› አለ፡፡

‹‹ምኑ?›› አልኩት

‹‹ስለ ሲልቪያ ፕላት ልነግርህ ነው፡፡ አሜሪካዊት ገጣሚ ናት፡፡ ጥሩ! የምታፈቅረውን አግብታ ወደእንግሊዝ ሄደች፡፡ ፍቅር ሰመረ፣ ጥሩ! ሁለት ልጆች ወለዱ፣ የበለጠ ሰመረ፡፡ ግን ለጥበብ ሰው፤ ያውም ለገጣሚ ይሄ የፍቅርና የኑሮ ስኬት ምኑም አይደለም፡፡ ልጆቿን በመንከባከብ በማስጠናትና ዕድገታቸውን በመቆጣጠር ብቻ ‹‹ተመስገን›› ብላ የምትኖር የቤት እመቤት መሆን አልቻለችም፡፡ ለጥበብ የምትሰጠው ጊዜ በልጆቿና በባሏ እየተወረረ ሲመጣ መኖር ትርጉም አልባ እየሆነ ሄደ፡፡ ስለዚህ ገና በሰላሳ አንድ ዓመቷ ጭንቅላቷን ዳቦ መጋገሪያ ምድጃ ውስጥ ከትታ ሞተች፡፡››

ስደነግጥ

‹‹ጥሩ›› አለ፡፡

ወዲያው በሩ ተንኳኳ፣ ተንጋጋ፣ እስኪናጥ ተደበደበ… ስለጠናጋሻው ያለኝን የግምት ምስል ሊለውጥ የሚችለውን መርበትበት ላለማየት ዓይኖቼን አሸሽሁ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ አራት

## የቆሌ ነገር

ጡረታ ድልድይ የፀጥታ ቅርፊት ተከናንባለች። ሥርየት በሌለው ዘለዓለማዊ ጭርታ ውስጥ እንደሰማዕት ከዝምታ ስቅይት የሚታደጋትን ሞት የምትጠብቅ መስላለች።

«አቤት ጭጭ!፣ አቤት ውርጭ!...»

ጡረታ ድልድይ የድምፅ ምንጯ ነጥፏል። ልሳኗ እንዳይከፈት ሆኖ በመቃብር ድንጋይ ታትሟል። ነዋሪዎቿ እንደቅማል ሽጥ፣ ሽጡን ይገጠግጣሉ እንጂ የተጋለጠ መንገዷን አይደፍሩም።

«ነፍስ ያለው የሚኖርበት አይመስል...»

ድንገት ከቤት ወጥተህ ኡ! ኡ! ኡ! ኡ! በል ይለኛል። ሰዎች በልሳነፀይን ያወራሉ፣ የሩፋኤል ቅዳሴ ደመና ሆኖ ያንገርብባል፣ አይዘንብም። የሼሁ ሆጄሌ መስጅድ አዛን የመንደሯ ቅርፊት ላይ ይነጥራል።

የጡረታ ድልድይ እናቶች እኔን ሲያገኙ የአይናቸው ልሣን ይሰላል። መጥፎ ትውስታቸው እንደሆንኩ የሚነግሩኝ ይመስለኛል። እንደልጆቻቸው እንደእኩዮቹ በሽጎሌ ፍንዳታ ወደምንምነት አለመለወጤ ጥፋት እንደሆነ በአይናቸው ይነግሩኛል።

ለመጀመሪያ ጊዜ የአይን ልሳናቸው የተፈታብኝን ጊዜ በቅጡ አስታውሳለሁ። የአስራ ሁለተኛ መልቀቂያ ፈተናን ያለፍኩ እለት ነው። እናቴ አድባርን የሚያስታውስ ጥድፍድፍ ያለ ዝክር መሰል ግብዣ አደረገች። ያኔ የጡረታ ድልድይ እናቶች የዝምታ ልሳናቸው በእኔ ላይ ሲፈታ ታወቀኝ። እስኪገባኝ በአይናቸው ተንተባተቡብኝ። ሳውቀውና ከቋንቋቸው አፌን ስፈታ በፀጥታ ሲንጣጡ አደመጥኳቸው። ከዚያች ዕለት አንስቶ የጡረታ ድልድይን የፀጥታ ቅርፊት በርቅሼ በመውጣት፦ ኡ! ኡ! ኡ! ኡ! ማለት እንዳሰኘኝ አለሁ። እሪሪሪሪሪ... ለዝንት ዓለም፣ ለዘልአለም...

...ምኞቴ ህልም እንጂ እውነታን አልወለደም። አንዳንዴ በሪን ከፍቼ እንደፈቆ ቀጥ ብላ የቆመች ቤቴ ላይ ወጥቼ የጩኸቴን ጠበል ለመሳው ጡረታ ድልድይ ሳረስርስ አልማለሁ። እሪሪሪሪሪሪ....



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

…እሪታዬን ጣሪያ ላይ ትቼው ወርጄ ቤቴ በመግባት ተንጋልዬ አደምጠዋለሁ። ጨኸቱ እየበዛ፣ እየተባዛ ምድርን እንደአብርሃም ዘር በእሪታ በረከት ሲሞላ ይታወቀኛል። የድምፅ ሾተላይ ያለባት ጡረታ ድልድይ በድንጋጤ ጩኸት ትፀንሳለች።

አንድ ሌሊት ጩኸቱን ተንጋልዬ ስሰማ እናቴ በሩን በርግዳ ገባች። በተርበተበተና በባተተ ፊት «ምንድነው?» አለችኝ

«ምኑ?» አልኳት

«ጩኸቱ?»

«እዚህ ነው?»

«ኧረ ውጭ ነው»

«የእኔ ነው?»

«ኧረ የሴት ነው»

በሩን በቀኝ እጇ እንደያዘች ፆሮዋን ወደ ውጭ ቀሰረች።

«በስመአብ ምነው? ልብህን ምን ወሰደው? ለምን በሩን ከውስጥ አልሸጎርከውም? በል ተነሳ ቀርቅርና ተኛ… በስመአብ!»

ጠዋት ስነቃ የእናቴን ድርጊት የህልሜ አካል አድርጌ አስቤው ነበር። ነገር ግን በሬን ለመክፈት ስሞክር ያለ አመሌ ሽጉሬው አገኘሁት። ደነገጥኩ፤ በሬን ከውስጥ ቀርቅሬው አላውቅም። አብዛኛው ሌሊት የሚያልፈው ቀን የተቀመጥኩበት ቦታ ላይ እንዳለሁ ስለሆነ ሲነጋጋ በሩን መቀርቀር አስፈላጊ እንዳልሆነ ይሰማኝና ትቼው እተኛለሁ። ዛሬ እንዴት ተሸጉሮ ተገኘ?

በሩን ስከፍት እናቴን በህልሜ እንዳየኋት ሆና ቀልቡ በተገፈፈ ፊት ተቀበለችኝ፤ የልጅ ልጇ እስሯ ተሸጉጣለች።

«እስኪ እህትህ ጋ ደውል፣ ረቂቅ ጋ ደውል። ዝም ብለህ ድምጿን ለምተህ እንዲህ ነው፣ እንዲህ ሆነ ሳትል ዝጋው… ታዲያ መጥተህ ንገረኝ። እሷ ናት ቀልበ-ቢስ…»

ረቂቅና እናቴ እናትና ልጅነታቸው ተደምስሶ ጓደኛሞች ከመሰሉ ቆይተዋል።

እየተጨናበስኩ ልወጣ ስል

«ፊትህን ታጠባ፣ ፀጉርህንም አሻሸው»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹የረቲት ውሃ እምጭልኝ›› እልኪት እናቴ ስር የተሸጎጠችውን የልጅ ልጅ። ሁሉንም የእህቶቼን ልጆች በእናቶቻቸው ስም ነው የምጠራው። የታናሽ እህቴን ልጅ ‹‹የአበባሼ›› እስታለሁ። አበባሽ ከየት፣ ወዴት እንደሆን ሳይታወቅ፣ ለማን፣ ከማን እንደሆነ ሳይገባን አንድ ልጅ ወልዳ ለእቴቴ በመስጠት አረብ አገር ከሄደች ሶስት አመት አሳለፈች፤ አንዳንዴ ደውላ ትንፋረታለች። ለአመሏ ‹‹ልቤን›› ትላለች።

ፊቴን ስታጠብ እቴቴ የአበባሽን እየጎተተች ከቤት ወጣች። የጠዋት አይኗን ጨፈር ተሀናወቶባት አጨንቁራለች። የቅንድቧ አካፋይ ላይ ያለውን ጠባሳ ፊቷን ዋሾ መከሳተር አላብሶታል።

‹‹ምነው እማዬ?›› አመሳትላ የለበሰችውን ነጠላ ወግ ለማስያዝ ሞከረች።

‹‹ኧረ ሲጮህ አደረ፣ አንቺ አልሰማሽም?››

‹‹እኔ'ቴ ማነው?››

‹‹እንጃ ልጄ፣ የልጆቹ ነገር ሀሳብ ላይ ጥሎኝ... ››

እራታዬ እስሴ ሆኖ ከባሪያ፣ ጣሪያ እየዘለለ ጡረታ ድልድይን ሲያሽብር ማደሩን ለእናቴ ማን በነገራት? ግን የህልም ዓለም ጨኸት ለእውን አለም ጆሮ ምን ነው? የእኔ ህልም እንዴት የእናቴ የእውን ጆሮ ተለብ ሆነ?

ከግቢ ወጥቼ ብዙም ሳልርቅ የረቲቅ መጥታ ‹‹ለስምረትም ደውል ብላለች እማዬ›› አለችኝ።

የሽጎሌ ፍንዳታ ኩርፊያ ውስጥ ያልከተተው የእኛን ቤተሰብ ብቻ ነው። እናቴ ሆነች አባቴ ከእህቴ ከቻይና ሞት በኋላ ሴት ልጆቻቸውን በማሰብ ‹‹ተመስገን›› ለማለት አልተጓደዱም። የልጅ ልጆቻቸውን በፍንዳታው ለሞተች ልጃቸው እንደመተኪያ በማየት ሌላ ‹‹ተመስገን›› ሳያክሉበት አልቀሩም። አባቴ ብቻ አንዳንዴ መጠጧን ሲወሳስድ ግንባሩ ላይ የነበረውን ጥይት ቤቱን ይዳብስና

‹‹ከእንግዲህ የእኔ ነገር አበቃለት! ሰባት ትውልዴ ወንድ አይታይበትም፣ አበቃ›› ይላል። ጋቢውን ገልጦ ከደረት ኪሱ ትንሽ ማስታወሻ ያወጣና ጣቱን በምራቁ እያረጠበ የትውልድ መዝገቡን ያገላብጣል። ከዛ ጥይት ተቋጥሮ የኖረበትን የግንባሩን ጠባሳ ዳበስ ዳበስ አድርጎ ማንበነቡን ይቀጥላል።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ስምረት በነሐሴ ወር ሌሊት ዘጠኝ ሰዓት ምግ ተይዛ ሆስፒታል ብትወልድ ሴት፤ ልክ በአመቱ በዚያው በነሐሴ ወር ንጋት ለሰኞ አጥቢያ ብትደግም ሴት፡፡» በምራቁ ጣቱን አርሶ ይገልጣል፡፡

«እሸቫ በጥቅምት ሌሊት ሰባት ሰዓት ሆስፒታል ልንወስዳት ስንንጎዳጎድ ቀድማን ብትወልድ ሴት፤ በአመቱ ወልዳ ቢጠፋባት ሴት፡፡

«ረቂቅ አ? (ስካ ቀዳሚዋ ኢሷ ኖራለች?) ልክ የእቦ እለት ቀን ዘጠኝ ሰዓት ተጠርተን እየተቻኮልን ብንሄድ ጋንዲ ሆስፒታል አናስገባ ብሉን እንደቆምን ብስራቱን በአጥር ላይ ሰማን፡፡ ‹ምን ወለደች?› ብዬ ብጠይቅ ሴት፡፡ እከደከበ

«አበዛሽ ዕንስ መያዟንም ሳናውቅ ወፈረች ወፈረች እያልን ተዘናግተን፤ የገንፎ እህል እንኳን ሳይዘጋጅ በሚያዝያ 13 ለ14 አጥቢያ ምጧን ችላ የተኛችበት ብትወልድ ሴትዘ... እበቃ! ከእግዚአብሀ ሰባት ትውልዱ የሴት መንጫጫት ነው፡፡»

«አንቱ ሰውዬ፣ ልጆቹን እየቆጠሩ ለሴጣን አሳልፈው አይስጡብኝ፡፡ እንዴት ልጅ ይቆጠራል? ከብት አደረጓቸው? እረ ከብትም አይቆጠር...»

እኔ ግን የአባቱ ተስፋ መቁረጥ ወደ እንጦረጦስ ወርዶ-ወርዶ ማረፍ ሲሳነው ይታየኛል፡፡ ከሰባተኛ ሰማይ፣ ሰባተኛ ትውልድ አይርቅ ይሆን? ቀፈን የሚለቅ ሀሳብ ውስጥ ገባሁ፡፡

የከበሰለ ድምጼ እንደተወጠረ ሳስቲክ ከልሳኔ ተቆርጦ ያንገፈበበትን የጡረታ ድልድይ አካባቢ ገመትኩ፡፡ ምናልባትም እዚያ ስልክ እንጨት ላይ አረፍ ብሎ ይሆናል፡፡ እንደ ገብርኤል ሰይፍ ድምጼ ምድርን እየሰነጠቀና እየገለባበጠ ለብዙ ቀለስተኛ መንደሮች መድኅን ይሆን ይሆናል፡፡

ቤቶች በውርጭ የወረዛ ክዳናቸውን ከምድር አንድ ጋት ብቻ ከፍ አድርገው ሲታዩ በቁማቸው እየሰመጡ ይመስላል፡፡ ግድ ካልሆነብኝ በስተቀር ጡረታ ድልድይን ሰንጥቄ ማለፍ አልወድም፡፡ ይቀፈኛል፡፡ በእኔ እድሜ ያ ልጆች ሁሉ ወደ ብናኝነት ተቀይረው ብቻዬን ስንጠራወዝ የከሀዲነት ስሜት ይወረኛል፡፡ ምናልባትም ኢየሱስ ይሄንን ችግር በደንብ ሳይረዳው የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ሄሮድስ እኩዮቹን ሁሉ አርዶ ስለጨረሰበት የኖረባት መንደር የምታሳድርበት ስሜት ከእኔ ብዙም የተለየ አይመስለኝም፡፡...

...ግን ሌሊት አንባረቀ የተባለው በእርግጥ የከበሰለው የእኔ ድምፅ ይሆን? ወይስ እንደራሄል መፅናናት ያልወደደች ቆሌ ከጭንቀቷ ለመገላገል የለቀቀችው?... በገዛ ትብታብ ሃሳቤ ተተብትቤ እርምጃዬን ሳፈጥን ስላልቻልኩ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ረድ ሠርዊ አባቱን አስቀድሞ ከወደኋላዬ ደረሰ። አባቱ በትከሻም ጥምጥማቸው እየገላመጡኝ አለፉ ረድ ሠርዊ ሲከተል ሆን ብዬ ሁለቱንም በነገር ነካካሁ

‹‹መሪጌታ ሠርዊ፣ እንተ›› አልኩ።

ረድ ሠርዊ በእናቱ የነገር ገመድ የታነቀችውን ለገንት መሰለ። እግሩን ከመሬት ጋር እያፋጨ ወደኋላ ቀረት አለ። አባቱ የግንድ ቁራጭ የመሰለ እግራቸውን በጤዛ አወርዝተው ሲቆሙ ዳግም የማይንቀሳቀሱ ይመስሉ ነበር።

‹‹ሠመ ወይ የእሜቴ ልዥ፣›› አሉኝ ጋኔን የፈተሰው ትልቅ ልቃቂት የመሰሰ ጥምጥማቸውን ወደኋላ እያዞሩ። ፊታቸው ያሽሟጥጣል፦

‹‹መሪጌታ ነኝ አለ እንዴ? አጀብ መንጠራራት እሱን እዚያ ማን አደረሰው? እኔ ልንገርዎ የማዕረግ ሥመ በፊትም አሁንም ረድ ነው። በፊት ለአቡነ ኤርምያስ ወይባውን ለብሶ ወገቡ ላይ መቀነቱን አስሮ ውሃ በእንስራ እያዘለ ይቀዳ ነበር። አቤት የሚጠምቅላቸው ጠላ፣ አቤት የሚጥልላቸው ጠጅ። አቤት የሚሠራላቸው አተር ክክ ወጥ... አሁንም ያሉ እንደሆን ስላልፈለኩ ጠላና ጠጅ አያደርግልኝ እንጂ ወጥ መቀቀሉን አልተወም። ስለዚህ፣ ረድ ይበሉትማ፣ ረድ ሠርዊ ቢሉት ከሳሽ የለብዎትም። ዳግም መሪጌታ ብለው ሲጠሩት እንዳልሰማ።››

ረድ ሠርዊ የተወቀሰም ሳይመስል

‹‹የንታ የቀጠሮ ሰዓት እንዳያልፍብዎ፣ ንሡ እንሂድ›› አለ። ሲሄዱ ወደኋላ ቀረት ብሎ

‹‹ምቱረ ክሳድ መጥምቀ መለኮት ሻይ ይገቡልኛል፤ የንታን ሸኝቻቸው እመጣለሁ።›› አለ። ‹‹አቤት ብርድ፣ አቤት ቊር ማለት››

ፈገግ አልኩ።

ማርገጃው እንደደረስኩ የህዝብ ስልክ ፊልጌ ሳንቲም በማስገባት ደወልኩ። ረቂቅ እንደ ቆሌዋ ስትጮህ አደራ በተባዘተ ድምፅ ‹‹ሃሎ›› አለች። እናቴ እንዳለችው ድምጿን ሰምቼ መገዛት አልቻልኩም።

‹‹ደህና በዙረት አደርሽ?›› አልኳት

የአሽን ሳቅ አሰማችኝ።

‹‹ታዲያ እንደምን አመሸሽ? አሁን ልትተኚ ነው?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አሁንም ሿሿሿ የሚል ድምፅ የሚበዛበትን ሳቋን አሰምታኝ:: ‹‹ጌታዬ ነህ›› አለችኝ:: ሰምኑን ያወጣችልኝ ስም ነው:: በአለባበስ ጠናጋሻውን እየመሰልኩሳት ስለመጣሁ ይሆን?

‹‹እማዬ ሲሮህ አደረ፣ እስኪ ደውልላት ብላኝ ነው:: አንቺ ጮኸሻል እንዴ? ማለቴ እዚያ መጨፈሪያሽ ሳይሆን እኛ ሠፈር መጥተሽ››

የክረምት አግቢ ከንፍ ተሰማኝ::

‹‹እስኪ ለገነትጋ ደውል፤ እሷ ናት እዚያ ጉዳይ ያላት:: ልትሮህ ትችላለች::››

‹‹ተ-ይ ረቂቅ!›› ራሴ ነገር መፈለጌን ረስቼ የነገር ተፈላጊነት ስሜት ተሰማኝ::

‹‹ብል ልተኛበት ቻው! ዛሬ ትምህርት ቤትህ ደጃፍ ላይ ምሳ ሰዓት እመጣለሁ:: አምስተኛ በር-ጋ ጠብቀኝ እሺ?››

‹‹እሺ?››

ዘጋችው::

ስምረትጋ ስደውል አንስታ ከትክት ብላ ሳቀች ‹‹ብል ተወው እኔ መች አጣሁት፤ አንተ የፈለከው እሱን፣ እኔ ሳነሳብህ የማይሆን ነገር...›› ተትከነከነች...

..ዘጋሁት::

ረድ ሠርዌ ተጣራ፦

‹‹አልአዛር ዘአርምሞ››

ዘጋሁት:: አካሄዱን ሲያፈጥን እንዴት ይሆን? ያው እንደ አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ነው:: ደርሶብኝ ‹‹ያልሰማኸኝ ሆኖ ነው? ሻይ ግዛልኝ ብዬህ›› ከሩፋኤል ቤተክርስቲያን ዐፀድ ጋር አዳብዬ ሳየው ጨርሶ ከዘመኔ በሺህ አመታት የራቅሁ መሰለኝ:: የሩፋኤልን አደባባይ ትተን የሼህ ሆጀሌ መስጂድ መዳረሻ ላይ ወዳለ አንድ አሮጌ ሻይ ቤት ገባን:: ባለቤቱ የሼህ ሆጀለ ዘመድ እንደሆነ ይነገራል:: ልጅ ሆነን ቤቱ ደጃፍ ላይ ፓስቲ እየጠበሰ ይሸጥልን ነበር:: ተሻሽሎ ሻይ ቤት ከፈተ:: ሌላ ስለሌለ ሻይና ፓስቲ አቀረቡልን::››

‹‹ይሄን ስበላ ቢያዩ የንታ ሰውም አያደርጉኝ::›› አለና ብስኩቱን ቆርሶ ሻይ ውስጥ ነከረ:: ሻዩም ጉም እየሰራ የፓስቲውን ዘይት አንሳፈፈ::

‹‹ልጅ ሆኜ እናቴ ነበረች››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እናት ነበረችህ እንዴ?›› የእውነቱን ደግሞ ተገረምኩ። አባቱ ከሴት የወለዱት አይመስለኝም ነበር?

‹‹ነበረችኝ እንጂ፣ ያውም ሸጋ፤ የንታ በዚያ በደረቀ ከርናቸው አድርቀው አድርቀው አበረሯት። አንድ ልጅ የእኔን መንትያ ድርሻዋን ይዛ ጠፋች፣ ጠፋች።›› ፓስቲውን አፉ ውስጥ አንከላወሰው። ‹‹መቼም መናጢ ናቸውና እኔን ደግሞ ሊያበሩ ታጥቀው ተነስተዋል። ሌላ ትዳር ሊመሰርቱ ሳያስቡም አይቀር››

‹‹እንዴ ቄስ ከሕግ ሚስቱ ሌላ ያገባል እንዴ?››

‹‹እድሜያቸው ረዘመእ ምን ያደርጉት?››

‹‹ስንት ይሆናቸዋል?››

‹‹ሦስት መቶም አይጠቅማቸው›› ሻይ ላይ የተንሳፈፈ ዘይቱን ፉት አለ።

በሳቅ ትን አለኝ።

መሳቱ ስላናደደው የቆረሰውን ብስኩት ሻይ ውስጥ ሳይነክር እርግፍ አድርጎ የላስቲክ ሳህኑ ላይ አስቀመጠው። ሙሉ በሙሉ ዞሮ እንዲህ ተረከልኝ።

‹‹አባቴ ጎንጅ ሰደውኝ ሳለ መቃብር ቤት ውስጥ አባ ዘካሪያስ የሚባሉ ሰው አስጠርተው እውነት የአለቃ ዕጓ ልጅ መሆኔን ጠየቁኝ።

‹‹አዎን አባ›› አልኳቸው።

‹‹ይገርማል፣ ይገርማል››

‹‹ምኑ?››

‹‹መልአከ ብርሃን ዕጓን ታውቃለህ?››

‹‹ኸረ አላውቅም››

‹‹ዳሩ የት ታውቃቸዋለህ? ጠላት ሊወጣ ወር ሲቀረው አስጠርተውኝ ‹ይሄ ነጭ ነጫጭባ እህል ውኃው አብቅቶለታል። እኔ ግን አላየውም። እንደ ጢስ በኖ ይጠፋል› አሉኝ። እንዳሉትም ሳምንት ቆይተው መልአከ ብርሃን ዕጓ አረፉ። ሦስት ሳምንት ቆይቶ ጥሊያን ተባረረ። እና አሳቸው ምን ብለውኛል አያቴ አለቃ ዕጓ ናቸው አባቴ አባታቸውን ይወዱ ስለነበር ሥሜን ዕጓ አሉት አሉኝ።››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹አለቃ ዕጓ?›› ስል ጠየኳቸው

‹‹ያንተ አባት›› አሉኝ

‹‹እንዴት?››

‹‹መልአከ ብርሃን ዕጓ ሲያርፉ ከመቶ ሃምሳ በላይ እድሜ ነበራቸው። ይገርማል፣ ይገርማል። አሁን ይሄንን ማን ያምናል? አሉኝ።››

‹‹ይገርማል›› አልኩ እኔም።

‹‹ምን ይሄ ብቻ እነአለቃ ምላት፣ እነ እውር ፈንቴ፣ እነ አለቃ ለማ ወልደታሪክ፣ እነ አለቃ አካለወልድ... ሁሉ እሳቸው ዘንድ እየመጡ ይጠይቋቸው እንደነበር የንታ ባፋቸው ነግረውኛል። እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ታናናሾቻቸው እና መምህሮቻቸው ቢሆኑ ነው ያሉበት ሄደው መጠየቃቸው።››

ምንድነው የሚያወራው? በእውነቱ ላይ እየተዘባበተ ነው ወይስ?...

‹‹አለቃ ምላት ከአባቴ ላይ አራት ጠገራ ብር የተበደሩበት ውል በራሳቸው ብዕር የተፃፈ አይቻለሁ። ይሄ እንግዲህ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመን ነው። የተማማሉትም ‹አባታጠቅ ይሙት› ብለው ነው።››

‹‹ይሄንን ማስረጃ በአይንህ አይተሃል?››

‹‹በደንብ፣ አባቴ አሳይተውኛል። ከሆነልኝ አንድ ቀን ከኮሮጆአቸው አውጥቼ አሳይሃለሁ።››

እኔ ሞት ብነፈግና ዕድሜዬን አሳጥሬ የማየት ዕድል ባጣ ህይወትን ምን አደርግበታለሁ? በደዌ እሥር ተይዞ መማቀቅ አይሆንብኝምን? ባልንጀሮችህ ብቻ ሳይሆን ያገባሃቸው ሴቶች የተወለዱልህ ልጆችና እነሱ የወለዷቸው ሁሉ በሞት ሲያልፉ ተገትሮ መቅረት ዋነኛው መርገምት አይሆንምን?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ አምስት

## የእውነት ነገር

አለሌው ጩኸቱ በተደጋጋሚ ተሰማ። ሰማሁ የሚለው ከቀን ወደቀን እየጨመረ ሄደ። በደረት ሌሊት ደረት ሀዘን ያዘለው ጩኸት ሲሰማ የተለያዩ የጡረታ ድልድይ ነዋሪዎች በተለያየ ጊዜ ለአርዳታ ቢወጡም ሴቲቱ ሳትገኝ መቅረቷ ተዘውትሮ ተወራ። እኔ በንባብ፣ ወይም በጥናት፣ ካልሆነም በምርቃና ንውዘት ውስጥ ሆኜ አብዛኛውን ሌሊት የማሳልፈው ቢያንስ በግማሽ ንቃት ነው። ይሁንና ወጥቶ አደር ድምፄ የሴት ቅላፄ ለብሶ ልሰማው አልቻልኩም።

‹‹ቆሌ ናት›› አለች እናቴ ‹‹በዚያ በሸንሌው ፍንዳታ አንድ ልጇን አጥታ ሀዘን ሆዷ የገባ ቆሌ...››

‹‹ቆሌ ልጅ የታላትን?›› አለ አባቴ የጥይት ማደሪያ ቋጠሮውን እንደከረባት እያስተካከለ። ‹‹ጅኒ ትሆናለች እንጂ››

‹‹ቆሌ ናት››

‹‹ጅኒ ናት

‹‹ቆሌ ናት››

‹‹ጅኒ ናት ጣ!››

‹‹ጅኒዎትን እዚያው የተለከፉበት በረኻዎት ይፈልጉ፣ መንደር ጠባቂ ቆሌ ያሉ እንደሆነ የጡረታ ድልድይ ብቻ ወግ አይደለም...››

‹‹ዛሬ ሌሊት ቆሌዋ እሪሪሪሪሪ... ብላ ጮኸች›› የተባለ ዕለት እናቴ በማለዳ ቆሎ፣ ገንፎ፣ አነባበሮ፣ ድልህ፣ የተቀባ ቂጣ፣ ከተገኘ እምቡሸቡሽ ጠላ አድርጋ በቡና ሥነ-ስርዓት ቆሌዋን እዝን ትጠራለች። ስንደሉን ለኩሳ፣ እጣኑን ጊርጊራው ላይ በተን እያደረገች...

‹‹እኛስ ችለነው እንጂ የልጅን ነገር እናውቀው የለም ወይ፣ አንዴ ከሆነ በላይ ቻል ማድረግ ነው እናቴዋ፣ በደረቅ ሌሊት ቢጮሁት ምን ይፈይዳል? አትባክኚ! እናቴዋ፣ ተረጋጊ፣ ተረጋጊ ባንቺ መጀን...››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አባቴ ሳሪያን ኮቱን ጎተት ጎተት እያደረገ ከቤት ወጣ:: ጥይት ሰቃ የወጣችውን የቁስል ቋጠሮ እንደከረባት አስተካክሎ ወግ ጀመረ::

‹‹ቆሌ ያልሽ እንደሆን ቢከፋት ትርቃለች እንጂ በየስርጓጉጡ አትልጦለጦስም፤ አድባር ያልሽ እንደሆነ የነዋሪው ልብ እስኪመለስ ትታገሳለች እንጂ ድንገት ተነስታ ከፋኝ ብላ አትሰደድም:: ጉዱ ጅኒ የሆነች እንደሆነ ነው:: ሙሉ ቀዬ አሳስተኛ የማለት አመል ያለባት እንደውም ጅኒ ናት::››

እናቴ ብዙ ንዴቶች እንደማሽላ ቆሉ እየተፈነጣጠሩ በአይኗ፣ በአፏ፣ በእጇ... በኩል ይወጣሉ::

‹‹ያልተሰማመነውን ክፉ መንፈስ እየጠሩ እዚህ ቤት ላይ መአት እንዳያመጡ ብቻ!››

የጡረታ ድልድይ እናቶች የእናቴን ጭስ ምልክት አድርገው ያለ ጠሪ ይሰባሰባሉ:: ሁሉም በሽጎሌው ፍንዳታ ልጆቻቸውን የተነጠቁ ናቸው::

የሀጋ እናት - አንድ ልጅ

አትዬ አሰፋሽ - ሁለት ልጅ

የእናኑ እናት - አንድ ልጅ

የውዴ እናት - አንድ ልጅ

እማማ እጅጊቱ - አንድ ልጅ

እማማ ጊፍቲ - አንድ ልጅ

አትዬ ገነት - ሁለት ልጅ

እማማ ፀደቀች - አንድ ልጅ...

ዓይኔ ፊት ለፊት አይገጥማቸውም:: ይሸሻቸዋል:: የተራቆተ ወና ፊታቸው ለሀሊናዬ ወቀሳ ያቀርባል:: የተጠራቀመ ጩኸታቸው የብዙ ቆሌ ጩኸት ሆኖ ደረቅ ሌሊቱን ይንጣል:: እኔም ለእነሱ የደረቅ ሌሊት ጩኸት ሳልሆንባቸው አልቀረሁም:: ሲያዩኝ እኩያ የነበሩ ልጆቻቸውን የማስታወስ ሀመም ሆኜባቸዋል:: ከመጥፎው ይልቅ ጥሩ ነገር ሲገጥመኝ የበለጠ ሀዘን እንደሻሁላ የሚበላቸው ይመስለኛል:: አስራ ሁለተኛን በጥሩ ውጤት ያለፍኩ ዕለት (የዛሬ ሦስት አመት መሆኑ ነው) እናቴ ለቆሌዋ መሰማመኛ አይነት ቀለል ያለ ድግስ አዘጋጅታ መንደርተኛውን ጠራች:: የመጀመሪያው የእናቶች አይን ተኩስ ያኔ መጀመሩ ትዝ ይለኛል:: የብዙ እናቶች ዓይን ባሩድ አቀጣጥሎ፣



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አረር ሆኖ ተተከሶ አቆሰለኝ። እንደውም አንዳንዶች እንዲህ በማለት በዕጣ-ፈንታዬ መከፋታቸውን ገለጹ።

«ያ - የእኔ ከንቱ ቢኖር ኖሮ ይሄኔ ኮሌጁን በጥሶ ከታላ ጋር...»

«የኔስ?...»

«የኔስ?...»

«የኔስ?...»

ኢየሱስንም ለቅሶና ብዙ ዋይታ ያሰሙ፣ መፅናናትም ያልወደዱ እናቶች እንዲህ ያካሰቡት ይመስለኛል። የኢየሱስን ነፍስ የፈለገው ሄሮድስ በቤተልሔምና በአውራጃዋ ያሉትን ህፃናት ባያስገድል ያቺ እናት ልጇቿን ታጣ ነበርን? ስለዚህ ልጆቿን ያጣችው ያቺ እናት በየምኩራቡ እየተገኘች በአይኖቿ ኢየሱስን አትከሰውም ነበር ትላላችሁ? ስለሌሎት ልጆቿስ ማንነፀሪያ የምታደርገው ኢየሱስን አይሆንም ነበርን? ምናልባት የኢየሱስ የልጅነት ታሪክ ወንጌል ውስጥ የታጣው እነዚያን እናቶች በመሸሽ ወደ አደባባይ ባለመውጣቱ እንደሆነስ?...

እኔም ሸሸሁ። ወደቤቴ ገባሁ። ስለጡረታ ድልድይ እናቶች ወቀሳ ስል ወደ አደባባይ ባልወጣና ታሪኩ ሳይመዘገብ ቢቀር እመርጣለሁ።

አባቴ የጥይት ጎሬውን እየነካካ መሆን አለበት ለተበዳይ እናቶች ማብራሪያ መስጠት ጀመረ።

«እንግዲህ እኔ ጅኒ ናት ማለቴ ምክንያቶችን ይዤ ነው። ቆሌ ከሆነች ይሄን ሁሉ ዓመት የት ቆይታ አሁን መጮህ ጀመረች? እናቶች ይቺ ነገር ጅኒ ናት። ጅኒዋ መጀመሪያ ጥይት ፋብሪካው ላይ ላውንቸር የተከሰችውን የሻዕቢያ ሴት አይታታለች። ስለዚህ እሷን ለመበቀል ኤርትራ ድረስ ተከትላት ሄዳለች። እንግዲህ ሲመስለኝ የጠላቷን ህይወት መቅኖቢስ አድርጋ በቀሏን ካጠናቀቀች በኋላ እርሟን ለማውጣት ወደዚህ መጥታ ነው።»

የአባቴ ጣ| ፋሽን ነበር ማለት ነው? አሁን ፋሽኑ ስላለፈ መተው ይሆን?...

«ጉድ አቴ!» አለች እናቴ በሴቶቹ ፊት አባቴን ማንጓጠጥ ከብዷት እየተቁነጠነጠች ይሆናል። በሩን ገርበብ አድርጌ ለመመልከት ሞከርኩ። ሴቶቹ አዝን ደራሽ መስለው አቀርቅረዋል። ጢሱ መሐከል ላይ እንደተተከለ የእርግማን ጦር ቀጥ ብሎ ወደላይ ይምዘገዛጋል። ተመልሼ ፍራሹ ላይ ተዘረፈጥኩ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ጅኒ በተለይ ሴቷ ተበቃይ ናት፡፡ አንድ ጊዜ ልጅ ሳለን እንጨት ልቀመ ተብለን ወደ አረህ ወርደን ሳለ እስጢፋኖስ የተባለ ባልንጀራችን እኛ ሁሉ ገና ምንም ያህል ሳንሰበስብ ክምር የሚያህል ጭራሮ እንደታሰረ ተሸክሞ መጣ፡፡››

ሴቶቹ ከቀልባቸው ስላልሆኑ በሀዘኔታ ከንፈራቸውን ይመጣሉ፡፡

‹‹ቀድሞን እንጨቱን ለቤቶቹ ሰጥቶ ይመለሳል፡፡ ማታ የእነሱ ቤት በድንጋይ ይነረት ጀመር፡፡ አባቱ አቦይ ገብረማሪያም ቢያደፍጡ፣ ቢወጡ፣ ቢገቡ ድንጋዩ አልቋረጥ አለ፡፡ ታዲያ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ‹‹ኧረ ምንድነው ጉዱ!›› አሉ፡፡

‹‹ይሄን ጊዜ መልስ ተሰጣቸው፡፡ ‹‹ማገዶዬን ስለቅም የዋልኩትን ካልመለሳችሁ አትተኟትም›› አለቻ፡፡ አቦይ ገብረማሪያም ጅኒ መሆኗን አውቀዋል፡፡ ወደቤት ገብተው…

‹‹ዛሬ አረህ የወረደ ልጅ አለወይ?›› አሉ፡፡

‹‹ልጆቹ ሄደዋል፡፡›› እናት መለሱ፡፡

‹‹እናንተ እንጨቱን ከየት ሰበራችሁት?›› ሲሉ

‹‹የተሰበረ አገኘን እንጂ እኛስ አልሰበርንም፡፡››

‹‹'በሉ አምጡ' ብለው እንደታሰረ ከግቢ ውጭ አስቀመጡላት፡፡ ከዚያ በኋላ ድንጋዩ ጋብ አለ፡፡ ለተሰበረ እንጨት እንዲያ የሆነች ልጅ ሞቷትማ… አይደለም እንዴ፣ አባይ ቄስ?›› አለ፡፡

ደነገጥኩ፡፡ የረድ ሠርዌን አባት መስሎኝ ሰስት መቶ አመት የተብላላ እንደቁስል መዳኒቱ እራሳቸው ያደራጁት ድፍድፍ እርግማን አፍሰውበት ባለበት የጢያን ድንጋይ መስሎ ሲተክል ታየኝ፡፡ ተፈናጥሬ ተነስቼ በሩን ገርበብ አድርጌ ብመለከት ረድ ሠርዌ ኖሯል፡፡

‹‹እርስዎ ሰውዬ'ኮ›› አለች እናቴ ‹‹ቁጭ ይበሉ መሪጌታ፣ ወዲያውም ይባርኩልናል››

ያንን ነፋስ ወሰድ መለስ የሚያደርገው ፀሎቱን ጀመረ፡፡ ረድ ሠርዌ ለባዕድ አምልኮው ባዕድ ቄስ መሆኑ አሳቀኝ፡፡ ለአባይ እምነት አባይ ቄስ፣ ታዲያ አባቴ ምን አጠፋ?…

ረድ ሠርዌ ከባዕድ ቡራኬው በሰሐን ይዞ በትከሻው በሩን ገፋ አድርጎ ገባ፡፡

‹‹ሠላም ለጊርጊሴኖን››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ገዛም፣ ለጣፆት የተሰዋ ሳለመብላት እኔ ቤት ሲያስተምጠው መሰለኝ።

‹‹ሠላም ለአላዛር ዘአርምሞ›› በቂመ ከንፍሮው ቃም አደረገ። ሲያኝክ እልፎ-እልፎ የተቆላ ጥሬ ይሰማል።

‹‹እንዲህ ያለ ምግብ የቆሎ ተማሪ ቤትን አኩፋዳ ያስታውሰኛል። ጥሬ ከብስል ጥቁር ከነጭ የተደባለቀበት።››

‹‹ረድ፣ ለጅኒ የቀረበ መስዋዕት ይቋደሳሉ?››

‹‹ተማሪ ሳለን እንዲህ ያለውን ምግብ አኩፋዳ ባርኮታል ብለን እንበላ ነበር። ለባዕድ አምልኮ የታረደውን ዳግም ስትባርከው እንደ አዲስ ደም ይወጣዋል።›› እንባበሮውን አንስቶ ገመጠው።

የተገኘውን ለመብላት የሚያስችለውን ትውፊት ደህና አድርጎ ሰብስቧል። አልጋ ላይ ተቀምጦ በተንኮል እያየኝ ወገቡን ቀጠለ።

‹‹የኢቲሳው አቡነ ተክለሃይማኖት ብዙ መንፈሳዊ ተጋድሎ ያላቸው አባት ናቸው። ታዲያ አንድ ቀን ቅጠል ወዳለበት ሄደው እየበጠሱ ሲበሉ አንድ መጥፎ ፍጡር (ስሟ ለጨዋ አይገለጥም) ከቅጠሉ ጋር እጃቸው ገባች። ከቅጠሉ ጋር እንደተገኘች ከቅጠሉ ጋር በሏትና ‹ማን በዚህ ሰዓት ተገኚ አለሽ?› አሉ አሉ። እኔም ይኼን የባር ገክር ማን በዚህ ሰዓት ተገኝ አለህ ብዬ በላሁ።››

እንደጲላጦስ ‹እውነት ምንድር ናት?› ስል ጠየኩ። ጲላጦስም ሆነ እኔ፤ እኔም ሆንኩ የሚመጣው ጠያቂ ከገዛምታ በስተቀር ምላሽ አናገኝም። እውነት የውሸት ተቃራኒ ሳትሆን የልምድ ነፀብራቅ ናት። የአቡኑን ገድል ያነበበ ሁሉ ውሳኔው ‹‹በምግብ ሰዓት የተገኘ ሁሉ ምግብ ነው›› የሚል ድምዳሜና እውነት ላይ ይደርሳል። እዚህ ላይ እውነት የውሸት ተቃራኒ ሆኖ ሳይሆን ምክንያት ተደርጋ ቀርባለች። ለዚህ ይመስላል ፓስካል 'Custom is a Second nature that destroys the first' ያለው።

‹‹የንታ ወሎ ሀይቅ ደብር አስተዳዳሪ ሳሉ›› አለ ቆሎ የበዛበት ንፍሮ ቅሞ ሲያኝክ የሚቆጠረው ድምፅ በዝቶበት ‹‹ካሳሁን የተሰኘ ባልንጀራ ይገፎ ነበር። ለካ የአባቱ ስም አብዱለጢፍ ነው። ይሄን ያወኩት ኋላ እነሱ ቤት ከበላሁ በኋላ ነው። ለየንታ ይሄንን ሄጄ ነገርኩ።

‹‹እ? እስላም የባረከው ስጋ በላህ? ነይ ዐፀደማርያም ጉድሽን ስሚ፤ በልተህ ምንም አላለህ? ቆመህ መ!!ህ? ምን ጉድ ነህ? ሰማሽ ዐፀደማርያም ምን ጉድ

እንደወሰድን፤› አሉ። ይመቱኛል ብዬ ስጠብቅ ‹አንተማ ጉድ ነህ ዝም ብለህ ብላ› አሉኝ።››

ዋናውን ጉዳይ ትቼ ‹‹ዐሀደማርያም ማን ናቸው?›› ስል ጠየኩት።

‹‹እናቴስ? እናቴ ናቸዋ››

ከእኔ እናት የክርስትና ስም ጋር ገጥሞብኝ እንደተእምር አድርጌ አየሁት። በኋላ ግን ዘወትራዊ መገጣጠም ነው ስል ደመደምኩ።

‹‹ይሄንን መከፋፈል የፈጠረብን...››

‹‹የቱን መከፋፈል?›› ስል አቋረጥኩት።

‹‹የክርስቲያንና የእስላም ስጋ የሚለውን ያመጣብን አቡልፈትህ የተባለ የመናዊ ነው። ዕጨጌ ዕንባቆም ተብሎ የደብረሊባኖስ የበላይ አባት ሲሆን እንደ ትልቅ ነገር ህዝበ ክርስቲያን በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተብሎ ያልተባረከ አይብላ ሲል ግዝት አሰራጨ። እስከ አሁንም ግዝቱ ይዞን ከሥጋ፣ ሥጋ እናማርጣለን።...››

የጠበበውን ሁሉን የመብላት ፈቃድ የማንስራፋት ዕኑ ፍላጎት ያደረበት መስሎ ታየኝ። ከኢቲሳው አቡነ ተክለሃይማኖትም በላይ ‹ከምግብ ሰዓት ውጭም የተገኘ ሁሉ ምግብ ነው› የሚል ብሂል የህይወት መመሪያ ማድረግ ሳይፈልግ አልቀረም።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ ስድስት

## የወንድ ልብ ነገር

...ሶስት ክሬዲት ሀወር ያለውን The History of Philosopy ተምሬ ከክፍል ስወጣ ጨርሶ መደንዘዝ ውስጥ ነበርኩ...

...ከባህል ማዕከል ፊት ለፊት ወዳለው ካፌ አመራሁ::

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እዚህ ግቢ ስመጣ የሚሰማኝ የመጨረሻ ኋላቀርነት ነው:: ዕውቀትን የሚፈልጉ ልጆች አንድ ክፍል ውስጥ አጉሮ አስተማማኝ ትውስታ በሌለበት መንገድ በመስማትና በመፃፍ አዋቂ ለማድረግ መጣር ትልቅ ኋላቀርነት ሳይሆን አይቀርም:: በዚህ ላይ ነገ-ተነገወዲያ ይቋረጣል የማይባል ትውልድ አለ፤ አንዱ ሰምቶ ሲሄድ ያልሰማው የሚመጣበት የሰዎች ጎርፍ:: አንደኛ ደረጃ፣ ሁለተኛ ደረጃ፣ ኮሌጅ፣ ዩኒቨርሲቲ... ብዙ የሰው ኃይልና ንብረት የሚባክንበት ዙሪያ ጥምጥም የዕውቀት መዳረሻ...

...ከዚህ ሁሉ መታከት ይልቅ አንዴ እንደ አብሾ የሚጠጣ፣ ወይም ከደም ጋር የሚቀላቀል ካልሆነም በቀዶ ጥገና የሚገጠም ዕውቀት የማግኘት ምርምር ቢካሄድ ሳይሻል አይቀርም...

...ለመሆኑ የግሪክ አማልክት ለምሳሌ አቴና ጥበብን ለፈቀደችው ሰው ትሰጥ የነበረው እንዴት ነው? አለማወቅን እንደጨለማ ቆጥራ እውቀትን እንዴ «ተግ» የሚል ብርሃን ታደርገው ይሆን? ሳይንስ እኮ ከፍልስፍና ይልቅ ለአፈ ታሪክ የሚቀርብ ነገር ነው:: እውቀትን የሚማሩት ከማድረግ ይልቅ የሚሰጥ ቢሆን ያ-ሁሉ ልፋትና ብክነት አይቀርም?...

...የሆሜር «ኢሊያድ» መጽሐፍ ውስጥ ዘወትር የሚያጓጓኝ አንድ ሰው አለ:: የቴስተር ልጅ የሆነው ካልቼስ ነው:: ያለፈውን፣ ያለውንና የሚመጣውን እንዲያውቅ የተደረገው በአምላኩ በአፖሎ ነው:: ግልግል:: ሬጅስትራር የለ፣ ሌክቸረር የለ፣ አንድ ክፍል ውስጥ መታጎር የለ፣ አንደኛ ዓመት፣ ሁለተኛ ዓመት... ምናምን የለ፤ አፖሎ-ጋ ወይም አቴና ጋ ቀርቦ በጥበብ እንደዕዋ መሞላት::

«አንድ ኮርስ አልወሰድክም::»

«ስንት ክሬዲት ሀወር ነው?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ቁርሱ መቼ ይሰጣል?»

የፍልስፍና ትምህርትን የመረጥኩት በመፈለግ ነበር። ግን ሳይፈልጉ ከሚመደቡ ጋር መማር ግድ ሆነ። ሳይፈልጉ የሚያስተምሩ መምህራንም አሉበት። ማስታወስ አጠራጣሪ በሆነበት የሰው ልጅ አፈጣጠር ውስጥ አፖሉ ወይም አቴና የሞላችው ዕዋ መስሎ የሚመጣ መምህር ተሰማምጦ መማር ትልቁ የተማሪዎች ዕዳ ነው። ከዚህ ሁሉ ጣጣ ጣዖት አምላኪ ሆኖ ሁሉን ዕውቀት በሰስት ከፍሎ መቀበል። ትናንት፣ ዛሬና ነገ...

...ካፌው ከአካባቢው የተነጠለ ጠባይ አለው። በዕድ ተቸምችም ሰብቸኝነት ቅድሚያ ይሰጣል። በሲሚንቶ ከከበቡት ፕላስቲክ ወንበሮች አንዱን ስቤ ተቀመጥኩ። ሌላኛው ላይ ቦርሳዬን አኑሬ የጀመርኩትን ሀሳብ ቀጠልኩ።

ጀርመናዊው ኤሪክ ቮን-ዳኒከን የአማልክቶቹን የአቴናንና የአፖሎን «ጥበብ የመስጠት» ፀጋ በሳይንስ መተግበር ይቻላል ብሎ ያስባል። ድርጊቱ ቀድሞም መለኮታዊ ተአምር አልነበረም የሚል እቋም አለው። ጥበብን መሞላት ሳይንስ ነበር፣ ወደፊትም በሳይንስ ይደረስበታል ብሎ ዕፏል። እንደማስረጃ ያቀረበው የአንድ ምርምር ውጤት እኔን አሳምኖኛል። እንዴት አይጥ የምግብ ድርጎ ተሰጥቷት የተወሰኑ ድርጊቶችን እንድትለምድ ይደረጋል። አይጧ ተገድላ ጭንቅላቷ ውስጥ ያለውን ፈሳሽ በስሪንጅ በመምጠጥ ሌላ ምንም የማታውቅ አይጥ አንጎል ውስጥ ይከቱታል። አይጧ ያለምንም ስልጠና የቀድሞዋ አይጥ የምታከናውነውን ልማድ ቀጠለችበት። ዳኒከን ይሄንን እውቀትን በፈሳሽ መልክ ካንዱ ወደሌላው ማስተላለፍ ቀድሞ አቴናና አፖሎ ያደርጉት ነበር ብሎ ያምናል።

ሻይ አዝዤ ምሳ ሰዓት እስኪደርስ ጠናጋሻውን መጠበቅ ጀመርኩ። ይሄንን ሻይ ቤት ይወደዋል። ከቤተ መፃህፍት የሚዋሰውን መጽሐፍ እዚህ እንብቦ ቢሮው ውስጥ በማስቀመጥ ባዶ እጁን ወደቤቱ ይሄዳል። ሰውን እንኳን ሌላው ፍጡር እራሱ ፈጣሪውም ተቆጣጥሮ የሚፈልግበት ቦታ አላደረሰውም። ስምረት የጥንቱን አምላክ መስላ ታየችኝ። ኤደን ውስጥ የዕውቀት ፍሬ እንዳይበላ የሚከለከለውን ተፀፃች ፈጣሪ። ሁሉ እንዳይታወቅ የሚሰጋውን...

«ስምረት ጠና ጋሻውን በማግባቷ ተፀፀተች»

...የዕውቀት ፍሬ፤ ዛሬ ብትኖር ሐዋን እስከትሰጠኝ ሳልጠብቅ አንዴ በልቼ የምገላገለው እኔ ነበርኩ። ወይም እንደጀርመናዊው ገፀባህሪ እንደፋውስት ከመንገድ ውሻ መስሎ ሳጥናኤል ቢከተለኝ፣ ወደቤቱም ቢገባ፣ መደራደሪያውን በደም ፊርማ ዕውቀትን ከመቀበል ወደኋላ የምል አይመስለኝም።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እንዲህ እንድትመኝ ያደረገህ ስንፍና ነው::» አጠገቤ የተቀመጠ ሰው እንጂ ከእኔ የተከፈለ ሀሳብ አልመስልህ አለኝ::

«አይደለም::»

«ነው::»

«አይደለም፤ የሰው ልጅ ዕድሜ አጭር ነው:: በዚህ ላይ አፈጣጠሩ ፍፅምና ይጎድለዋል:: እንዴ የተነገረውን ደጋግሞ በማጥናት አጭር ዕድሜውን ያባክናል:: የሰው ልጅ ዕውቀትን ለማግኘት ሌላ አጭር መንገድና አስተማማኝ ዘዴ ያስፈልገዋል::»

ጠያቂዬ የት ገባ?

«ሠላም፣ ለጌቲሴማኒ መንፈስ ለምታሳርፈው የዐፀድ ስፍራ፤ ሠላም ለአሳባር ዘእርምጥ» ያልጠበኩት ቦታ ሳገኘው ያልጠበኩት ድንጋጤ መታኝ:: አለባበሱ ተቀይሮ ዘመናዊ ለመምሰል እንደጣረ ያስታውቃል:: ቢሆንም አጠቃላይ መንፈሱ የቤተክህነት ሰው እንደሆነ ከመለፈፍ አልታቀበም:: ምኑ? እንጃ!

«የት መጥተህ ነው?» የቀዘቀዘ ሻዬን ፉት አልኩ

"History of Theology አስመስከር ብሎኝ መጽሐፍ ተዛማጅ መረጃዎችን ፍለጋ ጦማር ይዤ መጣሁ:: ለመሆኑስ ምን ነበር እንዲያ ያስቀዘዘህ? እይንህ ወዳለበት እጄን በወዘውዝ ጨርሶ ልታየኝ አልቻልክም::»

«እኔ ዘእርምጥ' አይደለሁ?»

«እርግጥ ነው፤ እርምጥ'ኮ የአባቶች መዋኒያ ጦር ዕቃ ነው:: አንተ ማንን ወጋህ?» ተቀመጥ ሳልለው ከላባዋን የፕላስቲክ ወንበር ስቦ ተቀመጠ::

«እራሴን መሰለኝ»

«እራስን ለመውጋት እርምጥ መያዝ የትኛውም ቅዱስ አባት ዘንድ አልታየም:: እራስህን እንዴት ተዋጋኸው?»

«የሰው ልጅ ዕድሜ አጭር፣ ዕውቀት መሰብሰቢያ ጊዜው ረጅም የሆነበትን ምክንያት አምጣ አልኩት:: ስለምንስ የሰው ልጅ አፈጣጠር ከማወቅ ሳለማወቅ የተመቸ ሆነ?...» ረድ ሠርዌ ሳይሆን አባቶቻችን በዚህ ጉዳይ ላይ ያሉትን የማወቅ ፍላጎት አደረብኝ::

«ሰው የለም» አለኝ አለወትሮው ንግግሩን አሳጥሮ፤



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እንዴት?»

«እግዜሩ ገና ሰው መፍጠር አልጀመረም። እዚህ ግቢ ያሉትን ሁሉ ተመልከት፣. እኛ ግቢ ያሉትን እኔ አይቼልሃለሁ። እግዜሩ ሰው መፍጠር አልጀመረም። ግና ሞክሯል። በእኔና በአንተ ሞክሯል። በዓለማዊው ያልከ እንደሆነ አንተ፣ በመንፈሳዊው ደግሞ እኔን ለመፍጠር ሞክሯል። ሊቁ ክፍለ ዮሐንስ ምን ብሏል መሰለህ?

«እ? ምን አለ?»

«አ እግዚኦ ፍጠር ሰብአ፣

እስመ አድግ ወበቅል በቤትከ መልአ»

«ምን ማለቱ ነው?»

«ልንገርህ አይደል፣ አቤቱ ሆይ እባክህን ሰው ፍጠር፣ ቤትህን የሞላው አህያና በቅሎ ሆነ።»

«አትጠራጠር፣ እኔና አንተም አህያና በቅሎ ነን» አልኩት። ቅኔው አርክቶኝ ለምን እናደደኝ?

«እንዲህ ያሰኝህ እራስህን ለመዋጋት የያዝከው አርምሞ ውጤት ነው። ሻይ መግገር ትሰጠኛለህ? ወይስ ልሂድ?» ሲያስቀምጥ ያላየሁትን ቦርሳ አነሳ። መጀመሪያ የእኔን ቦርሳ ያነገተ መስሎኝ ነበር።

«ከመጠየቅ በድግምት መንጠቅ አይሻልም?» በነገር ልወጋጋው ሞከርኩ።

«በበረከት ለማብዛት ጥቂት ማግኘት ግድ ይለናል። ኢየሱስኮ ከሚዳ ተነስቶ የሰባት ገበያ ሰው አላበላም። መጀመሪያ ሰባት ዓሳዎችን መነሻ አድርጎ ነው።»

ሁለት ቦታ ተከፋፍለው ከተቋጠሩት ብሮች አንዱ ጥቅልል ፈትቼ ሰጠሁት። ሌላኛው ጥቅልል የጠናጋሻው ነው።

«ዛሬ የተሸለምከው አንተ ሳትሆን ባለቅኔው ክፍለ ዮሐንስ ነው።» አልኩት።

«አደርሳለሁ፣ በነፋስ ሠረገላ፣ በደመና ከለላ...»

አካሄዱን ሆን ብዬ አየሁት። እንደ አለባበሱ ለማለዘብ ቢሞክርም መንፈሱ ግን የተከሴ አቋቋም እንዳለበት ያስታውቃል።

ጠናጋሻውን እዚህ የመጠበቅ መንፈሴ ከሻዩ ጋር አብሮ ስለተዘዘ ቢሮው ለመሄድ ተነሳሁ። የማየው ተማሪና አስተማሪ ሁሉ «አድግ ወ በቅል»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

መሰሉኝ። እዚያ ወዲያ The Philosophy of History መምህር ቋጭ ብሎ እንቁላል ሳንድዊች ይበላል

‹‹አድግ›› አልኩት፣ ተማሪ ሲጠይቀው የመምህርነት ሉአላዊነቱ የተደፈረ የሚያስመስል። ከሱ ወዲህ የተማሪዎች ተወካዩ ተቀምጧል።

‹‹በቅል›› ከዕውቀት ይልቅ አገልግሎት የሚበልጥበት!! ወጣሁ። ብዙ አድግ ወ በቅል ወደ ባህል ማዕከሉ ለመግባት ተሰባስበዋል። የአገር ኗስ ሜዳው ደረጃ ላይ የተኮለኮሉ ታሪክ፣ ሥነ-ልቦና፣ ቋንቋ፣ ህግ፣ ፍልስፍና፣ የውጭ ቋንቋ... የሚማሩ አድግ ወ በቅል...

እኔስ?...

...እራሴን ከታዘብኩ በኋላ ዝንጉርክ ሩቦ ትዝ አለኝ እኔ የገጠመኝ ገጥሞት ሳይሆን አይቀርም ስለራሱ እንዲህ ብሎ ነበር፦

"I am different from all the man I have seen, if I am not better at least I am different" ከሌላው ሰው መብለጥ ቢያጠራጥር እንኳን ልዩ መሆንን ማወጅ ያስፈልጋል።

"At least I am different."

የጠና*ጋሻውን ቢሮ ላንኳኳ ስሞክር ከውስጥ ተከፍቶ ነፀብራቅ ወጣች። ምን አስደነገጠኝ?

‹‹አሉ?›› አልኳት።

‹‹አሉ›› ብላ ተመናጨረችብኝ ‹‹አሳይመንት ስላልሰራህ ልትጠይቀው እንዳይሆን? ልደትዬን አፍህን አታጥፋ የሆን...››

ጠናጋሻው እንዲሰማላት የፈለገችው ስድብ እንዳለ ገባኝና ከበሩ እርቄ ከጃሮው ለማራቅ ሞከርኩ። ከንዷ ላይ ያዝ ሳደርጋት አስለቀቀችኝ። ሆን ብዬ ለመያዝ በመሞከሬ ማፈር ሲገባኝ እንደውም ደስ አለኝ። ምክንያቱም 'I am different'

‹‹እና? ገብቼ ልለምነው ነበር? ይቅርብኝ?››

‹‹ልደትዬን ስልህ? አፍህን አታጥፋ›› ስትናገር ከንፈሯ ይደንሳል፣ አይኗ ይደንሳል

‹‹ወይ ጉዴ›› አልኩ። ለአይኗ ነው ለአፏ?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹በእኔ እልህ አሳይመንቱ የሚያዝበትን ማርክ ከፍ ሳያደርገው አይቀርም›› ደናሽ አፍ፤ ደናሽ አይን። ወሬ እንዴት ቢወዱ ነው?

‹‹ወይ ጉዴ›› አልኩ።

‹‹አይዞህ ምን ያመጣል? ዋናውን ፈተና አጥንቶ ጥንቅቅ አድርጎ መስራት ‹‹ሲ›› አናጣ።››

‹‹አይመስለኝም፤ አይመስለኝም።››

‹‹ለምን?››

‹‹ውጤቱ አሽቆልቁሏል...››

‹‹ወይኔ ልደትዬ...›› ክንዴን ያዝ አድርጋ ልታፅናናኝ እየሞከረች ነው። እንደ እሷ ማስለቀቅ ብፈልግም አልቻልኩም።

‹‹አቋርጬ ምን እሆናለሁ?›› መተላለፊያ ኮሪደሩ ላይ ቆጭ አልኩ።

‹‹እንዴ? በልደትዬ፤ ለማን ብለህ ታቋርጣለህ። ድሮም ጓደኞቼ ሲመክሩኝ ነው እምቢ ብዬ የመጣሁት እሱ ቆንጆ አይወድም ይቅርብሽ ብለውኝ ነበር››

ትልቅ ቀልድ ሆነልኝ። ቀና ብዬ አየኋት ደማቅ ቀይ ናት። መልክ አልፈጀችም እንጂ መልከኛ አይደለችም።

‹‹ልደትዬን፤ አንድ አስቀያሚ አለች እሷን እንልክበታለን። ይሄ ጤኔ፤ እውነትም ጠኔ። ተማሪዎች ጋሽ ጠኔ ሲሉት እንኳን የማያውቅ፤ ወታደር ነበር አሉ፤ ችክ፣ ችክክ ካለ የማይመለስ...›› አፏና አይኗ ተጣጥመው በወሬ አጃቢነት ጀረኩ።

ጠናጋሽው ተማሪ ‹‹ጠኔ›› ሲለው የማይከፋው ረቂቅን ስለሚያስታውሰው ይሆናል።

‹‹አይዞህ፤ ልደትዬን አይዞህ! ልጅቷን እንልካትና...››

ከተዘረፈጥኩበት ለመነሳት እጄን ዘረጋሁላት። ጎተተችኝ። ያቀረቀርኩበት ድረስ ጎንበስ ብላ እያየችኝ ከምንም ነገር የሚልቀውን ሀዘኔታዋን መገበችኝ።

‹‹ልደትዬን አይዞህ!››

እውነት በሆነ ስል ተመኘሁ። ጉዳዩን ከነፀብራቅ ጋር ሆኜ ለመከታተል።

‹‹እኔ ሒስትሪ ዲፓርትመንት ነኝ፤ አንተ የት ነህ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ፈሱ››

‹‹ስምህ ማነው?››

‹‹አልአዛር››

‹‹በቃ፣ አይዞህ፣ ልደትዬን አይዞህ››

በዚህ ሁኔታ ሳትለየኝ ጥቂት ብንጫወት ጥሩ ነበር። ከእኔ ከተለየች ውሸት መሆኑን ስለምታውቅ ጨዋታው ያበቃል። አዲስ ሴት፣ እኔ ላይ ፍላጎት ሳይኖራት እያናገርኳት ድብብቆሽ መሰል ጨዋታ ሲከናወን ደስታ ይሰጠኛል። ዛሬ ከንዷ ስለተያዘ የምትሆኖፍ ሴት ከተወሰነ ንግግርና መግባትን በኋላ አትፋሉ ለመተኛት የምትፈልገው?

‹‹ውሀ ወደምጠጣበት ውሰጂኝ›› አልኩ እንደዞረበት ሆኜ። ከንዷን ሰይዘው ፈቀደች። አላማው ድጋፍ መፈለግ ነዋ። ሳላሳገባት አልተረሀም!

‹‹እናቴ ጉልት ሸጣ ነው ያሳደገችኝ። ካሁን በኋላ አንድ ዓመት ቀርቶ አንድ ወር አልጨምርባትም። የሆነ ሥራ መፈለግ...›› ሴላ ሀዘን

‹‹የት? ምን? ወይኔ ጉዴ፤ ልደትዬ...›› ምን እንደምትለኝ ግራ ተጋብታ በሆዋታዋ እንደከበበችኝ እዚያ ገዳም መሰል ካፌ ደረስን በርሳዬን ካነገትኩበት አውርዳ አስቀመጠችልኝ። እኔ ውሃ በብርጭቆና ወተት አዘዝኩ። እሷ አልፈልግም ብላ ጠመመች። ከጉልት ነጋዴ ልጅ ሳለመጋበዝ ይሆናል። ይሄን የእናቴን ተግባር ረቂት ስትሰደብበት ከመስማቴ በፊት፣ አሳዛኝና ገመና እንደሆን አስቤ አላውቅም ነበር። ምናልባት ከእናቴ የተሻሉ ሴሎች እናቶችን በማነፃፀሪያነት ስላላገኘሁ ይሆናል።

‹‹አሁን መለስ አለልህ?››

ወተቱን እየቀመስኩ ያልተሻለኝ መሰልኩ። ከሄደች አትገኝም። ምላ ደርሷል አውቃለሁ! የተማሪዎች ካፌ ወረፋ ይበዛበታል-አውቃለሁ! ከትንሽ ጊዜ በኋላ ምሳ ሊያልቅ ይችላል-አውቃለሁ! ጓደኞቿ እሷን በመፈለግ ስለሚያረፍዱ የወጡ አስር ይደርሳቸዋል-አውቃለሁ! ግን መሄድ የለባትም።

‹‹እናቴ ከእኔ ውጭ ስድስት ሴት ልጆች አሏት። እኛን ለማሳደግ ዕድሜ ልኳን አልበላችም፣ አልተኛችም። አሁን እኔ ደርሼ...››

ሴቶች በምንም አይነት ሳያገኑበት የማያልፉት ታሪክ።

‹‹ልደትዬን አይዞህ››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አስተናጋጇን ጠርቼ እንቁላል በስጋ አዘዝኩ፡፡ ፊቷ ላይ ድንጋጤ ያነበብኩ መሰለኝ፡፡

‹‹እኔ ድንገት ከደርግ ስለወጣሁ ፍራንክ አልያዝኩም››

‹‹አልያዝሽም?›› አውቄ

‹‹እም፡፡

‹‹እኔ ይገባሰሁ፡፡››

በረጅሙ ተነፈሰች፡፡ ምግቡ ሲመጣ ወደ ፊቷ እየገፋሁ ‹‹ብይ›› አልኳት፡፡ ‹‹ላንቺ ነው ያዘዝኩት›› ነገሮች ተምታቱባት፡፡

‹‹አይዞሽ፣ የጉልት ሻጭ ልጅ ብሆንም ከውጭ እየረዱ የሚያስተምሩኝ ፈረንጆች አሉ፡፡ ኸረ እንደውም የሚልኩልኝ ለእናቴም ይተርፋል፡፡››

ደስ ሳይላት ሄዳ እጇን ታጠበች፡፡ መቆነጣጠር ጀመረች፡፡

‹‹እንብላ አይባልም››

‹‹ውይ በልደትዬ እንብላ››

የልደታ ልጆች ‹‹ልደትዬን›› የማለት ልምድ እንዳላቸው አውቃለሁ፡፡

‹‹አንድ የልደታ ልጅ ብጠይቅሽ ታውቂያለሽ?››

‹‹እኔ እንጃ ማን የምትባል?›› አፏ እየበላም ንግግሯን በከንፈሮቿ ማጀቡን አይዘነጋም፡፡ ዓይኖቿ… አፌ ላይ እንደመጣ

‹‹ሲፈን›› አልኳት

‹‹ኡይ፣ ሲፈን የምትባል? ልደትዬን አላውቅም፡፡››

‹‹እሷም ልደትዬን ትል ነበር፤ እሷም ቆንጆ ነኝ ብላ ታስብ ነበር፡፡ በእኔ ግምት ግን ቆንጆ አልነበረችም፡፡››

ሽሙጤ ገብቷት ደስ በሚል ቀለብላባ ዓይን አየችኝ፡፡ ‹‹ስሟ ግን ደስ ይላል፡፡ የምን ሥም ነው? ማለቴ ኢትዮጵያዊ ነች?››

‹‹ሲፈን በኦሮምኛ ላንቺ ብዬ ማለት እንደሆነ ነግራኛለች፡፡ ትንቢት ነው፡፡ ለእሷ ብዬ ያልሆንኩት የለም፡፡››

‹‹አሁን የለችም? ማለቴ ተለያይታችኋል?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እ›› ቅስሙ የተሰበረ ሰው እንዴት ነበር?

‹‹ልደትዬን እይዘህ››

‹‹ይሄ ትምህርት ከተሰናከለብኝ አንድ የምታደርጊልኝ ነገር አለ። ለእናቴ አንድ ደብዳቤ ታደርሽልኛለሽ።››

‹‹አንተስ? ማለቴ?...›› ምግብ መለካከፏን ተወች።

‹‹እኔ ድንበር አሳብሬ እሰደዳለሁ።›› ለምንድነው አዲስ ሴቶች ሲያገኙልህ ደስ የሚልህ? ሲያስቡልህ ልብህን የሚሞቀው?... ደስ አለኝ፣ ልቤን ሞቀው...

ሀዘኔታዋ ጥልቅ ስለሆነ ይመስለኛል ምግቡን ከፊቷ ገፋችው።

‹‹ሲፈን ነው ያልከኝ አይደል?››

‹‹አዎ››

‹‹የት ናት?››

‹‹ትታኝ ሄደች፣ የደሃ ልጅ አለችኝ›› ሌላ አዘኔታ እናማ።

‹‹ዋሽተሃት ነው የተዋወካት?››

‹‹ሁሉም ወንድ ውሸታም ነው›› ስሜቷን ከፍ ዝቅ ማድረግ ፈለኩ። ‹‹እንደምታይኝ ነኝ፣ ቆንጆ ነኝ፣››

ሳቅ አይኗ ላይ ተንቀዋለለ

‹‹የደሃ ልጅ አልመስልም››

‹‹ልደትዬን አትመስልም›› አቀረቀረች።

‹‹እ-ና? ሲፈን እስከታውቅ መጠበቅና አለመንገርም መዋሸት ነው።››

ዝም፤

ምን እንደገነባሁና፣ ምን እንዳፈረስኩ አላውቅም። ግን ደስ ብሎኛል።

ዝምታ ሲበዛ ‹‹ልሂድ›› አለች።

‹‹እሺ›› እንደቆመች እጇን እንደዘረጋች ጥቂት አቆየኋትና ‹‹መጥፎ ትዝታ ውስጥ ገባሁ፣ ይቅርታ›› ብዬ ጨበጥኳት። እጇ መዳፌ ውስጥ ሟሟ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹አሁን ክላስ አለህ? ማለቴ አነጋግረን የደረስንበትን እንድነግርህ! እዚህ ትቆያለህ?››

‹‹አዎ፣ አለሁ›› አልኳት እንጂ እንደማልኖር አውቀዋለሁ፡፡ ነፀብራቅ በሚቀጥለው የምትፈልገኝ ለፀብ እንደሆን አውቃለሁ፡፡ ለፀብ ደግሞ እኔ የለሁም፡፡››

‹‹ቻው ልሂድ››

‹‹እሺ›› ቆይ እንድላት ፈልጋለች እንዴ? ሰላምታ አበዛች፡፡

‹‹ስምህን ማን ነበር ያልከኝ››

‹‹አልአዛር››

‹‹የእኔን አልጠየከኝም ታውቀዋለህ?››

‹‹አዎ፣ ቆንጆን የማያውቅ የለም››

‹‹እንደዚህ አትበል፣ በልደትዬ››

‹‹ነፀብራቅ፣ ለማንኛውም እንኳን አወቅሽኝ›› ፈገግ ብላ ሄደች፡፡ ተጨዋች አይንና ከንፈር፡፡

ጠፋሁ፤ ከነውሸቴ ጠፋሁ፡፡ ግን ውሸቱ የትኛው ነው? አሳይመንቱ እንዳመለጠኝ መናገሬ ብቻ! ይሁንና የወንድ ልብ ባዶ የስንቅ አገልግል ነው፡፡ የአዲስ ሴት ፈገግታና አዘኔታ አግኝቶ መሙላት ግድ ይለዋል፡፡

‹‹አመሰግናለሁ ነፀብራቅ!››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ ሰባት

# የነፀብራቅ ነገር

የግቢውን ቀኝ ጎን ሸሸሁ። አምስተኛ በርን መጠቀም አቆምኩ። አዛች ገዳም ካፌ አለመሄዴ ብቻ ይቆረቁረኛል። በዋናው በር አገባና ኬኔዲ ሳይብረሪ አንብቤ፣ በዋናው በር እወጣለሁ። ክላስ ካለኝ ሹልክ ብዬ ገብቼ ሹልክ ብዬ ልወጣ ስል…

‹‹ነፀብራት ትፈልግሃለች›› እባላለሁ።

‹‹የቷ ነፀብራትን?›› ድርቅ፤ ሶሥሚ እረጅም አጥር ሆኖ መገለያ አሳጣኝ። ምን አስባ፣ ምን ልታደርግ? ምን እንድሆን እንደምትፈልግ ያሳስበኝ ጀመር።

ለረቲት ስደውል፡-

‹‹..ጌታዬነህ›› ትለኛለች። ‹‹ደህና ናችሁ?››

እኔና የእናቴን ቤተሰቦች እንዳላለች አውቃለሁ፤ ሌላው ቀርቶ ልጇን እንኳን እዚህ ውስጥ አታካትትም።

‹‹ደህና ነን››

‹‹እ ዛሬ ምሳ ሰዓት ልምጣ?››

‹‹ነይ››

‹‹እሺ፣ አምስተኛ በር በስድስት ሰዓት››

‹‹ኖኖ›› እላታለሁ። ‹‹በዋናው በር ድባብ ካፌ ሆኜ እጠብቅሻለሁ።››

ዋናው በር፣ ኬኔዲ፣ ድባብ… የዕውር መሸፈቻዎች ኖረዋል። መናፈሻው ውስጥ ቁጭ ብዬ ሳነብ ነፀብራት መጣች። ትመጣለች ብዬ የፈራኋትን ያህል ስትመጣ አልፈራኋትም። እንደውም ሳቂ መጣ። አለባበሷ ለድብድብ የሚያመች ይመስላል። ራንግለር ሱሪ ዲዛይን ካለው ካናቴራ ጋር ለብሳለች።

‹‹ቁጭ በይ፣ ቸብ ቸብ፣ እዚህ አትታዘዝም? ማነህ አስተናጋጅ።›› መጽሐፌን እጥፌ እጠገቤ ያለው ቦርሳ ውስጥ ከተትኩ። አወጣሁ፣ ገለጥኩ፣ አጠፍኩ።

‹‹ምን ልታዘዝ?››

‹‹ሻይ›› አለች



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሻይ አይሆንም፣ ውኃ በብርጭቆ ወይም አምቦ ውሀ ይሻላታል፡፡››

‹‹ለምን?›› እንደቆመች

‹‹የምትደፊብኝ ከሆነ››

‹‹ከተደፋብህ ቆየህ፤ ሻይ አምጣልኝ››

‹‹አቀዝቅዘው›› አልኩ፡፡ ሳትወድ በግድ ሳቀች፡፡

‹‹ቂጭ በይ፣ ይቅርታ!›› አልኳት

‹‹ልደትዬን፣ እንደ እባብ አትሹለከለክ የጠኔ ሰላይ ነህ አይደለህም?››

‹‹ነኝ››

‹‹እና? እኔን ፋራ አድርገህ ስለልከኝ?››

‹‹እንዴት? የምን ፋራ ማድረግ? ቂጭ አትይም? ሻይ እስኪመጣና እስክትደፊብኝ›› እንድትደፋብኝ ፈልጌአለሁ እንዴ? እንደ ሪቂቅ ያልተናደዱ መስሎ ደባደቦ ፊት ላይ ቢራ ከመድፋት...

‹‹ቆይ፣ ስልለሀለት ምን ያደርግልሃል?›

ዝም

‹‹ራንክ፣ አይደል? ከማቃጠር ብታጠና አይሻልህም?››

ዝም

‹‹ተናገር፣ ልደትዬን ተናገር!››

‹‹ይሻለኛል››

‹‹ምን?››

‹‹አንቺ ብታስጠኚኝ፡፡›› ዝም ብላ አየችኝ፡፡ ‹‹ቂጭ በይ ሻዩ...››

ቂጭ ስትል ከኋላዋ የብዙ ሴቶች ሳቅ ተከተለ፡፡ ዘወር ብላ አይታቸው ሀፍረት ተጫዋች አይኖቿን ጎበኛቸው፡፡

‹‹እንዳትቀመጪ፣ ያዘዘውን ድፊበትና ነይ ብለውኝ ነበር፡፡ ነውር እኮነው፣ ልደትዬን፣ አንተን የመሰለ ልጅ ሲያቃጥር››

‹‹ምን ሳድርግ ስላልቻልኩ ነው››

‹‹ምኑን?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ማቃጠሩን ማለቱ ማቃጠር ማቆሙን››

‹‹ማቃጠሱን በል እንጂ፣ ልደትዬን፣ ደግሞ እኔ እንጂ ፋራ ሆኜ ጓደኞቹ ፊት…››

‹‹አለቀስሽ?››

‹‹ይለቀስልህ፣ ላንተ ነው የማለቅሰው? ልደትዬን ለምን ቴአትር ብትማር አይሻልህም?››

‹‹እሱንማ በተፈጥሮ አውቀዋለሁ፤ የማላውቀውን ብማር አይሻለኝም?››

‹‹አስቀያሚ ነገር!››

‹‹ቁንጅና ባንቺ ይብቃ ብዬ…››

ሻዩ መጣ…

…አየችኝ

…አየኋት፣ ፈራኋት… ስታነሳው ብርጭቆውን እንዴት መያዝ እንዳለብኝ ማሰብ ጀመርኩ፤ ፊት አለችው… ያ በፊት የነበረው ሳቅ የብዙ ቆሴዎች ማውካካት መስሎ ተደገመ። እንገቷን ደፋች።

ዝም!

ጨነቀኝ መጽሐፌን ማንበብ አለኝኝ። መጀመሪያም የተሰጠጠ ዕትድ ይዛ ነበር የመጣችው። ሰው ፊት መጠጥ ለመድፋት እንደ ረቂቅ አድፍጦ ጉዳትን ማብሰልሰል እንጂ መርከር አያስፈልገውም ነበር።

‹‹ነፀብራቅ?›› ቀና አለች ‹‹ይቅርታ! ጓደኞችሽ ፊት ይቅርታ ልጠይቅሽ? እ?…››

‹‹ተወው!››

ከበስተኋላዋ ረቂቅ ወደ ድባብ ስትገባ ትታየኛለች። አለባበሷ… እንዴት ህብር ሊፈጥር እንደቻለ ግራ ያጋባል። ህብረ-ቀለማት ህብረ-ዝማሬ ሆኖ እላይዋ ላይ ፈስዋል። ብዙ ሰዎች በተለይ ብዙ ሴቶች በቅናት አይን እየላሿት መጣች። እጇን ስወዘውዝላት ነፀብራቅ ዞራ አየቻት። ከሴት ጋር ስለሆንኩ ሳትቀርብ ቆም አለች።

‹‹ኀይ፣ ተዋወቂያት፣ ነፀብራቅ ትባላለች›› ሲጨባበጡ ሆን ብዬ ረቂቅን ቀደምኳት…



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሲፈን ትባላለች››

ረቂቅ ግራ ተጋብታ፣ ነፀብራቅ በድንጋጤ ተመታ ዝም ዝም ተባባሉ:: ይህ እጭር ግንኙነት እንደ ዳንቴ አዘል አላማዋ የጥበብ ምንጭ ለመሆን አያንስም:: ፍቅሯን ለማስታገስ በር ገነጣጥላ ከምታድረው ሴት በላይ በእንዲህ ያለ አለመደፋፈር ውስጥ የሚለዋወጡት ስሜት ጠንካራ ነው:: ሂሳባችንን የሚመጥን ብር የእምነበረዱ ጠረጴዛ ላይ አኑሬ ከረቂት ጋር ተንቀሳቀስን:: አንድ ነገር ግን ልቦናዬ ላይ ተሸንቅሮ ቀርቷል:: ነፀብራቅን ለጓደኞቿ ማንጓጠጥ ትቻት እየሄድኩ ነው:: የሆነ ነገር ማድረግ የለብኝም?

ረቂትን ነይ ብዬ እጇን እንደያዝኩ ወደ ነፀብራቅ ጓደኞች ሄድኩ:: አምስት አድግ ወ በትል ትኩረታቸውን ከነፀብራቅ ወደ እኛ መለሱ::

‹‹ተዋወቋት፣ እህቴ ናት ረቂት ትባላለች::›› ወደ ነፀብራቅ እያመለከትኩ ‹‹እሷ የምወዳት፣ ስለወደድኳት የምፈራት ነፀብራቅ ናት:: ቅድም ስላልነገርኩሽ ነው:: አቤት ስወዳት!!›› አልኩ::

ረቂት ፈገግ ብላ ‹‹ደስ ይላል›› አለች:: የነፀብራቅ ጓደኞች የጨበጡበትን እጃቸውን እንዳንከረፈፉ ቀሩ:: ስንርቅ ረቂት የተደገፈችው ክርኔ ላይ የመቆንጠጥ ያህል አጥብቃ ይዛኝ...

‹‹ጌታዬ ነህ፣ በጣም በጣም አደገኛ እየሆንክ ነው፤ ይገባሃል? ሲፈንን ለምን አትረሳትም?››

ከሩቅ፣ መኪና ውስጥ ሰገነት ተቀምጣ አየኋት:: ጊዜ የሚጠብቅ ያልፈነዳ መንፈሷ ሚሸሸ ፍቅሯን ገርታ ጥሩ ሰጋሪ ወጥቷታል:: ስታገኘኝ ትደሰት ትከፋ ምንም የሚለይ ነገር የለም:: ደብዝዛ ትቀርባለች:: እንዳለፉት ጊዜያት ብዙ ጥያቄዎች የሏትም::

‹‹ትሄጃለሽ?››

‹‹እኔ እንጃ››

‹‹ታድሪያለሽ?››

‹‹እኔ እንጃ›› ዝም ስል ‹‹አንተ ምንድነው የምትፈልገው?››

እንድትሄድ ብፈልግማ ዝም እል አልነበር?

ዛሬም ከጎኔ ተቀምጣለች:: ምርጫውን ለእኔ ስትተው ነው:: ከፈለኩ ከረቂት ጎን ካልሆነም ከእሷ ጋር እንድሆን::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሰላም ካልኳት ሰላም፣ ከጨበጥኳት መጨበጥ፣ ከሳምኳት መሳም። አታስትስም አትስትም። አትከፋም፣ አትደሰትም። ውስጧ ጊዜ የሚጠብቅ እሳተ ገሞራ ያለ እየመሰለኝ ብዙ ጊዜ ለማጣራት ሞክሬአለሁ።

ሰው እንዴት በዚህ መጠን ራሱን ሊቆጣጠር ይችላል? ተአምር የሚያስከትል ተአምር እንዳይሆን እንጂ። ኩርፊያ አይደለም፣ ቅሬታም የለበትም። መናቅ ሊሆን አይችልም፣ መፍራትም ፈፅሞ... የሆነ ስመግለፅ የሚያዳግት ውሳኔ ይታየኛል። ምን አስባ፣ ምን ትክክል እንዳልሆነ አረጋግጣ እዚህ ውሳኔ ላይ ደረሰች ብዬ ሳስብ ይጭበረበርብኛል። አንዳንድ ጊዜ እራሴን እጠይቃለሁ። የምወደውን ሰው ለማግኘት እራሴን እንደዚህ ገድዬ አቀርባለሁ? ሌላውንስ እራስህን ገድለህ ካልሆነ አታገኝም ማለት አደገኛ ራስ-ወዳድነት አይደለምን?...

ሪቂቅ መኪናውን ቆስቁሳ ቀድማ ወደወሰነችበት ምግብ ቤት አመራች። ምርጫን መነጠቅ በምግብ ቤት እንኳን ጠንከር ያለ ስሜት እንደሚያሳድር አውቃለሁ። ግን... ምን ይሁን? ከፍቅር ያለፈ የቋሚ ኑሮ ምስረታ ነገር በሴቶች ሲታሰብ ያመኛል። ፍርሃት-ፍርሃት ይለኛል። የማላውቀውን መዘዝ ወደማላውቀው ጉድጓድ እጄን ሰድጄ በራሴ ላይ መጥፎ ዕጣ ያወጣሁ ይመስለኛል።

ጊዜ የጣለው የመኳንንት ጊቢ ውስጥ ገባን። ከመኪና ሳንወርድ የሚታዘዝን መጣ። በብብቱ የምግብ ዝርዝር ይዟል። ለሪቂቅ ሲሰጣት ሳትቀበል የራሷን አዘዘች። የእኔንም እንድታዝዝልኝ ነገርኳት

‹‹እርቦሃል? ማለቴ...››

‹‹አይ፣ ብዙም አልራበኝ...››

አዘዘችልኝ። ለጎኑት የራሷን አዝዛ መጣ፣ በሥጋ፣ በድንች፣ በፎስሊያ... የሂሳብ መማሪያ የልኬት መሳሪያዎች ተዘርግፈው መጡልኝ። ሶስት ጎን መስሪያ፣ ክብ መስሪያ፣ ማስመሪያ፣ ላፒስ፣ እርሳስ የመሳሰሉ ነገሮች። አካያቸው ላይ የሴንቲ ሜትር መጠቆሚያ የሚመስሉ ቅመሞች አሉበት። ጂኦሜትሪዬን በሹካ እያነሳሁ መብላት ጀመርኩ።

‹‹ጌታዬ ነህ?››

‹‹እ?›› ይሄ ጥሪ ‹‹መሪጌታ›› እየመሰለኝ መጣ።

‹‹አብረኸን ትውላለህ?››

‹‹አ-ይ፣ መመለስ አለብኝ››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ጥሩ›› ከጠናጋሻው የወረሰችው ብቸኛ ቅርስ ጥሩ የሚለው ቃል ሳይሆን አይቀርም። የእኩሉ ቀን ጨረር ልብሷ ላይ አያረፈ ሲነሳ ብዙ አይነት ቀለም ይይዛል።

‹‹ጌታዬ ነህ›› (መረጊታ ቃለ ብትለኝ)

‹‹እ?›› ምግቧን በሹካ ታንከላውሳለች እንጂ ወደአፏ አትለውም። ለካ አፍ ውስጥ ከትቶ ማንከላወስም አንድ እርምጃ ነው?

‹‹ቅድም ባየሁት አልተደሰትኩም፣ ዕድሜህ ነው፣ አውቃለሁ። ግን፣ በቃ፣ አለ አይደል??...››

ለገነት መዋሯን ዘንግታ እሷ ፊት የማይወራ ልታወራ መሰለኝ...

‹‹ሰጊ፣ እየበላሽ›› አልኳት

‹‹እሺ››

‹‹እና›› ረቂት አስታውሻትም ቀጠለች። ‹‹የምትፈልገውን በፍፁም፣ በፍፁም ማጣት የለብህም። ለሰው ቀርቶ ለእግዚአብሔርም ብለህ መተው አይገባህም። ግን ደግሞ ምርጫን ገድቦ ፍላጎትን አንድ ሴት ላይ ማድረግ ተገቢ ነው።››

የአንድ ቀን መሰናከያዋን የዘልአለም የህይወት መመሪያ ለማድረግ በመጣር ላይ ያለች መሰለችኝ። እሷ ምርጫዋን ገድባ ፍላጎቷን አንድ ሰው ላይ አድርጋ ነበር? ከሆነ የልጇን አባት በአንድ ጀንበር ከጓሮ ሽመጠጠችው? ቢያንስ እሱ እንድታገባው ሲጠይቃት እንዳይደፍርም ተስፋ እንዳይቆርጥም አድርጋ አቆይታው አይደለም?

‹‹የምትጎዳውን ሰው ማብዛት ነው፣ ሌላ ምን ጥቅም አለው? የጎዳ ብቻ ነው ደግሞ እራሱን የሚጎዳው። አይምሰልህ የተጎዳ በስጋ እንጂ በነፍስ አይበደልም። አሁን እኔ የልጄን አባት ካላሰብኩ በጠኔ በኩል ነፍሴ ንፁህና ደስተኛ ናት። አይደል?››

‹‹እዎ›› ምን አከራከረኝ? ብቻ ለገነትን እንዳፈዘዘካት ተረከባት እንዳትለኝ? ዘወር ብዬ አየኋት። የረቂት ንግግር እሷን እንደማይመለከት ሁሉ ከምግቧ ጋር በሹካ ትጫወታለች። እንዴት ያለ የተፈጥሮ ህግን በአፍጢሙ የደፋ ለውጥ ነው? ወይም እንዴት ያለ መለወጥን እንዳያጠራጥር አድርጎ የመተግበር ጥበብ ነው?... ፍራንዝ ካፍካ እንዲህ ያለውን ድርጊት ይሆን እንዴት ከሰው ወደ ትል በሚቀየር ገጸ-ባህሪው የገለፀው? "The metamorphosis" ቀጥር ሁለትን እኔ ሳልፈፅመው አልቀርም።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ ስምንት

## የፍስጋ ነገር

አባቴ የቆሴዋ መሰማመኛ ገከር ላይ እንዲህ አለ፦

‹‹ዛሬ ሌሊት ሲያቃዠኝ አደረ፤ ምን ቅዠት ነው? እንዲሁ በገኃድ አየሁት እንጂ። ኮዳዬ ጠፍቶ ይመስለኛል ጭንቅ ብሎኝ አልጋ ሥሩን ሁሉ ስገለባብጥ አደርኩ። ደግሜ ባይ ይሄው፤ ደግሜ ባይ ይሄው...››

የአባቴንጣ ያየሁ ና ወዲህ በለኝ አልኩ።

‹‹አባይ ቂስ፤ ህልም መፍታት አታውቅም? በህልም ኮዳ ምንድነው?››

ቤት ውስጥ ሆኜ ስለማዳምጥ ረድ ሠርዌ ድምፁ እንጂ ያለበት ቦታ አልታየኝም። ‹‹አባይ ቂስ›› በመባሉ አስከፍቶት የቅሬታ ማመልከቻ በንግግር ያሰማል ብዬ ጠበኩ።

‹‹እንግዲህ ኮዳ፤ ኮዳም አይደል?›› በማለት ነገር እያረቀቀ ጀመረ። ሴቶቹ ሁሉ ወደ አንድ አቅጣጫ ያያሉ። የእናቴ ጢስ አዲስ የፈነዳ ውኃ መስሎ ሽቅብ ይምዘገዘጋል።

‹‹ኮዳ ነው ያሉኝ?››

‹‹አዎ›› አባቴ ድምፅ ላይ መሰላቸት ይነበባል። የጥይት ጎሬውን ግንባሩ ላይ ዳሰሰ።

‹‹እንግዲህ... ሕልም በኹለት ይፈታል። የአፈታቱ ነገርስ እንደምን ነው ቢሉ፤ የያዕቆብ አስራ አንደኛ ልጅ፤ የራሄልም ልጅ የሆነው ፈካሬ ሕልም ቅዱስ ዮሴፍ በፈርዖን ቤት እንዳደረገው ነው። ከዕለታት በአንዲት ቀን ፈርዖን ሰባት መልካቸው የከፋ ሥጋቸውም የከሳ፤ ሰባት ደግሞ መልካቸው ያማረ ሥጋቸው የወፈረ ላሞችን በሕልሙ አየ። ሕልሙን ሰመፍታትም የሱ ዐዋቂዎች አልቻሉምና ዮሴፍን አስጠርቶ «ሐለምኩ ሕልመ ወዘይፌክር ሊተ ኀጣእኩ፤ ወሰማዕኩ እነ በእንቲአከ ከመ ሰማዕከ ሕልመ ወፈከርከ» ባለው ጊዜ፤ መልከመልካሞቹን ላሞች የበረከት ዘመን ምሣሌ መልከጥፉዎቹ ደግሞ የረኃብና የምንዳቤ ዘመን ትእምርቶች ናቸው ብሎ እንደፈታለት፤ ይኸውም በኋለኞቹ ዓመታት እንደተፈጸመ፤ ዮሴፍም ምገሥን እንዳገኘ ተጽፎ የለምን?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እስኮ መች አጣነው? ጣ!»

የአባዬ ‹ጣ› ተገኘች።

«ነገርን ከሥሩ ውኃን ከምንጩ እንዲሉ አበው፣ ኮዳውም በሁለት ይፈታል፣ይፈከራልም። ይሄውም ኮዳው አንድም የጥማት ጊዜ ውሃ አጣጪ ነውና የክፉ ቀን ወዳጅን ያመለክታል።»

«ምንድነው የሚለው?» አለ አባቴ «የክፉ ቀን ወዳጅህ ይጠፋል፣ ይሞታል እያልክ ነው?»

ከረድ ሠርዌ ቀድመው ጋሽ ተገኔ ተናገሩ «ብዜን ሌላ ማን የክፉ ቀን ወዳጅ አለው? እኔው ነኝ! እኔው ነኝ! ድግስ ጠርቻችሁ ሞቴን ታረዱኝ? ምን አልኳችሁ?...»

«አባይ ቄስ አኮ ነው፣ ተገኔ አታውቀውምና ነው? አባይ ቄስ አምነህ?...ጣ!» የጋሽ ተገኔ ድምፅ እየራቀ ሄደ። የመቀመጫ መንኮራኩራቸውን ጎማ እየገፉ ስለሚሄዱ «አድርሱኝ» አላሉም። ሬቻት ነፃ አወጣቻቸው።

«በል ወንድሜ ሁለተኛውን ቀጥል፣ ሁለተኛው የኮዳ ፍቺ ምንድነው?»

«ኮዳው አንድም ጦርነትን ይወክላል»

«ኧ? ምን አልክ አንተ?»

እንደ ሬቻት አማጮች የግቢ መቀርቀሪያ መዘ ረድ ሠርዌን ሊያሳድደው መሰለኝ። ረድ እንዴት ይሮጥ ይሆን? መቼም ነፍስ ይዞት የተከለሉን እቋቋም በአሯሯጥ እተገብራለሁ አይልም።

«አልኩ'ኮ፣ ምሥጢሩ ይሄው ነው » አለ።

«አይ አንተ ሩፋኤል! እንዲያ ከሆነማ ይኸው በጆማው ፊት በግ እርዳለሁ» አባቴ ለቆሌዋ ይሁን ለሩፋኤል ብቻ ተሳለ። እውነትም ልጁ ሬቻት አጥግባዋለች። አንድ ብርሌ ጠጅ የሚጠርበት በግ?

«እናት፣ በይ ተዘጋጂ! ይሄ አባይ ቄስሽ ከያዘለት ስንቅሽን አደራጂ»

ሊዘምት? ሌላ ጥይት ባፍንጫው ሊስብ?

«ሊዘምቱ?» እናቴ

«ሉ-ይ፣ ቁጭ ብዬ ጠላት እዚህ እስኪደርስ እጠብቀዋለሁ።» አባቴ አሾፈ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ለካ አባቴ እንደ እኔ ልብለድንግል ‹ጦር አውርጅ› እያለ መሬትን እርባ ሲያስገርፍ ኖሯል፡፡ ‹‹ጥይታችንን ከግንባራችን አጣን፣ የጦር ምልክታችን ጠፋን፣ ልጆቻችን እነ ታሰ በቂም ናዋዥ፣ እየሄዱ ተካዥ ሆኑ፡፡ አንቺ መሬት ኧረ ጦር አምጪ!!ኧረ ጦር አውርጅ!!›› አባቴ ቀጠለ፡፡

‹‹ጦርነትና የስጦታ ፈረስ ጥርሱ አይታይም፡፡ ዝም ብሎ መቀበል ነው፡፡ ግና ጦርነቱ መምጣቱን መጣ፣ ከማን ይመጣል? ሱዳን እንደሆን ስናፈጥባት ተርበትባች ናት፤ ሱማሌ የተባለ እንደሆን እስክዝንታለሙ እንዳይለመዳት አድርገናታል፡፡ ታዲያ ማን? ለኬንያ የቦረና ኦሮሞ በቂዋ ነው፡፡ እኛ እዚያ እስክንደርስም አያስተርፍልን፡፡ ቱርክ ይሆን እንዴ?››

ይሄኔ በገና ያደመጥኩ መሰለኝ፡፡

....እኔ መዩ

....ቱርክ ባይ

....የምሸሽ ነኝ ወይ

ታጠቅ ብሎ ፈረስ ካሣ ብሎ ሥም፣

እርብ እርብ ይሸበራል ኢየሩሳሌም፡፡

‹‹የደርግ ወታደር ጦርነት ያልማል?›› አለ የአባቴ ምክሼ ብዙን፡፡ ‹‹እዚሁ እንዳላችሁ በሰላም ኃይሎች በቁጥጥር ስር ትውላላችሁ››

እንደለመደው እናቴ ትበቃዋለች፡፡

‹‹ና አንተ ሽንታም›› ስትለው ጠበንጃውን እያንገጫገጨ ሮጠ፡፡ የአባቴ ምክሼ ዛቻ ያላማራቸው የዝክሩ ታዳሚዎች ረድ ሠርዋ ሳያሳርግ ቀስ በቀስ ተበተኑ፡፡

* * *

አምስተኛን በር ከነፀብራቅ ባስለቅቅም ተጠቅሜበት አላውቅም፡፡ አረፋፍጄ ድባብ እገባለሁ፡፡ ቦታ አልቀይርም፤ ነፀብራቅ አጋጣሚ አስመስላ ትመጣለች፡፡

‹‹የእኔን ጓደኞች አላየህም?››

‹‹አላየሁም››

‹‹እዚህ ነን ብለውኝ የት ሄዱ በልደትዬ?››

‹‹ተቀመጭ፣ ውኃ ወይም አምቦ ውሃ ይምጣልሽ››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አይገና ከንፈሮቿ የተሳተፉበት ሳቅ ‹‹ሻይ››

‹‹ቁጭ በይ፣ ቀገቃዛ ሻይ››

‹‹ያቺ ሲትዮሀ አትመጣም፣ በልደትዬ››

‹‹አትመጣም›› ረቂቅን ጠልታታለች።

‹‹ብትመጣ እንጣላለን፣ ልደትዬን›› ቁጭ

‹‹እህቴ እኮ ናት››

‹‹ሲፈን ናት አላልከኝም?››

‹‹አይደለችም፤ ረቂቅ ነው የምትባለው። ረቂቅ ቢዘን፣ የአልአዛር ቢዘን እህት።››

‹‹ኡ-ሺ ሲፈን እንዴት አይነት ልጅ ነች?››

‹‹ቀጭን፣ አይኗ እንዳንቺ የሚያምር፣ ከንፈሯ ስታወራ እንዳንቺ ከንፈር...››

‹‹እንደሱ አትበል በልደትዬ››

‹‹የመልክ አብሪት ያለባት፣ ቆንጆ ነኝ ስትል የማታፍር...››

‹እንደሱ አትበል፣ በልደትዬ። የልደታ ልጅ ናት አላልከኝም? ልደትዬን እያለች ትምላለች አላልከኝም? ልደትዬን እያልኩ እንዳላስታውስህ ልደትዬን አልልም ብዬ ምዬ ነበር።››

ኀዘን፣ መስዋዕትነት ተጀመረ...

‹‹የልደታ ልጅ አይደለችም››

‹‹ያኔ ግን ያልዋሸሽኝ ምንድነው? ወይኔ አፈር በበላህ፤ ልደትዬን ብትምት ይሻልሃል እኮ››

ዝም

‹‹እሺ የት ነው ሰፈሯ?››

‹‹ናዝሬት። የናዝሬቷ ሲፈን እያልኩ ነበር የምጠራት። ‹እንዳታስቀስፈኝ› ትለኛለች።›› ውስጤ መቁነጥነጥ ተፈጠረ። ነፀብራቅ የአይኖቿ ብርሃን እጅ ሆኖ ሲያቅፈኝ ታወቀኝ። ከአካል በላይ በአይን መተቃቀፉ ስሜት ሰጪ ነበር መሰለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እምስቱ እድግ ወ በቅል መጥተው ከስሜቱ አናጠቡኝ። ሁካታ፣ ጫጫታ፣ ኳኳታ የተቀላቀለበት ሳቅ...

‹‹እንቺ? እንቺ? እንቺ?...›› እምስት እንቺ አዋጡ። እህያና በቅሉ አንድ እንቺ አይበቃውም።

‹‹እንቺ? በየት በኩል ሸውደሽን መጣሽ?››

ነፀብራቅ ከእነሱ ይልቅ እኔን አፍራ የሚያማምሩ አይኖቿን መደበቂያ አጣች። ሰደድ ስታደርጋቸው ቅልብ አደርግባታለሁ። የእድግ ወ በቅል ወቃሽ አይን የእህቶቼን ትዝታ ቀሰቀሰብኝ። ረቂት ማፍቀሯን ሲያውቁ፡-

‹‹ምነው? ቀልቧን ምን ነሳት?››

‹‹አፈር ትብላ፣ ምነው ሞታ ባለቀስን?››

‹‹ታስ ይሙት፣ እኔማ ውሃ ነው የሆንኩት!››

‹‹ወይ ቅሌት፣ ምን አሳበዳት ልጄ?››

‹‹ኦሆሆሆሆሆይ!››

‹‹በኢየሱስ ስም!!›› አሾቫ

‹‹ዝም በይ! ዝም በይ! ዝም በይ!››

ስለፍቅራቸው ‹‹የብዜን ፉርጎ›› ይባሉ የነበሩ፤ ለስራ እና ለፀብ የተባበሩ... እነማን ነበሩ?...። ፈገግ አልኩ። በእሷ ላይ መስሏት ነፀብራቅ ሽምቅቅቅቅቅቅ... አለች። ቀስ ብዬ ወደጆሮዋ በመጠጋት፡-

‹‹ቅድም ግን ያልዋሸሽኝ ምንድነው? ‹ጓደኞቼ እዚህ ነን ብለውኝ› አላልሺኝም? ወይኔ አፈር በበላሽ፤ ልደትዬን፣ ብትሞቺ ይሻልሻል እኮ››

ቀልድ ሆኖ አልተሰማትም። ንዴት ፊቷ ላይ አነበብኩ።

‹‹ወደደቺኝ እንዳይሆን? ልደትዬን››

‹‹እዎ››

‹‹ኧረ እንዳማረብህ ዞር፣ ልደትዬን። አልወድህም።›› ጓደኞቿ ራቅ ብለው መቦጨቅ ጀመሩ።

‹‹አንድ ቀን እንደ ሲፈን እስብልሻለሁ።››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ምን? በልደቴዬ?››

‹‹'ስወድህ... ስወድህ... ስወድህ... እንዴት ነው የምወደህ ሲያስፈራ!' ነዋ!››

‹‹እኔ አስብልሃለሁ ልደትዬን››

‹‹አሁን ለምን አልልልሽም? ስወድሽ፣ ስወድሽ... ስወድሽ... እንዴት ነው የምወድሽ ሲያስፈራ››

‹‹ምንድነው የምትፈልገው?›› ጓደኞቿ ቀልባቸውን ሰጡ። የሆነ የደበቀችው ስሜት ስለተነካ ይሆናል እንጂ ምን ያናድዳል?... አላፈገፈኩም፤ ተጋፈጥኳት...

‹‹አንቺ የመጣሽው ንገሪኝ እንጂ››

‹‹አልመጣብህም አቃጣሪ! ልደትዬን››

‹‹እናት ካለሽ በእናትሽ፣ አትምጪ››

አምስቱ እድግ ወ በቅል ጭምር በጥላቻ አዩኝ። ግድ አይሰጠኝም። ከዚህ በኋላ የሚኖረውም አያጓጓኝ። ደግሞ ስለተገፈተረች የምትሄድ ሴት የለችም። መሳደቧም አይቆረቁረኝም። እንደውም እሷን እየቆረቆራት እንዳትረሳኝ ያደርጋታል። ደግሞ የበለጠ እንድትመጣ ከፈለኩ የበለጠ እገፈትራታለሁ። ከዚያስ? እውነት ምንድነው የምፈልገው?...

በእድግ ወ በቅል ታጅባ እየተባበለች፤ ሄደች የመናፈሻው አጋማሽ ላይ ስትደርስ ጮሃ በተነቻቸው። ማባበላቸው መሸነፏን የመስከረባት ስለመሰላት ስሜቱን ጠልታው ይሆናል።

እንዳች መጥፎ ነገር እንዳደረኩ ይሰማኛል። እኔ ላይ ሙሉ መብት እንዳላት የደመደመችው ነፀብራቅ በሙሉ መተማመን ስትከፍተው ባዶ! ያልተጠበቀ ነገር ያልተጠበቀ ስሜት ይፈጥራል። ይህ ሁሉ ግን ለምን? መልስ እንደሌለኝ አውቃለሁ...

...ይሄን ተራ ስሜቴን፣ ግለሰብ ያጠቃሁበት ያልተገለጠ መነሻ ነጥቤን ፍልስፍና ወይም ርዕዮተ ዓለም፣ ወይም ሥነጽሑፍ፣ ወይም የአንድ ታላቅ ሰው ታሪክ ሆኖ ወደሚቀየርበት ቦታ መሄድ አሰኘኝ። ያም ቦታ የጠናጋሻው ቢሮ ነው። ተነሳሁ፣ ሂሳብ ከፈልኩ፣ ከድባብ ወጣሁ፣ በአንደኛ በር ገባሁ፣ ወደ ጠናጋሻው ቢሮ አቀናሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ከሩቅ አንዲት ልጅ ከቢሮው ስትወጣ አየሁ:: ፊቷ እንደፈገገ ይሁን እንጂ መልኳ ጠይም አረሩ የተደፋበት ደባደቦ አይነት ነበር:: በነሁብራቅ የተጠቆመችው አስተያሚ መሆን አለባት፣ እሺ ተብላ መሆን አለበት:: ለምን? በመልክ የተበደሉ ስለሚመስለው?.. ወይስ...

እንኳኩቼ ገባሁ:: ጠና ጋሽው ጠረጴዛ ጫፍ ላይ ተቀምጦ በመስኮት አሻግሮ እያየ ነበር:: የተለመደ አለባበሱ፣ ቡኒ ሹራብ፣ ሰብኒ ሱሪ፣ በስክ ጫማ... በመስለቻቸት ሲዞር አየኝ::

"Thales, the first philosopher" አለኝ በቀልድ:: ‹‹ለምንድነው Thales መባልህን እስካሁን ያልነገርከኝ? ማነው ያወጣልህ? ታለ መባልህን ያወቀ መሆን አለበት?››

‹‹እራሴ ነኝ››

‹‹እንዴት? ጥሩ!››

"Introduction to philosophy ስንማር የጋራ ‹አሳይመንት› ተሰጥቶን ነበር:: ስለመጀመሪያዎቹ የግሪክ ፈላስፎች አትርቤ Thales ሁሉም ነገር ከውሃ እንደተገኘ መናገሩን እኔ በሙከራ ያረጋገጥኩት በመሆኑ እንደምቀበለው አስረድቼ ከቤት ስሜ ጋር የፈላስፋው ስም መግጠሙ እንደሚያኮራኝ አስረዳሁ:: ትርፍ ነገር ነበር:: ከዚያ በኋላ Thales ይሉኝ ጀመር::››

‹‹ሁሉም ነገር ከውኃ መገኘቱን በሙከራ አረጋግጠሃል እንዴ? ጥሩ!››

‹‹ውኃ ያልኩት መጠጡን ነው፣ የሚያውቁ ሳቁ፣ ለማያውቁት ነግረው አሳቁ:: በመጨረሻ መምህሩም ለምቶ ሳቀ:: ትምህርታችን ላይ ሳቅ ይጎድላል መሰል ያ የሳቁበትን ቀን መርሳት ተስኗቸው ሰስት ዓመት ሞላ››

‹‹ፍልስፍና በባህሪው በሞት ሽረት ክርክር ውስጥ ያለፈ በመሆኑ ሳቅ ይጎድለዋል:: አንዳንዴ ብቻ መልስ የሚሰጥበት መንገድ ሽሙጥ ይሆንና ፈገግ ያሰኝ ይመስለኛል:: ለምሳሌ...›› ብሎ ተንከተከተ

‹‹ምነው?›› አልኩት ወንበር ስቤ እየተቀመጥኩ

‹‹መምህር ነገር ለምሳሌ ማለት ጀመርኩ:: any ways ሶቅራጠስ ‹የሰውን ልጅ ላባ ያልለበሰ በሁለት እግር የሚጓዝ ዶሮ ነው› አለው:: ኒቼ ይመስለኛል ለዚህ ሲመልስ ‹ዶሮ ላባዋን ብትላጭ ያው ዶሮ ነች:: የሰው ልጅ ግን ሁለት እግሩንም ተቆርጦ ያው ሰው ነው::› አለ:: ጥሩ!››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ማነው ‹ታስስ› መባሌን ከዚህ ጊዜ በኋላ የነገረህ?››

‹‹ፈተና ያመለጠህ የመሰላቸው ልጆች ሲያስመዘግቡ ነው:: ‹ታስስ› ይሉኛል:: እንግዲህ ፍልስፍና የተማረ አባት ልጁን ታስስ ብሎ ስይሞት መስሎኝ ነበር:: ሙሉ ስምህን ሲያመጡ አንተ ሆነህ አገኘሁት:: ጥሩ!››

‹‹የምን ፈተና ነው ያመለጠኝ?›› አውቂ ለማጣራት::

‹‹ተዋቸው! ተሳስተው ነው፤ ጥሩ ከታሪክ ትምህርት ክፍል የመጡ ልጆች ናቸው::›› ከጠረጴዛው ጫፍ ተነስቶ ‹‹ህይወት እንዴት ይዛኻለች?›› አለኝ::

‹‹እንደ ዳክዬ››

‹‹እንዴት? ጥሩ!››

‹‹ከላይ ተንደላቆ መንሳፈፍ፤ ከውሃ ሥር ለመቅዘፍ መንደፋደፍ››

ደስ የሚል ሳቅ፤ ድምፁን ከፍ አድርጎ ለመጀመሪያ ጊዜ ሳደምጠው ነው:: ውትድርናና ፍልስፍና ሳቁን ነጥቀው አቆዩት:: በኋላ ደግሞ ስምረት...

ቢሮው በተለያዩ መጻሕፍት ተሞልቷል:: በስምረት የፈቀደችለት የፍልስፍና ማስተማሪያ "Questions that Matter" መጽሐፍ ሁለት ቅጅ አየሁ:: አንዱ አዲስ፤ ሌላኛው አሮጌ::

‹‹የሁላችንም ህይወት የዛች ዳክዬ ቅጂ ነው:: በሚስቶቻችን ማነቅ የተዛነፈ ሽሚዛችንን ሳናስተካክል ከቤት አንወጣም:: የውሃውን ውስጥ መንደፋደፍ ሳይሆን ላይ ላዩን መንሳፈፍ ነው ለተመልካች የምናቀርበው::›› በስምረት የተፈነከተው ትዝ ብሎኝ ጭንቅላቱን አየሁት:: በቆብ ሳይሸፈን ለአይንና ለነፋስ እንደተጋለጠ ቁስሉ ጠግጓል፤ የተላጨው በቅሏል:: አይኔን ተከትሎ የገባው ነገር ሳይኖር አልቀረም::

"What we choose for ourselves, that we become and what we become, that we..." ሲል እኔ አገዘኩት

"...contribute to the definition or essence of humanity" ጨረስኩለት::

‹‹ጥሩ! እኔ የራሴ ምርጫ ውጤት ነኝ:: ይሄን ፍልስፍና እንዴት ልክደው እችላለሁ? የመምረጥ ነፃነት፤ ያ ነፃነት ደግሞ ለሰው ልጆች ሁሉ የቀረበ ፍርጃ ነው:: We are condemned to be free ጥሩ!››

ጠናጋሽው ቢሮ በተደጋጋሚ መጥቻለሁ:: እንደዛሬው ግን ፍፁም መምህር ሆኖ አያውቅም:: በሚስቱ የተመረጠለት መንገድ ይሄ እንደሆነ አውቃለሁ::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ቀጥቅጣ-ቀጥቅጣ፤ ከመምህርነት ውጭ ግራና ቀኝ የማየት የንባብ አማራጮቹን በማጥፋት ለኑሮ የሚኖር ማድረግ የስምረት ፍላጎት እንደሆነ እራሱ ይነግረኝ ነበር:: ተሳካላት? ወይስ አጋጣሚ ነው? የመጣሁበትን ሳንወያይበት ሂድ! ሂድ! ሂድ! የሚል መንፈስ ተጠናወተኝ:: እንደ ረድ ሠርዌ የቅኔ ትምህርት ጠናጋሻቸውን ትቼ መሄድ::

እጁን ዘረጋሁለት:: የመሰናበቻ መዳፌ ብቻውን አልነበረም:: የስፌት መኪና ክር መስሉ የተጠቀለለ ብር ነበረበት::

‹‹አያስፈልገኝም፣ አለኝ:: ባለፈው የሰጠኸኝ መሳቢያ ውስጥ አለ፣ አላለቀም:: ጥሩ!››

ኩርፊያ እንዳልሆነ አውቃለሁ:: ብሩን ለግራ እጄ አቀብዬ ጨብጬው ወጣሁ:: አሁን ወደየትም መሄጃ የለኝም::

‹‹ጥሩ! ከጠናጋሻው ስሸሽ የመጀመሪያ ቀኔ ነው:: ስድስቱ አድግ ወ በቅል ቢሮው አካባቢ (ሣር እየጋጡ) ሲጠብቁኝ ነበር::

‹‹ሃ! ሃ! ሃ! ሂ! ሂ! ሂ!›› የሚል የአህያና የበቅሎ ሳቅ:: ጥሩ!

‹‹ታለስ! ታለስ! The philosopher"

‹‹ውሃ ነህና ወደውሃ ትመለሳለህ›› መጠጥ አለኝኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# አስራ ዘጠኝ

## እንግዳ ነገር

ሦስት ቀን ከቤት ሳልወጣ፣ የጡረታ ድልድይን ጸጥታና ብርድ ስመገብ ቆየሁ። ስወጣ የአባቱ ፓትሪስ ሉሙምባ ካፖርት ሽቦ ላይ ተንጠልጥሎ ሀሀይ ይቃብዛል። ረቂት ሰፈር ወስዶ ካልሰተሰው እዚህ መቀትም፣ ጨኸትም አያገኝም። ትልቁ ቤት በር ላይ በአሮጌ ትሪ ሳንጃ፣ ሴንጢ፣ ጢም መላጫና አንድ የማላውቀው ብረት ዘይት ተቀብተው ዝገታቸውን እንደ ቅንቅን ያራግፋሉ። የክት ልብሴን ከትልቁ ቤት ሳወጣ እቴቴ ደረት ጡቷን የአበዛሽን እያጠባች ነበር። የእንጀራ እናት ጡት ነው የሚባለው?

ግቢው ታምሶ የሚጠብቀኝ መስሎኝ ነበር። ያመለጡኝ ትምህርቶች ቢኖሩም አልተጨነኩም። እንደውም Withdrawal form ብሞላና ሪፍት ብወስድ ተመኘቻለሁ። የትኛውም አመታዊ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ከአመታት የግል ንባብ በኋላ ቢካሄድ ሳይሻል አይቀርም።

ገዳማዊት ካፌ ጉብቹ ቦርሳዬን ከትከሻዬ አወረድኩ። ከፍቼ የAlbert camusን The Happy Death መጽሐፍ አወጣሁ። ደም ነካክቶታል። የጠና ጋሽው ደም። የካሙን ፊት አየሁት። ከጆሮ መዳረሻ እስከ አይን አቃፊው ድረስ ያለው የፊቱ አጥንት ጎልቶ ይታያል። እንደ ረቂት በድብቅ ሳይሆን በግልጽ ሲሸራ ያጨሳል። የጉንጩ ቆዳ ወደ ውስጥ ሰጥሞ አንድ አምስት ቡግሮች ወረውታል።

ቀና ስል አምስቱ አድግ ወ በቅል ፊት ለፊቱ ካለ የእምነበረድ ወንበር ላይ ቀዝቅዘው ተቀምጠዋል። እዚች ካፌ ውጨኛ አጥር ላይ «ለ አድግ ወ በቅል የተከለከለ» ተብሎ መጻፍ ይኖርበት ነበር። ከመካከላቸው አንዷን ገፋፍተው ላኳት። መጥታ ፊቱ ተደቀነች። ፊቷ የሆነ ትዝታ ቀስቅሶብኛል። የት አውቃት ይሆን?

«እንድትታረቃት ነበር የመጣነው?» እህያ አስታራቂ የሆነበት ዘመን…

«መጀመሪያ አንቺ ብትታረቂኝ አይሻልም?»

«እኔ ምን አደረኩ?» ፊቷን ለማስታወስ ውስጤ ይጥራል



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ጭንቴን ገልብጠሽ፣ መሃል ሜዳ ላይ ጥለሽኝ አልሮጥሽም?»

«እ?» ወፈርፈር ያለች፣ በደንብ የተያዘች አህያ

«ማለቴ ከጠናጋሽው ቢሮ ስወጣ አልሳቅሽብኝም?»

«የእኔ ግዴለም...» ጓደኛቿ (ዝርያዎቿ እንጂ) በጉጉት

«ሳይታረቁ ማስታረት አይከብድም?»

«እሺ ይቅርታ»

«አልተበልም! አሁን ሂጂ» ወደንባብ። ከአህያ ጋር የማወራ የተረት ሰው የሆንኩ መሰለኝ።

«ሃ! ሃ! ሃ! ሃ!....»

ሳቀች? ወይስ አናፋች? ቀና ብዬ አየኋት፣ ገርሚታል። አህያ ተገርሞ ስመለከት የመጀመሪያ ጊዜዬ በመሆኑ እኔም ተገረምኩ።

«ምንድነኝ ብለህ ነው የምታስበው? ማለቴ እራስህን አታውቀውም? ማለቴ...»

«እስታራቂ አይሳደብም የራስሽ ጉዳይ እኔጋ ካለ (ያለ አይመስለኝም) እንነጋገር እንጂ የሰው ጉዳይ ይዞ መጥቶ ነገር ማባበስ፣ ከነፀብራቅ ጋር እንድንቆራረጥ የፈለግሽ ያስመስልብሻል። ያንቺ ሥራ የነገርኩሽን ማድረስ...»

«ምን ላድርስ?» የአህያ ነገር!

«አልፈልግም»

«ማን ፈልግ አለህ? ታረቅ ነው እንጂ»

«ያው ነው፣ አልታረቅም። ይሄንን ወስደሽ ንገሪ ያንቺ ሥራ ይሄ ነው።»

«ይሄማ ያንተ ስራ ነው» አቃጣሪ ስትለኝ እንደሆን ገባኝ

«እስታራቂ አይሳደብም»

«እንዴ? እንዴት ያለ ጉድ ነው» ሄደች

የእህቶቼ ወንድም ነኝ። ሴት ዝም ስትል ልቧን፣ ስትናገር ነፍሷን አነባለሁ። የሴትን ጠመዝማዛ አፈጣጠር ያለመሪ ተመላልሼበታለሁ። ያለ ኮምፓስ ቀዝፌበታለሁ። ገላዋን ታብዬበታለሁ። ወደንባቤ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

"…All he could see now was a white patch where marthe's face was, it's the same as when we make love he realized…."

አንድ ሌላ የአህያ እና በቅሎ ቤተሰብ አባል ፊቴ መጥታ ቆመች፡፡ ንባቡን እደግመዋለሁ፡፡ ገፅ 25 መሆኑን ልብ አልኩ፡፡

‹‹ምን ነበር?››

‹‹ነሀብሬትን እንድትታረቃት…››

‹‹የቅድሟም ስትጀምር ነፀብሬትን ታረት አለችና ስትጨርስ እሷን ትተህ ለእኔ ይቅርታ አድርግልኝ ብላ ደመደመች፡፡ ወንድ የመነካጠት ባህል አዳብሬችኋል ልበል?›› ፊቷ ነጭ መጎናፀፊያ መሰለ፡፡ White patch, White Patch…

ዘወር ብላ በፊት የመጣችውን ጠራቻት፡፡ ‹‹ቢመኙ!›› ስትመጣ ‹‹ለእኔ ይቅርታ አድርግልኝ ብለሽዋል እንዴ?››

ሌላ White patch…

‹‹ብለሽዋል?››

‹‹አላልሺኝም?›› አፋጠጥኳት፤ ቢመኙ ይሄን ሥም የት ነው የማውቀው?

‹‹ይቅርታ ጠይቂኝ ስትለኝ…››

እኔ የለበጣ ሳቅሁ፡፡ ሁለተኛዋ እስታራቂ ሙኝች ‹‹ወይኔ! እንዴ? ምንድነው?…›› ሄደች፡፡ የመጀመሪያዋ ቆማ ድርቅ ባለ ስሜት ታየኛለች፡፡ 'it's the same as when we make love' I realized!!! ወደ ንባብ፡፡ ዕሁፍ ውስጥ አድፍጨ ቆይቼ እግራቸው ከገዳማዊት ካፌ እንደወጣ ኮቴቱን ሸከፌ ተከተልኩ፡፡ ወደ አምስተኛ በር፡፡ አድግ ወ በቅል ምን ብለው መልዕክታቸውን ያደርሱ ይሆን? ከሴት ጋር እውርቶ ለመግባባት የጦርነት ዕቅድ ያስፈልጋል፡፡ ሊያጠቁ ሲመጡ መጥፋት፣ ካልሆነም ድልድይ አፍርሶ ማዶ ለማዶ መተያየት፡፡ ስታጠቅ ደግሞ ሽምቅ እንጂ ሴትን በአጠቃላይ ጦርነት ገጥሞ ያሸነፈ ወንድ የለም፡፡ ፊት ለፊት ልታጠቃ ከሄድክ መሰናከሉ ብዙ ነው፡፡ እግር ጠብቆ የሚፈነዳ፣ እግር ጠብቆ የሚይዝ ወጥመድ፣ ጊዜ ጠብቆ የሚፈነዳ…

…ሙትና ቁስለኛ፤ እንደጠናጋሻው፡፡ የገዛ ምርጫህ ያዋቀረው የሚመስል ጠንካራ እስር ቤት ውስጥ ይከቱሃል፡፡ እንደ ፈረንሳዊው ፈላስፋ እንደ ሳርት "We are condemned to be free." እያልክ ትኖራለህ፤

ከየት ተነስቼ የት እንደረስኩ ጠፋኝ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

. . .

«እሪሪሪሪሪ... ልጄ፣ ልጄ!»

ከእኔ ተቆርጦ ተንከራታች የሆነ ጩኸቱን ለመጀመሪያ ጊዜ የሰማሁት መሰለኝ። በደረቅ ሌሊት በጫት ንውዘት ውስጥ መዓፍና ማንበብ ተስኖኝ ስመተኛት ስመኘ እሪታውን ሰማሁ።

«ኡኡኡኡ... ልጄን!»

ተደገመ። ሁለተኛውን እንደመጀመሪያው አልተጠራጠርኩም። እሰሱ እሪታዬ፣ በዝቶ ተባዝቶ ተጠናዋች የምድር ጋኔን ይሆን ይሆናል። ሌሊት ሌሊት የተኛን እያስደነገጠ መስማመኛ የመስዋዕት እርድ ይቀበል ይሆናል።

እናቱ የማይሸነገር ደጃፌን በርግዳ ቆመች፣ እንቅልፍ ጠብቶ ያልጠገበ ፊቷ እንዳበጠ ሳብ ቸፈፈፍ ብሎብታል።

«ምንድነው? የምን ጩኸት ነው?»

«እዚህ ነው?»

«ኧረ ውጭ ነው»

«የእኔ ነው?»

«ኧረ የሴት ነው።» ጆሮዋን ጣል አድርጋ ስታዳምጥ ቆይታ «ምነው ልጄ ልብህን ምን ወሰደው? በደረቅ ሌሊት ደጃፉን ሳትሸነገር የምትተኛ? በል ተነሳ! በስመአብ እቴ! ምን ጉድ ነው? እኛ ምን እናድርግ? እኛ ልጅ አልሞተብንም? ችለነው ነው እንጂ...» ቆሌዋን እየተቆጣች ሄደች።

ተነስቼ በሩን ከውስጥ ቀረቀርኩ። ፍርሃት፣ ፍርሃት አለኝ? የገዛ ጩኸቱ ከእኔ የድምጽ አብራክ ተፈጥሮ እኔው ላይ በማንባረቁ ልፈራ? እናቴ ከአብራኳ ተፈጥሬ አይኔ ሲወጋት መግቢያ ታጣ አልነበረምን? እናስ? ይሄ በእኔ ላይ ቢሆን ይደንቃል?...

...ጠዋት ደጃፌ ተቆርቁሮ ስከፍት ግራ ተጋብቼ ነበር። ልማድ ሁለተኛ ተፈጥሮ ይሁን እንጂ ቀደምቱን ተፈጥሮ ማጥፋቱ እሙን ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ጠናጋሻው መንፈስ መስሎ በሬ ላይ ቆሟል። ፈራሁት እንዴ? ቆሌ፣ ጂኒ፣ አድባር፣ ዛር፣ ጨሌ፣ አዶከበሬ...የእውነቱ ተጋሪ ሆነው አብረውኝ ይኖሩ የለም? ስለምን ጠናጋሻው መንፈስ ስለመሰለ አስፈራኝ?...

...አይኖቹ ከረዋል። ዳርዳራቸው ጠቋሮ የመከረሪቸው ማጠናቀሪያ ሆኗል። ጉንጮቹ እንደ አልበርት ካሙ ጎድጉደው ከንፈሩ ላይ ሲቋጭ ጥቂት የቀረው ሲጃራ ይዟል። ያጨስ ነበር? እንደመንፈስ እግሩን ሳያነሳ እየተመመ አልጋው ላይ ተቀመጠ። ተሳስቼ በሩን ከውስጥ ቀርቅሬ መልሼ ከፈትኩት ሰውነቱ ስላለቀ ጉልበቱ በሱሪው ላይ ሾሎ ይታያል።

‹‹ሌባ የሆንኩ እየመሰለኝ ነው።›› አለ። በከንፈሩ የያዛትን ቁራጭ ወደመሬት ጥሎ።

‹‹መንፈስ የሆንክ ቢመስልህ ትክክል ነበር›› ስል አሰብኩ። በፊት ጠናጋሻው ሲናገር ሲያስብ ገና ከውስጤ የሚቁነጠነጥ አንዳች ነገር ሲያቆበቁብ ይሰማኝ አልነበር? ዛሬ ስለምን መንፈሴ መርዶ ጠባቂ ሆኖ አፈግፍግ፣ አፈግፍግ አለኝ?

‹‹ስርቆህ ማንበብ፣ ስርቆ ከመብላት በምን ይለያል? ጥሩ ህግ ፍትሃዊ ሆነ አልሆነ የሞራል ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። የተጫነብህ ህግ አግባብነት ከሌለው እዚያው ለማስለወጥ መሞከር እንጂ ከተደነገገብህ በኋላ ተደብቆ መሸፈጥ ከህሊና ተጠያቂነት አያተርፍም። ጥሩ፣ ከሚስቱ ተደብቄ ማንበቤና ቤት ስገባ ያላነበብኩ መምሰሌ እየቆረቆረኝ ነው። ሌባ! ሌባ! ሌባ! የሚል ቃል ከውስጤ ወደእኔ ይወነጨፋል። እራሴን ለማክበር እየተቸገርኩ ነው።›› ከአልጋው ላይ ተንሸራቶ ቁራጯን እረገጠ።

‹‹ይቅርታ አድርግልኝና እውጉስቲን የትኛውም ህግ ከሥነ-ምግባር ጋር ተጣጥሞ መደንገግ እንዳለበት ያስረዳል። ስነ ምግባርን ከግምት ያልከተተ ህግ አካላችንን እንጂ ህሊናችንንና መልካም ፈቃዳችንን ለመግዛት ኃይል የለውም ይላል።››

አንድ መምህር እንደ ጠንቋይ ለራሱ የማያውቅ ይሆን ይሆን እንዴ?

‹‹ትክክል ነው! ጥሩ! ሄነሪ ቶሪዮ ደግሞ ፍትሃዊነት ለሌለው ህግ አንድ ህሊና ያለው ሰው መገዛት የለበትም ይላል። ጥሩ! ይሄ ሁሉ ግን የፍልስፍና መከራከሪያ እንጂ ህይወት ውስጥ ቅንጣት ቦታ የለውም። ቦታ ያለው አስተዳደጌ፣ አኗኗሬና ቀድሞ ስፍራ ይዞ የተደላደለው ባህላዊ የህይወት መመሪያዬ ነው።››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እኔኮ ብዙ ሰዋዊ ችግሮቼን ወደ መወያያ ሀሳብነት ቀይሬ ነው የማቀርባቸው:: የፍልስፍና መከራከሪያዎችን እንጂ ችግሮቼን አልተወያየሁባቸውም ማለት ነው? እየሸሸሁ ነው የኖርኩት?

ጠናጋሸው የለበጣ ሳቅ አሳይቶ ማልጎምጎም በመሰለ መንገድ መናገር ጀመር:: ፍራሹ ላይ ተቀምጬ ጆሮዬን አቆበቆብኩ::

«ቲዮዶሪክ የተባለው የሮማ ንጉስ አንድ ፈላስፋ ወዳጅ ነበረው:: ቦኢቲየስ የሚባል:: ስልጣን ቢሰጠውም ቆይቶ በምሁራን ላይ በተለይ በፈላስፎች ላይ ፍርሃት እያደረበት መጣ:: ስለዚህ ቦኢቲየስን ሴራ በመጎንጎን ከሶ አሰረው:: ክሱ ሞት የሚያስፈርድ እንደሆነ ይታወቃል፤ የማይታወቀው እንዴት አይነት አገዳደል እንደሚፈፀምበት ነው:: ይሁንና ቦኢቲየስ መሞቻው እንደተቃረበ ሲያውቅ አንድ የፍልስፍና መጽሐፍ ማዘጋጀት ጀመረ:: የሱ ችግር ሞቱ እና አሟሟቱ ሳይሆን መጽሐፉን ሳይጨርስ እንዳይሞት ነበር:: ጨረሰ De consolatone Philosophiae የሚገርም ጥበብ የነበረው ስራ ሆነ:: የሶቅራጥስን የመጨረሻ ንግግር የሚስተካከል::»

በረጅሙ ተነፈስና ኪሱን ፈተሸ ሲጋራ ለማጨስ ፈልጎ እንደሆነ ገባኝ:: አጣ:: በረጅሙ ተንፍሶ ንግግሩን ቀጠለ::

«ቲዎዶሪክ የፈራው ፍልስፍናና ፈላስፎችን ከሆነ ስለምን ቦኢቲየስ እርስ ቤት ሆኖ እንዲፅፍና እንዲያነብ ፈቀደለት? አይታወቅም:: ያም ሆነ ይህ ጨካኝነት የበዛበት የሞት ፍርድ ቦኢቲየስ ላይ ተፈፀመበት:: ጭንቅላቱን በገመድ ድር አስረው እያጠበቁ እያጠበቁ፣ እያጠበቁ ከፍተኛ ስቃይ ለቀቁበት:: ከህመሙ መከፋት የተነሳ አይኖቹ ታወሩና ሞተ:: ይሄን እንደ ጭካኔ እንዳላየው የሚያደርገኝ ቦኢቲየስ እስር ቤት ሆኖ እንዲፅፍና እንዲያነብ መፈቀዱ ነው:: አንድን ሰው ነፃ አድርጎ እንዳያነብና እንዳይፅፍ ከመከልከል እስሮ መፍቀድ፣ ብሎም በጭካኔ መግደል ምን ያህል የርህራሄ ስራ መሰለህ? ጥፋ!»

«ለምን አትፈታትም?»

«ምርጫዬ ያስከተለው ስህተት ትዳርን በማፍረስ ብቻ የሚስተካከል አይመስለኝም:: ምርጫ ውስጥ የገባሁበት መንገድና የመረጥኩበት አግባብ ይሄን ፍርድ በፀጋ እንድቀበል ግድ ይለኛል:: I deserve!» ኪሱን መፈተሹን ረስቶ ዳግም መፈተሽ ጀመረ:: "I deserve!! It is just!!" ደረቱን በጨበጠው እጁ ደቃ!

ገዞም

«እርሳው!!»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ዝም

የተለየ ነገር ለማውራት ያህል ስሜቱን ዘና አድርጎ «ትናንት ግቢ ሰው ቀጥረህ ነበር?» አለኝ።

«ኧ-ይ፣ ማንንም አልቀጠርኩም»

«አንድ ቀን እዚህ ስትመጣ የነበረችውን ልጅ እምስተኛ በርጋ አይቻት ነው።»

«ሰገነትን?»

«ሰገነት ነው ስሟ? አሷን! አንተን ለማፈላለግ መስሉኝ ነበር፣ ከሆኑ ተማሪዎች ጋር እያወራች ቆይታ አብረዋት ሄዱ።»

እነ ነፀብራቅ እንደሆኑ አልተጠራጠርኩም። ግንባር ምስረታ ላይ ይሆኑ? ምን አፈላለጋቸው? አጠቃላይ ጦርነት ሊከፍቱብኝ ይሆን? ሰገነት መፍዘዟ ለቋት ወደ ተዋጊነት ተሸጋገረች? የግንባሩ ሊቀመንበር ማን ይሆን?»

"Withdrawal መሙላት እፈልግ ነበር» አልኩት፡-

«ለምን? ማለቴ ብትጨርስ...»

«ቋጭ ብዬ ያለጣጣ ማንበብ ፈልጌ ነው። መመላለስ ሰለቸኝ።» ቁስሉን እንደነካሁት ካተነፋፈሱ ኃይል ተረዳሁ። እሱ ያጣውን እኔ ስንበሸበሽበት ምን ሊሰማው እንደሚል ግልጽ ነው።

«ጥሩ፣ ላቲኖች እና ግሪኮች ‹ስኮላ› (Schola) የሚሉት አንደኛ ዘመናዊ ትምህርትን አይደለም እሉ። የጥሞና ጊዜን ነው። ከየትኛውም ግዴታ ነፃ የወጣ ጊዜ (Leisure)ን መሆኑ ነው በተለይ ግሪኮች የሥራ አላማ ነፃ ጊዜን ማስገኘት ነው ብለው ያምኑ ነበር። እኛ ደግሞ በመንግሥት የተፈቀደን የእረፍት ጊዜ በገንዘብ እንለውጣለን። «ጥሩ! ዛሬ እኔም ያንን ነፃ የወጣ ጊዜ ልጠቀምበት። ቁርሳችንን ጠቀም አድርገን በልተን ጫት እንጀምር።»

እንደከዚህ በፊቱ ባይሆንም በመጠኑ ደስ አለኝ። ተፍ፣ ተፍ ማለት ጀመርኩ። እቴቱ ጠቀም ያለ ቁርስ እንድትሰራ ገንዘብ ሰጧት። ጫት ለማምጣት ተዘጋጀሁ። በፀጥታ የፈዘዘውንና በብርድ የደነዘዘውን ጡረታ ድልድይ፣ በእናቶች ድብቅ አይን ታጅቤ፣ በተዘጋ ልሳን ተሰድቤ ማለፍ ቢከብድም።

አባቴ መሬትን «ጦር እምጭ» እያለ እንደ አፄ ልብለድንግል ለመግረፍ ስለ ብልቷን ፍለጋ ሳይሄድ አልቀረም። ፓትሪስ ሉሙምባ በካፖርቱ እንደተሰቀለ ይወዛወዛል። ብረታ ብረቶቹ በእሮጌ ትሪይ ላይ እንደተሰጡ ነው - ጡረታ ድልድይ ውስጥ ሙቀትና ጨኸት ያለ ይመስል....»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ሃያ

## የኀልቀተ ዓለም ነገር

ለገነት መጣች፤ ግንባሩን ወክላ ይሆን? እራሷን ወክላ ይሆን? እኔን ወክላ ይሆን?... አይታወቅም፡፡ እናቴን አልተጣራችም ሙሉስ ብላ አልጋ ላይ ተቀመጠች፡፡ ፊቷ መፍዘዝ እንዳረበበበት ነው፡፡ እረጅም ቀሚስ በነጠላ ጫማ አድርጋለች፡፡ ለአንድ ሳምንት ያህል ከቤት ስላልወጣሁ ያፈነችው ናፍቆት አቅሟን ነስቷት ሳይሆን አይቀርም፡፡ በሻርፕ የጠቀለለች እራሷን ቀና እስከታደርግ ጠበኳት - አላለችም፡፡

‹‹ልሄድ ነው›› አለችኝ፡፡

‹‹አሁን መጥተሽ?›› አልኳት፡፡

‹‹አ-ይ ወደሌላ አገር››

ሳላባርራት ትሄዳለች የሚል ግምት አልነበረኝም፡፡ አላሳዘነችኝም፣ እንደውም አንዳች ከባድ ጥላ ከትከሻዬ ላይ ሲገፈፍልኝ ታወቀኝ፡፡ ቅልልልልል...

‹‹የፍቅር ልምድ ልፃፍልሽ?››

ቀና ብላ አየችኝ፡፡ ዓይኖቿ ለጥላቻ የተነቃቁ መሰለኝ፡፡ ሆን ብዬ ቀጠልኩት...

‹‹ወይዘሪት ለገነት ሺፈራሁ ለተከታታይ ሦስት ዓመታት በታማኝነት (ማረጋገጫ ባይኖርም) እና በዕናት በፍቅር ሲያገለግሉን...››

‹‹አይበቃም? ታለ? ዛሬ እንኳን...››

‹‹ምን? ልቅበጥ ነው? ደስ አሰኘኝ ነው?... ወይስ ምን?››

ዝም!

‹‹በድለኸኛል፤ ታውቃለህ ታለ? ግን አሁንም እወድሃለሁ፡፡››

‹ለትጉል መቀደስ የተኛ ሰይጣን ለመቀስቀስ› ዝም አልኩ፡፡

‹‹ለነገሩ አንተን ከማጣት ብዬ ነው የተበደልኩት››

‹‹...እውቄ የፈዘዝኩት›› እንደማለት ሆኖ ተሰማኝ፡፡ እብደቷን፣ የበላይነቷን፣ ያልተገደበ መብቷን እንደ አደገኛ ጦር መሳሪያ ማስፈታቴ ነው በደሉ? መቼ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እንደሚፈነዳ የማይታወቅ ‹የሰዓት ቦምብ› መሰል ንዴት ይዛ እንዴት አብሬአት መሆን እችል ነበር? ማገናዘቢያውን የተነጠቀ ይሉኝታ ቢስ ናፍቆቷን እያፈርኩበት እስከመቼ እዘልቅ ነበር?...

‹‹አንተ ጎን ልምጣ?››

እንደ ፍዘቱ ዘመን እስክትጠየቅ መጠበቅ አላስፈለጋትም።

ዝም አልኳት

ዝም አለች።

ዝም ስትል ጠራኂት ‹‹ነይ ቁጭ በይ እዚህ›› አልኳት። የማነበውን ግዙፍ መጽሐፍ አጠፍኩት። "Guns, Germs, and steel" ይላል። የሰው ልጅ ማህበራዊ መስተጋብር ውስጥ ምግብ፣ አካባቢ የአየር ሁኔታ፣ ጠበንጃ ጀርም እና ብረት ያላቸውን አስተዋፅኦ የሚተነትን መጽሐፍ ነው። ለእኔ ጠበንጃና ብረት ያለው ‹‹ፍቅር›› ላይ ነው። ትዳር ከተመሰረተ የቀረው ጀርም ተግባር ላይ ይውላል፤ መጽሐፉ ውስጥ በከብት ተዋፅዖ ላይ ጀርም ያለው አስተዋፅኦው ቀጥተኛ ተዕፅኖ እንደታየው በትዳር ውስጥም ያለው ይተነተናል። አንስቼ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩት። ለገነት ያልሰማች መስላ ዝም። ጠበኩ፤ የለም። ሰውነቷ ውስጥ ያለው ኃይል ለመነሳት እንዳያስችል ሆኖ ተጠፍጥፎ አልቋል፤ ወይም ያ ፊቷ ላይ አድፍጦ እመለከተው የነበረ የበቀል ስሜት መውጣት ጀምሯል። ስጋት...

‹‹አልሰማሽም?››

ቀስ ብላ ተነሳች። ለእሷ ይሄ በየአመቱ ክብረ በዓል የሚዘጋጅለት ድል ነው። ለኔ ሽንፈት? አጠገቤ ተቀመጠች። አንድ እግሯን አጥፋ አንዱን ዘረጋችው። ሰፊው ቀሚሷ የአሞራ ክንፍ ቤት ጣሪያ መሰለ። አቀርቅራለች። ፊቷ በጨርቅ እጥፋቶች ተከቦ ዓይኗ፣ አፍንጫዋ እና ከንፈሮቿ ብቻ ይታያሉ። እጥፋቱን ገልጬ የጋለ ጉንጯን ሳምኳት።

‹‹ተው›› አለችኝ ያለልማዷ።

ስትሸሽኝ፤ አይደለም፤ የሸሸችኝ መሰለኝ። በፊትም መንፈስ ነበር የሚጠጋው? ታዲያ አካሏ ሳይርቀኝ እንዴት የሸሸችኝ መሰለኝ? መንፈሷን በመንፈሴ መጠጋት አሰኘኝ።

‹‹ተው›› ብላኝ አታውቅም።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ያልሸሸኙ ገላዋን ለመንካት ፈራሁ። እንዴት? ያበደ የምስክር ወረቀት የሚያስፈልጋት አገልጋዬ አልነበረች? እና? እጄን በወገቧ በኩል ሰደድኩት። ከገላዋ ቀድሞ ጥቅል ወረቀት የቀሚሷ ወገብ ውስጥ ተወሽቆ እጄን ተከላከለው። እሷና ሲፈን የቀሚሳቸው ወገብ ውስጥ ዕቃ መወሸቅ ይወዳሉ።

‹‹ምንድነው?››

‹‹ላንተ የመጣ ደብዳቤ ነው።››

የስምረት መንፈስ የረበበበት ደብዳቤ፤ ምናልባትም መሄዷ ስለሆነ ያለሀፍረት የምትሳደብበትና ገመና የመሰላትን የምትጠቅስበት። ወደፊት ጠጋ ብዬ በግድግዳው በኩል ላስተኛት ሞከርኩ።

‹‹ታሰ? ተው? ታሰ? ታሰ? ተው? ተው...››

አፏ እንጂ ገላዋ አልተከላከለኝም። አልፈለገችም እንጻልል እንኳን አከላቷ አልተቆጣም። ልስልስ እንዳለች ልስልስ ባለ ድምፅ፦

‹‹ተው? ተው? የእስከዛሬው ምን ጠቀመህ? ተው በእናትህ?...››

ስስ ቀሚሷን ገልቤ ከነሱሪዬ ጭኗ ውስጥ ገባሁ። በዚህ ሰዓት ‹‹ተው›› ተቃራኒ ፍቺ አለው። ምናልባት ‹‹ብላ›› ቢባል ተው ማለት ሊሆን ይችላል።

የፊቷን ጥምጥም ፈታሁ። አቤት እርዝመቱ! የረድ ሠርዌን አባት የሚያገቡ ሴት እንደእኔ ጥምጥም የመፍታት ዕዳ ቢኖርባቸው ኖሮ በአንደኛው እንደምንም አከናውነው በሁለተኛው ‹‹አፋቱኝ›› ይሉ ነበር።

‹‹በሩ አልተዘጋም።››

ተነስቼ ከውስጥ ሸንጉሬው ስመልስ ሁሉንም ነገር እንደነበረ አላገኘሁትም። ያንን አንጀት የሆነ የፊት መክበቢያ ጨርቅ ጠምጥማ ጨርሳለች። ሐሞት ቢያፈስም እንደግሪኩ አምላክ እንደ ሲሲፈስ የተንከባለለውን ድንጋይ ዳግም ለመግፋት ተነሳሳሁ። ዕጣ-ፈንታ አይደል?

‹‹ታሰ? ተው? ተው?...›› ታጀብኩ።

‹‹ታሰ?››

‹‹ተው››

‹‹ታሰ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ተው››

‹‹እህ››

‹‹ተው በእናትህ››

‹‹ወይኔ ጉዴ...››

...የመጨረሻ እራት? ሆድ የሚያባባ፣ ባላሰቀ የሚያሰኝ:: እወዳታለሁ እንዴ? የሚጎድለኝ መከልከል ነበር? ወይስ ምንድነው? ፊቷን ለማየት ሞከርኩ፤ ጠመዘዘችብኝ:: ፊቷ አይያዝም እየተረሳ አስቸግሮኛል:: ለገነትን ሳስብ ሲፈን እየመጣች ትደቀናለች::

‹‹በሩን ክፈተው::››

ከፍቼ እስከመለስ እግሮቿን አስኮርፋ ተቀምጣ ፊቷን በእጥፋት እየከበበች ቆየችኝ:: አጠገቧ ደብዳቤው ተቀምጧል:: ስምረትን መሆንና ባሏን ማመስ፣ ማተራመስ ያቃታት ሴት ሮሮ መሆን አለበት፤ ካልሆነ ሌላ ምን? እኔ ስቀመጥ እሷ ተነሳች::

‹‹ልሂድ::››

‹‹መሽቷልኮ::››

‹‹ከዚህ በላይ አምሽቼ አስወጥተኸኝ፣ ውጭ አድሬ አላውቅም?››

ዝም

‹‹በል መልካሙን ሁሉ እንዲገጥምህ እመኝልሃለሁ::››

ምን ማለት ነው?

‹‹በቃ?››

‹‹በቃ!››

‹‹በምንድነው የምንገናኘው? በስልክ? በደብዳቤ?...›› ዝም አለችኝ:: በእጥፋት እስር ቤት ውስጥ ያለ ፊቷ ላይ ምን ተፅፏል? ይሄን በር ካለፈች በኋላ መልኳን እንኳን በአይነ-ህሊናዬ ማምጣት የማልችላት ሴት ጥቂት ፍላጎት ስላሳየሁ ኮርታብኝ፣ ምናልባትም እንደበፊቱ ገንፍላና ተደባድባኝ መለያየት የፈለገች መሰለኝ::



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ምንም ቢሆን...» ትዝብት መሰል ነገር ያሙለቀ ፊቷ ላይ አንገሮበበ። ምን እያለችኝ ነው? ግንባሩ የላከብኝ ሽምቅ ተዋጊ መሆኗ የገባኝ መሰለኝ። በዚህ አጠራጣሪ ባህሪዋ የትኛውን ድክመቴን ለማጥቃት እንደፈለገች ሊገባኝ አልቻለም።

«ቻው» በረጅም ቀሚሷ እግሯ እንደተሸፈነ መሰስ ብላ ወጣች፤ እግሯን ተከትዬ በሩን ከውስጥ ሸጎርኩት። ድንገት ሊለዋወጥ የሚችል ነገር ቢኖርስ? አላውቅም። ደግሞ ቢኖርስ? የሸጎርኩትን በር ከፈትኩ። ወይስ ልቤን ነው የከፈትኩት?.. የማይጨበጥ ግልብጥብጥ ስሜቱ እንኳንም ሰለገነት ለኔም አስጠላኝ። «ጥሩ!»

«ምኑ?» ማፋጠጥ አሰኘኝ እራሴን።

ጠና ያሽው የሴቶች የፍቅር ቅጥ እንደሆነ የነገረኝ ዘዴ ለወንዶችም እንደሚሰራ ተገለፀልኝ። ያፈቀረች ሴት ያላፈቀረች መስላ፣ መቆየት የፈለገችው የቸኮለች መስላ፣ የፈለገችው ያልፈለገች መስላ... ከሆነ ወንድ ጅል ነው እልህ ይጋባል።

በሩን ገፍቼ አጨላለሙን በማየት ሰዓቱን ለማወቅ ጥረት አደረኩ። እኩለ ሌሊት ቢሆን ምን ላደርግ?...

...በራሴ ማላገጡን ትቼ ገሰፅኩ። ወደ ፍራሼ ሄጄ ተቀመጥኩ። መንፈሴ እንዳቆበቆበ ነው። አሁን ካሁን በሩ ተከፍቶ...

...በግራ አይኔ እይታ፤ ጥግ ላይ ነጭ ነገር ይታየኛል። ዞሬ አየሁት፤ ደብዳቤው እንደተንጋለለ እኔን ይጠብቃል። አነሳሁት፤ ማሸጊያው ክፍት ነው። የታሸገው ተገልጦ እንጂ ሳይታሸግ ተረስቶ እንዳልሆነ ያስታውቃል። «ምን ብላ የስንብት ዕፋልኝ ይሆን?»

• • •

«ሲፈን ነኝ» ይላል ደብዳቤው ሲጀመር። ለገነት «ሲፈን ነሽ» ስለምላት መሰለኝ «ልክ የጥላሁንን ዘፈን ደግመው እንደሚጫወቱት ድምጻውያን አንቺነትሽ ትዝታ የለውም። የተኳሽት ናት ባንቺ የምትጎላው። ታሪክ አልባ...» አይ እኔ?

«ሲፈን ነኝ፤ በእኔ ተፀፅተህ ከቤትህ የማትወጣ፣ መናኒ መሆንህን ስምቼ ካንተ ያገኘሁት መፅናኛ አድርጌ ቆጥሬው ነበር። መከራን ለመግፋት እንደምክንያት እጠቀምበትም ነበር። ብኩን ለመሆን ቆርጠህ ትምህርትህን



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ስታቋርጥ እሱስ ቢሆን ከዚህ በላይ ምን ያድርግ? እያልኩ እራሴን አፅናና ነበር።

«ጠልቼህ አይደለም! ለሱማ መች ታደልኩ?...»

(ምንድነው? ሲፈን በለገነት በኩል?...)

«ታለ? አሁንም እወድሃለሁ። አንተም እንደምትወደኝ ያወኩ ቢመስለኝም። እርግጠኝነት ግን ይጎድለኛል። እስኪ ለራስህ ታማኝ ሆነህ ከአፍህ አውጣው ትወደኛለህ? ተገኜ ይሙት! ያንተ ምላሽ ምን ይሁን ምን እወድሃለሁ።»

(እስካሁን ለገነት እንደጻፈችው እየጠረጠርኩ የሆነ ጠቋሚ ነገር እፈልግ ነበር። ግን ሲፈን የድብት አባቷን ሥም ስትጠቅስ ጥርጣሬዬ ተገፎ ከነገመናዬ አደባባይ ላይ የተገኘሁ መሰለኝ።)

«እኔ እንዲህ ስወድህ በአግባቡ ላላወካት ሴት ለምን አንጓጠጥከኝ?...ስወድህ! ስወድህ! ስወድህ!... እንዴት ነው የምወድህ? ሲያስፈራ አለች› አልኩ። ብያለሁ፤ ግን እኔና አንተ ብቻ ስለሆንን፣ ባንተ በምወድህ ተማምኜ፣ መውደዱ ስላላስቻለኝ፣ ተገድጄ አልኩ። ታዲያ ይሄ ለሌላ ሰው፣ ያውም ለሴት ይነገራል? አይ ታለ? ምን እንደተሰማኝ ታውቃለህ። የተደበኩበት ድረስ መጥተው ሲያጠቁኝ ሌላ ምን ሊሰማኝ ይችላል?»

(አይኔን ጨፈንኩ፤ ሲፈንን እዚህ ደብዳቤ ውስጥ ፈለኩ። እስካሁን የአባቷን ሥም ከመጥቀሷ ውጭ የለችም። ደብዳቤውን አስጠግቼ አሽተትኩት ማግሁት...አእምሮዬ ቀጥታ የናዝሬት ራስ ገዝ አደረሰኝ። ጃኬቴ፣ አይናቸው፣ ጫት፣ ለቀብር የተዘጋጀችው ጉድጓድ መኝታ ክፍል... ደንግጬ ከአፍንጫዬ ላይ አሸሸሁት። ረቂቅ የጠናጋሻውን ቆብ፣ ስምረት እጄን... አላሸተቱም? እኔ በዚህ ድርጊታቸው አልላትሁም? ማነፍነፍ የውሻ ነው አላልኩም?... የሲፈን ደብዳቤ እንደሆነ እርግጠኛ ሆኜ ማንበቤን ቀጠልኩ።

«ላንተ ከሆንኩት የተናገርከው እምንቱን ነው። የማታውቀውን ላንተ የሆንኩትን ስማ፦

«...ሰባት ዓመት ሙሉ ልጅህ እኔ እናቷን አታውቀኝም። ይገርማል እንዴ? ያንተ እኔን አለማወቅ ነው ሥጋዬን ነክሶ፣ እንጎቁሎ፣ አብቦና አፍርቶ ልጅ የሆነው። ትግዝ ይልሃል እዛች ትንሽ ቤት ውስጥ የሚቅሙት ፈላስፎች ‹ሁልጊዜም ተፈጥሮ ግብረመልስ አላት› ይሉ ነበር። ልብ በል! ሁልጊዜም!!

«አንተን ባላፈቅር ኖሮ፣ ከህደትህ እጅ እግር የሌለው ልጅ ሆኖ ሲመጣ መካድ ይቻለኝ ነበር። ድብቅ ፍቅሬን በድብቅ ባላከናውን ኖሮ ልጄን ሀሖይ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አይናፍቃትም ነበር፤ የጓዳ ፍቅር ከንውኑ ግብረ መልሱ የጓዳ ልጅ ማስታመም ሆኖ መጣ።

«ይገርምሀል፣ የቹቹ እናት ትዝ ትልሃለች? ልጇን ለአደባባይ ሀሀይ አመቻችታ ደጃፏ ላይ ማስተመጧ? የፍቅሯ ግብረ መልስ ነው። ልጇን ለአንተ ጥላ መከብለሏስ? ባሏ-ቀረች የመካዷ ተፈጥሯዊ ግብረ መልስ ነው። ተፈጥሮ የራሷ ግብረ መልስ አላት። የአንዱ መጨረሻ የሌላው ጅማሬ መሆኑ የግድ፣ ግድ፣ ግድ... አለው።

«ያቺ ያቺ ሌሊት «አርግግርለሁ» ስልህ የከዳኸኝ፣ ልቦናህ እያወቀ ያባረርከኝ ለዚያም ተፈጥሮ ግብረመልስ አላት። በድብቅ የዘራኸውን በግሃድ ትቀበላለህ። ልጅህን ለእናትህ ለአንጓች አምጥቼ እሰጥልሃለሁ። ይሄ ነው ተፈጥሯዊው ግብረ መልስ። እንጓች እንደቹቹ የልጅ ልጇን ባሌ ወስዳ ለሸኸናው ሁሴን ትሰጣት እንደሆን እናያለን። ይሄ ደሞ የእሷ ተፈጥሯዊ ግብረ መልስ ይሆናል። በአሳቻ ሰዓት ልጅህን እስክጥልልህ ድረስ ቻው!!

• • •

ለሦስት ሌሊትና መዐልት. . .

ቀን አንድ

ለስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስተኛ ጊዜ አነበብኩት። እያንዳንዱ ንባብ የራሱን ሽንትር ልቤ ላይ እንዲያሳርፍ ፈቀድኩ። ገራፊነት ለሰው ልጅ ሁሉ የተሰጠ «ኃጢያት» እንደሆነ አየሁ። ተገራፊነት ለእያንዳንዱ ሰው የምትቀርብ የጽድቅ ዕጥ ናት። «ይቺ ዕጥ ከእኔ ትለፍ» እስካላልን ድረስ የጽድቅ በረከት ደጃፋችንን ትቆረቁራለች። ብንከፍትላትም ከእኛ ጋር ትበላለች።

የሾህ አክሊሏ አይቆረቁርም። የጥም አትርቦቷ በሰፍነግ ነው ግን አይሰነፍጥም። ጦሯ በጎናችን ውስጥ ‹ገባ-ወጣ› እንደሚል ለማዳ ነው። የጠፋ አይን ይፈወስ ዘንድ ደምና ውሃ ይፈልቀናል። ከአደባባይ አውጥተው አማራት ገምበኛ ጠርተሩ እያሰደቡ ጽሕማችንን ሰማኒያ ጊዜ ለነጩን እናዝናለን። «ስቅሉ ስቅሉ ስቅሉ» ሳሉት እንንሳፈፋለን። «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ይሁን» ሳሉት «አይሁን» ኦንላለን። የከሰሱን እንዳይከሰሱ እንሰጋለን። ተገራፊ በንዴት ገራፊውን ባሰበ ጊዜ ወደ ገራፊነት ተቀላቅሏል። የተገራፊዎች አለቃ «የመጣባችሁን መከራ ሁሉ በእኮቴት (በምስጋና) ተቀበሉት እንጂ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አታማሩት›› ያለው እርሱ ነው። ተጠራጣሪዎች በጎናችን ቁስል ጣታቸውን ከተተው እስኪያረጋግጡ ድረስ እንጠብቃለን። የመጻፋችን ሽንቁር እስከ ትንሳኤ አብሮን የሚጓዝ ህያው ምስክራችን ይሆናል።

## ቀን ሁለት

በሲፈን ቃላት ስጋዬ የቆሰለው ሶስት መቶ ስድሳ ስድስት ጊዜ፤ ደሜ የነጠበው ሰባ ስድስት ነው። የቀረው ግን ያበጠው፣ የበለዘው እንደ ሰማይ ኮከብ፣ እንደምድር አሸዋ ነው። አይቆጠርም። እኔ ስለሲፈን ደብዳቤ ስል የተቀበልኩት መከራ ሺውን አንድ እያሉ በአሥራ ሶስት ክፍልም ተዘርዝሮ አያልቅም። የእህቶቼ ወንድም አይደለሁም። ሴት ዝም ስትል ልቧን፣ ስትናገር ነፍሷን አላነብም። የሴትን ጠመዝማዛ አፈጣጠር አልተመላለስኩም። ያለኮምፓስ የቀዘፍኩ ከመሰለኝ እርሱ ትዝታ ብቻ ነው። ገላዋን የታበይኩበት የመሰለኝ ተላላነት ስለሚያጠቃኝ ነበር። ሴትጋ ገመና ያለው ከሴት ጋ ልፊያ መግጠም አልነበረበትም።

ለፍቅር በመጣች አንዲት ሴት ሌሎቹን ሴቶች መለካት ወንድን ብቻ የሚያጠቃ የድድብና በሽታ ነው። ደደብ ነበርኩ። በድድብና ላይ መታበይ ታክሎ አንገላቶኛል።

## ቀን ሦስት

የታየ ራዕይ ገረብኩ፤ ሰባት ሴቶችን አየሁ። የእግዚአብሔር ቁጣ በእነርሱ ስለሚፈፀም የኃለኞቹን ሰባት መቅሰፍቶች የያዙት እነርሱ ለወንዶች ታዩ...

(ይሄን ራዕይ አንብቤዋለሁ ወይስ አይቼዋለሁ?)

...ከዚህ በኋላ አየሁ፣ የምስክርም ድንኳን መቅደስ በሰማይ፣ ተከፈተ፣ ሰባቱንም መቅሰፍት የያዙ ሰባቱ ሴቶች ከመታገኝ ቤታቸው ወጡ። ከተልባ እግርም የተሰራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ፤ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ። ከአራቱም እንስሶች አንዱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኖር የእግዚአብሔር ቁጣ የሞላባቸውን ሰባት የወርቅ ዕቃዎች፣ ለሰባቱ ሴቶች ሰጣቸው። ከእግዚአብሔርም ክብርና ከኃይሉ ጢስ ሞላበት። የሰባቱም ሴቶች ሰባቱ መቅሰፍት እስኪፈፀም ድረስ አንድ እንኳ ወደ መታገኛው ቤት ይገባ ዘንድ አልቻለም። ታለ የሚሳደበውን ስድብ ሊታገሉት እንዳይቻል፤ ብልግናው



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የአጥንት ብል እንደሆን፣ ማሰናከያውም በአፍ ሰይፍ ይዋጉት ዘንድ የሚቻል እንደሆን ሁሉ እንግዲህ ፀፀትና ጥርስ ማፋጨት ይሁንበት።

* * *

ለሦስት ሌትና መዐልት በሚማስል አለም ውስጥ የምጨብጠውንና የሚተኮርበትን ማግኘት ሳልችል ቆየሁ። በመጨረሻ አካሌ እስኪደክም ከመብል እና ከድሎት እራሴን ከልክዬ ቆየሁ። እቴቱ የምታመጣልኝን ምግብ በጉጉት እራሴን መቅጫ አደረኩት። የተፈጥሮን መፈታተን ተፈታተንኩ። እንደ ያዕቆብ ካልባረከኝ ለምን ፈጠርከኝ ብዬ ፈተርኩት። ከተፈጠርኩ ለምን ተፈጠርኩ? ከኀደልኩ ለምን ኀደልኩ?... አልኩ። ዕጣ-ፈንታዬ ይህ ከሆነ ስለምን ከመፈጠር ባሻገር ባለ ዘልአለማዊ ጥልቅ ውስጥ እንድቀር አልተደረገም?...

...ደከምኩ፤ ከሦስት ቀን በኋላ እንቅልፍ ሸለብ ሲያደርገኝ ሲፈን ልጇን ታቅፋ ‹‹በምስለ ፍቁር ወልዳ›› ስልት ፊቷ ተደቅና ቀሰቀሰችኝ። ስንት ዓመታት አስቀምጬአት ተኙቱ ይሆን? ሲፈን ላይ የፈፀምኩት መካድ በተፀነሰ ልጅ ውስጥ ገብቶ አወሳከፈ? ያንን ያህል ክህደት ከየት አመጣሁ? ስፈዕመው እንዴት አልታወቀኝም?...

...ሲፈን! ሲፈን! ሲፈን!...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ሃያ አንድ

## የነገር ነገር

«…ሲፈን! …ሲፈን! …ሲፈን!…

ምድር ሳትገነዝ፣ ሰማይ ሳይከፈን

እንደ ቀርነበግእ በውል መቆላለፍ

ምሥለፍቁር ወልዳን መስሎ መተቃቀፍ

አካል ሆኖ መርቀቅ፣ ጥላ ሆኖ መግዘፍ»

የሚል ጉብረዝማሬ በለሆሳስ የሚሰማኝ ይመስለኛል። ጆሮዬ እየረዘመ የሄደ ይመስለኛል። የሰውነቱ የከሸፉ ፀጉሮች ሳይቶሩ ወደ ጆሮነት ተቀይረው ያቆበቆቡ ይመስለኛል። የእናቴ ድምፅ ከፍ ካለ ሲፈን ልጅ ጥላሳት ሄዳ የተወረ ይመስለኛል።

…ጉድ! …ጉድ! …ጉድ!…

ብዙ ጊዜ ቤትህ ውስጥ፣ አንዳንዴ መንደርህ ውስጥ፣ ሌላ ጊዜ ከተማህ ውስጥ፣ አልፎ አልፎ ሀገርህ ውስጥ መገኘት እንደሌለብህ አይሰማህም? የአንተ ዕዳው ገብስ ነው። ሀገርህን መሸሽ-መሰደድ! ጉዱ ዓለም ውስጥ ለአንተ ቦታ እንደሌለ ስትደመድም ነው። መፍትሄው በአንድ ጊዜ ከስደት እራስን ወደማጥፋት ይሸጋገራል። ለእኔ ዓለም ላይ ቦታ የለም፤ ሲልቪያ ፕላት ከማይፈታ ቤተሰባዊ ችግር ውጭ ለእርሷ የሚሆን ቦታ ዓለም ላይ በማጣቷ ነው ጭንቅላቷን ዳቦ መጋገሪያ ውስጥ ከትታ የሞተችው።

ገመና የሚያነፈንፍ ጆሮዬ የእኔን ሲያጣ የረድ ሠርዋን ቅገርት ቃርሞ ይመለሳል። መቼ እንደሚሆን የማይታወቅ ነገር ከመጠበቅ በላይ መባከን የለም። ያደረኩባትን አደረገችብኝ።

ደጃፌ ተቆረቆረ። በግምት ዕኩለ ሌሊት መዳረሻ ነው። ማነው? ልቤ ተፈራገጠ።

«ጌታዬ ነህ?» (መሪጌታ ያሰች መሰለኝ)

ረቂቅ ነች። እንደተልከስካሽ መንፈስ አሳዎ ሰዓት አስወድዷታል። ከፈትኩላት። እንደለገነት ረጅም ቀሚስ ለብሳለች። የቀሚሱ ጫፍ መሬት ለመሬት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እንደተጎተተ ያስታውቃል። እራሷን የጣለች ይመስላል። በጉሯን ለቅስታ በሻርፕ አስራዋለች። ቁመቷ አለቅጥ የረዘመ መሰለኝ።

‹‹ግቢ።››

‹‹ምን ሆንክ?›› ትዝትዝ ብላለች። የሰከረች መስሎኝ ነበር። እንደውም እህል በአፏ የዞረ አይመስልም። ከንፈሯ ጠውልጎ እንደወትሮው ቀለም አልተቀባም።

‹‹ይሄ ሁሉ ለምን?›› አልኩ የተናገርኩ አልመሰለኝም ነበር።

‹‹ለፍቅር›› አለች የቅሬታ ፈገግታ እያሳየችኝ። ‹‹መቼም ለገነት አይሆንም።›› ልትቀልደኝ ሞከረች።

‹‹ግቢ።››

ገባች። መንሳፈፍ የመሰለ እርምጃ አልፋ መዳፍ የማትሞላ ጌጠኛ ቦርሳዋን አልጋ ላይ ወርውራ ተቀመጠች።

‹‹የሆንኩትን ላሳይህ ነው አመጣጤ›› አለች።

‹‹ምን ሆንሽ?››

‹‹እንዳትደነግጥ።››

‹‹እሺ።››

‹‹ኧረ ለወሬም አይመችም፤››

‹‹ምንድነው የሆንሽው?›› እንደቆምኩ ተንከርፍፌ ቀረሁ።

‹‹ዝም ብሎ ገላዬ እየጠፋ ነው። መጀመሪያ ቅዠት ነው የመሰለኝ። የሆነ ብርሃን ከውስጤ እየፈለቀ ገላዬን ያጠፋዋል። ተመልከት›› ረጅሙን ቀሚስ ገለጥ አደረገችው። እግሮቿ ከቁርጭምጭሚቷ በታች የሉም። ያደረገችው ጥልፍልፍ ጫማ ብቻ የወለቀ ያህል ከቀሚሷ ዘርፍ ስር ቁጭ ብሏል።

‹‹ምንድነው? ረቂቅ ምንድነው?››

‹‹ጌታየነህ በምን አውቃለሁ። ተመልከት እግሬ አይታይም እንጂ አለ። ጫማዬን ሳነሳው አይታይህም?›› አነሳችው።

ቅዠት መሆን አለበት። በሲፈን ላይ የዋልኩት ግፍ ቅዠት ለቆብኝ መሆን አለበት።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እስኪ ጨብጪኝ» አልኳት ጨበጠችኝ፡፡

«እጅህ ይሞቃል» አለች፡፡ «ተመልከት ደግሞ ስተኛ ጎኔ አልጋ አልነካም፡፡ በእኔና በአልጋው መካከል ጥቂት ብርሃን አለ፡፡ አየህ? እስኪ እጅህን ክተት? ገላዬ የለም አይደል? የተንሳፈፍኩ ይመስለኛል፡፡»

«ምንድነው ረቂቅ?» የማደርገው ባጣ እንገባዬ መፍሰስ ጀመረ፡፡

«እንጃ! ግን አያመኝም፡፡ እንደውም ቅልል የሚል፣ ረፍት የሚሰጥ ነገር አለው፡፡ ስለታከትኩ አብዝቼ ፀለይኩ፣ እሱ ይሆን?»

አልጋው አጠገብ ተንበርክኬ በረቂቅ ገላ እና በተነጠፈው በብርድ ልብስ መካከል ባለው ክፍተት እጦለኩ፡፡ እንዳች የብርሃን ጭጋድ የመሰለ ነገር በመካከል ቢኖርም ግድግዳውን ለማየት አላስቸገረኝም፡፡

«በህልሜ ነው?»

«እኔ ልጠይቅህ እንጂ ጌታዬ ነህ?» ፈገግ አለችልኝ፡፡ «እስኪ አቀፈኝ እናረጋግጥ» እንደተኛች ሁለት እጆቿን ዘረጋችልኝ፡፡ አቀፍኳት፡፡ በህልምም ማቀፍ አለ፡፡ ከእውኑ ጋር ምን ይለያየዋል?...

«እማዬን ልጥራት»

«ተው፣ እንዳትነግራት፣ ጨርሶ እንዳትሰማ፡፡ ቻይና በንና መጥፋቷ፣ የሚቀበር ነገር አለመገኘቱ እንዴት እንደሚያብሰከስካት አያውቅህ? አሁን ተኛ ጠዋት ደግሞ የሚሻሻል ነገር ካለ እናያለን፡፡»

ፍራሿ ላይ ተኛሁ፡፡ እንቅልፍ እንዳይወስደኝ ተጠነቀቅኩ፡፡ እንደዚህ ያለነገር የተፈፀመበት ታሪክ፣ ተረት፣ ገድል፣ አፈታሪክ፣ ሳይንስ... ምንም ሊመጣልኝ አልቻለም፡፡ ኤልያስ በእሳት ሰረገላ ተመነጠቀ እንጂ ብርሃን ሆኖ ከሀሐይ ጋር አልተደባለቀም፡፡ ቅዱስ ያሬድም ራስ ደጅን ተሰውሮ አለመሞቱ ተነገረ እንጂ...

...ተነስቼ ገላዋን ነካኋት፣ ነቅታ ወይም የተኛች ከመሰለችበት ዓይኗን ገልጣ አይታኝ ሀዘኔታ ቅልቅል ፈገግ አለች፡፡

«አይዞህ ተኛ» አለችኝ፡፡

ስምረትስ ምን ሆና ይሆን? በረዶ? ገላዋ እየቀለጠ ተንገርቅኝቶ በእርጥበት መልክ አገሯ ስር ይፈስ ይሆን?... እንዲህ ያለ ተአምር ለምን አስፈለገ? ስለበደሏ ስትካስ? ወይም ስለጥፋቷ ስትከሰስ?...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

...እራሴን እንቅልፍ ወስዶኝ አገኘሁት። ስነቃ ደንግጬ ተነሳሁ። ህልም እንደሚሆን ቅንጣት ያህል አልተጠራጠርኩም። ሰረቂት እየነገርኳት ሰመሳቅ ቸኮልኩ። ወደ አልጋው አይኔን አጨናብሼ ላኩ። ረቂት አልጋው ላይ አልነበረችም። ከፍተኛ እረፍት ተሰማኝ። ደግሞ ቢሆንስ? ብዬ ክፉኛ ተጨነቅሁ። ለጊዜውም ቢሆን የሲፈንን ዕዳ የዘነጋሁበት ጉዳይ ነውና አልጠላሁትም። ማሰዳ እናቴ የጉልት መውጫዋ ሰዓት ሲደርስ ደጃፏን ሳትቆረቁር ከፈት አደርጋ ሰገግ ብላ ወደ ውስጥ አየች። ያየችው ወደእኔ ሳይሆን ወደአልጋው ነበር።

‹‹ያቺ ዕብድ ሄደች?››

‹‹ማን?›› ልቤ መታ።

‹‹ረቂት፣ ወፈፌዋ››

‹‹መጥታ ነበር እንዴ?››

‹‹ድምጿን የሰማሁ መስሎኛል። እንዴ? አንተጋ አልገባችም እንዴ? አላደረችም?››

የምመልሰው አጣሁ። እውነቱ በትዝብቱ ተምታታ። እናቴ መልስ ስታጣ ጣጥላ ሄደች። እኔ ግን ከእውነቱ ጋር ተፋጠጥኩ።

አልጋውጋ ሄጄ ፍንጭ ፈለኩ። ያቺ ጌጠኛ ትንሽ ቦርሳ ነበረች።

ድንግጥ!!

የረቂት ጉዳይ የሰውን ልጆች ሁሉ ወክዬ የተመለከትኩት የዚች ምድር ተአምር ነው። የሰማና ያነበበ እንጂ እኔ በፍጹም አልጠራጠረውም። ረቂት ጠፍታ ከውስጥ የተሸነጎረ በሯ ተሰብሮ፣ መኝታ ቤቷ ፖሊስ ሲገባ ሰው እንደነበረ ፍንጭ የሚሰጥ ምንም ነገር አልተገኘም። ረጅም ቀሚሷ መሬት ላይ ወድቆ ያየሁበትን መንገድ አንዳች ነገር ጠቋሚዬ ነው። የቀሚሱ ትክሻ ረቂት አንገት ሥር እንደተንጠለጠለ እስከ መጨረሻዋ ተአምራዊ ክንውን ድረስ አብሯት እንደነበር አወላሰቁ መስክሮልኛል። ምናልባትም ኤልያስና ኤልሣዕ ቆመው ሲጫወቱ የእሳት ሰረገላና የእሳት ፈረሶች መጥተው በመካከላቸው ሲገቡ፤ ኤልያስም በአውሎ ነፋስ ወደ ሰማይ ሲነጠቅ መጎናፀፊያው መሬት ሲወድቅ የተገኘው እንደዚሁ እንደረቂት ቀሚስ ነው።

ፖሊሶች አሽራና ፍንጭ ፍለጋ ቤቱ ውስጥ ሲንጎዳጎዱ እኔና እናቴ ወደ ደጃፍ ወጣን። የጊቢው ጠባቂ በጥርጣሬ በቁጥጥር ስር ሲውል። ‹‹ገብታለች፣



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አልወጣችም›› ብሏል፡፡ አባቴ ፖሊሶቹን ‹‹ይሄን እዩ›› እያለ ፈትሮ ይሂቸዋል፡፡ በዚህ መካከል ነበር የረቂት ስውር እጁ ትከሻዬ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ያረፈው፡፡ ሙቀቱ እንዳለ ነው፡፡ ለቀቀችኝ፡፡ ከማንም ማመን ጋር ትንትንቅ መግጠም አልሻም፡፡ ይሄ የሰውን ልጆች ሁሉ ወክዬ የተሳተፍኩበት የዚች ምድር ምናልባትም የመጨረሻው ተአምር ነው፡፡

አመናችሁም ቀራችሁ ረቂት ወደ ብሔረ ብፁአን፣ ወይም ወደብሔረ ኅያዋን ሄዳለች፣ ወይም በተአምረ መሰኮቱ ወደ ሰማየ-ሰማያት ተነጥቃ ከእነ ኤልያስ፣ ከእነ ሄኖክ፣ ከእነ ነአኩቶ ለአብ፣ ከእነ ቅዱስ ያሬድ… ጋር ተቀላቅላለች፡፡ መላእክተ ብርሃን እያሸበሸቡና ‹‹ንሴብሖ ለአምላክነ›› በማለት እየዘመሩ አቀባበል እያደረጉላት ነው፡፡ የሰው ልጅ በደል አንዱን ቅዱስ፣ ሌላውን እርኩስ እንዲያደርገው እነሆ በአይኔ አየሁ፡፡…

…ሲፈን እርግማን ውስጥ የገባችው በእኔ ክህደት ከሆነ ረቂትስ ስለገጠማት ክህደት እንዴት ከሥጋ ድካም የመገላገል ዕድት ሆነላት?…ዋናው ጉዳይ ይህ ነው? እራሴን ወቀስኩ፡፡ ዋናው ጉዳይ ከእኔ የተወለደችው ልጅ ናት? ከዚህ በፊት እንዴት አደገች? ወደፊትስ?…

…ለጥቂት ቀን የታገሰልኝ ጭንቀት ጀመረኝ፡፡

ፖሊሶቹ አባቴን አስቀድመው ወጡ፡፡ የሚያደርጉት ግራ እንደገባቸው ያስታውቃል፡፡ እንኳን እነሱ እኔም ሁሉንም ያየሁት ግራ ተጋብቻለሁ፡፡ አንዱ ፖሊስ ትንሽ ማስታወሻ አውጥቶ እስከረገቶ ደገነና

‹‹የምትጠረጥሩት ሰው አለ? በልጅቷ መጥፋት?››

‹‹እንዴ? ሞታለች ወይስ ምንድነው?›› እናቱ ቱግ አለች፡፡

የነብዩ ኤልያስ ዘመዶች እንዲህ ግራ እንደተጋቡ ጠረጠርኩ፡፡ የእሣት ሰረገላውና የእሳት ፈረሶቹ መጥተው መካከላቸው ሲገቡና ኤልያስን ይዘውት ሲመነጠቁ ያየው ነብዩ ኤልሳዕም እንደእኔ የሚያስረዳበት ቋንቋ አጥቶ ዝም ብሎ ይሆናል፡፡

‹‹ረቂት ከእግሯና ከቀኝ ጎኗ የጀመራት…››

‹‹ምን?›› (ፖሊስ)

‹‹የብርሃን ፍልቀት›› እኔ

‹‹እሺ?›› (ፖሊስ በሹፈት)



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ሰውነቷን እየጋረደና አካሏን እያንሳፈፈ. ቆይቶ በመጨረሻ የሰራ ሰውነቷ መታየት የማይችልበት ደረጃ ላይ ደረሰ።»

ፖሊስ ማኅተም ያለው ወረቀት አንስቶ ለሆስፒታል ይፅፋል። «የአእምሮው ሁኔታ ተጣርቶ ይላክልን። ደህና ከሆነ በእኛ መንገድ ደግሞ የወንጀል ሁኔታውን እናጣራለን...» ጣጣ፤ አፌን ያዘኩ።

ሳይንሳዊ ምርመራ ወይም ኃይማኖታዊ መገለጥ ያዳገተው ፖሊስ ወደ አሉባልታ ገባ።

«ከማን ጋር ተጣልታለች?»

«ገንዘብ ለማን አበድራለች?»

«የማንን ውሽማ ነጥቃለች?»

«ማን ዝቶባታል?»... ከሳይንሳዊው ወይም ከኃይማኖታዊው ይልቅ አሉባልታዊው ምርመራ ፖሊሶቹን ሥራ የሰሩ አስመሰላቸው። ተጠርጣሪዎች...

- የልጇ አባት (ሡንጋ፣ ሡንጋ የሚያካክሉ አማጮች ያሉት ሌላ ሡንጋ)
- እህቷ (ስምረት ቢዘን)
- ጓደኛዋ (ለገነት ለካ አልሄደችም?)
- ዘበኛው
- ደባደቦ፣ ድብዳብ ፊቷ (አንድ ቀን ፊቷ ላይ ቢራ ስለተደፋባት?)

* * *

ጠናጋሽው ፊቱ አብርቶና መንፈሱ ተነቃቅቶ ሳየው ልቤ ታዘበው። እርግጥ ከስምረት ጭቅጭቅና አስሮ መያዝ ነፃ ወጥቶ ይሆናል፤ ልጆቹንም ለእናቴ አስተላልፎ ነፃነቱ እንደተሟላ ተሰምቶት ይሆናል። ቢሆንም...

«ነቃ ያልክ ይመስላል።»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እ›› ብሎኝ ዝም አለ፡፡

‹‹ጊምህን ተላጭተሃል? ቀለል እንዲልህ የፈለክ መስለሃል፡፡››

‹‹ጥሩ!››

‹‹ምኑ?›› ለምን ፈትሬ መያዝ ፈለኩ? ዝም ብሎ ኪሱን መፈተሽ ጀመረ፡፡

‹‹ዛሬ በምስጢር ጠርተውኝ ነበር፣ ጥሩ፡፡››

‹‹ስለረቂቅ ሊጠይቁህ ይሆናል፡፡››

‹‹አይደለም›› ቆሞ የሱሪ ኪሱን ፈተሸ፡፡ የሚፈልገው ሲጋራ ሳይሆን አይቀርም፡፡ አጥቶ ተቀመጠ፡፡

‹‹ታዲያ?››

‹‹ወደ ሠራዊቱ ተመለስ፣ የቀድሞ ማዕረግህ ከነሙሉ ጥቅሙ ይሰጥሃል አሉ፡፡ ጥሩ! ዳግም ወደ ጦርነት ልንገባ ነው፡፡ ኤርትራና ያለው መንግሥት መጨረሻ ደረጃ ላይ እንደሆኑ ነገሩን፡፡ ጥሩ!›› መፈተሹን አረስቶ ዳግም የጃኬቱን ኪስ ፈተሸ፡፡ ክብሪት አወጣ ጫረው፡፡ ቱግ ያለ እሳት፡፡ በትንፋሹ አጠፋና ሳቀ፡፡

ምነው? በሚል መገረም አየሁት፡፡

‹‹ጓድ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ሀራሬ ሆነው የሰጡትን መግለጫ የግል ጋዜጦች ይዘውት መጥተዋል፡፡ ጥሩ ምን አሉ መሰለህ?››

ምን? በሚል አየሁት፡፡

‹‹ድሮም ሲባ ሲሰርቅ አይጣላም፤ ሲከፋፈል ነው አሉ አሉ፡፡ እንግዲህ የአንዱ ‹ሲባ› ሠራዊት ሆኜ የሲላውን ‹ሲባ› ሠራዊት ልወጋ ነው፡፡ ጥሩ!››

ፊቱ አብርቶና መንፈሱ ተነቃቅቶ ያየሁት የመሰለኝ እንዴት ነበር? መዘመሙን እንደ ክፉ ዕጣ አላየሁበትም፡፡ እንደውም የተሻለ ጥሩ ዕድል ሆኖ ተሰምቶኛል፡፡ ምክንያቱም አንድ ቀን የሲልቪያ ፕላት እራሱን የማጥፋት ድርጊት እንደአማራጭ ሊታየው እንደሚችል ስለምጠረጥር ነው፡፡ ጊሙን ብቻ ሳይሆን ሀገሩንም አሳጥሮ ወታደራዊ ግዴታውን ከወዲሁ ተወጥቶ እንደመጣ አሁን ልብ አልኩ፡፡

‹‹የኢማኑኤል ካንትን "Practical reason" እና የሶትራጠስን Moral philosophy የምናገኘው ውትድርና ቤት ውስጥ ነው፡፡ ካንት ሰውቀትን ገድቦ፣



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ማመን እንዲከፋፋ የሚተጋ ፈላስፋ ነበር። ዉትድርና ቤት ስትገባ ዕዉቀት ይገደባል የጋራ «እምነት» ይስፋፋል። ስትራጠስ ደግሞ ዕዉቀት ንድፈ ሀሳባዊ አይደለም ይላል፤ ተግባራዊ ነዉ። ተግባራዊ ዕዉቀት ያለዉ አሁንም ዉትድርና ቤት ዉስጥ ነዉ።»

ፍልስፍና ዉትድርና ዉስጥ ቤት መሠረት ይዞ እንዲጠብቀዉ ሲመኝ መስሎ ተሰማኝ። እኔ ዉትድርናን ባላዉቅም ይሄን ዓለም የተረዳሁበት መንገድ አለ። ሾፐንሀወር እንዳለዉ የዓለም ሥረመሠረት በጭፍንነትና በግብታዊነት ላይ የተገነባ ነዉ። ሳይንስና ስሌት አይገባዉም። በዚች ዓለም ላይ በእዉነት ስም የሚሰበከዉ ጭፍንነትና ግብታዊነት ነዉ። ሰላዉ ቀርቶ ትናንት ያሰብከዉን ዛሬ እንዳትደግመዉ የሚያስገድድ ሁኔታ በምክንያት አልባነት ተቆጣጥሮህ ቁጭ የሚልበት ጊዜ ብዙ ነዉ። ትናንት ያሰብኩት ዛሬ አለ? ትናንት የተለምኩት ለዛሬ ሰራ? እሆናለሁ ያልኩት የታለ? እዚህ ክፍል ቁጭ ብዬ እብደትን መጠበቅ ሰጣ-ፈንታዬ አልሆነም?...

«እኔም እዘምታለሁ» አልኩት። ቃሉ ከአፌ ሲወጣ ጭንቀቱ ሲቃለል ተሰማኝ። የመገዘመት ፍላጎቴን ለጠናጋሸዉ መንገር ነበረብኝ?

«ጥሩ!»

የትኛዉ ጥሩ?

«አሁን ግን አጠቃላይ የጦርነት አዋጅ የተሰሬፈ አልመሰለኝም። ነገሩ ስላላማራቸዉ ነዉ እኛን የጠሩን።»

ሀገር፣ ድንበር፣ ሉአላዊነት፣ ነፃነት፣ መደፈር... እዚህ ሁኔታ ዉስጥ ቦታ አላቸዉ? ጠናጋሸዉ የስምረትና የረቂት ጉዳይ ባይገጥመዉ ዳግም ይዘምት ነበር? እኔስ ሲፈን ምሽጌን ባታስለቅቀኝ ‹ጠበንጃ በአፈሙዝ!› ብዬ እጮህ ነበር? ሁሉም ዘማች የየራሱን አላማ በልቡ ይዞ ነዉ ለጋራ አላማ የሚዋደቅ የሚመስለዉ። ጀብዱና ጀብደኛ ከዚህ እዉነታ ዉስጥ ይወለዳሉ። ብዙ አመፀኛ ሴት ያለዉ ሀገር ብዙ ጀብጁ የሚሰራ ጀብደኛ ወታደር ይኖረዋል።

«ሕመሰግናለሁ» አለኝ አንድ ወረቀት እየሰጠኝ።

«ጥሩ!» አልኩት። ለምኑ ማለት አላሰኘኝም። ወረቀቱን እየሁት Withdrawal የተፈቀደበት ደብዳቤ ነበር።

«እኔም አመሰግናለሁ» አልኩት።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ሃያ ሁለት

## የብድራት ነገር

ሠላም፣ መረጋጋት የለያየውን ጦርነት አንድ ያደርገዋል። ጡረታ ድልድይ ባትሟ መቀተና ጨኸት አስጨነቃት።

‹‹አቤት መቀት፣ አቤት ጩኸት›› ረድ ሆርቄ ደጃፍ ላይ ቆሞ ለአባይ ቁስኒ ከአባቴ አስር ብር ተበረከተለት።

‹‹እኔ፣ ጦርነት ይመጣል ሲሉኝ አጡንትም አልመሰለኝ›› አለ አባቴ። ‹‹እንግዲህ እናቴ ድርቆሽሽን፣ ዝቦቆሎሽን፣ ጭኮሽን፣ በሶሽን... አሰናዳሺ፤ እንግዲህ እርግጥ ሆኗል።›› አባቴ ደግሞ የሚዘምተው ለምን ይሆን? የጀግና ምልክት አድርጎ የሚቆጥራት ጥይት ከግንባሩ ስለሾለከች ሴላ ጥይት በአፍንጫው ለመሳብ?

የአሸዋ ገበያ ደጃፍ ላይ አዘጋጅ። የጦርነት ነጋሪት ከመቃኑ የቀሰቀሳቸው የጡረታ ድልድይ ነዋሪዎች ከበቡት።

‹‹እንግዲህ ባድመ እዚህ ናት። ያኛው ወንበዴ የመጣው በዚህ ነው፣ ይሄኛው ወንበዴ የሚከላከለው በዚህ ነው። እነዚያ እዚህ ድረስ ገብተው ‹ሰባ ምሽግ› ሲቆፍሩ የኛዎቹ ደግሞ እዚህ ጋ ሴላ የመከላከያ ሴባ ምሽግ ያደራጃሉ። ቦታውን ስለተመላለስኩበት አውቀዋለሁ...››

አባቴ ጦርነቱን የሴባ ግሩፕ ሁብ አስመሰለው።

ጠናጋሸው በዘመተ ልክ በአስራ አምስተኛው ቀን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ማብራሪያ ሰጡ።

‹‹...ይቺ አገር ተወራለች›› አሉ። ወኔ በሚቀሰቅስ ሳይሆን ተኝቶ በሚያስተኛ መንፈስ። ተወረርን ካሉ ትንሽ ቁጣ አያስፈልግም ኖሯል? አባቴ እንኳን ጦር የሰበቀበትን፣ በአነጋገር የተዘባበተበትን የአማጭ ሠንጋ በንዴት እያሳደደ የጡረታ ድልድይን አቧራ ለሦስት ቀን አላስነሳም?

ሒሩት በቀሰና መሰስ ዜናዊ ለጦርነት ቅስቀሳ አይሆኑም። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ትካዜ የበዛበት የጦርነት መግለጫቸው በትዝታ መንፈስ የተዘፈነውን የሒሩት ‹‹ወኔ ቀስቃሽ›› ሙዚቃ አስታወሰኝ፦

‹‹አለብህ የጎበዝ አደራው፣



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

አለብህ ቃልኪዳን አደራው

እስኪ በጎፈሬህ በል ጎራው።›› ሲዋጋ የተነሳውን አያስተኛም? እንደውም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከመግባታቸው በፊት ያደመጡት ይሄንን የሂሩት ዘፈን ነው።

ጦርነቱን ሒሩትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዝታ አደረጉት ብሎ ህዝቡ አልተከዘም። እንደውም ምታ ነጋሪት ከተት ሠራዊት ያለው ሕዝቡ እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አልነበሩም። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለማፈግፈግ ሰበብ እየፈለጉ ስለመሰለው ይሆናል፤

‹‹ስንቅ›› ሲል፣ ይኸው!

‹‹ሞራል›› ሲል፣ ይኸው!

‹‹ወታደር›› ሲል፣ ይኸው!

አባቴ እንኳን የጠፋች ‹‹ጣ!››ውን እየደጋገመ ‹‹ይሄ ሰውዩ ጣ! ግንባር ሄጄ ሠራዊቱን አነቃቃለሁ ካለ ነገር ይበላሻል። ጣ! እንዲህ ነው እንዴ ሞራል? ጣ! ለዚህ ለዚህስ የእኛው ባሻዬ ይሻላል ጣ! ‹ጠንቀቅ› ሲል እንኳን ያለማጋነን ከዚህ እንጦጦ ይሰማል። ጣ!›› አለ።

ሂሩትም ግንባር ሄጄ ሠራዊቱን አነቃቃለሁ ካለች ነገር ይበላሻል ስል አስቢ ሳቅሁ። በሂሩት ትዝታ ወታደሩ ከሚስቱ የመታረቅ ህልም ያበጅና ይበተን ይሆናል።

ጠረጴዛዬ ላይ ብጣቂ ማስታወሻ ትቼ ወደ እንዱ ቀበሌ ሄጄ ተመዘገብኩ። ወደቤታችን ከተመለስን ያናደዱን ሴቶች ሲሳዘቡና ህሳብ ልንቀይር ስለምንችል ይመስለኛል አፈሳ አስመሰሉት። ነገሮችን አጣድፈው የጤና ምርመራ በማድረግ መኪና አቀረቡ። ዘንባባው ተዘጋጀ። ያስፈራሩንና ምኞጋችንን በፕሮፓጋንዳ የቀሙን ሴቶች በየመንገዱ ዳር ዘንባባ ይዘው ይሸኙን ጀመር።

ናዝሬት ደረስን። የናዝሬቷ ሲፈን! አባም በአህያ ውርንጫ ተሳፍሮ እንደሄደው በዘንባባ ተቀበሉን።

‹‹ሆሣዕና በአርያም››...

...ብለዋል? የናዝሬት ሴቶች ወደ ገሊላ ሲሸኙን ይሆን። ልጅ የታቀፉ ሴቶች ስመለከት ልቤ ብትን እያለብኝ ናዝሬትን አለፍናት። እንግዲህ ምኸኔ ባዶ ሆኖ ስታገኘው ሲፈን ምን ትል ይሆን? አዘማሪውስ?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ብዙ ተጓዝን፤ ብዙ ወጣቶች መንገድ ላይ ተቀላቀሉን። አንዳንዶቹም መኪና ላይ እየተንጠለጠሉ ተደባለቁን። በጤና ምርመራ የወደቁ ወደ ሴቶቻቸው መመለስ ስለማይችሉ ብቻ አሳብረው ወደማስልጠኛ ለመሄድ መኪና ተንጠላጠሉ። ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?...

ሐረር፣ ሁርሶ ማስልጠኛ ማዕከል የሚል ጊቢ ውስጥ ገባን። ከገባን በኋላ በመኪና ከአስር ደቂቃ በላይ ሄድን። ጊቢ ነው ሀገር? ከመኪና ስንወርድ ያ እስከ እንጦጦ የሚሰማው ጨኸት ተቀበለን። ማዋከብ አለበት። እየተዋከብን ፀጉራችንን በወረፋ ላጨን። ቱታ ልብስ ታደለን። ያ ሁሉ ዝንጉርጉር በአንድ ጊዜ ተመሳሰሉ ቁጭ አለ። ያየኸው ቀርቶ ያናገርከውና የተጋባኸውም ተደባልቆ ጠፋ... እራሴ ተደባልቄ እንዳልጠፋ። አንድ የሱፊዎች ታሪክ ትዝ ብሎኝ ብቻዬን ሳቅሁ።

ሙላ ናስሩዲን ሃጂ ለማድረግ ወደሳውዲ ሄዶ ነው። ሰው ከመብዛቱ የተነሣ ናስሩዲን ማደሪያ ማግኘት አልቻለም። በመጨረሻ አንድ ሆቴል ውስጥ ጥንድ አልጋ ያለው አንድ ክፍል አግኝቶ ገባ። ብዙም ሳይቆይ ሁለተኛው አልጋ ተከራይቶ ሰውየው መጣ። ናስሩዲን ሰውየውን ሲያየው ልክ እንደሱ ነበር የለበሰው። ቁርጥ እራሱን። መተኛት አልቻለም። ሰውየው ነቅቶ

‹‹ወንድሜ፣ ለምን አትተኛም?›› አለው።

‹‹አንድ ችግር ገጥሞኝ ነው።››

‹‹ምን?››

‹‹እኔና አንተ ተመሳሳይ ነን። ተኝተን ስንነቃ እራሳችንን መለየት ቢያቅተንስ?›› አለ ናስሩዲን።

ሰውየው ለካ ተንኮለኛ ኖሯል። ዞር ዞር ሲል አንዲት አሻንጉሊት ጥግ ላይ ተቀምጣ ይመለከታል። ያነሳና እግሩ ላይ አስሮ...

‹‹አሁን ተኛ፣ አሻንጉሊት እግሬ ላይ የታሰረው እኔ ነኝ።›› ይለዋል።

ናስሩዲን ችግሩ ስለተፈታለት አመስግኖ ይተኛል። ሰውየው በጠዋት ሲወጣ አሻንጉሊቱን ከእግሩ ላይ ፈቶ ናስሩዲን ላይ አስሮት ይሄዳል። ናስሩዲን ሲነቃ ደነገጠ። እየሮጠ ወደአደባባይ በመውጣት እንዲህ አለ።

‹‹አንድ ሰው ተሳስቶ እኔነቴን ይዞ ሄዷል። እሱ እኔ ነውና የት ነው የሚገኘው?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

እኛም ተደበላልቀን ያንዱ መዝመቻ ችግር የሌላ ሆኖ እንዳይዛነት ሰጋሁ። «ምልምል ወታደር» ሆናችኋል ተባልን። እስካሁንስ? ከመሸ በኋላ መኝታ ክፍሎቻችንን አውቀን እየተባደንን ገባን። ለመጀመሪያ ጊዜ የመንገላታት ውጤት የሆነ እንቅልፍ ጥርግ አድርጎ ወሰደኝ። ሲንገዋለሉ ማደር አብዝቶ የማሰብ ወይስ በአካል ያለመንቀሳቀስ ውጤት ነው?

ለሳምንት ያህል ስልጠና አልተጀመረም። ሐሩሩ የአካል እንቅስቃሴም ሳይኖር ያደክማል። ውኃ አብዝቶ መጠጣት በራሱ ዋነኛ ሥራ ይሆናል። በቀን ሦስት ጊዜ ዳቦ እራሱን እየተያየረና የተለያዩ የምግብ አይነቶችን እያስከተለ ይጎበኝናል። ጠዋት አያ ዳቦ ከሻይ ወይም ከወተት ጋር ይመጣል። ምሣ ሰዓት ከሽሮ ወይም ከሥጋ ወጥ ጋር። ማታም እንደዚያው ከሆነ ወጥ መሰል ነገር ጋር!

እየሩጋና ምግቡን እየተላመድን ስንመጣ ወሬ ተከተለ። ምልምሉ ሁሉ የፍቅር ታሪኩን ጨምሮ የፈፀመውን ጅብዱ ያወራል።

ስልጠና ይሄ ነው? አካሉ ሲያርፍ አእምሮዬ ሲፈንን ይጎትት ጀመር። በረሃው እግሬን ይበላዋል። ከረጅም ቀሚሷ ሥር፣ ከቁርጭምጭሚቷ በታች መጫሚያዋ ብቻ ያለ እግሯ ምሪት ይገባል...

ከስልጠና በፊት የነበረው እረፍት ጊዜ ለካ ወሬ መቃረሚያ ኖሯል። ተሰብስበን ግምገማ የሚባል ጣጣ ውስጥ ገባን። ብዙ ምልምሎች የገዛ ወሬያቸው መሰከረባቸው። ወንጀል ፈፅመን ሸሽተን ማሰልጠኛ ገባን ያሉ ተለዩ መዝጋቢ መጥቶ «ብል በጀማው ፊት በገዛ አፍህ የተናገርከውን ወንጀል ድገም» ሲባል አንዳንዱ ካደ። መካድ አላዋጣም። ያመነው ደግሞ እያለቀሰ እንዲህ አለ፦

«ወሽካታ፣ ቀዳዳ ነኝ። በፊትም በሬ ወለደ ማለት እወድ ነበር። አድንቁኝ ብዬ እተረተራለሁ። አፈር ልብላ! ቱሪናፋ፣ ሸርካት፣ ወናፍ፣ ትርትር፣ ውሸካት፣ የማልታመን... ነኝ። ማሩኝ!» አለ። ከዚያ በኋላ አዲስ ድልደላ ተደርጎ አዳዲስ «ጋንታ» መሠረትን ስልጠናው በማለዳ እስፖርትና በከሰዓት በኋላ ሰልፍ ተጀመረ። አብዛኛው ምልምል ግራና ቀኝ ስለማያውቅ በአንድ እጃችን ሳር በሌላኛው ድንጋይ ያዝን።

ግራ እና ቀኝ እጅ የማያውቅ ወጣት እምን ውስጥ ተወልዶ አድጎና ጎርምሶ እዚህ መጣ?

«ወደፊት ሂድ! ወደግራ ዙር!! ወደድንጋይ ዙር!!» አንዳንድ አካባቢ አለ። ቀኝና ግራ ዕውቀት ሆኖ የአቅጣጫ መሀይም ሆነህ የምታድግበት። ሰው ምንድነው? መንፈስ ዝት ይላል። እዚህ እንኳን ቀኝና ግራህን እንዳታውቅ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

በሳርና በድንጋይ ተቀይሮብሃል። ሣርና ድንጋይ መያዝ ዕውቀት ሆኖ ትናንት በግራ የያዘውን ሳር ዛሬ በቀኙ ይዞ መጥቶ የሚዋከብ አለ።

‹‹ቅጣው!›› ቅጣቱ እስፖርት ነው።

ካካባቢያችን በምናገኘው ነገር ጠበንጃ እንድንሰራ ታዘዝን። ቆርቆሮ፣ ጣውላ፣ የመጥረጊያ እንጨት ‹‹በዚህ ሊያዋጉን ነው እንዴ?›› ያሰ ምልምል፦

‹‹ቅጣው!›› ተባለ።

ያንን የቅራቅንቦ ጠበንጃ ጓደኛው ላይ ደግኖ ‹‹ተማረክ›› እያለ የቀለደ ምልምል

‹‹ቅጣው›› ተባለ። ‹‹አፈሙዝ በወገኑ ላይ የደቀነ ከሃዲ፣ ቅጣው!››

ለካ ጠበንጃ ተብለሃልና፣ ጠበንጃ ትሆናለህ ተብሏል። የተጠጋገነው የቅራቅንቦ ጠበንጃ የጠፋበት በእንዝላልነት መሳሪያ ለጠላት እንዲደርስ በማድረግ ወንጀል

‹‹ቅጣው!››

ቅጣቱ ያን ያህል ተካብዶ አይታየኝም ነበር። እዚህም ስፖርት እዚያም ስፖርት እያልኩ እንቀዋለሁ። አንድ ቀን ደርሶብኝ ስቀምሰው ግን መፈጠርን የሚያስጠላ ነው ለካ። የተቀጣሁት በማለዳ ወደ ስፖርት ስንወጣ በጋራ እየዘመርን ነበር...

‹‹ተከብረሽ የኖርሽው ባባቶቻችን ደም፣

‹‹ባባቶቻችን ደም፤

እናት ኢትዮጵያ የደፈረሽ ይውደም፤››

አንድ ወጣት መቅንን አስቆመን። አሰልጣኝ መሆኑ የሚታወቀው እኛ በለበስነው ቱታ ላይ ቀበቶ ስለሚያስር ብቻ ነው።

‹‹አላችሁ?›› ብሎ ጮኸ። ለምልምሎች የሚቀርብ ሠላምታ መሆኑ ነው።

‹‹አለን!!›› ብለን ጮህን። በደንብ የጮህን ካልመሰለው ይደግመዋል - ደገመው።

‹‹አላችሁ!››

‹‹አለን!›› ጮህን።

‹‹አንተ ማነህ?›› ሁሉም የየራሱን የጋራ ስያሜ ጮኾ ጠራ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ማርታ!››

‹‹አብዲሳ!››

‹‹ሐየሎም!››

በዚህ መሃል አሰልጣኙ መኮንን ጠናጋሻው መሆኑን አወኩ። ልቤ መታ፤ ብቸኝነት ተሰምቶኝ ነበር? ምንድነው?... አፌን ሳላዘው ተጣራ።

‹‹ሻምበል ጠናጋሻው!›› ሁሉም ወደ እኔ ዞረ።

‹‹ማነው? ውጣ!›› አለ ወጣቱ መኮንን ወጣሁ። ‹‹ቅጣው!›› ብሎ ራቅ ላለ ባሻ አሳልፎ ሰጠኝ።

ለካ ቅጣት የፍጥነት ስፖርት ናት። እስከ እንጦጦ በሚሰማ ድምፅ እየፈጠነ ያዛል።

‹‹ዙር! ተኛ! ተነስ! እዛጋ!... እዚጋ!...

‹‹እንደ አቆጣጠሬ

‹‹ፈርዶብሃል ዛሬ

‹‹ተሽከርከር እንደ ሄሊኮፕተር

‹‹እኮብኩብ እንደ እንቁራሪት

‹‹ተንከባለል እንደበርሜል

‹‹ሩጥ! ሩጥ! ሩጥ! አንበሳዬ፤

‹‹አንተም በጥፋትህ

‹‹እኔም ለእንጀራዬ!...

‹‹ቁም! ተቀመጥ!!

‹‹አታልምጥ!!...››

የትኛው ፈጣን ፍጡር ትዕዛዙን ሊፈፅም እንደሚችል ግራ ያጋባል። እዛ ብሎ እዚህ፤ በዚህ ላይ ባሻው የአፉን ያህል ያልፈጠነ ጠላቱ ይሆናል።

‹‹ንቀት ነው? በል፤ ኖቬል ሸልመው››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ምን ይሆን ናቤል? የመኪና ጎማ መጥቶ ፊንገቱ ላይ ጠለቀ። እንደወፍ የሚበረውን የባሻ ትዕዛዝ ለመያዝ መንደፋደፍ። ሲጨርስ ቅጣቱን ሳዘዘው መኮንን ያስረክባል።

‹‹ተጠንቀቅ!›› ትዕዛዝ።

‹‹ፅና!!›› ብሎኝ ሄደ ሲላ ቅጣት። አንዳንዴ ሙሉ ሌሊት ‹‹እንደፀናሁ›› እንድታድር ይፈረድብሃል። የቀጣህ ሳያሳርፍህ ማንም አይለትህም። እኔ ይሄንን ሁሉ መከራ አልጠላሁትም። በአካል ጉስቁልና የሚነፃ ነፍስ እንዳለኝ አምናለሁ።

‹‹አሳርፍ!››

‹‹ላብ ደም ያተርፋል›› ይላሉ።

‹‹ላብ ነፍስ ነው የሚያተርፈው።››

‹‹ቅጣው!!››

ህልም ሁሉ በ‹‹ቅጣው!›› ይሞላል። ያውም ህልም ካለ። ሁሉም ነገር በትዕዛዝ እሽርክሪት ውስጥ ይከናወናል። በዚህ ሰዓት ነው እውነተኛው ተደበላልቶ መጥፋት የሚከተለው።

ዶስተየቭስኪ፣ ቶልስቶይ፣ ሌርሞንቶቭ፣ ሔሚንግዌይ፣ ስቴንቤክ… ይሄን ሁሉ የውትድርና ቤት መከራ አልፈው ነው መልሰው እራሳቸውን ያገኙት? እንደእኔ በመከራ የቆፈሩትን የነፍስ ወከፍ ምሽግ መልሰው እንዲደፍኑ ተጠይቀዋል?

‹‹ጠላት የውጊያ ስልት ስለቀየረ የቆፈራችሁትን መልሳችሁ ድፈኑ። መቆፈሩ እንዳይታወቅ። የቆፈረውን በአግባቡ ያልደፈነ መልሶ ቆፍሮ እንዲደፍን ይደረጋል።››

ሁሉን ቻይ ፈጣሪ ሳይሆን ምልምል ወታደር እንደሆነ አየሁ። በይበልጥ እኔ ሁሉን ቻልኩ። ከጎኑ ያለውን የሚሸሽ ከፊት የሚጋረጠውን ጥሶ ከማለፍ ውጭ ሌላ ምን አማራጭ አለው?

ምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ አላውቀውም። በዚያ ሁኔታ መቁጠር ዘበት ነው። አንድ ቀን ከጠዋት ስፖርት በኋላ ወደ ቁርስ ልንሄድ ስንል ‹‹ፎሌ ተነፋ›› ተሰለፍን። የኢላማ ተኩስ አሰልጣኞችን አንድ ሃያ የምንሆን ምልምሎችን ሥም ጠራና ውጡ አለን።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ወጣን፣ አስልፎን ወደ አንድ ቢሮ ወስዶ አስረከበን:: ጠናጋሽው ነበር:: ወደበረንዳው ወጥቶ ‹‹ተጠንቀቅ!›› ሲል ጮኸ::

ተጠነቀቅን::

‹‹አሣርፍ!!››

አሳረፍን::

‹‹ለምን እንደጠራናችሁ የምታውቁ ይመስለኛል::›› እያለ ንግግር ሲጀምር ሌሎች ምልምሎች ተሰልፈው መጡ:: እስክንጠረታቀም እንድንቀመጥ አዘን ገባ:: በጥቂት ጊዜ ውስጥ ወደ ሁለት መቶ ደረስን:: ጠናጋሽው ሌሎች ሁለት መኮንኖች አስከትሎ ወጣ:: ‹‹ተጠንቀቅ!››

ተጠነቀቅን::

‹‹አሳርፍ!››

አሳረፍን::

‹‹ለምን እንደጠራናችሁ ሳትጠረጥሩ አትቀሩም:: ሠራዊቱን የማጥራት ስራ ተሰርቶ እናንተ ተለይታችሁ ወጥታችኋል:: ውጊያው ከሻዕቢያ ጋር ይሁን እንጂ ጠላት አንዳንድ ሠራዊቱ ውስጥ በምልምል ወታደርነት የገቡ ኤርትራውያን ተጠቅሞ የጥፋት ሥራ ለመስራት ማቀዱ ተደርሶበታል:: በመሆኑም ሠራዊቱን አጥርቶ ለጠላት ቀዳዳ ላለመተው በተወሰደው እርምጃ መጀመሪያ በአባታችው የኤርትራ ስም ያላቸውን አጥርተናል:: ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ የሶስት ወር ደሞዝ ተሰጥቷችሁ ከስልጠናው በክብር እንድትሰናበቱ ተወስኗል::››

የወር ደሞዛችን ሃምሳ ብር ናት::

‹‹ዲሽሚስ!››

ያለ ሠልፍ መሪ መሄድ ሳንችል ቀረን:: መታዘዝ ተፈጥሯችን ሆኖ:: ምንድነው? ምን አድርጉ ነው የተባለው?...

ለመጀመሪያ ጊዜ ማሰቢያዬን ከሸንጎጥኩበት አውጥቼ ለመጠቀም ሞከርኩ:: ምንድነው የተነጠኩት? ምንድነው ያገኘሁት?....

በተናጠል ተበትነው መሄድ የተሳናቸው ምልምሎች በግድ ሠልፍ ያዙ:: ከመካከላችን አንዱ ምልምል ወጥቶ ‹‹ወደፊት ሂድ!›› ብሎ ጮኸ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ማር፣ ድንጋይ፣ ማር፣ ድንጋይ...»

የሦስት ወር ደሞዝና የስንብት መናኛ ወረቀት የብርጌዱ በር ላይ ጠበቀን:: ስማችን እየተጠራ ሲሰጥ የእኔ ወደ መጨረሻ ሆነ:: ሌሎቹ እስከ በር የሚያደርሳቸው «ማክ» ላይ ሲወጡ እኔን ባሻ ወደኋላ ጎትቶ አስቀረኝ::

‹‹ሊቀጣኝ?››

‹‹ወዲ ፍሬው ይፈልጉሃል::››

ብዙ ወዲ ቢኖርም ዝም ብዬ ጠበኩ:: ጓደኞቼን የጫነው መኪና ሲንቀሳቀስ ሆዴን ባርባር አለው::

‹‹ተከፋለሁ? ወይስ ምንድነው?›› እስካሁን አልገባኝም:: ወዲ ፍሬው ጠናጋሻው ነው:: ትንሽ ግልፅ ወታደራዊ መኪና ይዞ በሾፌር መጣ:: ከፍቶ ከኋላ አስገባኝ:: መኪናዋ ተንቀሳቀሰች::

‹‹ሁርሶ ከተማ ላይ እህትህ ትጠብቅሃለች::››

‹‹ማን?›› ማለት ተሳነኝ:: ትዕዛዝ መቀበል ብቻ::

‹‹ስምረት መጥታለች:: ለተፈጠረው ነገር አዝናለሁ:: ለአንተ እንደውም ጥሩ እድል ይመስለኛል:: ምክንያቱም...›› በረጅም ተንፍሶ ብዙ ቆይቶ...

‹‹ሁሉንም ነገር ስምረትን ስታገኛት ታውቀዋለህ:: እስር አለቃ ያልኩህ ቦታ አድርሰውና ከሰዎቹ ጋር ከተገናኘ በኋላ እስከ ድሬደዋ አድርሳቸው::›› ጠናጋሻው ወረደ::

ሄድን፣ የሁርሶ ከተማ የእሸዋ ቆብ አናታቸው ላይ በደፉ ቤቶች የተመሰረተ ነው:: መኪናው ሲቆም ከአንድ አቧራማ ቤት ውስጥ ሁለት ሴቶች ወጡ:: ቀጥታ መኪና ውስጥ ለመግባት ተሰለፉ:: ከኋላ የነበረችው በተቃራኒው በር በኩል ለመግባት መኪናውን ዞረች:: ስምረት ከስታለች፣ ጠቁራለች:: አይኖቿ ዕንባ ህመም ያስተናገዱ ሆነው ታዩኝ::

«ከፈትላት» አለችኝ::

ልከፍትላት ስዞር ልቤ ትርትር ብሎ አደገኛ ህመም ተሰማኝ::

ሲፈን፣ ሲፈን፣ ሲፈን... ልጇስ? ከፈትኩላት፣ ገብታ አንገቴ ላይ ተጠመጠመች::

«ይቅርታ! ይቅርታ! ታለ? ይቅርታ...»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ልዝመት ብዬ ያስቸገርኩባትን የልጅነት ዘመኔን አስታወሰችኝ።

«ገድዬሃለሁ፣ እንዴት ከስተሃል? ገድዬሃለሁ እንዴት ጠቁረሃል። ይሄ ሁሉ በእኔ? ኡ! ኡ! ኡ! ኡ!...»

አንዳንድ የሁርሶ ነዋሪዎች ብቅ ብቅ አሉ።

«ውሸታም ነኝ፣ ግደለኝ!!» እጇን ስባ አንገቷ ላይ አሳረፈችው። «እነቀኝ ግደለኝ፣ እንደዚህ ይሆናል ብዬ አልነበረም!! ኡ! ኡ! ኡ!...»

«በቃ! በቃ!» ስምረት ታለቅሳለች።

ሁኔታውን በቀላሉ ልረዳው አልቻልኩም።

* * *

ቆይቶ ገባኝ። ሲፈን ልጅ አለኝ ብላ ዋሸችኝ፣ ይሁን ታዲያ ምን ተጎዳሁ? የተጎዳሁት በሌላ ነው። እኔ ኤርትራዊ ተብዬ ከስልጠና ተባረርኩ፤ አባቴ ኤርትራዊ ተብሎ ከድንበር ወዲያ ተላከ... ለጠላቶቹ ተላልፎ ተሰጠ?

እንዴት? እንዴት? እንዴት?. . .

ምን እንዴት አለው? የዓለም ስረ-መሰረት ከምን ተገንብቶ? ከጭፍንነትና ከግብታዊነት አይደለምን?...።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# ክፍል ፯

## ወደ መሥራ ባቡር ሰዎች



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

*መታሰቢያነቱ*

ለእህቴ ሰረቂት ብዜን እና

በፀሐይ ግባት ዘመቻ ላይ ለተሰዋው ለሻለቃ ጠናጋሻው ይሁንልኝ፤፤



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## 1
## ወደ ውስጥ



ተጀመረ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## 2

## ወደ ውጭ

ምክንያት ኖረም አልኖረም አመፅ ግድ ያሰበት ወቅት ላይ ነን። የጭራሴ ልምሻ ባይኖርብኝና ሁሉን በመናቅ ባልለከፍ ኖሮ የማጠፋው ሰውና ነገር ብዙ ነበር።

እውነታን በመጥላትና በመፍራት የህልም ቁራኛ ሆኛለሁ። እውነታው የብዙ ሰዎች ጩኸት ነው። ጩኸቱን ህፃናት የተዘጋ ደጃፌ ድረስ በጨዋታ መልክ ያመጡልኛል።

‹‹ወያኔ ሌባ!›› ይላሉ በዛ ያሉ ልጆች

‹‹ካ.ካ.ካ.ካ.!!›› ጥቂት ልጆች በአፋቸው ይተኩሳሉ።

‹‹ልጄ፣ ልጄ!›› የሚሉ ሴት ህፃናት ይተካሉ። ይሄ የትላልቆቹም ‹‹ጨዋታ›› ነው።

‹‹ድምፃችን ተሰርቋል!››

‹‹የተሰረቀው ድምፃችን ይመለስ!››

‹‹ካ.ካ.ካ.ካ....››

‹‹ውኃ፣ ውኃ፣ ውኃ...››

በፊት ያልጠማው ጥይት ሲመታው ለምን ውኃ ይጠይቃል? ጥይቷ የምታርፈው መጠሚያው ላይ ነው እንዴ? አባቴ በግንባሩ ጥይት ይዞ ሲኖር ስለምን ውኃ፣ ውኃ.. እያለ አልኖረም? ሰው ጥይት ሲያገኘው መጠሚያው ቢነካ ኖሮ አባቴ ውኃ እንደጉልኮስ ተሰክቶለት ይዞ በዞረ ነበር...

...አባቴ በኤርትራ ምድር ላይ፣ የወጋቸው ሰዎች መፍለሻ ቢርካ መስለው እንደተገጠገጡ! ልብሱ አልቆ፣ የተራቆተ ገላው ነትቦ እንዳቀረቀረ ሲጓዝ ይታየኛል። በጎንና ጎን ያለው የሰው ግድግዳ ሲናድበት እያዘመመ ስድብ እንደ ምራቅ እየተፈናጠቀበት...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

...ይሄን የፈረደበት ማነው? አንድ ሰው አትበሉ፣ አንድ ድርጅት አትበሉ፣ አንድ ማህበረሰብ አትበሉ፣ አንድ መንግሥት አትበሉ... ዘመን ነው፤ እንደ ሸንኮራ ተመጥጦ ያለቀው ዘመን...

‹‹...በዚያ ዘመን በሰዎች መካከል መከዳዳት ይሆናል›› የተባለው የመጽሐፍ ቃል ሆኗል። ሐሜት፣ ትዕቢት፣ ስድብ፣ ራስን መውደድና ማክበር፣ መማለጃ ተቀብሎ ፍርድን ማጣመም፤ ገንዘብ መቀማት፣ ወንድምን መግደል፣ በሐሰት መመስከር፣ መስረቅ፣ ሐሰት መናገር፣ ድንበር ማፍረስ፣ ወሰን መግፋት፣ እጥር መስበር፣ ወንድም ወንድሙን ለገንዘብ መሸጥ፣ ፍትርም ከእነርሳችን መሬት›› ሆኗል።

ዘመን ያመጣው እውነት አስተያሚ ነው።...

...ባለትርፌት ህልም አለኝ። እዚያ የህልም ማህፀን ውስጥ ተሰርቶ ያላለቀ ጫጩት ሆኜ ተጣጥፌ ማሽሰቤን እወደዋለሁ። እውነታን በህልሜ ትርፌት እየመከትኩት መኖር ለኔ ህይወትም፣ መንገድም መዕናኛም ሆኖኛል።

በእውነት ሥም ነቢዮች የዓይንህን ቆብ ያንኳኳሉ፣ በርህን የሚቆረቁሩ መሲሆችና መንደርህን የሚያተራምሱ እድማ በታኞች፣ አገርህን በጉልበት የሚወክሉ መሪዎች፣ ዓለምህን ካላናጋን የሚሉ ፈላስፎች... ኑሮህን እንዳሻህ እንድታበጅ አይፈቅዱልህም። ህልምህ እንጂ እውነትህ ያንተ አይደለም። አይንህን ግለጥ! የትኛው ቤት ሰቃ አንተን ይወክላል? ደጅህን ከፌት እየርህ በሌሎች ጠረን አልታወደም? ወንዝህ አልተበከለም፣ የምትረግጠውን መሬት ማን እንዲመቸው አድርጎ ደለደለብህ? ጥሻህን ማን መነጠረብህ? የተፈጥሮ ህግህን ማን ቀማህ? ሁለተኛ ተፈጥሮን ማን ተካብህ?... ወዳጄ እውነታ ግለሰብን ወክሎ የማያውቅ አስተያሚ ነገር ነው።

ተመልከት! አይኔን ስገልጥ እህቶቼ ያመጡት እቃ ከበኛል። ሌላው ቀርቶ ያቀማመጥ ሥርዓቱ እንኳን የእኔ አይደለም። ልብ በል!! ደጃፌን ስከፍትስ? ሊሊ ያዘለችው እንጋዳ ወንድሟን እያንዘለዘለች ትመጣለች። ወንድሟ ላይ እኔን ደርባለች? ካልሆነ የደጃፌን መከፈት አዋጅ ለምን ጆሮዋን እንኳ ትቀላውጣለች?

‹‹አውራኝ›› ትለኛለች።

‹‹ምን?››

‹‹እንጃ!››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ግራ ይገባኛል። ወንድሟ ላይ ተደርቤ ስንዘጠዘግ ልቤ የተናጠ ይመስለኝና ይጨንቀኛል። እግሬ ይንጠለጠልብኛል። ዕድሜዋን የቀማ ከግራ ቁመና አላት። ከእሷ ያዘለችው ይገዝፋል። አንገቷ ላይ ያረፈው የማዘያ አግድም ስላነቃት ደም ሥሯ ፈጥጦ ሲታይ ይጨንቃል። ጣቶቿን አንገቷ ሥር ፈልፍላ በማስገባት ማዘያውን ትነትተዋለች። ደም ሥሯ ያፈጠጠ ዓይኑን ይሰብራል።

«ታስ አውራኝ።»

«ምን?»

«እንጃ!»

በዚች ልጅ እውነቱ ብቻ ሳይሆን ህልሜም ይበላሻል። የተንጋደደ ልጅ እንዳዘለች፣ እጇን ከእጄ አቆላልፋ፣ ወና አደባባይ ስንዞር ይታየኛል። እዳዬን አላወኩም። አንድ ቀን ሳወራት ሞክርኩ፤ ምን አወራች ታዲያ? ከዕለታት በአንዱ ቀን ወንድሟን ሳታዝል ከሠባራ ባቡር ወጥታ ሞንትራሊ የሄደችበትን ነዓነት። ደገመችልኝ፣ ደገመችው፣ ደገመችው...

...ባትቀምሰው ይሻል ነበር። ለካ ልጅ አለማዘሌ ላጣጥመው የሚገባ የዘልአለም ነፃነቱ ኖሯል? ጥያት ስሄድ ባለመንቆር አይኖቿን ልቤ ላይ ቀብቅባ ትንጠላጠላለች።

ይህ እውነት ነው...

...የማዘል ቁራኛ የሆነች ልጅ ላይ የመደረብ አስቀያሚ እውነት...

...የእውነታ ማርከሻ ህልም ነው፤ አይንና ደጃፌን አለመክፈት። ግን እውነታ የሚከደን እፊያ በሌለው ጆሮ በኩል ይገባል።

«ሳይሞቅ ፈላ እስኪ የሰው ደጃፍ ልቀቂ ኦሆሆሆሆ... ይ! የሰው ደጃፍ አንቀሽ ምን ይሁን ነው?...» አከራዬ፣ የሊሊ አክስት የእሷ ውጋት፣ የእኔ መቅሰፍት...

ሊሊ በታነቀ ጉሮሮ መልስ ሰጠች። አጥርቼ አልሰማኋትም። ሳይሞቅ ፈላ አይደለሁም ነው? የሰው ደጃፍ አላነኩም ነው? ምንድነው የምትለው? እውነት ሳይኖር መልስ ይሰጣል? በማዘያ አንገቷ መታነቁን ዛሬ ሳትወደው አልቀረችም።

«ወያኔ ሌባ! ወያኔ ሌባ!» የሊሊ ወንድሞች፣ የጆርባዋ ባለርስቶች የነበሩ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ኳ! ኳ! ኳ! ኳ!... አንተን ገድያለሁ፤ መሮጥ የለም፤ ውደቅ...» ተፈሪ የሚባለው የሊሊ ወንድም።

«ልጄ! ልጄ!» ሲት ህገናት።

ሊሊ ሳይሞት ፈሳ ከሆነች እኔስ? ምንድነኝ? ሳይሞት የማፈሳ?

«ማነች? የልጄን ደጃፍ ያነቀች? ሳይሞት የፈላች?...» የቹቹ እናት ከማደ ሆና ጠየቀች። ይቺ ናት እውነት፤ ለአንተ እናትህ እውነት ናት፤ አይደል? ግን፤ ልትሆንም ላትሆንም ትችላለች። በዚች ዓለም እውነትና ውሸት ተመጋጋቢዎች ናቸው።

የእኔን እውነት ልንገርህ...

...በዚያ ሰሞን ከገዳም ሠፈር ወደ ሠባራ ባቡር ስሻገር የሊሊቱን የቆሊ ጩኸት የሚያስታውስ ለላ ጩኸት ሰማሁ። ስዞር የቹቹ እናት የጠማማ ግንድ ጣውላ መስላ እጇን ታውለበልባለች።

ምን ፈለገች? ከዚህ በኋላ ቹቹን ትጠይቃለች? እናት አይደለች? ብትጠይቅ ምን ይመለስላታል? እናቴ እሩሲ ወስዳ ለእሩሲዋ እመቤት አደራ ሰጥታልሻለች? ይባላል?... አልጠበኳትም። ዝም ብያት ወደተከራየሁበት ቤት ሄድኩ። በቀጣዩ ቀን መጣች። ቤቱ ሆኜ ድምጿን ሰማሁ። ከአከራዬ ጋር ታወራለች።

«ልጄን ፍለጋ ወጥቼ፤ ካስቀመጥኩበት አጥቼ፤ እህቶቹን እነ እቱቱን እንዳልጠይቅ ፈርቼ፤ እዚህ አይቼ፤ ተጣርቼ፤ አጠገቡ እኖራለሁ ያንቺን ቤት ተከራይቼ...»

«አንቺ ማን የሚሉሽ ነሽ? እህቶቹን ትተሽ የታለ እናት የሆንሽ?»

ባይጠየቅ የምመኘውን አከራዬ አነሱ፤ እውነት እንደሆን እራሱን ችሉ የማይቆም እንደ ሊሊ ወንድም ያለ እናቱ ታዛይ ነው።

«ልጅ ሆኖ ነው ከአሳዳጊው ጋር የተቀያየርነው። ነገሩ ረጅም ነው።»

ከእውነት ጋር ቀስትና የለኝም። ሊሆን ከሚችለው ይልቅ ሊሆን የማይችለው ያስፈራኛል። የእናቱ የአንገትን እናትነት የካደ ትርክት ምኔን አፍርሶ ምኔን እንደገና የሚገነባ እውነት ነው? ያስፈራል። ለማረጋገጥ አልጠይቅም፤ ለማረጋገጥ የሚሞክር ሰው ሲጠይቅም መስማት አልፈልግም።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ጆሮዬን በትራሴ ከደንኩ። እውነት በጆሮ ይገባል። ህይወት ሽሽት ሆኖብኛል። የማያቋርጥ እውነታን የመሸሽ ተጋድሎ ውስጥ ነኝ። ፍሬዲሪክ ኒቼ እውነቱን ነው። «ገሃዱን ዓለም እፈራዋለሁ» ("I'm afraid of the real world") ነበር ያለው። አፍንጫው ስር እጅብ ያለው ሙስታሹ ገሃድ እውነት አይደለምን? ህልም ውስጥ በመኖር የከንፈር ጭገርን መሸሽ ይቻላል?

የኒቼ ህይወት የተመሰረተው በሊች በሚፈራት ገሃድ ዓለም «ሽሽት» ላይ ነው። ገሃድ ተሸሽቶ ወዴት? እውነት ተፈርቶ ምን?... ግን...

ኒቼ "The birth of ancient tragedy" የተሰኘ መጽሐፉን አዘጋጅቶ ካጠናቀቀ በኋላ ለእህቱ በፃፈው ደብደቤ "I'm afraid of the real world... I am afraid ...I do not see, I am afraid to see..." ማለቱን ሳነብ ገርሞኝ ስቄ ነበር።

የገዛ ሳቁ ከእኔ ተነጥሎ እንደ ጂኒ በራሴ ላይ አስካካብኝ። ያ ሁሉ የኒቼ የልቦለድ ጀግንነት፣ ያ ሁሉ ጦርነት መናፈቅና ጦረኛነት ለካንስ እውነትን፣ እውነታን ያለመጋፈጥ የመጨረሻ ሽሽት ኖሯል? «ሠላም በሁለት ጦርነት መካከል ያለ የአፍታ ፋታ ነው» ያለው እንደ እኔ ቤቱ ተሸሽጎ ነው? ሳቅ!...

...ሳቅ ዞሮ ሲመጣ ለቅሶ ይሆናል። ካስለቀሰህ ይልቅ ያሳቀህ በአንተ ላይ የማይሽር ጠባሳትነት እንዳበጀ እወቅ። ያ-ሣቁ በእዙሪት ለቅሶ ሆኖ በህይወቴ መጣ። እውነትን ተጠራጠርኩ፣ እውነትን ፈራሁ፣ እውነትን ሸሸሁ...

...የተጠራጠርኩት፣ የፈራሁት፣ የሸሽሁት... እውነት በአስቀያሚ ሐሰትነት የያዝኩት ሁሉ እጄ ላይ አነከረብኝ፤ ፀያፍ አደረገብኝ። ከተዘጋው ደጃፌ ውጭ ያለ ሁሉ አስፈሪና አስጸያፊ እውነት ነው። ገሃድ እና እውነት ሐሰት የተሰኘችው በቅሎ ወላጆች ናቸው።

ሊሊ በሬን ትፋጭራለች።

እግዚአብሔር ቀልድ ሲያምረው እኔን በሊሊ እንድፈቀር አደረገ። ወደ ህይወት የሚንገዝና ከህይወት መልስ ሰታከተ ሌላ ሰው እንዲት የነ-ሮ መገናኛ ነጥብ አለች። ይቺ ነጥብ ናት የእግዚአብሔር ቀልድ። ሊሊ በሬን ስትፋጭር እግዜሩ ላይሆኖ ይስቅ ይሆን? እንዴት ያለ ቀልድ ነው? ቢያንስ ለሰው ልጅ ይሄ ቀልድ እንዳልሆነ ልመሰክር እችላለሁ። መቼም የታዘለ ወንድሚ ላይ የእኔ መደረብ ሊያስቅ አይችልም።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

# 3

# ወደ ውስጥ እና ውጭ

ደጃፌ ተቆረቆረ...

...ከእህቶቼና ከልጆቻቸው ውጭ ደጃፌን ለመቆርቆር የሚደፍር አይኖርም። ሊሊም በሬን ትፋጥራለች እንጂ ደፍራ አታንኳኳም።

«ታለ? ታለ?.. የቡናውን ዕቃ ስጠንና ተኝ» እቴቱ ነበረች።

«ይበቃዋል» ስምረት ናት፤ «ይነሳና ቤቱ ይጠራረግ፣ ይጫጫስበት፣ ቡናውም ከደጅ ይልቅ ውስጥ ቢፈላ ይሻላል።»

ተነስቼ በሩን ከፈትኩት። ቤቱን የምግብና የመጠጥ መቀቀያ ዕቃ እየሞላው ነው። መጻሕፍቶቼ በጆንያ ከአልጋዬ ግርጌ ቆመዋል። ኩንታል ባቄላ ወይም ጤፍ እንዲመስሉ ተፈርደባቸዋል።

ቀድማ የረቲቅ ገባች። ከዚያ ትልቋ የስምረት ተከተለች። እቴቱ በሰው ሰራሽ መከላተር ቤቱን በንቃት ቃኘችው። የማደርገው ስላጣሁ መስኮቱን ከፈትኩት። ምድር ስለሰዎች ጥፋት እየተቀጣች ነው። በትናንሽ ምንጮች ፈንታ ወንዙን የሚገብሩት ሠገራ ቤቶች ናቸው። አፋፉ ላይ የትዱስ ዮሐንስ ጠበልተኞች ነጠላ ተከናንበው ቁጢጥ ቁጢጥ ብለዋል። ነጫጭ አሞሮች ይመስላሉ። ወንዙ ዳርና ዳር የበቀሉት አንዳንድ ችግኞች ጎርፍ ያመጣውን ላስቲክ አሸርጠዋል። በእርግጥም ምድር ስለሰዎች ከፋትና ግዴለሽነት ታማለች። መሬት አፍ አውጥታ ፈጣሪዋን እንደጠየቀች «ፍካሬ ኢየሱስ» ላይ አልተገለፈምን?

«ምን አደረግሁ ጌታዬ?» አለች መሬት

«ጋንቺ ያለው ሰው ሁሉ እኔን አላወቀምና ይህን ምልክት ማድረጌ እንዲያውቁት ነበር» ከፈጣሪዋ የተሰጣት ምላሽ ነው።

ከጎላዬ ልብሴ ሲጎተት ዞርኩ። የረቲቅ ነበረች። «አሳየኝ» አለችኝ። ትልቅ ሆናለች። አቅፌ በመስኮቱ ወደውጭ አሳየኋት። ትልቋ የስምረትና ትንሿ ተደረደሩ። ተራውን አደረስኳቸው። የትውልዱን ገመና ለመጪው ትውልድ እየገለጥኩ መሰለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ምድርን ያሳመመው የቢች አገር ገመና በሚያፍሩበት ትውልዶች ዘንድ እንዲወሳ አደርጋለሁ።...» ስል ትንቢት መሳይ አሳብ ዳሰሰኝ።

«...እንደበታቸው እንደተሳለ ምላጭ ነው። አፋቸው ለአመፅና ለተንኮል እንደንቃቃት የተከፈተ ነው። ከእውነት ይልቅ ሐሰት መናገር ይወዳሉ፣ ልባቸው ለክህደት፣ ሆዳቸው ለክፋት የተዘጋጀ ነው» ተብሎ እንደተገፈ።

እህቶቼ ሲመጡ ሊሊና የቹቹ እናት እንደ ጥላ ከምድር ያፈገፍጋሉ።

ስምረት ገብታ «እስኪ ውጡ፣ ቤቱን ላዘጋጀው» አለች ልጆቹን «አንተ አልጋው ላይ ሁን» ህልሟን በነጋሪት ጋዜጣ እንደታተመ አዋጅ ማመን ከጀመረች ቆይታለች። እሱኑ ልትለፍፍልኝ መሆን አለበት።

«ዛሬ ሩፋኤል በህልሜ ተገለጠልኝ፤ ህልምም አይባል፤ ገሃድ ነው። ሬቲትና ጠኔ ልጆች ድብብቆሽ እንዲጫወቱ ሆነው እኔን በዛፍ ተከልለው ሲሳሳቁ ብንን አልልም?»

«የተደበቁበት ዛፍ ጎርፍ ያመጣው ላስቲክ አሸርጦ ነበር?»

«እ?»

«ማለቴ፣ እንዴት?» ደነገጥኩ። ያሰብኩ እንጂ የተናገርኩ አልመሰለኝም ነበር።

«እንዴ የሆነውን ልብ ብሎ ማየት አይበቃም? ሬቲት...» ብላ ልጇ እንዳትሰማት ገልመጥ አለች። «ሬቲት ጠፋች በተባለ፣ ዕለቱኑ ጠኔ ወደ ውትድርና ሄደ። ሳይፈልጉት ለምኖ ነው አሉ የሄደው፤ ከዚያ እሱም እንደ ሬቲት የዘመተበት ግንባር ላይ ጠፋ፤ ይሄኮ ግልፅ ነው። እኔ የዋህ ስለሆንኩ ሩፋኤል በህልም እስኪገልፅልኝ ጠበኩ እንጂ አንድም አያጠራጥርም።»

እውን አይሆንም የሚባል ህልም እና ወደ እውነት አይለወጥም የሚባል ውሸት የለም። ሬቲት ከብርሃን ትብዕቷ ተላቃ፣ ጠናጋሻውም መሞቱን በእናት ክፍሉ አስመዝግቦ፣ የተቀጣጠሩበት ተገናኝተው፣ ከስምረት ጋር የልጆች ድብብቆሽ ቢጫወቱ እንደተአምር አላየውም። እንደውም ሬቲት የብርሃን ኮረዳነቷ ቀጥሎ ጠናጋሻው አትፏት በፒያሳ አደባባይ ሲዝዙ ብመለከት ተገርሜ እጅን አፌ ላይ አልጭንም።

የከፈትኩትን መስኮት ዘግቼ አልጋው ጫፍ ተቀመጥኩ። የእህቶቼ ቤት ማዘገጃጀት የእኔ የሆኑ እቃዎችን እየወሸቁ የእነሱ የሆኑትን ማውጣት ነው።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

መጽሐፍቶቹን በጆንያ እንደታሰሩ ከግርጌ አንስታ ወደ አልጋ ሥር ስመከተት ትንደፋደፍ ጀመር።

‹‹ውይ! እንዴት ይከብዳል? ምን ጉድ ነው፤ መማገድ ነበር›› ትነጫነጫለች።

ስለሳ ነው። ዝም ካልኩ በጆንያ የመከተት ነፃነቷን እንዳረጋገጠች ሁሉ፣ እሳት ውስጥ የመማገድ መብቷን አውን ታደርጋለች። ቀና ብላ ስታየኝ በክፉ አይን ቀለበኚት። ተደኑጋገረችና ጆንያውን የገጠመችውን ነፃ ትግል ተሸንፋ ተወችው።

ሦስት ቀን፣ ሦስት ሌሊት የሰበሰኩትን አውልቂ ሌላ የታጠበ ለፈልግ። እቴቴ ገባች።

‹‹ምን ልትሆንን?››

‹‹መስሪያ ቤት ሄጄ...››

‹‹አገር ምድሩ አብዷል፤ ጥይት እየተተኮሰ የት ነው የምትሄደው? አርፈህ ተቀመጥ፤ እኛ ካሰጠላንህ ቡናውን ውጭ እናፈላለን።››

ዝም ስል እንደ ‹‹አዎ›› ቆጥራው ስምረት ያቀራረበችውን የቡና እቃዎች ማወጣጣት ጀመረች። ምክንያት ኖረም አልኖረም አመፅ ግድ የሆነበት ጊዜ እንደሆነ አውቃለሁ። ሩሲያዊው ደራሲ ሌቭ ቶልስቶይ የህዝብ እንጂ የግለሰብ ታሪክ ስራ የለውም እንዳለው ነው። አንድ ሰው ብዙ ሰዎች ጎርፍ ሆነው፣ ጠራርገው የፈለጉበት ቦታ ያደርሱታል እንጂ ታሪክ ልስራ ብሎ ከቤቱ የሚወጣ የለም። እኔ ደግሞ የልብ ድካም መስል የሞራል መሰለብ ባይኖርብኝ ኖሮ የማጠፋው ሰውና ታሪክ ብዙ ነበር። በናትሁት እውነት መመናተል ዕጣ ፈንታዬ ሆኖ አልጋ ላይ ወጣሁ።

...የጠላሁት፣ የፈራሁትና የሸሸሁት እውነት ሊሊን እና የቹቹን እናት ብቻ መሠረት እንዳላደረገ አውቃለሁ። አየሩ፣ ፀሐይዋ፣ ሠፈሩ፣ ወንዙ፣ ሰው መሆኔ፣ እግዚአብሔር መኖሩ፣ ህገበ፣ ልምዱ፣ ባህሉ... በተለይ እህቶቼ መኖራቸው የአስፈሪ እውነታዎቼ ምክንያቶች ናቸው።

እህቶቼን ሽሽት ጣሊያን ሠፈር ቤት ተከራየሁ፣ መጡ... ገዳም ሠፈር ገባሁ፣ መጡ... አባኮራን ሠፈር ተሸሸግሁ፣ አገኙኝ... ቄስ ሠፈር ገብቼ በረድ ሠርዌ አባት ጥምጥም ተከለልኩ፣ ጥምጥሙን ፈትተው እንደ ራስ ቅማል ለቀሙኝ... ተረት ሠፈር አደፈጥኩ፣ የተረት መጽሐፍ መሀል ተጣጥፌ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ትርክት አድማቂ ምስል ሆኚ ያገኙኛል። የት ልሂድ? ጠላፊ ሠፈር፣ ቋሚ ሠፈር፣ ልምጭ ያዥ ሠፈር፣ ፓፓ ላሬ፣ አቧሬ፣ ካራቆሬ...

...እናታቸው ያወረሰቻቸውን ረከቦት፣ ስኒና ጀበና ይዘው ነው የሚያፈላልጉኝ። ሲያገኙኝ ማንደጃ ከጎረቤት ይዋሳሉ፣ ብረት ምጣድ ይቀበላሉ፣ ቡናውን ከመቀነታቸው ላይ ይፈታሉ፣ ይቆላሉ፣ ይወቅጣሉ፣ ይጥዳሉ፣ ያፈላሉ... ቡና ቁርስ እኔን ያደርጋሉ። አበቃ! በተዋወኩበት ሳይሆን እህቶቼ በሚጠሩኝ ስም የሰፈሩ ሰው መጥራት ይጀምራል።

ታሰ! ታሰ! ታሰ! ታሰ!...

...ጊዜ ሲገፋ መንደሩ ውስጥ እንደእህቶቼ «ታሰ ይሙት!» እያሉ እንደ ዘዴ የሚጠቀሙ ይበዛሉ። «ሌስኪ ታሰ ይሙት በይ!» የሚለው የመሃላ ዘዴ ሹፈት ሆኖ ይሽንትረኛል። ሠባራ ባቡር ውስጥ መኖር ያስጠላል፣ ሽንት ቤት የሚያስገባረውን ወንዝ ማሰብ ስሜትን ያስፀይፋል፣ የቤት ኪራይ ደረሰ አልደረሰ ብሎ አለማሰብ ሰው መሆንን የሚጋፋ ነው፣ የተቋጠረ ስህን ቤት እንደሚጠብቅህ እያሰቡ መስከር ክብረነክ ይሆናል፣ ደሞዝ ደረሰ አልደረሰ ለማለት አለመቻኮል ከሰው ልጅ የጊዜ ግንዘቤ ጋር ይጣረሳል። ጋዜጠኞች ሁሉ በሚቸገሩበት በዚህ ሰዓት አለመቸገር ጥገኛ ተባይነት እንዲሰማ ግድ ይላል፣ በሲሲ መፈቀር ሊከላከሉት የማይቻል ውርደት ይሆናል፣ በቹቹ እናት «ልጄ» መባል ህልምና እውነን ያጣርሳል...

ሲሲ የደጃፏን መከፈት ልትጠቁምበት የማትደፍራቸው እህቶቼን እያሰፈች ትመላለስ ጀመር። አንድ ቀን ሲያለቅስ ስሜቴ የማላውቀውን ልጅ እያባበለች። አንድ ቀን ነትቶ ያላየሁትን ልጅ ለማስተኛት እየወዘወዘች። ረሃብተኛ አይኖቿ ያስፈራሉ። እኔን ለማፍቀር ሳይሆን ለመብላት የጎመጀች ያስመስሉባታል። በበሬ እንዳሰፈች ሳትመለስ በሬት ደጃፏን መለስ አደረከት።

በእኔ መጨነቅ እግዚአብሔር እየሳቀ ነው። እንዴት ከእኔ ከፍጡሩ ያንሳል? እንደ ልጅ ኢያሱ በልጅነቱ በውርስ የተሾመብን ሌላ አምላክ ይሆን እንዴ? የፈጠረን፣ የሚያውቀንስ በዚህ ድክመታችን አይላለትም፣ ይሄን አስቀያሚ ነገር አይሸምንም። እኔን ይተው ሲሊን አያይም? አሁን የእሷ ኑሮ ፍቅር የሚያሻው ነው? እኔ ያየሁትን እንዴት እግዚአብሔር ሳያይ ቀረ? ሲሲ ወንድሟን እንደተጫነች ውላ ማደሯ በቂ አይደለም? እንዴት እኔን ይጨምርባታል? ሰላው ቀርቶ እናቷ ከገሏት ሲመጡ ጭንቷን አያራግፉላትም፣ እንዳዘለች ልጇን ተስቅሰው ጀርባዋ ላይ እንዳለ አጥብተውት



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ይሄዳሉ። በዚህ መንገድ ስንት ወንድሞቿን አሳደገች? ወደፊትስ ስንት ታሳድጋለች?...

አልጋው ጫፍ ላይ ስቀመጥ እግሮቼ ተንጠለጠሉ። ሊሊ ላይ የታዘልኩ ያህል ተሰማኝ። ቶሎ ወዳልጋው ወጥቼ ተንጋለልኩ።

እንዴት እንዳፈቀረችኝ አወኩ? ያላፈቀረችኝ እንደሆነስ? ፍቅር የሚመስሉ ብዙ አይነት ስሜቶች የሉም?...

...እዚህ ሠፈር የገባሁ ሰሞን የሊሊ ሁኔታ አይኔን ይስበው ነበር። የተነባበረ ሁለት ካስ መስሉ ጀርባዋ ላይ የተሸፋፈነ ልጅ አዝላ የተለሰነው ደጃፊ ላይ በክሰል አስምራ «ካሬ» ትጫወታለች። አንድ ቀን ለማናገር ሞከርኩ። ስመጣ ተደነባብራ በሩን ስትሰት

«ያዘልሽው ወንድምሽ ነው?» አልኳት።

«አዎ።»

«ሁሌ አንቺ ነሽ የምታዝይው?»

«አዎ» ፊቷ ስልክክ ነው።

«እናትሽስ?» ችግር ይሆን ሰልካካ ያደረጋት?

«ሞንትራሌ ሄዳ ፍራፍሬ ታመጣና ትሸጣለች።»

«ከምታዝይ አንቺ ብትሸጪ አይሻልም?»

ቤተሰባዊ አመፅ ልቀሰቅስ ነው? እያልኩ።

«ትባልጊያለሽ፣ አይሆንም» አለችኝ።

የመከሳቷን ሁኔታ ላይ እንደ እቴቴ ወንድሟን የእንጀራ እናት ጡት ታጠባው ይሆን? የሚል ሀሳብ መጣብኝ።

«እህቶችህ መጥተው፣ የሚበላ ቤት ውስጥ በጎድጓዳ ሳህን አስቀምጠዋል። ብላ በሉት ብለዋል። ቡና አፍልተዋል፣» አለችኝ።

እህቶቼ ያመጡትን ሰሀን እንደተቋጠረ አውጥቼ ሰጠኋት።

«ለምን?»

«ከወንድምሽ ጋር ብዪ።»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እኛ አንበላም፡፡››

‹‹ለምን?››

‹‹እናታችን ትገድለናለች፡፡››

እናቶች ‹‹ንፁህ ደሀ ነኝ›› የሚሉት ይሄንን እየተራቡም የተገኘውን አለመብላት ይሆን?...

በሶስተኛው ቀን ግብገር እኔ ቤት ገብታ በሩን መለስ አድርጌላት፣ መብራቱን አብርቼላት ጥቂት በላች፡፡

‹‹ሲጣፍጥ!››

‹‹ብዬ እንጂ፡፡››

‹‹ብቃኝ ይለምድብኛል›› አለች፡፡

‹‹ከማያዛልቅ ጥጋብ የለመድኩት ረሃብ›› ማለቷ እንደሆነ ሲገባኝ ሀዘን አናወጠኝ፡፡ ‹የሰማይን አእዋፍ እዩ›› የተባልነው የምግብ ቃል-ኪዳን የታል? ‹‹አያርሱም፣ አያጭዱም›› ማለት ካልሰጠን ማዘናጋቱን ምን አመጣው? ‹‹አትረሱ አትጨዱ›› አይደለም? ‹‹የሰማይ አባታቸው ይመግባቸዋል›› ማለት እናንተንም የሰማይ አባታችሁ ይመግባችኋል አይደለም? የታለ? ያላረሱት ቀርቶ ያረሱትም እየተራቡ አይደለም?

‹‹ስምሽ ማነው?››

‹‹ሊሊ››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹እንጃ፣ ስወለድ ስም የለኝም ነበር፣ የአክስቴ ልጅ ሊሊ አለችኝ፡፡ እናቴን ስም አውጪልኝ ስላት ትምህርት ቤት አትገቢ ምን ያደርግልሻል? አለችኝ... ልሂድ!›› ሹልክ ብላ ሄደች፡፡ ከእሷ የተረፈውን (እሷ የነካካችውን) ለወንድሞቿ አበላኋቸው፡፡ ሁሉም በእናታቸው ሲደበደቡ አደሩ፡፡

‹‹እኔ፣ ከሌሊት እስከ ሌሊት የምለፋው ለማን ሆኖ ባለቤት እንደሌለው ውሻ የሰው ድስት ጥራጊ የሚጣልላችሁ?››

ልጆቹ ባለባቸው፣ በተለይ ተፈሪ ይመጣና ‹‹የድስት ጥራጊ አላችሁ?›› ይላል፡፡

‹‹አለ›› እለዋለሁ ፈገግ ብዬ፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ትፈልጉታላችሁ?›› አይኑ ብልጠት ተከሏል።

‹‹እንፈልገውም።››

‹‹እንግዲያው እኛ እንፈልገዋለን።›› ገብቶ ሲበላ ሊሊ ትሳቀቃለች። ማታ ይደበደባል። ጠዋት ይመጣና

‹‹የድስት ጥራጊ አላችሁ?››

‹‹የለንም።››

‹‹ስሙኒስ አላችሁ?››

‹‹አለን።››

‹‹ትፈልጉታላችሁ?››

‹‹አንፈልገውም።››

‹‹እንግዲያው እኛ ፓስቲ እንገዛበታለን።››

አንዳንድ ጊዜ ሊሊ መጥታ የተዘጋ ደጃፌን ትፋጭራለች። ስከፍት ሳታስበው ለማስመሰል ትደነግጣለች። አስገብቼ እህቶቼ ካመጡት አቋድሳታለሁ።

‹‹ሊሊ የአበባ ስም ነው›› አልኳት አበባ የምታውቅም አልመሰለች።

‹‹አቤት ሲጣፍጥ!››

ምድር ስለሰው ጥፋት ፍዳዋን በምትበላበት በዚህ ዘመን ሊሊን አበባ ቢጠፋት ልትወቀስበት?

እየቆየ ሲመጣ አይኖቿ መራብ የጀመሩ ይመስለኛል። አላግባብ ካላየሁህ ትለኛለች። ጆሮዎቿም ረሃቡ የተላለፈባቸው ይመስለኛል።

‹‹አውራኝ።››

‹‹ምን?››

‹‹እንጃ!››

ግራ መጋባት ጀመርኩ። ወንድሟ ላይ ተደርቤ መታዘል ዕጣ-ፈንታ ሆኖ ብቅ ያለ መሰለኝ። አከራዩ እትዬ ደጅይጥኑ ጉዳዩን ተረድተው ‹‹ሳይሞቅ ፈላ...›› ከማለታቸው በፊት ያነበብኩት አንድ መጽሐፍ ፍንጭ ሰጠኝ። የፊዮዶር ዶስተየቭስኪ ልቦለድ "Insulted and Humiliated" አንዲት ኒሊ የምትባል



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የአስራ ሁለት ዓመት ገበባህርይ አለች፡፡ የወላጆቿን ቂም ተሸክማ እንድትኖር የተፈረደባት፡፡ እናቷ ያለማንም ድጋፍ በልመና ወንድ አያቷን እንድታስተዳድር ፈርዳባት ትሞታለች፡፡ ይቺ ልጅ በአጋጣሚ ከኖናው ገበባህርይ ጋር ተገናኝታ ከተግባቡና አብረው መኖር ከጀመሩ በኋላ ብዙ ነገሮች እየተለወጡ ይሄዳሉ፡፡ ሁለት ዓመታት ያህል ከኖሩ በኋላ የኖናው ገበባህርይ እጮኛ የኒሊን መቅበጥበጥ፣ ካላጎረሰከኝ አልበላም ማለትና መደ፡ንኒቷን ለመውሰድ የእሱን ልመና መፈለግ ስትመለከት

‹‹አፍቅራህ እንዳይሆን›› ትለዋለች

‹‹እንዴ? ትንሽ ልጅ ናትኮ›› ይላታል፡፡

‹‹ለማፍቀር አታንስም››

ለማፍቀር የማይታነስበት ዕድሜ ስንት ነው? ኒሊ አስራ አራት አመቷ ነው፡፡ ሊሊ ከአስራ ስድስት አታንስም፤ ከአስራሰባት አትበልጥም፤ እና? የምትበላው ሳቀርብላት በመንቶራም ዓይኗ ምን አይኔ ላይ ያንጠለጥላታል?

‹‹አወራኝ?››

‹‹ምን?››

‹‹እንጃ!››

የሚወራላትን ሳታውቅ የምን ጆሮ አቁሞ መቸገር ነው? የምኖር ሳይሆን እንደ ዶስተየቭስኪ የምፅፍ ብሆን ኖሮ በሊሊ ብዙ ወተሳ አይደርስብኝም ነበር? ልቦለድም ከሆነ እንዲህ ያለ ጭካኔ ከእውነት ውጭ ውሸት ውስጥ ይገኛል? ከዶስተየቭስኪ ምናብ ውጭ ያለመው ሌላ ደራሲ ይኖራል?...

‹‹ይሄን አውጣው›› አለኝ በማረም የሚያግዘኝ ዓለማየሁ ገላጋይ፡፡

‹‹የቱን?››

‹‹የዶስተየቭስኪን፡፡›› ሳያኮርፍ ያኮረፈ ፊት አለው፡፡

‹‹ለምን?››

‹‹ሌሉም ከልቡ አመንጭቶ አልፃፈማ፡፡ ለጓደኛው በፃፈው አንድ ደብዳቤ ላይ ‹ሁሉም ልጆችን የሚመለከቱ ታሪኮች በእኔ አልተፈጠሩም፡፡ ሁሉም ጋዜጣ ላይ የወጡ ስለነበሩ በማስረጃነት ላቀርብላችሁ እችላለሁ› ብሏል፡፡››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሙሉ በሙሉ በፍቅር የማስታየት ወንጀሉ ወደፈጣሪ ዞሯል ማለት ነው፡፡ ምን አልነው?

በተጣፍ ቀን የዶስቶየቭስኪን ምስክርነት መጽሐፍ ላይ አስምሮ አመጣልኝ፡፡ አነበብኩት፡፡ "All the stories about children happened, were printed in the papers, and I can show where, nothing was invented by me" ይላል፡፡

ዓለማየሁ አኩራፊ ብቻ ሳይሆን እንደማይቀር ገመትኩ፡፡ እርቃኢነቱን ያልተቀበልኩት ስለመሰለው ነው ሳይረሳ ማስረጃ ይዞ የመጣው፡፡ ትዝ እንደሚለኝ እንጣላ ይሆን? የሚል ሥጋት ሳይኰከኝ አልቀረም፡፡

አንድ ቀን ረድ ሠርዊ እኔ ቤት መጥቶ ቁጭ ብለን ስናወራ ተፈሪ መጣ፡፡

‹‹እኔ የምለው?›› አለ፡፡ እንደሰውነቱ እንጎሉም በኑሮ እጥረት ቀንጭሮ የተልቅ ሰው ሳይሆንበት አልቀረም፡፡

‹‹አንተ የምትለው?››

‹‹የድስት ጥራጊ አላችሁ?››

‹‹ልጅ ተፈሪ፣ የለንም›› አልኩት እየሳቅሁ፡፡

‹‹የኪስ ጥራጊስ? አላችሁ?››

‹‹የኪስ ጥራጊ ምንድነው?››

‹‹ሰሙኒ ነዋ፡፡››

‹‹እሱስ አለን ልጅ ተፈሪ››

‹‹ትፈልጉታላችሁ?››

‹‹እንፈልገውም፡፡››

‹‹እንግዲያው እኛ እንፈልገዋለን፡፡››

‹‹ለምናችሁ?››

‹‹ፓስቲ እንገዛበታለን፡፡›› ረድ ሠርዊ ከኪ ተሽቀዳድሞ ሰጠው፡፡ ከዛች እለት በኋላ ረድ ሠርዊ ቤቱ ሆነ ቢሮዬ ሲመጣ ጭንቅላቱን ብቅ አድርጎ ‹‹እኔ የምለው፣ የድስት ጥራጊ አላችሁ?›› ይል ጀመር፡፡



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## 4

## ወደ ዝቅ

እህቶቼ ከመምጣታቸው በፊት ማልጄ ከቤት ወጣሁ፤ ሠንበትን ተዘግቼ ለማሳለፍ አልፈለኩም፡፡ ደጃፌን የመቆለፍ ልምድ የለኝም፡፡ አንድ ሁለት እርምጃ እንደራቅሁ ከኋላ ተጠራሁ፡፡ አዝላ ስትሮጥ ድምጿ እየተናጠ እንደረድ ሠርዊ ስብከት ግማሹን ንፋስ የወሰደው ይመስላል፡፡

‹‹ታ- - ታስ- - ስ- - -ታ››

ቦር ብዬ አየኋት የወንድሟ ጭንቅላት ተንጋዶ ባለሁለት ራስ መስላለች፡፡ አብሬህ ልሂድ ልትል ይሆን? ያ-አንጋዳ ህልም ትዝ አለኝ፡፡ ወንድሟን እንዳዘለች እጆችንን አቆላለፍን ወና አደባባይ ያካለልንበት፡፡

‹‹የት ልትሄድ ነው?››

‹‹መጣሁ፡፡››

‹‹ቤት አትለቅም አይደል?››

ሥጋቷን፤ የእኔ ሥጋት ምንድነው? ቢበዛ የሲፈን ልጅ ውሸት እንደተባለው በይርጋ እንዲቀር፣ ወደ እውነታ እንዳይሸጋገር፤ የእኔ ብቸኛ ስጋት እሱ ነው፡፡ ውሸት እንደሆነ ቢነገረኝም ጭንቅላቴ ውስጥ የገባው፣ ሀሳብ ሀረግ ይመስል በቅሎ አንጎሌን እንደ ደም ስር አልብሶታል፡፡ እናቴ ከሲፈን ተቀብላ አሩሲ ይዛት ሄዳ እንደሆነስ? ሲፈን ውሸት ነው በይ ተብላ እንደሆነስ? ልጁ አድጋ ስትጎረምስ አምጥተው ሊሰጡኝ እንደሆነስ?...

‹‹እ? ቤት አትለቅም አይደል?››

‹‹አዎ›› እኔም እንደወንድሟ አስተዛዝሏ ያንጋደደኝና ባለሦስት ጭንቅላት እንግዳ ፍጡር ያደረጓት መሰለኝ፡፡ እንደቆመች ጥያት ፋንዶ ሜዳን ወደግራ ትቼ ጠበል የሚወስደውን ኮረኮንች መንገድ ያዝኩ፡፡ ግራቀኙን የጠላና የአረቄ ቤት ሁከት ነግሷል፡፡ ሐሪፍ ህይወት ያስተናል፡፡ ነጋጠባ ሥጋት የአረቄ መጠጫ ማጣት፤ በቃ! ሰው የመሆን ጣጣ በአረቂ መጠጫ መገኘት ሲጣጣ...

‹‹እስጢፋኖስ፡፡››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«አይደለሁም!» ያቺ ባሌስትራ መሰል ሴት።

«እስጢፋኖስ ንጉሱ።»

«አይደለሁም አልኩ፤ እኔ አልአዛር ብዜን ነኝ።»

«እሱ አሳዳጊዎችህ ያወጡልህ ነው» ጥቁር መልክ ላይ ቀይ አይን የእብደት ምልክት መሰለኝ። ቢሆንም መስማት አልፈለኩም። እውነትን የተማመነ ጉም የዘገነ መሆን ሰልችቶኛል።

«ተይኝ እባክሽ፣ ልጅሽ ቺቺ ነበር። ምናልባት እስጢፋኖስ ንጉሱ የእሱ ስም ሊሆን ይችላል።»

«ሳላውቅ እኔ የቺቺ አሳዳጊ ያወጣሁለት። አሁንም እናቴ እኔ እመስለዋለሁ አሉ። ከእናትህ ላይ የተረከቡት ፈረንጆች ስሙን ወደ እንግሊዝ አፍ ቀይረው... ማነው ያሉት? ማነው እስጢፋኖስ በእንግሊዝ ምንድነው ፍቺው?» ጠየቀችኝ ለመገላገል:-

«ስቲቨን» አልኳት።

«አዎ፤ ንጉስስ...»

«ኪንግ» ካልኩ በኋላ ገጣጥሜ ከት ብዬ ሳኩኝ። «ስቲቨን ሀውኪንግ ቺቺ ነው?»

«አዎ፣ የወሰዱት አማካሪዎች ስሙን ተርጉመው፣ የሚነዳ ወንበር ገዝተው፣ እሱ ያላለውን ብሏል እያሉ ለአሜሪካን ህዝብ ይገልጣሉ። በእናትህ ዘር ኮኮብ ቆጣሪ ከየት መጥቶ እሱ ኮከብ ይቆጥራል? ብቻ ፈረንጅ ተላላ ነው። አምኗል አሉ።»

«ኪንግ ብቻ አይደለም፣ ሀውኪንግ ነው። ሀው ምንድነው?»

«እናትህ የአሩሲዋ እመቤት ጋ ሄዳ ከሰለመች በኋላ ሀዋ ተብላለች። ስለሚወዳት የእናቴን ስም ጨምሩ ብሎ ይሆናላ።»

አይሆንም አይባልም፤ እውነት አያስተማምንም። ቢሆንም ያስቃል። ይሄን የእውነት ተረት ገጣጥሞ የነገራት ማን ይሆን?

«እስጢፋኖስ ንጉሱ አንተ ነህ። እናትህ እኔን በድግምት አነሁልላኝ ሳይገለጥልኝ አንተን የእሷ ልጅ አድርጋ ቆየች። አሁን እድሜ ለአባቴ ድኛለሁ። ገለታ ይግባለት! እውነተኛ ልጄን አንተን እፈልጋለሁ።»

ዝም!



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«አንድ ምስጢር አለኝ። በዚች ይገኘት የኖርኩት» የተጨማደደ ሆዳቸውን በመዳፋቸው ጠፈጠፉና፤

«አንዳንተ ሶታ ወጣት ሳለሁ ለዓለም ብርሃንነት ታጨሁ። እኔ ግን መስቀለ ህማማቱን ፈራሁ። እንዴት ችዬ ጎኔን ልወጋ? እንደምን ሆኖልኝ ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ጊዜ ልገረፍ? መሀፋቱንና መንጓጠጡን ልቻል፤ የሕጀንና የእግሬን መቸንከር እንደምን አድርጌ? ይቅርብኝ አልኩኝ። የዓለም ብርሃንነቱ ይቅርብኝ። እራሱ ባለቤቱ «ይቺ ፅዋ ከእኔ ትራቅ» አላለም? እሱ ያልቻለውን እኔ ብሸሽ ይፈረድብኛል?»

ጥቂት አንሸነፍም ባይ ወጣቶች ድንጋይ ይዘው «ወያኔ ሌባ፣ የተሰረቀው የቅንጅት ድምፅ ይመለስ! ወያኔ ሌባ» እያሉ ቁልቁል ወረዱ። ነገሩ ተገለባብጧል። «ሌባ» ያሉት ሰው ጣት እንደሚቆርጥ ዝቷል። «ሌባ» እጁ ሊቆረጥ የነበረበትን ዘመን ለመበቀል ሌባ የሚያሳድደውን ሊጎማምድ ነው። እውነት እንዲህ ናት።

«መንታ ወንድሜ መቼም ሲፈጥረው የእሳት እራት ነው። እኔ የዓለም ብርሃን እሆናለሁ አይልም። ብለው፣ ብሰራው እምቢ አለኝ። እኔ የገዛ ሥጋዬ ለዛ ሁሉ ሥቃይ ሲታጭ አላይም ብዬ ጠፍቼ አዲስ አበባዬ ገባሁ። አሁን በቅርቡ ደግሞ ምን የሚል መልእክት ይመጣልኛል። አርጅተሃልና ለዓለም ብርሃን አትሆንም። ከሆነልህ ኢየሱስ ዓይኑን የሚያበራው አዛውንት ሁን። ልብ በል አይኔን ሊያጠፉኝ!!»

«መንታ ወንድም አልዎት?» ነገር አጠናቅረው መረዳታቸውን ለመፈተሽ።

«አለኝ እንጂ፤ እኔ ወዳዲስ አባ ስጠፋበት የዓለም ብርሃንነቱ ቀርቶበት ጠልቶኝ ኖረ። እስጢፋኖስ ይባላል።»

ተያያዥነት ያለው ቅዠት ህይወት እያልኩ የምኖር ሆኖ ተሰማኝ።

«ቴአትር ነው የምትሰሩት? ማለቴ ለስቅለት ወይም...»

«አይደለም፤ የእኛ አገር ሰው መናጢ ነው። የወንጌሉን ታሪክ ወደ ኢትዮጵያ አመጣለሁ ባይ ነው። አጓጉል ህልም ይዞ በገዛ ልጁ ላይ ይፈርዳል። የእኛ አገር ሰው ግም ነው» ብርሌአቸውን በፀሐይዋ አንጥረው ተመልክተው ወደ አፋቸው አጓ ቱ። ጠጁ ሲንቆረቆር ተሰማኝ።

«ቆይ ቆይ ቆይ ቆይ...»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የስተርጅና እብደት ለማመፅ ጉልበት ስለማይኖረው የተፋለሰ ነገር የማሰብ ትጋት ይታይበት ይሆን? የቹቹ እናት፣ አሁን ደግሞ እኚህ አዛውንት... ማን ያውቃል በእብደት ተከልዬ አለፍኳቸው እንጂ ፊትሬ ብይዛቸው ኢየሱስን የመሆን እድላቸው እውነት ሆኖ አገኘው ይሆናል። እውንን እምኜ ጉም ዘግኜ መመለስ የሰለቸኝ ሰው ነኝ።

ከረድ ሠርዊ ጋር የማወራው በተቻለ መጠን የተረጋጋና መሬት ያስቀቀ እንዲሆን ተመኘሁ። ጣሊያን ሠፈር ከስምረት ቤት ጀርባ አንድ ክፍል ተከራይቶ ብቻውን ይኖራል። ስምረት የምትኖርበት ቤት የጣሊያን ሠፈር ተጎራባች ይሁን እንጂ የገዳም ሠፈር አካል ነው። የጥንቱ ቤት የጥንቱ ታሪክ እንደ አዛውንቱ በሆዱ ይዞ የሚያመናትል ይመስላል። ጠናጋሽው እንደነገረኝ ቤቱ ሁለት ታሪክ የሰሩ ወንድማማቾች ያደጉበት ነው። መንግሥቱ ነዋይና ግርማሜ ነዋይ፣ አባታቸው አለቃ ነዋይ በዘመኑ እውቅ ሙያተኛ ያሰሩት ደርባባ ቤት። ስምረት እንዳታየኝ ተጠንቅቄ ወደ ጣሊያን ሠፈር ተሻገርኩ።

ጣሊያን ሠፈር ሲገቡ አምስት አመት ብቻ መገዛታችንን የሚያደናግር ነገር ይፈጠራል። ጣሊያን ሥሙን፣ ዘሩንና መታወቂ ቅርሱን አፍስሶት ሲታይ ሃምሣ አመት ቢቆይ ኢትዮጵያ ሥሟም፣ ዘሯም፣ ቅርሷም ተሸጎርጉሮ አደናጋሪ ሀገር ሆና ትቀር ነበር ማለት ነው? ያሰኛል። የእኔም ሥም አንዴ ታለ፣ ሌላ ጊዜ ታለስ፣ ቀጥሎ አልአዛር፣ ቆይቶ ደግሞ መጥምቀ መለኮትና ጌታየነህ፣ ክሊያ እስጢፋኖስ... እየሆነ ከምቸገር አንዴ ጁሴፔ ተብዬ እገላገል ነበር። በብዙ ትይጥ ልጆች መካከል፣ ሉሚ ፀጉር እየዳበስኩ አልፌ የረድ ሠርዊን ደጃፍ ቆረቆርኩ፣ ደገምኩ፣ ድምፅ ሳጣ ባይኖር ነው ብዬ በሩን ሞከርኩት፣ ተከፈተ።

«ረድ ሠርዊ።»

«ምቱረ ከሳድ መጥምቀ መለኮት» የሚል ምላሽ ስጠብቅ የለም። ሠርዊ አልጋው ጫፍ ላይ ተቀምጦ እንዳቀረቀረ ነበር። ግንባሩ ላይ ሽንትር ቁስል ተጋድሟል። ቤቱ ውስጥ ጥቂት መጻሕፍት እዚያም እዚህም ተበታትነው ይታያሉ። ክብር የሚያስፈልጋቸው መንፈሳዊ መጻሕፍት እንኳን አንዱ ተደፍቷል፣ ሌላው ተገልጧል። አንደኛው ላይ ደግሞ የሻይ ስኒ ተቀምጦበታል። ከምሳ ማምጫ ጎድጓዳ ሳህኖች ውጭ ሁለት የቆዳ በርጩማዎች ጥግ ጥግ ይዘው ይታያሉ። ሁለት ሙሉ ልብሶች ከላውንደሪ ላስቲክ ጋር ግድግዳ ላይ ተንጠልጥለዋል።

«ምን ሆነሃል?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ምን የሆንክ አመስላለሁ?››

ፊትህ በፍሳሽ ውኃ እንደተቀቀለ እግር ነጭ ሆኗል፤ አካልህ ጎስቁሏል፤ ግንባርህ ላይ የአባቱን ጥይት መፍለቂያ የመሰለ አግድም ቁስል ይታያል... ለበሰው?

ዝም!

‹‹የአባት ደመኛ ሰቶኛል። ባለፈው ጊዜ ለምን እንደሆነ ሳላውቀው የሚያስተዳድሩት ደብር ሄጄ የንታ ፊት ተንተርኩ።

‹‹'ደግ ነው ስጠራህ መምጣት' አሉኝ።

‹‹'እረ አልተጠራሁም የንታ፤ ማን ጠራኝ?' አልኳቸው።

‹‹'ኢስመ ልብ ይኤዝዝ ከመንግሥ አልተባለምን?' አሉኝ። በልቤ ጠርቼህ ነው ሊሉኝ ነው። ገባኝ። ነገር እንደፈለጉኝ ገባኝና እኔም፤ ከድርሳኑ ዮሐንስ አፈወርቅ ውስጥ ‹‹'ኀሊና ልብኒ ዘይከብር እምኔሁ አይትከህሎ ይጠይቅ ምንተኒ እምኔሁ። ይልብዎታል የንታ' በማለት ነገርን በነገር ለመዝጋት ሞከርኩ። ('ኅሊናና ልብ የጌታን ነገር ማወቅና መረዳት አይቻላቸውም' ያለውን ማመሥጠሬ ነበር።)

‹‹አሁን ገና ክጌታ መንበር ወጣህ? ታበይክ፤ የለከፈ ለክፎህ ነው። አልረገምህም፤ መረገሚያህን ግን እሰጥሃለሁ። ለግርማ ሞገሥ እንደተነቀስክና መድፈነበር እንደምትደግምም አሉቃ ሞገሴ ነግረውኛል። አሁን የድጋምህና የመቅበርትህ ፍቱንነት የሚረጋገጥበት ጊዜ ደርሷልና እስኪ ተከብረህና ተፈርተህ ትኖር እንደሆን አያለሁ።' ብለውኝ ሲሄዱ መቼም መናጢ ናቸውና እግራቸውን ይዤ ተማጸንኳቸው። 'እርስዎ ይቅጡኝ' አልኳቸው። አሻፈረኝ ብለው ሄዱ። 'ወትሮስ የልጅ ነገር ምን ይገድዎታል፤ የንታ' አልኳቸው። እኔም ተጸፍሬአለሁ፤ እያየሁት ጥምጥማቸው እንደኪስ ጉኖ ተመሬት ወደቀ። የዕድሜአቸውን ምስጢር ልገልጥባቸው እንደሆነ ሳይጠረጥሩ አልቀሩም።››

ቁጭ በል ብሎ ሳይጋብዘኝ የቆዳ በርጩማው ላይ አረፍ አልኩ። ቁርበት ቁርበት ሸተተኝ።

‹‹ሦስት መዐልት ሦስት ሌሊት ጸለይኩ። የንታ የሚመጡበትን ሁሉ ያጠርኩ መስሎኝ ነበር። በኋላ ግን ዓይኑ ከዓይኔ የገጠመ ሁሉ ከእኔ ፀብ መከጀሉ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ሲደጋግሙብኝ የንታ የመጡበት ገባኝ:: «መስተጻልእ» አድርገውብኛል ማለት ነው:: ከትናንት በስትያ ቢሮ ሄጄ አድማ በታኝ ፖሊሶች ግቢውን ወርረው ሌሎቹን ጋዜጠኞች ትተው እኔን እንዳልሞት እንዳልሽር አድርገው ቀጠቀጡኝ:: ፊኛዬን ረገጡኝ:: ከዚያ ህመሜን እስታገሽ ስወጣ ‹ወያኔ ሲባ› የሚሉት ‹የወያኔ አቃጣሪ› ብለው ወረዱብኝ:: ነፍሴን አድማ በታኝ አትርፎት ሳለ እነሱም ሁብ ከጆሉኝና ጥቂት ጎሸሸመው ሰደዱኝ:: የገዳም ሠፈርና የጣሊያን ሠፈር ሴተኛ አዳሪዎች ሳይቀሩ ለኢየሱስ በአይሁድ የተቀጠሩትን ተሣዳቢ ገንቦኞች ሆኑብኝ:: መናጢ ናቸው እንጂ አባት ልጅን እንዲህ ያደርጋል? ቢጨንቀኝ ዐቃቤ ርዕስና መፍዝዝ መድገም ጀመርኩ::»

«ሕሱ ደግሞ ምንድነው?»

«ሰው ከፉ እንዳያስብብህ፣ የሚያፈዝዝ፣ ሊመታህ የተነሳን አይኑን ጨለማ ጉልበቱን ቂጠማ የሚያደርግ ጥበብ ነው:: ለነገሩ ስድቡም አገር ያስለቅቃል::»

ዝም!

ረድ ሠርዌ የሚነግረኝን ማመን ነበረብኝ? የተማርኩት ይሄን አይፃረርም? የተጨባጭነት ተቃራኒ አይደለም? እንዴት የልቤን ይሁንታ አገኘ? ለመሆኑ በህይወታችን ጥርት ያለው እውነት የቱ ሆኖ አለማመን ይቻለኛል? የሬዲዮ ቴክኖሎጂ የአባቶች ጥበብ ቅጂ እንደሆነስ? በአየር ሞገድ ተጠቅሞ አእምሮ ላይ ተፅዕኖ መፍጠር እንደሆነስ አባቱ የደገሙበት ዓይነቱ? ድግምት የርቀት መቆጣጠሪያ (Remote Control) ባህርይ ያለው ቢሆንስ?... ተጨባጫዊነት ለሌለው ነገር ተጨባጩ ሳይንስ የሄደበት መንገድ ምስክር አይደለም?...

«እስኪ ለእኔም...»

«ለአንተ ምን?...»

«ያሳፍራል ግን ከባች ልጅ... ለባች ልጅ...» የእናቱ ጦስ መልኩን ቀይሮና ሳይንሳዊነትን ማስተንተኛ አድርጎ ሊያስግደኝ እንደሆነ ተሰማኝ::

«ለልጅ ተፈሪ እህት ነው?» አለ ፈገግ ብሎ፤ እሳሳቱ እኔን የሚመለከት እንዳልሆነ ገብቶኛል:: የተፈሪ የምግብ አጠያየቅ ስልት...

«ሕ»

«አይሆንም!»

«ለምን?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«የሰይጣን ሥራ፣ የሰለሞን ጥበብ በሰው ወይም ሌላ አማካኝ የሚባል ነገር አያውቅም። ያልበዛ ወይም ያላነሰ የለውም። ታፍቅረኝ ካልክ ውድድ፣ ትጥላኝ ካልክ ጥምድ ነው። አለመጥላት፣ አለማፍቀር የሚባል አማካኝ ነገር በድግምት የለም! ለዛች ልጅ የሚያስጠላውን ብታደርግላት ዓይንህን ለአፈር ትላለች።»

«ይሻላል።»

«እንዴት?»

«ቤት መቀየር ነዋ!»

«ቤት ብትቀይር ተከትላህ ትመጣለች። ለፀብ መፈለግ አዋራጅ ነው። ያውም የአጋንንት ተራዳኢነት ያለበት ፀብ!»

«ታዲያ ምን ይሻላል? እራሴን እየጠላሁ ነው በእሷ ልጅ»

«አባበላት፣ ይሻላል...»

ያ የማባበል ሀልሜ ታወሰኝ፤ እጇን ከእጄ አቆላልፌ፣ ልጅ እንዳዘለች፣ ወና አደባባይ ላስስ? ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር ጠንክሮ ታየኝ። ያውም የጥላቻን ሚና ሲጫወት።

«እስኪ ዛሬ እንጠጣ» አልኩት። መፍትሔ መስሎ የታየኝ ነበር።

«አዬ፣ ፊኛ ፊኛዬን ረግጠውኝ መነሳቱም አልሆንልኝ ብሎ እኮ ነው።»

«ወይ ካልሆነ የምትታከምበት...»

«ይሻላል።»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

5

# ወደ ከፍ

መታከም አዳጋች ሆነብን። ብዙ ሰዎች ተፈንከተዋል፣ በጥይት ተመተዋል። ሀኪሞች ተሰላችተዋል። ሁሉንም ማመናጨት የሥራቸው አካል ቢሆንም ረድ ሠርዌን ሲመለከቱ ጎፈሉ።

‹‹አንተ ቅድም ሀኪሙ አይቶህ አልሄድክም? መዝናኛ አደረከን እንዴ?›› ነጭ ገዋን የለበሰች ፊቷ በመሰላቸት የተመነጫጨረ። ረድ ሠርዌ ለእሷ ከመመለስ ይልቅ እኔን አየኝ።

‹‹ገና አሁን መምጣታችን ነው እመቤት።››

‹‹እንዴ? ቅድም ለምን ደጋግመህ ትመጣለህ ብዬ አልመለስኩትም? እስኪ እስኪ...›› አመናጭራ ጆርባውን አየችው ‹‹ይኸው፣ ይኸው፣ ጆርባህ የደም መቋጠር ነው በቅባት ስትታሸው ይበተናል አላልኩህም?... የግንባርህን እሽግ ለምን ላጥከው? የምትፈልገው ሌላ ነገር አለ እንዴ?...››

ነርሷ ከጣሊያንና ከገዳም ሠፈር ሴቶች የተሻለች አልመሰለችኝም። በቁስለኞች መካከል ስንሸሽ ‹‹ጥበቃ! ጥበቃ!›› እያለች ጮኸች። ከበስተጓላዋ የረድ ሠርዌ አባት የላኩት ጆኒ ወይም አጋንንት ወይም ጆሮዋ ላይ ሹክ እያለ ወደ ፀብ ሲገፋፋት ታይቶኝ ፈገግ አልኩ። ፀባችን የራሳችን ካልሆነ፣ መውደዳችን የድግምት ውጤት ከሆነ... የእኛ የዚች ዓለም ተሳትፎና ነፃ ፍላጎት የቱ ነው?... ደግሞስ ጉዳዩ የድግምት ከሆነ እኔ ሠርዌን ሳየው ለምን ነገር ነገር አላለኝም? ለምን ከመጣላት ይልቅ ሀዘኔታ ተሰማኝ?

ከራስ ደስታ ሆስፒታል ወጥተን መሄጃችን ተደናግሮን ቆምን።

‹‹እንዳልከው ብንጠጣ ሳይሻል አይቀርም።››

‹‹ጥሩ››

‹‹መዓፊያ ይዘሃል? ብዕር ብጣቂ ወረቀትስ?›› ግንባሩ አሞልሙሎ ተንጋዶ የሚያይ መስሏል።

‹‹ለምን?›› ሊናዘዝ መሰለኝ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ሕስኪ ስሜን ፃፍና ስጠኝ»

«ለምንᵓ»

«እነግርሃለሁ፤ ብቻ ፃፍና ስጠኝ»

ብዕር እንጂ ወረቀት አልነበረኝም። በአይኔ መሬት ስዳብስ የሲጃራ ወረቀት አየሁ። እንስቼ ዕሬ ሰጠሁት። የዘመኑ የአማርኛ ዕውቀት ላይ ተመስርቶ ሙግት ሊገጥመኝ መስሎኝ ነበር።

«አየህ ስሜ በሁለት መንገድ ይፃፋል። ሁለት ፍቺም ይሰጣል። አንተ ‹ሠርዌ› ብለህ የፃፍከው በንጉሡ ሠ ነው። ፍቺው ሠራዊት፣ ምስሶ፣ ኀልማሳ ማለት ነው በግዕዝ። የንታ ሥሜን ሲፅፉ ግን በእሳቱ ‹ሰ› ነው። ያኔ ፍቺው ‹ጉድፍ› ማለት ይሆናል። ‹ቆሻሻ› መቼም የንታ መናጢ ናቸውና ትርጉሙ ሳይገባቸው ቀርቶ አይደለም።»

ገዳም ሆቴል ተዘግቷል።

«ወላንሳጋ እንሂድ» አለ።

ወላንሳ ግሮሰሪ ተዘግቷል። አካባቢው ጭር እንዳለ ነው። ሴተኛ አዳሪዎች ሳይቀሩ ተከተዋል። ‹ወያኔ ሌባ› ከማለት ‹ወያኔ ሽፍታ› ቢሉ ይሻላቸው ነበር። ‹ሌባ› ይሄን ያህል ከተማ ጭር የሚያደርግ ጉልበትና ልብ የለውም። ሽፍታ ነው በዚህ መልኩ የሚያስገብር።

ገዳም ሠፈር ምናልባትም ከአርባ አራት ዓመታት ወዲህ በመጀመሪያው ጭርታ ስትመታ መሆን አለበት። በ1953 ዓ.ም የታህሣሡ ግርግር በሁለት የገዳም ሠፈር ልጆች ሲከናወን የጃንሆይ ተከላካዮች የእስቃ ነዋይን ቤት ለመቆጣጠር ገዳም ሠፈርን ጭር ሳያደርጓት አልቀሩም።

«ታለᵓ ታለᵓ መሪጊታᵓ» ስምረት እንደሆነች አልተጠራጠርኩም። «ጉ ግቡ! ምን ታደርጋላችሁᵓ» የጥንት ጊቢ በር ተከፈተ፤ የዚያ ዘመን ጥጋብ ነውንጂ የግቢ በር ሣንቃ ይሆናልᵓ እንደቤተክርስቲያን ደጃፍ ረጅም መግቢያ በር ያለው አሮጌ ቤት ተከፈተ።

«ወለተ ዮሐንስ» አለ ረድ ሠርዌ ድምፁን ቀይሮ የነፍስ አባት በማድረግ። ስምረትም ምቱሬ ክሳድ ልትሆንᵓ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹መሬቷ በዚህ ክፉ ቀን ከቤት ይወጣል? ክፍሉ ብዙ ነው እዚሁ ተካፍሮፍችሁ ታድሩላችሁ…››

‹‹ወለተ ዮሐንስ የት ነበር የምንተዋወቀው?›› አለች። እንዲህ ነገር እየጎተተ ይሆን የንታ ደገሙብኝ የሚሉው?

‹‹እዚህ ነዋ፤ የባሻ ለንጥቂን ቤት ተከራይተው፤ አይደለም እንዴ?››

‹‹አይመስለኝም፤ እዚህ ማንም መሬቷ አይለኝም። የእናትሽን ቤት ከአባቴ ጋር ተከራይተን መኖራችንን ታውቂያለሽ?››

‹‹ጡረታ ድልድይ?››

‹‹ለ›› እንደ አባቴ የጥይት መከሽፊያውን አሹሉ።

‹‹ኸረ እኔንጃ፤ እዛ ነበራችሁ እንዴ?››

ረድ ሆርዊ ዞሮ እኔን አየኝ። ምን እያረጋገጠ እንደሆን ገብቶኛል። ‹‹አትንጋደድብኝ!›› ልለው ከጀለኝ። በጥይት መከሽፊያው የሚያየኝ መሰለ። ምን እያስታወሰኝ እንደሆን ገብቶኛል። ያኔ ጉዳዩን ንቄ ትቼው ነበር። እንዴትስ ሊታመን ይችላል?

ከውትድርና ስልጠና ተባርሬ በመጣሁ በሶስተኛው ቀን ወደ ፒያሳ ሂድ ሂድ አለኝና ከቤት ወጣሁ። በሥልጠና ላይ አሠልጣኞች የሚሰጡን ሠላምታ ጆሮዬ ውስጥ እያስተጋባ የተቸገርኩበት ወቅት ነበር። የመኪና ጡሩንባ ድንገት ሲያንባርቅ ‹‹አሳችሁ!›› የተባልኩ ያህል ‹‹አለን!›› ብዬ ለመጮህ ይገፋፋኛል።

‹‹አንተ ማነህ?››

‹‹አብዲሳ!›› ማለት ይተናነቀኛል።

ፒያሳን አቋርጬ በሲኒማ አምፒር በኩል ወደ ሠራተኛ ሠፈር ወረድኩ። ቀጥታ ናዝሬቷ ራስ ገዝ አመራሁ። ዝናብና ፀሐይ የተፈራረቁበትን የሳንቃ በር ገፍቼ ወደ ውስጥ አየሁ። ስድስቱ ሻከሰኖች ጫት በመቃም ላይ ነበሩ። የማሪያ ትሬዛ ብር በመሰለ ክፉ አይናቸው አዩኝ። እግሬን ሳስገባ በጋራ ‹‹ሆ!›› ብለው ጮሁ፤ ያፏጨም አለ፣ ያጨበጨበም አለ።

‹‹ምንድነው?››

‹‹እንኳን ደህና መጣህ›› አለ በድንግዝግዝ እይታ ውስጥ በቅጡ ያለየሁት።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«እንኳን ደህና ጠበቃችሁኝ። ከዚህ በፊት መጥቼ አጥቻችኋለሁ» አልኩ።

ሁሉም በጋራ ሳቁ። ፊት ለፊታቸው ስድስት እግር የማይሞላ ጫት ተቀምጧል።

«እዚህ መካከል በደንብ የምታውቀው ሰው አለ? ቢም እስኪመብራት አብሪ።»

መብራቱ በራ፤ ስድስቱም በፀጥታ የእኔን አፍ ይጠብቃሉ። እንደቆምኩ ልብ ብዬ ሳይ ወደ ላይ ከተሰቀቁት የዓይን ጨረሮች መካከል ረድ ሠርዌ ቁጭ ብሏል።

«ረድ ሠርዌ!»

ሁሉም እንደመጀመሪያው ሆነው ጮሁ፤ ሳቁ አጨበጨቡ፣ አፏጩ... ግራ ተጋባሁ። እያጃጃሉኝ መሰለኝ። በአንጎሉ ድንግዝግዝ ተመርቼ ያበራችውን ልጅ አየሁ። ተሳቀቀላለች እንጂ ቢም እንደሆነች ለየኋት። ፊቷ ላይ ማዲያት እንደ አምራ ያንገርብባል።

«ቢም?»

አሁንም ሌላ ሳቅ፣ ሌላ ጩኸት፣ ሌላ ፉጨት... የሚያናድድ አይነት ሆነብኝ።

«ገልጃ ማነው?»

«እኔ ነኝ» አለ አንዱ መካከል እንደተቀመጠ በኩርፊያ።

«ምንድነው? ምን ተፈጠረ?...»

ሁሉም ሳቁ ረድ ሠርዌ ብቻ ፊቱ ላይ መገረምና ሳቅ አልነበረም።

«ቁጭ በል፣ ላስረዳህ» አለኝ።

ከቢመኙ ጎን ቁጭ አልኩ። ከዚህ በፊት በሲፈን ጉዳይ እዚሁ ቤት አልተነታረክንም? ማዲያቷ ከፊቷ ላይ ተነስቶ እኔ ላይ እንዳያርፍ አልሰጋሁም? ምንድነው? እንዴት ከዚያ ወዲያ ግቢ አግኝቼ ተጣላኋት?... ቀድሜ ረድ ሠርዌን ጠየኩት።

«አንተ ረድ ሠርዌ አይደለህም?»

«ነኝ» መለሰ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እዚህ ምን ታደርጋለህ? ማለቴ…››

‹‹ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈን ይዛህ ስትመጣኮ እዚሁ ነበርኩ።››

‹‹ታዲያ?››

‹‹ታዲያማ በሌላ የጊዜ ንፍቀ ክበብ ውስጥ ካንተ ጋር ተዋወቅን?››

‹‹ምን ማለት ነው?››

‹‹ጊዜ ወደፊት ይሄዳል።››

‹‹አዎ፣ ግልፅ ነው።››

‹‹ወደኋላስ?››

‹‹አይሄድም!››

‹‹ስለማይሄድ አይደለም፣ እኛ ማስኬድ ስላልቻልን ነው። ለምሳሌ ለመጀመሪያ ጊዜ አሜሪካዊው ሚስተር ፎርድ የሰራው መኪና የኋላ ማርሽ አልነበረውም። መታጠፊያ ኩርባ ካለፍክ አለፍክ። ያ መኪና ወደኋላ ያልተነዳው መኪና ሁሉ ወደኋላ የመሄድ ዕድል ስላልነበረው አይደለም። እንደውም ወደፊት የተንከባለለ፣ ወደኋላ የመመለስ ዕዳ አለበት። ጊዜጋ ስንመጣ፣ ጊዜ ወደፊት እንጂ ወደኋላ የማይሄደው እኛ ወደኋላ እንዲሄድ የሚያስችል ዘዴ ስላልተጠቀምን ነበር።››

‹‹ምንድነው ግራ የምታጋባኝ? ጊዜን ወደኋላ ነዳኸው? እና እኔ…››

‹‹አዎ፣ ጊዜ'ኮ ግም ነው።››

‹‹አባትህ የት ናቸው?››

‹‹እኔና አንተ እዚህ ቤት ከተዋወቅን አንስቶ ናዝሬት ኪዳነምህረት አስተዳዳሪ ሆኖ የእነሱን ቤት ተከራይቶ ይኖራል›› አለኝ ገልጀን እየጠቆመኝ።

‹‹እኔ ደግሞ በዚህ ሰዓት የማውቀውን ልንገርህ?››

‹‹ንገረኝ››

‹‹አላችሁ???›› ብዬ ጮህኩ፣ ደነገጡ።

‹‹አለን!!!›› ደገምኳቸው



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹አንተ ማነህ???››

‹‹አብዲሳ!!›› በድንጋጤ ውስጥ እያሉ ድምጼን አርግቤ ‹‹ይሄንን ነው የማውቀው፣ ጫት ብትም ደስ ይለኛል፣ ይቺ ልጅ ካጠገቤ ብትነሳ ደስ ይለኛል፡፡››

ረድ ሠርዌ ስምረት ቤት ውስጥ እያለን ድንገት ጠፍቶ በሌላ የጊዜ ንፍቀ ክበብ ውስጥ የመገኘት ፍላጎት እያሳደረ እንደሆነ ገባኝ፡፡ ለእኔ እብደት ነው፡፡ ምንም እንኳን እውነት ቋሚ ናት ብዬ ባላስብም፣ ምንም እንኳን እውን በህልም ሳለመለወጡ ዋስትና ባጣም ጊዜን እንደ ረቂቅ መኪና የኋላ ማርሽ አስገብቶ የሚያሻን ዘመን ላይ ማረፍ (ቢያንስ እኔ እንደማልችል) ይገባኛል፡፡

* * *

መቃም ጀመርኩ፤ ጫት በብዛት ስለገዛሁ በተለይ አንድ የማውቀው ፊት በተደጋጋሚ እየተነጠለ ይሰጠኛል፡፡ የት ነው የማውቀው? ተለውሟል፡፡ ዛሬ ቀን የጊዜ በትሎአችንን በር ላይ አስረን ስለገባን የትኛው ቦታ ላይ በትክክል እንዳረፍን አልተረዳሁትም፡፡ ልጁን ያስታወስኩት መሰለኝ፤ ረድ ሠርዌ ሲናገር፣ እኔ ስደናገር እያፏጨም ነበር፡፡ እየመረቀንኩና ጀርባዬን እያሳከከኝ ሲመጣ የተስማሙብትን ህልም ለማፍረስ አቶበቶብኩ፡፡

‹‹ጆርጅ በርክሌይን ታውቃለህ?›› አልኩት ረድ ሠርዌን ‹‹ ካህኑን፣ የቤተክህነቱን ሰው፣ ጳጳስ የሆነውን››

‹‹አዎ›› አለኝ ተረጋግቶ፡፡

‹‹የምናስብበት አእምሮ ነገሮችን ወደ ሀሳብ ቀይሮ ካልተረዳና ግንዛቤ ካልፈጠረ በስተቀረ ቁስ የመኖሩ ህልውና ያልተረጋገጠ ነው ይላል፡፡ ስለዚህ ይህ ዓለም፣ እናት አባት፣ ወንበር፣ ድንጋይ፣ ጥምጥም፣ ፀናዕል፣ መቋሚያ፣ ክበሮ፣ ጫት፣ ዛፍ... ሁሉንም አእምሮ የሚረዳቸው ቁሶቹን በማይወክል ሀሳብ ላይ ተመስርቶ በመሆኑ ሀሳብ እንጂ ቁስ የለም ባይ ነው፡፡››

‹‹ትክክል!!›› አለ ረድ ሠርዌ ልብ ብዬ ሳየው፤ ‹‹የቢሾፕ በርክሌይን ሀሳብ ሳይሆን አተርጓጎምህን ማለቴ ነው፡፡›› በማለት ለማስተካከል ሞከረ፡፡

‹‹መች ተረጎምኩት?››

‹‹ማለቴ...››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ልተርጉምልህ፤ ትክክል ነው፡፡ በርክሌይ ትክክል ነው፡፡ ቁስ አካል የሚባል የለም፡፡ ሁላችንም በህልም ግንኙነት፤ በሀሳብ መስማማት ያለን መሰለን እንጂ ይሄንን የሚያረጋግጥ ምንም ነገር የለም፡፡››

‹‹አሌክሳንደር ጆንሰን የተባለ አሜሪካዊ እኮ መልስ ሰጥቶታል፡፡›› አለ መልኩ ጠፍቶብኝ ያስቸገረኝ፡፡

‹‹ምን አለው?››

‹‹አልቀበልም!››

‹‹ከዚያ ምን አደረገ?››

‹‹አሻንጉሊት ከድንጋይ ጋር አጋጭቶ ብትንትኑ ሲወጣ ‹ህይወት ህልም ከሆነ በርክሌይ ልጄን እንዲህ እንዲያጋጭና ውጤቱን እንዲያይ እመክረዋለሁ›› አለ፡፡

‹‹እኔ ግን አረጋግጫለሁ›› አልኩ ኮስተር ባለ መንገድ፡፡

‹‹እንዴት?››

‹‹ልጄን አይደለም ከድንጋይ ጋር ያጋጨሁት፡፡ ውትድርና ስልጠና ላይ ሳለሁ አንድ ሰልጣኝ አስቸገረኝ፡፡ ሊያስቅብኝ ይሞክራል፤ ረጅም ጉዞ እንጓዛለን፡፡ ከካምፕ ርቀን እናድራለን፡፡ የነፍስ ወከፍ ጉድጓድ እንቆፍራለን፡፡ ቆፍረን ስንጨርስ እንደፍናለን፡፡ ድፊት ስንባል በጭለማ ያንን ምልምል በአካፋ መትቼ ጉድጓዱ ውስጥ ጨመርኩት፡፡ ጉድጓዱን መለስኩት፡፡››

‹‹እና?››

‹‹ያ-የገደልኩት እዚህ ቤት አለ፡፡››

‹‹ማን? ማነው?››

ጫት ቀንጣሹ ላብ በላብ ሆኖ በድንጋጤ ያየኛል፡፡ ‹‹እሱ›› ብዬ ጠቆምኩበት፡፡ ‹‹ሁርሶ ስልጠና ላይ ነበርክ አይደል?››

‹‹አዎ››

‹‹እንዴት እዚህ ተገኘህ?››

‹‹ከስልጠና አምልጬ፡፡››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹እንዴት አመለጥክ?››

‹‹ተደብቄ…››

‹‹እሱ ሌላ ህልም ነው፡፡ ያንተ ህልምና ማስብ መቀጠል ስለነበረበት እዚህ ተገናኘን፡፡ ይሄንን ተገዳድሎ በሌላ ህልም የመገናኘት ትንግርታዊ ሂደት በሁላችሁም ላይ ማረጋገጥ አሰብኝ፡፡››

ፀጥ!

የጊዜ እሽክርክሪት ላይ አንጋጦ የማይጨበጥ ነገር ሰመጨበጥ የሚሞክረውን የጃክሰን ቤተሰብ ወደ ናዝሬት ራስ ገዝ ጎትቼ አመጣሁት፡፡ ሞት-መመከቻ ኖረው አልኖረው ማስደንገጡ ይቀራል? ኢየሱስ እራሱ በሶስተኛው ቀን እንደሚነሳ እያወቀ ‹‹አባት ሆይ ይቺ ፅዋ ከእኔ ትለፍ›› አላለም? ጃክሰኖች በሞት ላይ ምን መተማመኛ አላቸው? ምንም!!



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## 6

# ወደ ዝቅ እና ከፍ

ሦስት ሌሊት ሦስት መዐልት «ሌቦቹ» አላስወጣ ብለው አቆዩን። «ሌቦች ባደባባይ ይፋንናሉ፣ ንፁሃን ግን ያፍራሉ ይደበቃሉ» የሚል ቃለትንቢት በፍካሬ ኢየሱስ አልተጻፈምን? ባይጻፍም በእኛ ላይ የደረሰው ይሄ ነው።

እየመላለሱ የግቢውን በር ይደበድባሉ። ያገኙትን ወጣት እንደጆንያ መኪና ላይ ይወረውራሉ። የተደበቅንበትን የስምረት ቤት ሻለቃ ጠናጋሻው ታደገው። በር ሲደበደብ ስምረት ትወጣና

«የሻለቃ ጠናጋሻው ቤት ነው» ትላለች።

«የቱ ሻለቃ?»

«ዘመቻ ፀሐይ ግባት ላይ የተሰዋው»

የታሪክ ማኅበሪያው እንደዚህ በአጋጣሚ የተሞላ ነው። ረድ ሠርዌን ለመጠየቅ ባልወጣ፣ ለመታከም ባይወጣ፣ ለመጠጣት ባናስብ፣ ስምረት ባታገኘን የዚህ መጽሐፍ ትርክት እራሱ ወደሌላ መልክ ይቀየር ነበር። ታፍሰን፣ አንዱ ወታደራዊ ካምፕ ተወስደን…

ስምረት የሚጠጣና የሚበላ ባቀረበችልን ቁጥር እየተንሚነጨች ነው። ረድ ሠርዌ ሲያናግራት በሞከረ ቁጥር «አንተ ሰውዬ ሲጣኔን አታምጣው» ትላለች። ተያይተን እንጠቃቀሳለን። የአባቱ ጦስ የስምረትና የእሱ ኮከብ እንዳይገጥም አደረገባቸው።

«እንደውም የሆነ ነገርህ ጠኔን ይመስላል፤ ከሀዲዎች። እሱም እሷም፣ ሩፋኤል ባይገልጥልኝ ኖር፤ እኔውም እንጃ ይሄኮ ግልፅ ነው። በወዲህ የልጆቹ አባት፣ በወዲያ እህቱ የናቱ ልጅ እያልኩ ለሁለቱም አለቅሳለሁ። እነሱ የተቀጣጠሩበት ተገናኝተው…»

ረድ ሠርዌ የምትለው ስለማይጨበጥለት ግራ ይጋባል። እኔ እነግረዋለሁ። በህይወት ታክቶ የነበረው በወሬው እየተነቃቃ ይሄዳል።

«ምን፣ ምን፣ ምን?…»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ረቂቅን አይቻታለሁ። ገላዋ ወደብርሃን ሲለወጥ። እንዲህ ያለ ነገር ለሰው የሚነግሩት አይደለም። ያስገምታል›› አልኩት።

ዝም...

‹‹...ስሟን ማን አልከኝ?››

‹‹ረቂቅ››

‹‹ህም...›› ብሎ ዝም፤ ዝም ብሎ ሲናገር እንዲህ አለ፦

‹‹ሕስመ ስሙ ይመርሖ ኀበ ግብሩ እንዲሉ አበው፤ ስሟ ግብሯን መራው ማለት ነዋ ›› በውነቱ ረቂቅ መባል ሕይወትን ከማርቀቅ ውጭ ሌላ ምን ግብ ይኖረዋል?...››

የራሴን ሥም ከዕጣ ፈንታዬ ጋር ለማገጣጠም ሞከርኩ። ታለሰው፤ አልአዛር፤ ታለስ፤ መጥምቀ መለኮት፤ እስጢፋኖስ... የቹቹ እናት ወደፊት ጎብደድ እንዳለች በቀያይ አይኖቿ ስታየኝ አየኋት።

‹‹ከፀራቱ የሰው ልጅ ባሕርያተ ሥጋ ምሳሌዎች መካከል፤ በረቂቅነት የሚታወቀው ነፋስ ሲሆን፤ ከነፋስ መላእክት፤ ከመላዕክት ደግሞ ሥላሴ ረቂቃን እንደሆኑ ሊታውንት ይተነትናሉ።›› የነፍስ አባትነት በረድ ሠርዊ ሁኔታ ላይ ረበበት...

‹‹ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ ‹ሕሳትና ነፋስ በመጨረሻው ዘመን የሚያልፉ ናቸው› ይላልና እህትህ ረቂቅ እንደነፍስና እሳት እስከ ምጥአት ቀን ትቆያለች። ምናልባትም እዚህ አለች።››

እንደጥንቱ የግዕዝ ጥቅስ ጣል ባለማድረጉ የሚናገረው ነገር ከአንጀቴ ጠብ አልል አለኝ።

‹‹ሁም›› እያለ ይደመማል።

ዝም...

‹‹...‹ተፈጥሮቶሙስ ለመላእክት እምብርሃን እምላካዊ› ይልብሃል። የመላክት ተፈጥሮ ከብርሃን ፈለግ እንደሆኑ ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ ሲነግርህ ነው ሁም››

‹‹ሰው መልአክ ይሆናል?›› የልጅ ጥያቄ ሆነብኝና እንደማፈር ሞካከረኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሰውማ ሲፈጠርስ መልአክ አይደል?›› አለኝ

‹‹እንዴት?››

‹‹ወሶበ ኢያዕኮትት ለዘፈጠረከ እምነፋስ ወእሳት፣ ፈጠረ ሕየንቴከ ሰብአ ዘማሬ ይልብሃል፡፡››

‹‹ምን ማለቱ ነው?››

‹‹ልመልስልህ ነው፤ ዲያብሎስ ሆይ! ከእሳት ከነፋስ የፈጠረህን ፈጣሪዬ ብለህ ባታመሰግን ባንተፈንታ አንደበቱ ከምሥጋና የማያቋርጥ ሰውን ፈጠረ›› ሲል ነው፡፡

‹‹የሠይጣን ምትክ ሆነን ማለትም አይደለም?››

የደብተራ የማይመስል ሳቅ...

‹‹ሣቅ እንጂ አንተማ...›› ስምረት መጥታ አፈጠጠችበት፡፡

‹‹አባቴ ሳኩሽ?›› ብሎ ዳግም ሳቀ፡፡

‹‹ቁርጥ ያንን ከሃዲ...›› ልጆቿን ገብታ አተረማመሰቻቸው፡፡

* * *

ጣሊያን ሠፈር ተዝትዟል፣ ገዳም ሠፈር ፈዟል፣ ሠባራ ባቡር ነፍዟል... ምን አተዘተዛቸው? ምን አፈዘዛቸው? ምን አነፈዛቸው?... ወጣቶቹ ጎዳና ላይ አይውሉ፣ አያድሩ፡፡ ወጣቶቹ ቤታቸው ሆነው በትንፋሻቸው ከተማውን ያሞቁት ነበር? ካልሆነ ስለታፈሱ ለምን ከተማው ተዘተዘ ለምን ነፈዘ? ለምን ፈዘዘ?...

...ሠባራ ባቡር እንደ ብረት ድስት ቶሎ የሚግለውን ያህል ለመተዝተዝ መፍጠኑ ግርም እያለኝ ወደውስጥ ዘለቅሁ፡፡ የመከላከያ ወረዳዬ በጠላት ሲሰበር በፍርሃት የተሸሸግሁ ያህል ሀፍረት ተሰማኝ፡፡ እነ ልጅ ተፈሪ ባለፉት ሦስት ቀናት ያዩትን እየተወኑ ይሯሯጧሉ፡፡

‹‹እጅ ወደላይ!››

‹‹እዚህ ቤት ወጣት አለ?››

‹‹እስኪ የፎቶ አልበም አምጡ፡፡››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ይሄ የታል?››

‹‹ና ውጣ!›› የእንጨት ጠበንጃ ተቀባበለ።

‹‹ኡ! ኡ! ኡ! ልጄን!›› (ሴቶቹ)

አረቄ እና ጠላ ቤቶች ጭር ብለዋል። ሠባራ ባቡር የሚሞቀው ከአረቄና ከጠላ ቤቶች የሚፈጠር እንፋሎት ይሆን? በእንፋሎት የምትሰራ ሠባራ ባቡር?...

ደጅይጥን ግቢ ስደርስ የሚቀፍ ዜና እየጠበኩ ነበር። ድንገት የሩፋኤል ጆኒ የሎሽችውን የመሰለ ቀጭን ድምጽ ጆሮዬን በስቶ አለፈ።

‹‹ኡ! ኡ! ኡ! ኡ!...››

ሲሲ ሁለት እራስ ሆና በር ላይ ታለቅሳለች። የማይነቃ ወንድሟን እየነቀነቀች። ቆሜ ሳያት ከብዷት ዞረች። ስትደነግጥ ከረድ ሠርዌ አባት ጭንቅላት ላይ የተፈናጠረውን ጥምጥም የመሰለ ቁልል ቀልብ ከራሷ ላይ ተፈናጥሮ ሲወድቅ ያየሁ መሰለኝ። ፍርሻ!

‹‹ምንድነው? ምን ሆናችሁ?...››

‹‹እናቴ ከሞንትራሴ ስትመጣ ገፍትረው እጇን ሰበሯት። እየታሸች ነው።››

እነ ልጅ ተፈሪ አንድ ልብ ያላሉት እውነት ተከናውኖ አልፏል ማለት ነው። ሲሲን ቢያዩ ‹‹እናቴ! እናቴ! እናቴ!...›› እያሉ ይጮሁ ነበር።

‹‹የት ጠፋህ? አውራኛ፣ ታፍስህ ነበር? እዚህ ቤት ያሉት ሴትዮ...››ብላ ወደቹቹ እናት ቤት ጠቆመች።

‹‹እ? ምን ሆነች?››

‹‹አንተን ፍለጋ ወጥተው፣ ልጄ! ልጄ! ልጄ! እያሉ ሲጮሁ ወታደሮቹ ደበደቧቸው። እራሳቸውን ስተው እቤታቸው ካስገባናቸው ሁለት ቀናቸው...››

ለምን ከፋቱን፣ ተንኮሉን፣ ግዴለሽነቱን፣ የማጥቃት ፍላጎቱን፣ የመበደል ጥማቱን... ለምን በእኔ ያላከካል? ያልከፋሁባቸው፣ ተንኮል ያልሰራሁባቸው፣ በግዴለሽነት ያላጠቃኋቸው፣ ነገር ያልሰራሁባቸው... በከሳሽነት ከፊቴ እንዲቆሙ የፈረደብኝ ስለምንድነው?... ይሄ፣ የምፀፀተው ፀፀት የማነው? ይሄ እራሴን የምወቅሰው መውቀስስ በእርግጥ የእኔ ነው?...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ኢጭ!... ኢጭ! ኢጭ! አሁንስ በዛ» ብዬ ወደ ክፍሌ ገባሁ። ሲሲ ድምፅ አውጥታ አለቀሰች። ለእኔ? ለእናቷ? ለአምላኳ? ለዕድል ፈንታዋ?... ለማን?... ያቺስ እዚያ ተጋድማ የምታቃስተው ለማነው? የስህተት ግርፋት የተቀበለችው ለማነው? ጎኗ የተሰበረው፣ እራሷ የተፈለጠው፣ መተንፈስ የተሳናት፣ ምናልባትም ባዶ ቤት ሆና «ተጠማሁ» ያለችው ለማነው? በማን፣ ስለምን ተመዝግቦ እከሰስበታለሁ?...

የተዘጋ ቤቴ ውስጥ ከወዲያ ወዲህ አልኩ። እውነት ይሄ ደባ፣ ሴራና ተንኮል የእግዚአብሔር ነው? እዚያ የሰማይ አውላላ ላይ ሆኖ በእግሩ መረገሚው በምድርና በእርሷ ፍጡር ለመዝናናት ነገር ይሸምን ይሆን እንዴ? ለእርሱ ተውኔት እኔና በዙሪያዬ ያሉ ሰለባ መሆን ይገባናል? ይሄ ፍርድ ነው? እንኳን እርሱ ነገር የሰራው፣ እኔ የተሰራብኝ ሀሁት ልቤን እየዳበሰው አይደለምን? ጊዜና ቦታ እንደ ሪድ ሠርዊ ቢጠቀለሉልኝ እዚህ ጊዜና ቦታ ውስጥ አንድ ደቂቃ እቆይ ነበር? ወደኋላ ወይም ወደፊት ወደማላውቀው ጊዜ አልሰደድም?...

ጆሮዬን ወደ ውጭ ባልኩ። ለማይ ነው ያለቀሰው? ምድር ናት ያቃሰተችው? ደጃፌን የሚፋጭረው ማነው? የሚያስፋጭረውስ?... ይሄንን የምሸሸው እንዴት ነው? ሲሲ ሆንቶ የቺቺ እናት ጭንቅላቴ ውስጥ አይደሉምን? ጭንቅላቴን የት ጥዬ ነው የምሰደደው? ወደየትኛው የጊዜ ጥሻ እደበቃለሁ? ምን አይነት ቦታ ይነጥለኛል?....

ደጃፌን ከፈትኩ። ሲሲ እንዳልፏጨረች ሁሉ የደነገጠች መስላ ሸሸት አለች። ወንድሟ ላይ እኔ ተደርቤአለሁ። ለአምላኳ በተነፋረቀ ፊቷ እያሳጣችኝ ነው።

«ወዴት ልትሄድ ነው? ቤት ልትለቅ ነው?...

አሳዘነችኝ። አጀን ኪሴ ከትቼ ያለኝን ድፍን ሃምሳ ብር አወጣሁ፣ አከራዩ የቺቺ እናት ደጃፍ ላይ ቁጭ ብለው ወደ ቺቺ እናት ጆሮአቸውን እንጋደው ያዩናል። ብሩን ለሲሲ ሰጠኋት?

«ለምን? ምን ላድርገው?» ሦስት ጭንቅላት ይታየኛል። የወንድሟ፣ የእሷ፣ የእኔ...

«ለእናትሽ ለቺቺ እናት አጥሚት ስሪ፣ ሾርባ ስሪ፣ ወተት ግዢ...»

«አንተ የት ልትሄድ?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ሕመጣለሁ›› ጎንበስ ብዬ እፏ ላይ ሳምኳት ‹‹ሕመጣለሁ›› ይሄን አይደል እግዜሯ የሚፈልገው? የተዋረደ ድርጊት...

‹‹ሕንዴ? ምንድነው?›› አከራዬ ደጅደጊፑኑ ‹‹ነገሩ ሕንዲህ ነው? እሷ ሳይሞት ፈሳ የሆነች እንደሆን እንዲህ ይደረጋል? ደሞ የት ነው የምትሄደው? ይቺ ሴት አንተን ብላ ነው የመጣችው? እኔ የት አውቃታለሁ? ዕዳህን ጥለህ ወዴት?...››

አከራዩ እግዜርን መሰሉኝ። ይጠተውታሉ... እግዜርን እንዲህ መራቅ ቢቻል... ከእሳቸው የተሻለ ያስብ ይሆን? ዓለም ሰብሳቢ እንዳባ ገባኤ የፍጡራን ኑሮ እንዲህ የተቀየጠው እርሱ እያለ ነው? ወይስ ኒቼ እንዳለው እግዚአብሔር ሞቶ ይሆን?...

...ከሰባራ ባቡር ወጥቼ ወደ ጉለሌ ማትናቱን አውቃለሁ። አካባቢው ደግንጧል። የማይሰማ ጩኸት አለ፤ ከልጆቻቸው መቃፊስ ያልተዕናኑ እናቶች ወገባቸውን በነጠላ አስረው በአዙሪት ውስጥ ይሽከረከራሉ። ከተማው ላይ የእኔ አኩዮች የሉም፣ ብቻዬን ኝኝ፤ መክብብ በጥቅሱ መጥቶ ነገሬ ውስጥ ምስግ አለ። ‹‹ከፀሐይ በታች ያየሁት ክፉ ነገር አለ። እርሱም ከገዢ የሚወጣ ስህተት ነው፤›› ይቺ ሀገር ከገዢዎቿ በሚወጣ ስህተት በሞት ሽረት ህመም አልጋ ይዛለች። አስታማሚ የለም፣ ተቆርቋሪ የለም፣ እሷ የሆነችውን ለመሆን የሚደፍር የለም!! ሥርዓት ፈርሶ የሰው ልጅ ልቡና ሞትን እንደአረፍቱ ይናፍቃል። መድረሻ ሳያዘጋጅ ይጓዛል፣ የደረሰበት ትቶት ከመጣው የከፋ ነው። የታመመውን ለማትናት፣ የሞተውን ለመቅበር ጊዜ ያጣል። ከሞት ወደ ሞት መጓዝ የህይወቱ ፈለግ ናት።

ምሽት ላይ እራሴን ሩፋኤል አገኘሁት። አደባባዩ ጭር ብሏል። አረቄ ቤቶች ያዛጋሉ፣ ጠጅ ቤቶች ጣመን ይሂችዋል። አንድ ሰው ብቻ ተከናንቦ እኔን ያስተውላል። ትከሻው ላይ ጋቢውን እንደድንኳን የወጠረ ቅስት ይታያል። መሳሪያ እንደሆን አወቅሁ። የዚህ ጠበንጃና መጠቆሚያ ጣት መዋደድ በእኔ ላይ ብዙ ጭንቀት ያራግፋል። በደንገዝጋዛው ብርሃን ውስጥ ሰውየው ወደእኔ ሲመጣ አየሁት። የአፈሣ ማሳረጊያ ሊያደርገኝ ይሆናል - ይሁን።

ሰውየው መጥቶ ጉልበቴ ላይ ወደቀ፤ ትከሻው ላይ ሆኖ ሰማይ ይጠቁም የነበረ አፈሙዙ ሰውየው ጉልበቴ ላይ ሲወድቅ በደረቴ ትክክል ተደቀነ።

‹‹ታለ? ታለ? ይቅርታ አድርግልኝ›› አለኝ ባለጠበንጃው ሊገድለኝ ስለሆነ በመጀመሪያ ይቅርታ እየጠየቀኝ መሰለኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ምንድነው?» ቀና ብሎ ሲያየኝ የጠበንጃው አፈሙዝ ጋቢ ተከናንቦ ግንባሬ ላይ ተደቀነ፡፡

«አባትህ በእኔ ዳፋ ወደ ኤርትራ ተልከዋል፡፡ ስሜ ከስማቸው ስለገጠመ ብቻ፤ እኔ ነኝ ኤርትራ ኢንባሲ ሄጄ «ናዕነት፣ ባርነት» የሚለውን አማራጭ አይቼ «ነፃነት» ይሻላል ያልኩት፡፡ በእኔ ዳፋ አባትህ ወደ ኤርትራ ተላኩ፡፡»

ብዜን እንደሆነ አወኩ፡፡

«ይቅርታ አድርግልኝ፡፡»

«አድርጌልሃለሁ፤ ተነስ፡፡»

«እውነት?» ብዜን ግራ ሲገባው ይቅርታ ለማድረግ አላግባብ እንደፈጠንኩና ስለበደሉ ክብደት ዋጋ እንዳልሰጠሁ ገባኝ፡፡

«አዎ፣ አባቴ አሜሪካ ገብቷል፡፡ እዛ በደህና ይኖራል፤» እውነት ይሆን? የቹቹ እናት...

«እንግዲያው ባለውለታቸው ሆኛለኋ?» ተነሣ፡፡ ድምፃችን ባዶ ጋን ውስጥ እንደገባ ሁሉ ያስተጋባል፡፡ «ታዲያ ዶላር ይላኩልኛ?...»

ነገሮቹ የተምታቱና ሥርዓት ያልጠበቁ መሆናቸው ከብዜን አልጀመረም፡፡

«አረቄ ልግዛልሃ፣ ለብሥራቱ፡፡»

«ጥሩ!»

ተያይዘን የሚያዛጋው አረቄ ቤት ገባን፡፡ ዓለም እና ፈጣሪዋ ያስከፉትን ቃንቡራ ያፅናናዋል?...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

7

# ወደታች

...ዓለም እና ፈጣሪዋ ያስከፋትን ቃንቡራ ያዕናናዋል? የመፅናኛ መምጪያ አትጣጫዋ በዕውኑ ይታወቃል? ስል እራሴን ጠየቅሁ። መፅናኛህን ከትቢያም ውስጥ ልታገኝ እንደምትችል ገባኝ። የእኔ ጊዜና ቃምቡራ የተፈላለጉበት ወትት ላይ ስለነበሩ የመጀመሪያዋን መስኪያ ወደእሬ ስል የብዙ ጥያቄዎች ምላሽ የተገኘ መሰለኝ።

‹‹እኔ አልፈራም! ከሰው ጋር ለመኖር ብዬ...›› ይላል ብሌን። ቃምቡራ ‹መፍትሔ ጭንቀት› ብቻ ሳይሆን መፍትሔ ፍርሃትም እንደሆነ አወቅሁ። እናቴ ከነጠበንጃው ያባረረችው ‹መፍትሔ ፍርሃቱ›ን ሳይቀምስ በመትረፉ ይሆን?

አንድ ሦስቴ ስለአለመፍራቱ እየነገረኝ ቆየ ‹‹እኔ አልፈራም!››

‹‹ጥሩ›› እንደጠናጋሻው።

‹‹እኔ አልፈራም!››

‹‹ደግ››

‹‹እኔ አልፈራም!››

ህይወት ጦርነት ሳይሆንበት አልተረም። ሁል ጊዜም የጀግንነት ጅብዱ የሚፈፀምበትና ካስፈለገ ስልታዊ ማፈግፈግ ተግባራዊ የሚሆንበት። ስልታዊ ማፈግፈጉ ጠበንጃ ይዞም እሰው እግር ላይ ወድቆ ይቅርታ መጠየቅ ሊሆን ይችላል። ዘወር ብዬ አየሁት አንቴናው የተመዘዘ የጦር ሜዳ ሬዲዮ ጋቢ አልብሶ የያዘ መሰሏል።

‹‹ለምን ጠበንጃህን አውርደህ አታስቀምጠውም?›› አልኩት።

‹‹እዬ ነገሩ ወዲህ ነው።››

‹‹እንዴት?››

‹‹እንግዲህ ወንድም ሆነናል አይደል?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«አዎ።»

«ሆነናል?» አረጋገጠ፤ አዲስ አረቄ እያስቀዳ።

«አዎ ሆነናል» አረቄዬን ቀመስኩ።

ጋቢውን ገለጥ አድርጎ ወገቡ ላይ የታጠቀውን የመጥረጊያ እንጨት አሳየኝ። የእንጨቱ ሰደፍ ከጭንቅላቱ በላይ ሆኖ ጋቢ ሲለብስ የጠበንጃ አፈሙዝ መስሏል። ያኔ እናቱ ብዜንን እንዳሳደደች ብትደርስበት ኖሮ የምትማርከው ጠበንጃ ሳይሆን የመጥረጊያ እንጨት ነበር? ፈገግ አልኩ ፈገግታዬን ቢያይ?...

«ጠላቱ ብዙ ነው፣ በሰላምና መረጋጋት ብዙ ሰው ጥርስ ውስጥ ገብቻለሁ። ታዲያ ኤርትራዊ ተብዬ ስባረር ከተራቡ ድመቶች አንገር የተቀመጥኩ ቋንጣ ሆንኩ። ምን ዋስትና አለኝ? አልጬ-አልፎ እንዲህ ስታይ ጠላቶቼ ጠበንጃ አይተው ብቻ ሳይሆን ታጣቂ በመሆኔ ከመንግሥት እንዳይጣሉ ፈርተው አይተናከሱኝም።»

ለምን ምስጢሩን ነገረኝ? መጥፊያውን ለምን እኔ ዘንድ ለማስቀመጥ ወደደ? እኔ ዘንድ ያለ ችግር ምንድነው? መስኪያዬን አስቀምጬ በጎን በኩል አየሁት። የዋህ ብጤ ነው፤ አሁንም በኩራት «ጠበንጃውን» ያስተካክላል። ሌላ ሰው የለም፣ አረቄ ቀጂያችን እንኳ ጓዳ እንደተከተቱ ካልጠራናቸው አይመጡ። ታዲያ?

«የተወለድኩት አባትህ ሀገር ደብረብዜን ይሁን እንጂ አስተዳደጌ አስመራ ነው። አንዳንዴ ያቺን ሀገር ስናፍቅ አለቅሳለሁ። ዘመዶቼ አሉ፣ ግን እነሱም አልደላቸው። ስናፍቅ አለቅሳለሁ፤ የፀሐይቱ ባራዊን ዘፈን እዘፍናለሁ፤ ስናፍቅ አለቅሳለሁ።»

እንደቹቹ አንዳንድ ቃላቶችን ይዞ አይለቅም። «ወይዘሮ ሐና...» እያለ መዝፈን ጀመረ። አይኖቹ እንባ እንዳቀረሩ ከዘፈኑ ወደ ቀረርቶ መሰል ነገር ተሸጋገረ። ግጥም እንደሆነ የተረዳሁት አጋማሽ ላይ ነበር ሲጨርስ

«የማን ግጥም ነው?» አልኩት።

«የአቦይ ፀጋዬ ገብረመድህን»

«እንዲህ የሚል ግጥም? ርዕሱ ምንድነው?»



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹'አስመራ' ይባላል። ትምህርት ቤት እያለን መምህራችን ዜማ ሠርቶለት ያዘምረን ነበር።››

‹‹እስኪ ድገመው?››

ደገመው።

ሰውነቱ ሙሉ በሙሉ ሲነቃቃ ታወቀኝ። ‹‹አቦይ›› ፀጋዬ ገብረመድህን እንደዚህ ያለ ግጥም እንዳለው አላውቅም ነበር። ከነገሮች ጋር ካልተያያዙ በስተቀር ግጥምን በተናጠል ማስታወስ መቻል ያዳግታል። ፀጋዬ በብዜን አንጡራ ፍላጎትና ትዝታ በኩል መጥቶ አጠመደው።

‹‹አቦይ ፀጋዬ ሴላም አለው።››

‹‹ምን የሚል?››

‹‹'ኤርትራ' የሚል ይመስለኛል። ይሄንንም መምህራችን ናቸው ያስጠኑን፣ ልበልልህ?››

‹‹እባክህ››

‹‹እንደምን ከረምሽ ኤርትራ፣ አአ አዎ የግጥሙ ርዕስ ይሄ ነው፤ 'እንደምን ከረምሽ ኤርትራ'››

‹‹ጥሩ›› እንደጠናጋሻው ወግ አቁነጠነጠኝ፤ ግጥሙን እንዴ ተወጣው፤ የፀጋዬ ግጥሞች ረጃጅም ስለነበሩ በሰፊው ስጠብቀው ቁምጥ አለብኝ። አረቄ ቀጂዋን ጠርቼ ብዕርና ወረቀት እንዲሰጡን ጠየኳቸው። የደብተር ግንጣይ ሰጡኝ። ብዜንን እንዲፅፍልኝ ስጠይቀው ሞክሮ ሳይችል ቀረ። ነፍሱ ስለምታዜመው ቃላት እየቆጠረ መፃፍ ተሳነው። እኔ እየፃፍኩ እሱ በፋከራ መልክ ተወጣው። መላልሶ እየፎከረ አስፃፈኝ። 'እንደምን ከረምሽ ኤርትራ' የምትለው ኢትዮጵያ ናት። በተለይ የግጥሙ አጋማሽ ላይ አንጀት የሚበሉ ስንኞች አሉበት።

. . . . . . . . .

እንደምን ከረምሽ ኤርትራ

አጥንትሽ የእኔው የእናትሽ፣ ደምሽ የኔው

የኢትዮጵያ ደም

o



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ህይወትሽ ዞሮ ህይወቴ፣ ዓለምሽ ዞሮ የኔ ዓለሜ፣

ቆስለሽም ቁስልሽ ቁስሌ ስትታገም የምታገም፣

ቲም አርግዘሽ የማዋልድ፣ እማርስሽ

የአንቺን ህመም፣

ከእኔ ከእናትሽ በስተቀር የሚያውቅልሽ

ሌላ የለም።

. . . . . . . . . .

ለኢትዮጵያ ማህፀን ብስራት ለ‹ራ› ፀሐይ ቀኝ ዐይኑ

አጥንትሽ የእኔው የእናትሽ፣

ደምሽ የእኔው የኢትዮጵያ ደም፣

ግፍሽ ወጋኝ እንጂ ልጄ፣ ልብሽ ከልቤ አልተለየም፣

ህይወትሽ ዞሮ ሕይወቴ፣ ዓለምሽ ዞሮ የኔ ዓለም።

እንደምን ከረምሽ ኤርትራ?

የአትባራ ልጅ አነስ እራ፣ የማለዳ ምስራቅ ጮራ።

‹‹እኔ የምለው?›› አለ ‹ጠበንጃውን› እያስተካከለ፤ ‹‹እኔ የምለው፣ ሀገር ማለት እንደዚህ ነው እንዴ? እንደ መንደር ጎረምሳ መንገድ አጥሮ አታልፉም ማለት? በቃ? እኔስ ይሄ ሀገር የሚባለው ነገር አነሰብኝ፤ ነገ የፒያሳን መንገድ ዘግተው አታልፉም ቢሉን ‹ፒያሳዊ› ‹ጉለሌአዊ› እያልን ልንሰደድ? ከሥፍራ ልናሳድድ?››

ከዚህ በኋላ ያወራነው ሙልጭልጭ የማይያዝ መጫጫህ ሆነብኝ። ግን አንድ ነገር መመስከር እወዳለሁ፤ ዓለምና ፈጣሪዋ ያስከፉኝን ቃምቡራና ግጥም አፅናንተውኛል።

ከቃንቡራ ቤት ተደጋግፈን ወጣን። የሚያስቅ እራስ ማዞር ሠፈረብኝ። ሲያዞረኝ ያስቀኛል። ብዜን ‹ጠበንጃውን› እያስተካከለ ብብቱ ውስጥ ገባ። እግሮቹ አንዳንዴ በአየር ላይ እየተራመዱ ወደጡረታ ድልድይ አመራን። የሰንሰል አጥሩ በቆርቆሮ ተለውጦ ጠበቀን። እንኳኳን፣ ደገምን፣ ሠለስን...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የደጅ መብራት በርቶ የወንድ ድምፅ ተከተለ።

‹‹ማነው? በኢየሱስ ስም››

‹‹እኛ!›› ሳቅሁ

‹‹እኮ እናንተ እነማን?››

‹‹እነ ቃሰ›› ያበረኛል፣ ያስተኛል እንጂ ውሴን አልሳትኩም።

‹‹ብኢየሱስ ስም›› በእህቶቹ ሲዋከብ የነበረው የኢህቷ አሸባ ፈጣሪ የአባቷንና የእናቷን ቤት ተቆጣጥሮት ያለውል ይጠራበታል።

ተከፈተ፤ ብዜን ለአሸባ ባል አስተላልፎኝ ሄደ። የሰራልኝን ውለታ ቢያውቀው፤

‹‹ምነው? ቃሰ? በዚህ በክፉ ቀን? ዲያብሎስ ደም ጠምቶት በሚወራጭበት፣ ምነው?›› አለች አሸባ። ባሏ ወደ ትልቁ ቤት ሲመራኝ ወደራሴ ቤት ጎተትኩት። ተከላከለኝ። መሸጎሪያውን ከፍቼ ገባሁ። መብራት አበራሁ፣ ተለውጧል። የሀሎት ቤት አድርገውታል። መሬቱ ምንጣፍ ተነጥፎ ወንበሮች ተደርድረዋል። አንዱ ጥግ ወንበሮቹን ገፍቼ ተኛሁ።››

‹‹ብኢየሱስ ስም››

እዚህ ሣምንት ብቆይ ከአሸባ ኢየሱስ ጋር ልንናናት እንችላለን ስል የስካር ስጋት ገባኝ።

* * *

ጠዋት...

...ስልብ ቂስ በመረዋ ድምፁ ሥርዓተ ፍታት የሚያካሂድ መሰለኝ...

‹‹አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ

ልቤ እንደሰም ሆነ

በአንጀቴም መካከል ቀለጠ።

ኃይሌ እንደገል ደረቀ

በጉሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ

ወደሞትም አሸዋ አወረድሽኝ

ብዙ ውሾች ከበውኛልና

የክፋተኞች ጉባኤው ያዘኝ

እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።

አጥንቶቼም ሁሉ ተቆጠሩ

እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም

ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ

በቀሚሲም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ...››

ዓይኔን ስገልጽ ቤተክርስቲያን ያለሁ የመሰለኝ ጠፋ፣ ስልቡ ቴስ ጠፋ፣ ሥርዓተ ፍታቱ ተሰወረ... የአለሁበት ሰጥቲት ጊዜ ጠፋኝ። ፍራሽ ላይ ተኝቻለሁ፤ ምንጣፍ የመሰለ አልጋልብስ ተደርቦልኛል፤ ጭንቅላቴን ይፈልጠኛል። የምታነበንበው ትልቋ፣ የአበባ ነች።

‹‹የአበባ›› ስላት

‹‹አቤት!›› አለች

‹‹ውኃ ስጪኝ››

‹‹ሴጣን የተገሰፀ ይሁን!››

በመጀመሪያ ትውስታዬ ሊሊ፣ ቀጥሎ የቹቹ እናት መጡብኝ። ከዚያ የአቦይ ፀጋዬ ግጥም። ጭንቅላቴ በሶስት ዛፍ ቆራጮች እየተፈለጠ እንደምንም ከኪሴ የማታውን ግጥም አወጣሁት። መዓፊያ ብዕሩ አብሮ አለ። በዚህ ብዕር አንድ ተማሪ አደናቀፍኩ ብዬ ተፀፀትኩ።

‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው?›› የአበባ ውኃ እያቀረበችልኝ ጠየቀችኝ። አለባበሷ ላይ የመለኮት ተራዳኢነት ያለበት ይመስላል። የተዛነፈና ያለቦታው የዋለ ነገር አይታይም። ሥርዓቷ የትልቅ ሰው ነው።

‹‹አይደለም››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ታዲያ?››

የምላት ጠፋኝ። ጊዜ ለመውሰድ ውኃውን ቀስ እያልኩ ጠጥቼ ብርጭቆውን አስቀመጥኩ።

‹‹ለማወቅ የምፈልጋቸውን አንዳንድ ዕሁፎች ገልብጬ እይዛለሁ።››

‹‹እኮ ከወንጌል?››

‹‹አይደለም፤ ከሰዎች ጥበብ...››

‹‹ቅዱስ ጳውሎስ 'እምነታችሁም በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ እንዳይሆን' ይላል›› አለችኝ። ይሄኔ የእህቶቼን መኖር ተመኘሁ። ቢኖሩ ኖሮ ‹‹ዝም በይ፣ ዝም በይ፣ ያንቺን እምነት እዚያው!›› እያሉ በማዋከብ ይገላግሉኝ ነበር።

‹‹ውኃውን በጠርሙስ ብታመጪልኝ ይሻለኛል። ብርጭቆው አልጠቀመኝም›› አልኳት። ‹‹ኢየሱስ እኔ የህይወት ምንጭ ነኝ ይላል›› በሚል እንዳትሞግተኝ እየፈራሁ። ተነሳች ካልሲዋ እንኳን ከፍና ዝቅ አላለም። ልብስ አልባሽ መላእክት ሳይኖራትም አይቀር። ክዚያች እለት በኋላ የአበባ ብቅ ስትል እክናነባለሁ።

ጭንቅላቴን የመፍለጥ ኮንትራት የያዙት ዛፍ ቆራጮች ሥራቸውን አላስተጓጎሉም። ከማጅራቴ እንስቶ እስከ መሀል አናቴ ይከተክቱኛል። ቤቱ አልተስማማኝም፤ የአበባ ቤተሰብም የአኗኗር ስልቱን ወደማደናቀፉ ስለተጠጋሁ በሙሉ ልቡ ሊቀበለኝ እንዳልቻለ ይገባኛል። ግን የት? ሊሊ በሺህ ተባዝታ የከተማውን መተላለፊያ ሁሉ ስታለቅስበት ይታየኛል። ልክ ሆነም አልሆነም የእኔ ሰበብ ህይወቷን ለአደጋ የሰጠችው የቹቹ እናት እንደጋማ ከብት በሚራመድ እልጋ ላይ ሆና የምታስሰኝ ይመስለኛል። የፀጋዬ ግጥም የእሷ ድምፅ ሆኖ ይሰማኛል።

. . . . . . . .

‹‹ህይወትህ ዞሮ ህይወቴ፣ ዓለምህ ዞሮ የኔ ዓለም



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

ቆስለህም ቁስልህ ቁስሌ ስትታገም የምታገም

ቂም አርግዘህ የማዋልድ አማርስህ ያንተን ህመም

ከእኔ ከእናትህ በቀር የሚያውቅልህ ሌላ የለም።››

ዛፍ ቆራጮቹ የሥራ ፍጥነት ያሳያሉ። አበባና ቤተሰቧን በዚህ ችግር ላይ ተመስርቶ ማወያየት አይቻልም። ለእነ አበባ የዓለም ጉዳይ በሁለት ይከፈላል። በርኩስና በቅዱስ መንፈስ ሥራ። መፍትሔውም መጸለይ።

በሦስተኛው ቀን ይመስለኛል ድንገት ግቢው ተተራመሰ። ‹‹በኢየሱስ ስም የተገሠፅክ ሁን! እርኩስ መንፈስ ከዚህ ሰው ውጣ!›› የሚል የቤተሰቡ ድምፅ ተደራረበ። የቤና አልመሰለኝም። እንደምንም ተጎትቶ ለነሳ እኔ ያለሁበት ቤት ደጃፍ ተከፍቶ አንድ ሰው ገባ። ፊቱ በጠንገና በአዳዲስ ቁስል ተሞልቷል። ጉርድ ሸሚዝ ለብሷል ባዶ፣ እግሩን ሆኖ ሱሪው እስከ ጉልበቱ ረጥቧል።

‹‹ሠላም እምይእዜሰ

ኮነ ፍስሃ ወሠላም›› አለ። ከኋላው የኢየሱስ ስም ተከታትሎ ይተኮስበታል።

‹‹ተዉት!›› ብዬ ጮህኩ። መጀመሪያ ልጆቹ፣ ቀጥሎ አባት፣ ከዚያ አበባ ዝም አሉ።

‹‹ተዉት ጓደኛዬ ነው። መረጌታ ሠርፂ ይባላል።››

‹‹ከባድ መንፈስ ነው ያለበት፣ ይፀለይለት›› አለች አበባ።

‹‹ተዉት አልኩ'ኮ››

‹‹ይፀልዩልኝ፤›› አለ የፊቱ ቁስል ላይ በጣቶቹ እየተሯሯጠ። ‹‹ነ ፀልዩልኝ፣ 'ቃለ እግዚአብሔር ቃል ንጹሕ' ይላል ንጉሥ ዳዊት። 'የእግዚአብሔር ቃል ንጹሕ ቃል ነው' አይልም እንዴ?›› ፊቱ ላይ ያገጠጠ የፈጠጠ ስሜት አየሁ። ከዚህ ቀደም የማውቀው የረድ ሠርፂ ፊት አፋራምና ሸርዳጅ ነበር። ጣቶቹ የአንድ የጠገገ ቁስል አግኝተው ላጡ።

‹‹ፀልዩልኝ›› ብሎ አይኑን ጨፍኖ ጭንቅላቱን አቀረበላቸው። አራቱም እጃቸውን ዘርግተው አናቱ ላይ አነባበሩት። ዓይናቸውን ጨፍነው በየግል አነበነቡ። እኔ ፍራሹ ላይ ተቀመጥኩ። ረድ ሠርፂ ፀሎቱን ከሙሉ ልቡ እንደተቀበለው ያስታውቃል።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«የሴጣን አሰራር በኢየሱስ ሥም የተገሰፀ ይሁን!» አበባ አለች፡፡ ሁሉም «አሜን!» አሉ፡፡ ረድ ሠርዊም «አሜን! አሜን! አሜን!» አለ፡፡

«በጌታ በኢየሱስ ስም አሁን ይሄን ሰው ለቀህ ውጣ!» አለች አበባ፡፡

«አልችልም!» አለ ረድ ሠርዊ በጣቶቹ አጣብቆ የያዘውን የቁስል ቅርፊት እያየ

«ውጣ!» አበባ

«አልችልም!» ረድ ሠርዊ «የት ልሂድ?» ቁስሉን በጣቶቹ አፈናጠረ፡፡

«ውጣ!» ጥቂት ጊዜ ተከራከሩ፡፡

«እሺ እወጣለሁ፣ እሺ እወጣለሁ»

ትንሽ ፀልየው እጃቸውን አነሱለት፤ እርስ በእርስ ተያይተው ፈገግታ ተለዋወጡ፡፡ ረድ ሠርዊን በፍቅር ደግፈው እኔ ጎን አስቀመጡት፡፡

«የሚለብሰው አምጡ፣ የሚበላው አምጡ፣ የሚጠጣው አምጡ...» አለች አበባ እኔን እንኳን እንዲህ አልተቀበለችም፡፡ ቤተሰቡ ደስተኛ ሆኑ፡፡ ልጆቹ የአባታቸውን ልብስ አመጡለት ረድ ሠርዊ አመስግኖ ተቀበለ፣ ጫማ አመጡለት አመስግኖ ተቀበለ፣ የሚበላና የሚጠጣውንም ተቀብሎ አጠገቡ አስቀመጠና፡፡

«ልብሱን እቀይራለሁ፣ ምግቡንም እመገባለሁ፣ ትንሽ አረፍ ልበል እና መጽሐፍ ቅዱስ ታስተምሩኛላችሁ» ብሎ አለናበታቸው፡፡

ዝም ብዬ አየሁት፡፡

«የሚያፀድቅ ከሰራን ልዩነታችን ሰውጥ አያመጣም፣ አንድ ጋ እንፀድቃለን፤ የሚያስኬነን እምነት ውስጥም ካለን ልዩነታችን ሰውጥ አያመጣም፤ እዚያው ገሐነም እንገናለን፡፡» ብሎ ፊቱን በጣቶቹ ዳብሶ መድረቅ የጀመረውን ቁስል መርጦ ፈነቀለ፡፡ ቁስሉ አዲስ ሆኖ ደም አቸፈቸፈ፡፡

«የሴለ አምላክ ካመለከንም ልዩነታችን ለውጥ አያመጣም እኩል እንከለራለን፡፡»

ፊቱ ምን ሆኖ አገጠጠ? አይኑ ምን ሆኖ ወዘናውን መጠጠ?...



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

‹‹ትናንት አንድ ታሪክ ሰራሁ›› አለኝ

‹‹ምን?››

‹‹ትናንቱኑ ልነግርህ ሦስቴ ቤትህ ተመላለስኩ፡፡ቤት ካደርክ ሦስት ቀን እንደሞላህ ተነገረኝ፡፡››

‹ማን ነገረህ?› ለማለት ፈለኩና ተውኩት

‹‹እዚህ እንደሆንክ መንፈስ መራኝ፡፡ ማታ ጀምሬ ስገሰግስ ደከመኝ፣ አረፍ ስል እንቅልፍ ወሰደኝ››

ገዘም!

‹‹ትናንት የሠራሁት አንድ ታሪክማ...›› ከፊቱ ላይ በጣቱ የደረቀ ቁስል ማደን ጀመረ፡፡

‹‹እ?›› ድርቅርቅ ማለቱን ትቶ ቁም ነገሩን በተለመደው መንገድ እንዲነግረኝ ተመኘሁ፡፡

‹‹ትናንት የሠራሁት አንድ ታሪክ የንታን መታኀቸው››

ከው አልኩ፤ ‹‹እ?››

‹‹እንስቱ እረገጥኳቸው፡፡ ሆዳቸውን ስለው እንደላስቲክ ጠርሙስ ከዳን ጥምጥማቸው መሬት ለመሬት ብዙ ተጓዙ፡፡ ‹ህእ› ብለው አቃሰቱልኝ፡፡ ደገምኳቸው ‹ህእ›› ብለው ሩሃቸውን የሳቱ መሰሉ፡፡ እኔ? ላዝንላቸው? መናጢ አይደለሁ... ደገምኳቸው፡፡ ምን ቢሉ ጥሩ ነው?››

‹‹ምን አሉ?›› እንዳች ዕድፍ ነገር ከሆዴ ለመውጣት ይተናነቀኝ ጀመር፡፡

‹‹በአቡዬ››

‹‹ቀድመው ያልተመኩባቸውን?›› አልኳቸው፡፡

‹‹በገብረመንፈስ ቅዱስ››

‹‹መረገሚያዬን የሰጡኝ በእሳቸው ሥም ነው?›› ብዬ ሳፋጥጣቸው፣ ስረግጣቸው በመጨረሻ ምን ቢሉ ጥሩ ነው?››

‹‹ምን አሉ?››



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

«ስለወንድ ልጅ አምላክ!» አሉ። አልራራሁላቸውም። እዚያው ላይ ረገጥኳቸው።

መለስ ብዬ አይኖቹን አየኋቸው። በሀፀት ይሁን በጅብዱ ከርረዋል። ቀጠለ...

«የንታ ቢቸግራቸው የተኙበት ሆነው ሆዳቸውን በጉልበታቸው ለመሸፈን ሞከሩ። ባሰብኝ! መናጢ አይደለሁ፣ ባሰብኝ! ደረታቸውንና ጉልበታቸውን ይገፍ አላቀቅሁት፣ ከዛ እዚያው ላይ ረገጥኳቸው። ምን አሉ መሰለህ?»

«ምን አሉ?» ምን ጉድ ነው?

«'አይለመደኝም!' አሉ 'ሁለተኛ አይለመደኝም' አሉ። ባሰብኝ፣ ምን እንዳጠፉ ሳይናገሩ አይለመደኝም ይባላል? ነውር አይደለም? ደጋግሜ ሆዳቸውን እረገጥኳቸው። ሽንታቸው የክብር ልብሳቸውን አራሰው።»

የሚናገረው ውሸት እንዲሆን ተመኘሁ፣ ህልሙ፣ እብደቱ፣ ትገርቱ... እንዲሆን...

«ይሄኔ 'በሉ ተነሱ' እግዚአብሔር ይባርኮት» አልኳቸው።

ለመነሳት ሞክረው አቃታቸው።

«'እኮ ተነሱ! የንታ ሰይጣኔን አያምጡት' አልኳቸው፣ በድግምት እንደቆመ መጫኛ ተልመጥምጠው፣ ተልመጥምጠው ቆሞ አሉ። 'በሉ ጉልበት ሳሙ' አልኳቸው። 'የእኔን ጉልበት፣ ቀጥሎ መሬት ሳሙ።'»

«ይሄ ምንድነው?» አልኩ ግራ ተጋብቼ

«ትንቢት ነው፣ የጌታ ቃል፣ የግድ መፈፀም ያለበት። 'ልጆች በወላጆቻቸው ላይ ይነሳሳሉ' ይላል። ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ግድ ይላል። ተፈፀመ!! ገና ሀሳቡ ከልቡናዬ ሲፈልቅ ፀለይኩ

«ልበ ንጹሐ ፍጥር ሊተ እግዚኦ

መንፈሰ ርቱዐ ሐድስ ውስተ ከርሥዬ

ኢትግድፈኒ እምቅደመ ገጽከ»

አልኩ። ክፋው ሀሳቤ ከፀሎቱ በላይ ሆኖ ፈተነኝ።

«'አቤቱ ንፁህ ልብን ፍጠርልኝ



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ

ከፊትህ አትጣለኝ››

ተነሣ። ከተሰጠው ልብስና ምግብ ሳያነሳ ወደ በሩ አመራ። መፀለዩን አላቆመም…

‹‹ልበ ንጹሐ ፍጥር ሊተ እግዚኦ…››

‹‹በኢየሱስ ሥም!›› እነ አበባ

‹‹መንፈሰ ርቱዐ ሐድስ ውስተ ከርሥዬ…››

‹‹በጌታ በኢየሱስ ሥም!››

‹‹ኢትግድፈኒ እም ቅድመ ገጽከ…›› ሄደ፣ ሳይመለስ ለእስከወዲያኛው እንደሄደ ገባኝ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

## 8

# የታች ታች

የቹቹ እናት ሞተች፤ በዘመድ አልባ ደንብ፣ ወድቆ በተገኘ አግባብ በከተማው ማዘጋጃ ቤት ተወሰደች። እህቶቼ አበባ ጋ እንዳለሁ መጡ፡-

«በኢየሱስ ሥም» ስትል

«ዝም በይ!»

«ዝጊ!» አሏት። አበባ ቤተሰቦቿን ይዛ ትልቁ ቤት እየሸሸች...

«ጌታ ይገስፅህ፣ ርኩስ መንፈስ!» አለች።

«አንቺን ይገስፅሽ!» እቴቴ

«ማነው ርኩስ መንፈስ?» ስምረት

ሲገቡ እኔ ፍራሽ ላይ ነኝ። እቴቴ የረቂቅን አስከትላለች፤ ስምረት እነ የስምረቶችን አልያዘችም።

«ምንድነው ጉዱ?»

«ታሰ?»

«ምንድነው?»

ሁለት አልመሰሉኝም። «ብዙ፣ ተባዙ» ያለው ይሄን ይሆን? ገበያ ሙሉ ሴት መሰሉኝ። እቴቴ በመፀየፍ የያዘችውን መዳፍ የሚያክል የሻማ ጨርቅ ቦርሳ ሰጠችኝ። በማንጠልጠያ ገመዱ ተሸምቅቋል ውስጡ እጅብ ያለ ጠንካራ ወረቀት እንዳለ ያስታውቃል።

«ሴትዮዋ ምን እያለች ነው?» እቴቴ

«ለምን አንተ ያለህበት ቦታ ድረስ መጥታ መኖር ጀመረች?» ስምረት።

መልስ ሳልሰጥ የቦርሳውን ሸምቅቅ አላልቼ ውስጡ ያለውን አወጣሁ። ብዙ ፎቶ ነው። እያንዳንዱን ፎቶ ስመለከት እግሬ እንደተጣጠፈ ከፍራሹ ላይ ተነስቼ የተንሳፈፍኩ መሰለኝ። ቀና ብዬ እህቶቼን አየሁ። ከእኔ መልስ ይፈልጋሉ እንጂ መልስ እንደሌላቸው አወቅሁ።



t.me/OLDBOOKSPDF VIA

የቹቹ እናት ከእኔ ጋር የተነሳችው የተለያየ ፎቶ፡- ቆሚያለሁ፣ ተቀምጫለሁ፣ እሷ ቆማለች ትከሻዋን በእኔ ታቅፋለች፡፡ የፎቶዎቹን ጀርባ ገልብጬ አየሁ፡፡ ‹‹ፎቶ ልዑል-ጎንደር›› ይላል፡፡ ዓመተ ምሕረቱ በአብዛኛው አስራ ዘጠኝ ዘጠና አንድ ነው፡፡

‹‹ማነው? መቼ የተነሳኸው ነው?››

ፀጉሬ አድጓል፣ የማላውቀውን ልብስ ለብሻለሁ እንጂ እኔ ነኝ፡፡ ነገር እየተገለበልኝ የመጣ መሰለኝ፡፡ እኔ አይደለሁም፡፡ አየር ላይ እየዋለልኩ ነው፡፡ ሁለቱ እህቶቹ ተንበርክከው ምላሼን ይጠባበቃሉ፡፡

‹‹እኔ አይደለሁም››

‹‹እ?››

‹‹መንትያ ወንድሜ ይሆናላ››

‹‹ምን?››

‹‹አዎ፣ ታዲያ…››

‹‹አንጓች..?›› እቴቴ

‹‹እማዬ…?›› ስምረት

‹‹አይደለም፣ የቹቹ እናት፡፡ እኔ ወንድማችሁ አይደለሁም ማለት ነው›› መንሳፈፌ አበቃ፡፡ እንደላባ ቀስ እያልኩ በተጣጠፈ እግሬ ፍራሹ ላይ አረፍኩ፡፡ ለምን አልገረመኝም? ለምን አልደነቀኝም? ሲሆን ማበድ አይገባኝም? ከዚህ ቤት መውጣት አሰኘኝ፡፡ እንደ እንቁላል ቅርፊት ካፈነኝ፣ አጣጥፎና አጨማዶ ከያዘኝ ህይወት ወጥቶ መሄድ…

…እንግዳ ዓለም፣ ነገሮች ሁሉ ተለዋወጡ፣ ፀሐይ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ የኃሊት ብትጓዝ ይደንቃል? የጨለማው ክፍለ ጊዜ ቢፀኸይ? የተኛንበት በእኩለ ሌሊት ብርሃን በጥፍራም ጨረሮቹ ቢያንቀን ይገርማል? ዛፎች ቢድሁ፣ ረባዳው ቢያብጥ፣ ተራሮች ቢጎደጉዱ በግርምት አፍ የሚያሲዝ ነገር አለ? አይጦች ቢያላዝኑ፣ ነፍሳት ቢያናፉ፣ ዶሮዎች እንደ አንበሳ ቢያገሱ፣ ኮሪደሮች ቅጫም ቢይዙ፣ ሀውልቶች ቢቀምሉ፣ ለቱሃኖች ሀዲድ፣ ለምስጦች ጎዳና ቢበጅ… እግዚአብሔር በእኔ ላይ ካደረገው በላይ ተአምር ይሆናል?



t.me/OLDBOOKSPDF VIA



- ትበላ ...
- የፍቅር ... እስረኛ
- ስብሐት ገብረእግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት
- ኢህአደግን እከሳለሁ
- የብርሃን ፈለገች
- ወሪሳ
- አጥቢያ
- ኩርቢት
- መልክአ ስብሐት
- በፍቅር ሥም
- መለያየት ሞት ነው

011 840 45 49

ዋጋ 150 ብር

t.me/OLDBOOKSPDF VIA